በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት

በ

ወሰን ባዩ

በ ፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ተስፋዩ ገሰሰ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል

የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

ነሐሴ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል

የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት

በ

ወሰን ባዩ

በ ፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ተስፋዩ ገሰሰ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ነሐሴ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል

የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት

በ

ወሰን ባዩ

በ ፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ተስፋዩ ገሰሰ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ነሐሴ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፍክሎር ትምህርት ክፍል

የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

ወሰን ባዩ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ	**ፊርማ**
የውጭ ፈታኝ	**ፊርማ**
የውስጥ ፈታኝ	**ፊርማ**

ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ያበቃኝን እግዚአብሄርን እና አናቱን (የአብማይቱ ማርያምን) አመሰግናለሁ፡፡ በዚህ ጥናት ዉስጥ በልዩ ልዩ መልኩ የበኩላቸውን ድጋፍ እና ትብብር ያደረጉልኝ ሰዎች ለሥራዬ መሳካት የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የተወጣው አማካሪየ ተስፋየ ገሰሰ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ላደረገልኝ በቃላት ልገልጸዉ የማልችለዉ የሞራል ድጋፍና የእውቀት ምክር እንዲሁም በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ ያለመሰልቸት የቅርብ ሙያዊ እገዛው ስላልተለየኝ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ከምንም በላይ እዉነትን ፣ ፍቅርንና ቅንነትን አይቸበታለሁና እንዲህ ልለዉም እወዳለሁ፡፡ ጋሽ ተስፋየ ሆይ ፡-

ፈጣሪ ለዘለዓለም ያኑርህ አልልህም እሱ አይሆንምና ጨርሶ ፣

ግን አብዝቶ ይጨምርልህ ከእኔ ዕድሜ ለአንተ ቀንሶ፡፡

በፎክሎር የትምህርት ዘርፎች እውቀት እንዲኖረኝ ያስተማሩኝ የኮርስ መምህራን፣ ይህንን ጥናት በየደረጃው በመፈተን ገንቢ አስተያየት ለለገሱኝ ምሁራን፣ በተለይ ለ ፕሮፌሰር ጀይላን ወልዬ እና ዶ/ር ሙሉጌታ ነጋሳ ከልብ የመነጨ ምሥጋናየን አቀርባለሁ ። አስተዳደራዊ ብቃትን ከትህትናንና ጋር የተላበሰው የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር ዶ/ር አለሙ ካሳዬ ብዙ አግዞኛልና በዚህ አጋጣሚ ፈጣሪ ውለታህን ይክፈልህ ልለው እወዳለሁ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህራንና ድጋፍ ሠጭ ሰራተኞች ላደረጋችሁልንኝ ልዩ ልዩ ድጋፍ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡ አንዲሁም ለጥናቴ መሳካት በየደረጃው ስህተቶቼን በማረምና አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ጓደኞቼ ዶ/ር ፍሬሕይወት ባዩ፣ ዶ/ር ዘላለም አበበ፣ ዶ/ር ጌታቸው ደዌ እና ዶ/ር በጅጋ ተካ ምሥጋናዬ የላቀ ነው። በሌላ መልኩ ከመጀመሪያ ዲግሪ የተማሪነት ዘመኔ አንስቶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የነበረኝን ልዩ ልዩ ማህበራዊ ተሳትፎና በዚያዉ መጠን ለመማር ያለኝን ተነሳሽነትና ፍላጎት በመመልከት በልዩ ልዩ መልኩ ድጋፋችሁ ላልተለየኝ

በየደረጃዉ የምትገኙ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማኔጅመንት አካላት፣ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ከልብ አመሠግናለሁ። ለጥናቴ መሳካት ትብብራችሁ ላልተለየኝ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር ሰራተኞችም ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ። በተለይ አርቲስት አዳፍሬ ብዙነህ ፣ ለሌ አሻጋሬ ፣ ሳሙኤል ተስፋየ ከልብ ላመግናችሁ እወዳለሁ። በተመሳሳይ ሁኔታ ፀሀፌ- ተዉኔት አያልነህ ሙላት፣ ጌትነት እንየዉ፣ አስታጥቃቸዉ ይሁን፣ ጫንያለዉ ወልደ ጊዮርጊስ ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ምስጋናየ የላቀነዉ። የኢቢሲ ጋዜጠኞች መለሰ ነጋሽ እና ዳምጠዉ ጋሻዉበዛም ላደረጋችሁልኝ ድጋፍና ትብብር አመሰግናለሁ። በዚህ ጥናት የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት በዋቢ የተጠቀሱ የጽሑፍ መረጃ ባለቤቶችን አመሠግናለሁ። በተመሳሳይ መረጃ የሰጡኝን በሙሉ እያመሰገንኩ፣ በተለይም ከቃቄ ወርዶወት ተዉኔት ጋር በተያያዘ ስለ ጉራጌ ባህል ሰፊ ማብራሪያና ትንተና ለሰጡኝ አቶ ተስፋየ ጎይቴ (የጉራጌ የባህልና የልማት ማህበር ዋና ዳይሬክተር) ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ ባለሙያዉ ግሩም መሳይ የጥናቴ ወረቀት ተገቢዉን ፎርማት እንዲጠብቅ በማድረግ ስላገዘኝና በጽህፈት (typing) ረገድ ያለብኝን ክፍት በመጠኑም ቢሆን ስለሞላልኝ አመሰግነዋለሁ። የ አማካሪየ ተስፋየ ገሰሰ ቤተሰቦች በተለይም ባለቤቱ ወ/ሮ መንበረ ግርማ እና የበኩር ልጁ አቶ ገሰሰ ተስፋየ የእናንተም ድጋፍ ለስራየ መሳካት አስተዋጽየ ስለነበረዉ በዚህ አጋጣሚ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። የልብ ጓደኞቼ የምላችሁ የትናየት ሙሉጌታ፣ አቶ ታደሰ አጥላባቸዉ እና ወ/ሮ መቅደስ ገብረየስ ላደረጋችሁልኝ ሁለንተናዊ ድጋፍ አመሰግናችኋለሁ። ቤተሰቦችና ዘመዶች፣ እናቴ ወ/ሮ ዘዉዲቱ አንተነህ፣ አጎቴ ሻምበል ምንዉየለት ይርሳዉ፣ ወንድሞቼ ንጉስ አንተነህ እና ሻለቃ ተስፋየ ባዩ ለሁላችሁም ምስጋናየን አቀርባለሁ። በተለይ አጎቴ ሻምበል ምንውየለት መቼም የማልረሳው ውለታህ አለብኝና በድጋሚ አመሰግንህለሁ። ሜሮን (ሚጡ) ፣ ሰለሞን ፣ ፋሲካ ፣ ኪሩቤል እና ሔርሜላ እናንተም ብዙ አግዛችሁኛልና አባቶች እንደሚሉት እራትና መብራት ያብዛላችሁ።

ማዉጫ

ርዕስ **ገጽ**

ምስጋና i

ማዉጫ iii

ሠንጠረዥ ማውጫ viii

የአህጽሮተ-ቃላት መፍቻ ix

ሙዳየ- ቃላት x

አጠቃለ/ Abstract xii

ምዕራፍ አንድ 1

1. መግቢያ 1

1.1 ዳራ 2

1.1.1 ፎክሎርና ቴአትር 2

1.1.2 የኢትዮጵያ ቴአትር አጭር ዳሰሳ 6

1.2 የጥናቱ መነሻ 11

1.3 የምርምር ጥያቄዎች 12

1.4 የጥናቱ ዓላማ 12

1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ 12

1.4.2 ዝርዝር ዓላማዎች 13

1.5 የጥናቱ ፋይዳ 13

1.6 የጥናቱ ወሰን 14

ምዕራፍ ሁለት 15

2. ክለሳ ድርሳናት 15

2.1. ጽንሰ ሐሳባዊ ጽሁፎች 15
2.1.1 የፎክሎር ምንነትና ፋይዳ 15
2.1.2 የፎክሎር ምደባ 18
2.1.3 ተግባራዊ ፎክሎር 19
2.1.4 የስነ ቃል ምንነትና ፋይዳ 22
2.1.5 የሀገረሰባዊ ልማድ ምንነትና ፋይዳ 23
2.1.5.1 ሐገረሰባዊ አምነት 24
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 25
2.2.1 በዉጭ ሀገር የተሰሩ ጥናቶች 25
2.2.2 በሀገር ዉስጥ የተሰሩ ጥናቶች 27
ምዕራፍ ሶስት 32
3. የጥናቱ ስልትና ዘዴ 32
3.1 የጥናቱ አይነት 32
3.2 የመረጃ ምንጮች 32
3.3 የመረጃ ናሙና አመራረጥ ስልት 33
3.3.1 የዒላማ ናሙና 33
3.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች 34
3.5 የመረጃ መተንተኛ ቲዎሪዎች 35
3.5.1 ተግባራዊ ቲዎሪ 35
3.5.2 ተምሳሌታዊ ቲዎሪ 37
3.5.3 አውዳዊ ቲዎሪ 38
3.5.4 የክዋኔ ቲዎሪ 42
3.5.5 የፎክሎር ዳያክሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ 43
3.5.6 የፌሚኒዝም ቲዎሪ 43

3.5.7 የሐይማኖት ቲዎሪ 45

3.5.8 የማህበረሰብ እዉቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ 46

ምዕራፍ አራት 48

4. በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት 48

4.1. ያላቻ ጋብቻ 48

4.1.1. ያላቻ ጋብቻ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 49

4.1.1.1 ኮከብ ቆጠራን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 49

4.1.1.2 ጠጠር መጣልን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 57

4.1.1.3 የሐይማኖት መቻቻል ባህልን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 60

4.2. ሾተላይ 63

4.2.1. ሾተላይ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 64

4.2.1.1 ሾተላይን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 64

4.2.1.2 የሙት መንፈስን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 66

4.2.1.3 ጸሎትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 69

4.2.1.4 ቆሌን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 71

4.3 አልቃሽና ዘፋኝ 74

4.3.1. አልቃሽና ዘፋኝ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 75

4.3.1.1 የሙሾ ግጥሞችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 76

4.3.1.2 የአዝማሪ ግጥሞችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 79

4.4. የቴዎድሮስ ራዕይ 81

4.4.1. የቴዎድሮስ ራዕይ ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 83

4.4.1.1 ተራኪ ቃል ግጥሞችንየሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 83

4.4.1.2 ባህላዊ ዘፈኖችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 85

4.4.1.3 ቀረርቶና ፉከራን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 87

4.4.1.4 የእረኛ ዘፈኖችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፍይዳ ትንተና 89

4.5. የቃቄ ወርዶወት 91

4.5.1. የቃቄ ወርዶወት ውስጥ የተነሱ ፎክሎረዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 98

4.5.1.1 ጀፎረን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 98

4.5.1.2 የእጆካ ባህላዊ ሽንኻ/ፍርድቤትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 101

4.5.1.3 አንቂትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 104

4.5.1.4 ምርቃትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 107

4.5.1.5 ምሳሌያዊ ንግግሮችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 109

4.5.1.6 ባህላዊ የማዕረግ ስሞችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 110

4.5.1.6.7 ቄግን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 111
4.5.1.6.8 ባህላዊ ዘፈኖችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 114
4.6. የአሻ ልጅ 117
4.6.1. የአሻ ልጅ ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና ..119
4.6.1.1 ጋብቻን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 119
4.6.1.2 የ"አሻ" ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 132
4.7. ፋቡላ 139
4.7.1. ፋቡላ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 139
4.7.1.1 ገላጭ ተረቶችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 140
4.7.1.2 ፋቡላዎችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና 145
ምዕራፍ አምስት 152
5. ከፎክሎራዊ ጉዳዮች የተገኙ ዋና ዋና ፋይዳዎች 152
5.1. ባህላዊ ፋይዳ 152
5.2. ማህበራዊ ፋይዳ 154
5.3 ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ 155
5.4 ስነ ልቡናዊ ፋይዳ 156
5.5 ፖለቲካዊ ፋይዳ 157
5.6 ትምህርታዊ ፋይዳ 158
5.7 ሞራላዊና ግብረገባዊ ፋይዳ 159
5.8 መንፈሳዊ ፋይዳ 159

5.9 ኪነ-ጥበባዊ እና ስነ ጽሁፋዊ ፋይዳ 159
ምዕራፍ ስድስት 161
6. ማጠቃለያ እና ይሁንታ 161
6.1 ማጠቃለያ 161
6.2. ይሁንታ 162
ዋቢ ምች 165
አባሪዎች 177

ሠንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1. አስራሁለቱ ከዋክብትና የባህርያቸዉ ምሳሌ 51

ሰንጠረዥ 2. የፊደላት አቆጣጠር አዋጅና ህግ 52

የአህጽሮተ-ቃላት መፍቻ

ገቢ. = ገቢር

ትዕ. = ትዕይንት

ምዕ. = ምዕራፍ

ዘፍ. = ዘፍጥረት

ጦቢ. = ጦቢያ

ዕብ. = ዕብራዊያን

ቆሮ. = ቆሮንጦስ

ፊሊ. = ፊሊጶስ

ማቴ. = ማቴዎስ

ሉቃ. = ሉቃስ

መዝ. = መዝሙር

AAU = Addis Ababa University

UNESCO = United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization

ሙዳየ- ቃላት

የተዉኔት አላባዉያን = አንድን ተዉኔት ለመጻፍ እንደ ግድግዳ ፣ጣራ ፣ ምሰሶ፣ በመሆን የሚያገለግሉት፣ መቼት፣ ገፀ-ባህሪ፣ ሴራ፣ ቃለ-ተዉኔትና ጭብጥ ናቸዉ ።።

ቴአትር= የተዉኔት ወይም የድራማ ኪነ ጥበብ አጠቃላይ ገጠመኝ ነዉ።። ቃሉ በአጠቃላይ ቤተ-ተዉኔቱን ወይም ህንጻዉን፣ የአገልግሎት ሰጪ ቢሮዎችን፣የተዉኔትን ድርሰት፣ የተዉኔትን ሙያ፣ የተዉኔትን ንቅናቄ፣ እና የአቀራረብ ስልቱ ጥቅል መጠሪያ ነዉ።።

ትዉፊታዊ ቴአትር= በህዝብ ልማዶች፣ እምነቶች ፣ክብረበዓላትና ስነ ቃሎች ላይ ተመስርርቶ የሚመደረክ ባህላዊ ትርኢት።።

ሙዚቃዊ ቴአትር= የተዉኔት፣የሙዚቃና የዉዝዋዜ አላባዉያን በአንድነት ተቀላቅለዉ የሚገኙበት የቴአትር አይነት ።።

ገቢር = የተዉኔት ድርሰት አቢይ ክፍል ወይም መዕራፍ ነዉ።።

ትዕይንት= አንድ ልቦለድ በምዕራፍ ከተከፋፈለ በኋላ ምዕራፉ እንደገና በንዑስ ምዕራፍ እንደሚከፈል ሁሉ በተዉኔት ድርሰትም አብይ ክፍሉ ወይም ገቢሩ በንዑስ ገቢር ሲከፈል ትዕይንት ይባላል።።

ታሪክ= በማንኛዉም ተዉኔታዊ ድርጊት ወይም ክዋኔ በጊዜ ቅደም ተከተል ተዘርዝሮ የሚቀመጥበት ነዉ።።

ገፀ -ባህሪ = በተዉኔት ፣በልቦለድ እና በተራኪ ግጥም ዉስጥ ተሰሎ የሚገኝ የድርሰት ሰዉ ነዉ።።

ተምሳሌታዊ የአጻጻፍ ስልት = ሃሳብን ወይም ቁሳቁስን ወይም ሕይወት ያላቸዉን ና የሌላቸዉን ነገሮች በባህሪና በትርጉም የሚመሳሰሏቸዉን ነገሮች ወክለዉ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ስልት ።።

ጭብጥ= በስነ ጽሁፋዊ ስራዎች ማለትም በተዉኔት፣ በልቦለድና በግጥም ፈጠራዎች ዉስጥ ማዕከላዊ ወይም ገዥ የሚባለዉ ረቂቅ ሀሳብ ነዉ።።

ቃለ-ተዉኔት= ሁለትና ከዚያም በላይ ቁጥር ያላቸዉ ገፀ-ባህሪያት በተዉኔት ድርሰት ዉስጥ እርስ በእርሳቸዉ የሚያደርጉት የምልልስ ንግግር፡፡

ፀሀፌ-ተዉኔት= የተዉኔት ደራሲ ወይም ፀሀፊ፡፡

ታሪካዊ ተዉኔት= በእዉነተኛ ታሪካዊ ሰዎች በተለይም በታላላቅ ነገስታት፣በጦር ጀኔራሎች፣በሃይማኖት ሰዎች እና በሌሎች ታዋቂ ግለሰቦች የህይወት ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚጻፍ የተዉነት አይነ፡፡

አጠቃሎ/ Abstract

ይህ ጥናት በኢትጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳ በተመረጡ ተዉኔቶች ማሳያነት በሚል ርዕስ የተደረገነዉ፡፡ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ጥናናትና ምርምሮች የተደረጉ ቢሆንም፣ በዋናነት የፎክሎርን በቴአትር ውስጥ ከማጥናትና ፋይዳውን ከማሳየት አንጻር እስካሁን በሀገራችን የተደረገ ጥናትና ምርምር የለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የመጀመሪያና ወጥ ሥራ ነው። ጥናቱ ይዞ የተነሳዉ ዓለማ በኢትጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳን በተመረጡ ተዉኔቶች ዉስጥ ማሳየት ነዉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ሰባት ተዉኔች በኢላማ ተኮር የናሙ አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህም ተዉነቶች ፡- ፋቡላ (ተክለ ሀዋርያት ተክለማርያም፣1906)፣ ያላቻ ጋብቻ (መንግስቱ ለማ፣1952) ፣ አልቃሸና ዘፋኝ (ፍስሀ በላይ ይማም፣1952)፣ ሾተላይ (አያልነህ ሙላት፣1991) ፣ የቴዎድሮስ ራዕይ (ጌትነት እንየዉ፣2000)፣ የቃቄ-ወርዶወት (ጫንለዉ ወልደ ጊዮርጊስ፣2005) እና የአሻ ልጅ (አስታጥቃቸዉ ይሁን፣2009) ናቸዉ፡፡ ጥናቱ በዋናነት ያተኮረዉ በተዉኔቶቹ ዉስጥ በተነሱ ስነ ቃልን እና ሀገረሰባዊ ልማድን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሲሆን ከልዩ ልዩ ቲዎሪዎች አንጻር ሰፊ ገለጻ እና ማብራሪያ ተደርጎባቸዋል። ትንተናው የተከናወነው በዋናነት ከተግባር ቲዎሪ አኳያ ሲሆን፣ ትንታናውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ደግሞ ሌሎች ልዩ ልዩ ቲዮሪዎች ማለት ተምሳሌታዊ ቲዎሪ፣አውዳዊ ቲዎሪ፣የክዋኔ ቲዎሪ፣የፎክሎር ዳይክሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ፣የፌሚኒዝም ቲዎሪ፣ የሐይማኖት ቲዎሪና የማህበረሰብ እዉቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ ደጋፊ መተንተኛ በመሆን አገልግለዋል።በተጨማሪም በቃል-መጠይቅ ከተለያዩ ሰዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመጠቀም በአንዳንድ ተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አካባቢያዊናባህላዊ ትርጉም በተሟላ ሁኔታ ተገንዝቦ ለመግለጽ፣ ለመተርጎምናለመተንተን ተሞክሯል፡፡በዚሁ መሰረት በተዉኔቶቹ ዉስጥ የተነሱት ስነ ቃል እና ሀገረሰባዊ ልማድን የተመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ባህላዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ስነ ልቡናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሞራላዊ፣ ግብረገባዊ፣ መንፈሳዊ፣ ስነጽሁፋዊና ኪነ ጥበባዊ ፋይዳ ያላቸዉ መሆኑን የጥናቱ ዉጤት ያመለክታል፡፡ እነዚህን ፋይዳዎች መነሻ

በማድረግም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹን በልዩ ልዩ መስኮች አገልግሎት/ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻልበት ሁኔታ በጥናቱ ይሁንታ ክፍል ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል።

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ገጻዮች ፋይዳን በተመረጡ ተዉኔቶች ዉስጥ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ለማጥናት ከገፋፉኝ ምክንያቶች መካከል አንዱ በፎክሎር እና በቴአትር መካከል ያለው ቁርኝት ነው፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን የቴአትርን አመጣጥ ስናጠና፣ በጥንታዊት ግሪክ፣ ሰዎች አማልዕክቶቻቸውን ለማስደሰት የተለያዩ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ፌስቲቫሎችን እና ከበራዎችን እያዘጋጁ ያቀርቡ እንደነበርና ቴአትርም በዚሁ እንደተጀመረ ይነገራል(The World Book Encyclopedia,Vol 5) :: ከበራዎችና ፌስቲቫሎች ደግሞ በፎክሎር ትምህርት ውስጥ “ህገርሰባዊ ልማድ” ተብለው ይጠናሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እዚህ ላይ መነሳት (መጠቀስ) ያለበት ሌላው ጉዳይ ቴአትር (ድራማ) ህገረሰባዊ ትውን ጥበባትን (Performing folk arts) የሚይዝ መሆኑ እና እነዚህ ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት ደግሞ ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች መካከል የሚመደቡ መሆናቸው ነው (ፈቃደ፣ 1995)፡፡ ይህም በአንድ በኩል ሲታይ የቴአትር መሰረት (Theatre background) ላላቸዉ እንደ እኔ አይነት ሰዎች ፎክሎርን በቴአትር ዉስጥ ለማጥናት የሚያስችል መልካም አጋጣሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ ፡፡ በዚህ ጥናት ፎክሎርን በቴአትር ዉስጥ ለማጥናት ይረዳሉ ተብለዉ የታመነባቸዉ ሰባት ተዉኔቶች የተዳሰሱ ሲሆን፣ እነሱም፡- ፋቡላ (ተክለ ሀዋርያት ተክለማርያም፣ 1906) ፣ ያላቻ ጋብቻ (መንግስቱ ለማ፣ 1952) ፣ አልቃሸና ዘፋኝ (ፍስሀ በላይ ይማም፣1973) ፣ ሾተላይ (አያልነህ ሙላት፣1991) ፣ የቴዎድሮስ ራዕይ(ጌትነት እንየዉ፣2000) ፣ የቃቄ ወርዶወት (ጫንለዉ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ 2005) ፣ እና የአሻ ልጅ (አስታጥቃቸዉ ይሁን፣2009) ናቸዉ፡፡

ጥናቱ በዋናነት ስድስት ምዕራፎችን ይዟል፡፡ በመጀመሪያዉ ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የምርምሩ ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ ፋይዳ ፣ የጥናቱ ወሰን ቀርበዋል፡፡ ክለሳ ድርሳናትን በሚመለከተዉ በምዕራፍ ሁለት፣ የጽንሰ ሀሳባዊ ጽሁፎች ዳሰሳና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ተደርጎአል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ዘዴ ሲሆን የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ አመራረጥ ስልትና የመረጃ መተንተኛ ቲዎሪዎች የሚሉት ቀርበዉበታል፡፡ ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተና ነዉ፡፡ በመሆኑም በተመረጡት ተዉኔቶች ዉስጥ የተሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች በዚህ ምእራፍ ተተንትነዉ ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ አምስት ከፎክሎራዊ ጉዳዮች የተገኙ ዋና ዋና የሚባሉ ፋይዳዎችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ስድስት የጥናቱ ማጠቃለያና ይሁንታ የቀረቡበት ሲሆን በመጨረሻም ልዩ ልዩ አባሪዎች ቀርበዋል፡፡

1.1 ዳራ

1.1.1 ፎክሎርና ቴአትር

በፎክሎርናቴአትር መካከል ያለዉን ቁርኝት ለመረዳት ወደ ኋላ መለስ ብሎ የቴአትር አጀማመርና እድገትን ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ ስለ ቴአትር አጀማመር ሁኔታ እርግጠኛ የሆነ ማስረጃ ባይገኝም፣ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ከሆኑ የአምልኮ ሥርአቶች ሳይመነጭ እንዳልቀረ እና መነሻውም ከወደ ግሪክ እንደሆነ በዘርፉ የተደረጉ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች ይጠቁማሉ፡፡ ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህልም፡-

"The origins of theater go back far into the past to the religious rites of the earliest communities." [1] ይህ ማለት የቴአትር አጀማር ከጥንት ማህበረሰቦች ሃይማኖት እና የአምልኮ ሥርአቶች ጋር እንደሚያያዝ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አጀማመሩን በተመለከተ እንደሚከተለውም ይባላል፡፡ ይኸውም፡-

… no one knows exactly how theater originated. We know where it emerged. In Greece in fifth century B.C.; in India in the fourth century after Christ, and - after being dormant in western civilization-again in Europe in the middle ages.[2]

---

[1] Hartnoll, Phyllis. *A Concis History of the Theatre*. London: Thames and Husson, 1968, p. 7.

[2] Edwin, Wilson and Alvin, Goldfarb, *Living Theatre: An Introduciton to Theatre Hisotry*, 2nd ed. 1994, p. 10.

ሲተረጎም፡-

ቴአትር እንዴት እንደተጀመረ ርግጠኛውን የሚያውቅ የለም፡፡ የሚታወቀው ነገር ቢኖር፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ5ኛው ክፍለ ዘመን በግሪክ፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ4ኛው ክፍለ ዘመን በህንድ እና በምዕራቡ ዓለም የስልጣኔ ዘመን ወቅት (ተደብቆ የቆየ ቢሆንም)፣ በመካከላኛው ዘመን ወቅት በአውሮፓ፣ የተከሰተ ስለመሆኑ ነው፡፡

ሌላው ስለ ቴአትር አጀማመሩ አስመልክቶ የቀረበው ሀሳብ ደግሞ መሰረቱ ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ከበራዎች እንደሆኑ የሚያነሱ አለ፡፡ ይኸውም፡-

... it is often argued that the roots of theatre lie in religious rituals, and this substantiated by Greek theatre's initial connection to rites honoring the god Dionysus, the Roman theatre's relation to festival of Juppiter (Zeus), and the medieval theater's tie with the Roman Catholic Church.[3]

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ከበራዎች ለቴአትር መጀመር ቀደምት መሠረቶች ስለመሆናቸው ብዙዎቹ የሚከራከሩ ሲሆን፣ ማስረጃቸው ደግሞ፤ የግሪክ ቴአትር ታሪክ ከዳይኖስስ ክብረ በዓል፣ የሮማ ቴአትር ታሪክ ከጁቲር (ዚዩስ) ፌስቲቫል እና የመካከለኛው ዘመን ቴአትር ታሪክ ከሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጋር የተገናኘ ነው የሚል ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ግሪክ የመጀመሪያዋ የቴአትር ሀገር ስትሆን፣ ለግሪክ ቴአትር ማደግና መስፋፋት አይነተኛውን ሚና የተጫወቱት ደግሞ የማንነታቸው መገለጫዎች የነበሩት፣ የተለያዩ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሥነ-ስርአቶች፣ በተለያዩ ወቅቶች ያዘጋጇቸው የነበሩት ፌስቲቫሎችና ከበራዎች፣ ለአማልክቶቻቸው ክብር ሲሉ የሚያቀርቧቸው ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡

[3]ibid., p. 21

በተለይ ግሪኮች የወይን፣ የልምላሜና የፈንጠዝያ አምላክ ብለው ለሚጠሩት "ዳይነሰስ" (Dionysus) ክብረ በዓል ይቀርብ የነበረው የ "ዲትራምብ" (The dithyramb) ዝግጅት ለግሪክ ቴአትር ማደግ ጉልህ ድርሻ ነበረው።

Important fore runners of theatre in Greece were religious ceremonies, which were prominent features of Greek society: Funeral services, festivals celebrating the seasons and, ceremonies honouring the gods. Of particular significance to theatre were ceremonies honouring Dionysus, the god of wine, fertility, and revelry.[4]

"ዲትራምብ" (The Dithyramb) ረጅም ስንኝ ያለውና ሃምሳ ዘማርያን "ኮረሶች" (Choruses) በጋራ ሆነው በዳንስ መልክ የሚያቀርቡት የመዝሙር አይነት ነው።

የዝግጅቱ መሪ (The Dithyramb leader) አንድ ታሪክ ድንገት ፈጥሮ (Improvise አድርጐ) ለዘማርያኑ (Choruses) ሲያቀብላቸው (ሲመራቸው) እነሱ ተቀብለው በህብረት ያስተጋቡታል።

በዚህ አይነት ይቀርብ የነበረው ዝግጅት በ600 ዓ.ዓ (600 B.C) አካባቢ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርፅ መያዝ ሲጀምርና ጀግናን የተመለከቱ ታሪኮች (Heroic stories) በስፋት መቅረብ ሲጀምሩ፣ ዝግጅቱ የቴአትር መልክ እየያዘ መጣ።[5]

በወቅቱ ቴአትር በግሪክ ይቀርብ የነበረው በኮረብታማ ሥፍራዎች በተከበቡ ሜዳዎች ላይ የነበረ ሲሆን፣ ተመልካቾችም ኮረብታዎቹ ላይ በሚዘጋጁላቸው መቀመጫዎች ላይ ሆነው ትርኢቱን ይከታተሉ ነበረ። በአብዛኛው ቴአትሮች ለእይታ ይበቁ የነበሩትም በዓመት ሁለት ጊዜ፣ በፀደይ ወር አዝመራ ተሰብስቦ ሲያበቃና በበልግ ወቅት መስኩ መለምለም ሲጀምር እንደነበር እንደሚከተለው ተገልጿል።

[4] Ibid., p. 28

[5] Ibid.,

As Greece is a very mountainous country the only leveled place in many villages would have been the circular threshing of floors, and it was here that the Dionysian dances, in which the whole village took part were probably first performed by 6th century B.C., these which were of a religious nature, took place each year at two great festivals; the first in the spring signifying the re-awakening of earth and the second in the autumn at the completion of the harvest.[6]

ከግሪክ ቀጥሎ የቴአትር ታሪክ የሚያመራው ወደ ጣሊያን ሲሆን፣ ሮማውያን ለቴአትር ዕድገት ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ አብርክተዋል። በተለይ በአቀራረብ በኩል በግሪክ ከነበረው ሁኔታ የተሻለ መሻሻልን አሳይቷል።

The theatre of Roman worlds were very different from those of Greece. They were built on flat ground, not on a hill side, with a vast surrounding wall of masonry, often elaborated, and decorated. The focal point of the Roman Theatre building was therefore the high stages, with tiers of benches in front and elaborate stage wall.[7]

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ቴአትር በሮማ ይታይ የነበረው በግሪክ እንደነበረው፣ በኮረብታማ ሥፍራዎች በተከበቡ ሜዳዎች ላይ ሳይሆን፣ ዙሪያውን በግንብ በተገነባ ለጥ ያለ ሠፊ ቦታ ላይ ነበር። ግድግዳውን በተለያዩ ጌጣጌጦች የሚያስውቡት ሲሆን፣ መድረኩ ለሁሉም ተመልካቾች በሚታይ መልኩ ከፍ ብሎ ይገነባል። በትይዩ ደግሞ ለመቀመጫ የሚያገለግሉ ወንበሮች በደረጃ መልክ ይደረደራሉ።

ከጣሊያን በኋላ ቴአትር ወደ ሌሎች ሃገሮች መስፋፋት የቀጠለ ሲሆን፣ በ16ኛው ክፍለ ዘመን በስፔን፣ በ17ኛው ክፍለ ዘመን በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ፣ በ18ኛው

[6] Hellen and Richard, Leacroft. *The Theatre,* London: Thames and Husson, 1958, p. 2.

[7] Hartnoll, p. 27

ክፍለ ዘመን በጀርመን፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በሩሲያና በአሜሪካ፣ ትልቅ ዕድገት አስመዝግቧል።።[8]

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ቴአትር ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ በመቀጠል ደግሞ በዚሁ ላይ አጭር ዳሰሳ እናደርጋለን።

1.1.2 የኢትዮጵያ ቴአትር አጭር ዳሰሳ

ልክ እንደተቀረው አለም ሁሉ በኢትዮጵያም ቴአትር መቼ እና በምን ሁኔታ እንደተጀመረ ባይታወቅም፣ የክርስትና ሐይማኖት ወደ ሀገሪቱ መግባቱን ተከትሎ ቅፀላው (አስመስሎ መስራቱ) ሳይጀመር እንዳልቀረ ግን ፍንጮች ያመላክታሉ።።

ተስፋዬ ገሠሠ፣ "አጭር የኢትዮጵያ ቴአትር ጥናት ከአጀማመሩ እስከ ከበደ ሚካኤል" (1966 እ.ኤ.አ)፣ በተባለዉ ስራቸው እንደጠቀሱት፣ በሀማማት (አብይ ፆም) ወቅት ካህናትና ቀሳውስት በክርስቶስና በቅዱሳን እየመሠለ መንፈሳዊ አምልኮት ስርዓቶችን ይሠሩ ነበር።። ይህንንም ሲያብራራ፡-

... በሆሳዕና ዕለት አንድ ቄስ ክርስቶስ እንዳደረገው በአህያ ላይ ተቀምጠ በደጀ ሠላም ውስጥ ሲሄድ ሌሎች ቀሳውስት ቄጤማና ዘንባባ በመንገዱ ላይ ያነጥፉታል።። በዕለተ ሰቅለትም ካህናቱና ቀሳውስቱ በክርስቶስና በሌሎች ቅዱሳን እየተመሠሉ ይሠራሉ።።[9]

ቴአትር በኢትዮጵያ ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቶ በመድረክ መቅረብ የጀመረው፣ ከሌሎች ሀገሮች አንፃር ሲታይ፣ በ20ኛው ክ/ዘመን መባቻ ዘግይቶ ሲሆን፣ ይህም የሀገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መሻሻልና ከሌሎች ሀገሮች ጋር ያላትን ግንኙነት ማስፋፋት ተከትሎ የመጣ እንደሆነ ይታመናል።።

[8]Helen and Richard, 1958 pp. 223-224

[9]ተስፋዬ ገሠሠ፣ "አጭር የኢትዮጵያ ቴአትር ጥናት፣ ከአጀማመሩ እስከ ከበደ ሚካኤል " ፣ ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሁለተኛው አለም አቀፍ ጉባዔ የቀረበ ጥናት፣ 1966 (እ.ኤ.አ.)

When Ethiopia has shed her policy of isolation that the first professional drama of the western concept was staged in the prescence of his Imperial Majesty Menelik II a comedy based on the fables of Lafontaine.[10]

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ቴአትር ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ተደርጐ የሚወሰደው "ፋቡላ" የተሰኘው የበጅሮንድ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም የቴአትር ድርሠት መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡-

...ለመጀመሪያ ጊዜ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት 1903 ዓ.ም እ.አ.አ "ፋቡላ" /የእንስሳት ተረት/ የተሰኘው ቴአትር ቀረበ፡፡ ይህ ቴአትር በእንስሳት እያስመሠለ በጊዜው የነበረውን ሹማምንት ጉድለት ስለሚነቅፍ ለህዝብ እንዳይታይ ተከልክሎ ነበር፡፡ ይህም በበጅሮንድ ተክለሐዋርያት የተደረሰው ቴአትር በመድረክ ላይ በመቅረብ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነበር፡፡[11]

ምንም እንኳ በጅሮንድ ተክለሐዋርያት በወቅቱ ይኖሩበት በነበረው ሥርዓት ያስተዋሏቸውን ህፀያችና ጉድለቶች ነቅሰው በዚህ የቴአትር ድርሠታቸው አማካኝነት ለማሳየት የሞከሩ ቢሆንም፣ ይህ ጥረታቸው ግን አልተሳካም፡፡

... ይህ ጥቅም ያለው የትያትር መፅሐፍ ከቡር በጅሮንድ ተክለሐዋርያት ጸፈው፣ ለህፃናት አስጠንተው በሺህ 9/03 ዓመተ ምህረት በሙሴ ቴራስ ሆቴል የትያትሩን ጨዋታ አሳይተው፣ ጥቂቶቹን ሰዎች እንጂ ብዙዎቹን ሰዎች ደስ ለማሰኘት አልሆነላቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚያ ዘመን ከአዋቂዎች አላዋቂዎች በህይል ሰለ በዙ ነው፡፡[12]

ይሁን እንጂ፣ በበጅሮንድ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም ፈር ቀዳጅነት የተጀመረው የኢትዮጵያ ቴአትር እያደር እያደገና እየተስፋፋ ከመሄድ የገታው ግን አልነበረም፡፡

---

[10] Hail Selassie I Theatre publication(1970) . Addis Ababa. Artistic Printers. P.19

[11] እዮኤል ሙሉጌታ፣ "የቴአትር ይዘት በኢትዮጵያ እስከ 1966 ዓ.ም" 1972 ዓ.ም፣ ገፅ 8

[12] ብርሃንና ሰላም (ጋዜጣ)፣ ፷ኛ ዓመት ቁጥር ፱፣ አ.አ ህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፱

ለዚህ ደግሞ፣ በተለይ፣ የዳግማዊ ምኒልክና የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቶች አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡

በ1917 ዓ.ም የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሲከፈት በመምህራንና ተማሪዎች እየተዘጋጁ የሚቀርቡ ትያትሮች ነበሩ፡፡ በዚህም ጊዜ ትያተር እየደረሱና እያዘጋጁ የነበሩት ዮፍታሔ ንጉሴ ነበሩ፡፡ አቶ ዮፍታሔ ንጉሴ በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ትልቅ ሰጠታ የነበራቸውና አያሌ ግጥሞችንና ቅኔዎችን የደረሱ ናቸው፡፡[13]

ከነዚህ ሁለት ትምህርት ቤቶች በመቀጠል በኢትዮጵያ የቴአትር ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ይዞ የሚገኘው የቀድሞው "የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር"፣ የአሁኑ የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር የተመሠረተው ሐምሌ 11 ቀን 1927 ዓ.ም ሲሆን፣ ዓላማውም በወቅቱ ኢትዮጵያን ለመውረር ተዘጋጅቶ የመጣውን የጣሊያንን ጦር ለመመከት በዚህ ማህበር አማካኝነት ቅስቀሳ ለማረግ ነበር፡፡

... ኢትዮጵያ የመጣባትን በዘመናዊ ትጥቅ የተጀራጀ ጦር ለመመከት አቅሟ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ያላትን ሰራዊት በአግባቡ አሰታጥቃ እንዳታዋጋ ቀደም ሲል ሦስቱ ሐያላን መንግስታት ፈረንሳይ፣ እንግሊዝና ኢጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ እንዳይገባ በሚል እ.አ.አ በ1930 ዓ.ም ተዋውለው አግደውባት ስለነበር ለጊዜው ባላት መሳሪያ እንኳን ሐይሏን ለማደራጀትና የዘማች ሠራዊቱ ስንቅና ትጥቅ እንዲሟላ ህዝቡን ለማስተባበርና ለመምራት የማህበሩ መመስረት አሰፈላጊ ነበር፡፡ በተጨማሪም ህዝቡ በመካከሉ የነበረውን የዘር፣ የጦሳና የሃይማኖት ቅራኔ አስወግዶ በአንድነት መንፈስ በመነሳሳት ሀገሩን ከባዕድ ተገዥነት ማዳን እንዳለበት ለማስገንዘብና የኢጣሊያን የፖለቲካ ቢሮ የሚያካሂደውን ሰውር ውጊያ ለማክሸፍ የመወያያ መድረክ አሰፈለገ፡፡[14]

---

[13]ተስፋዬ ገሠሠ፣ "አጭር የኢትዮጵያ ቴአትር ጥናት ከአጀማመሩ እስከ ከበደ ሚካኤል" ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሁለተኛው አለም አቀፍ ጉባዔ የቀረበ ጥናት፣ 1966 እ.ኤ.አ

[14]ሀገር ፍቅር (ልዩ መጽሄት)፣ 1991 ዓ.ም፣ ገጽ 2

የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር ሥራውን ያካሂድ የነበረው በስብከት፣ በግጥም፣ በዜማ፣ በስዕል፣ በፉከራና ቀረረቶ ወዘተ ነበር። እንደነ ዮፍታሔ ንጉሴ፣ መላኩ በጮሠው፣ አገኘሁ እንግዳ፣ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣ ተሰማ እሸቴ፣ ተስፋ ገብረስላሴ፣ ወዘተ.... የመሳሰሉት ባለቅኔዎች፣ ሰዓሊያን፣ ደራሲያን በግጥም፣ በመዝሙር፣ በስዕል ወዘተ... እንደነ መንግሻ ከፈላ፣ ሀጂ በዳሶ፣ ደምስ ወልደአማኑኤል፣ ተመስገን ገብሬ ወዘተ... የመሳሰሉ የንግግር ጥበብ አዋቂዎች በማራኪና ስሜት ቀስቃሽ ስብከታቸው በየአደባባዩና በተለይም ዳግማዊ ምኒሊክ አደባባይ ወደ ፒያሳ መቀልበሻ ላይ በተሰራ ፎቅ ህንፃ ሠገነት ላይ በመሆን ህዝቡን ቀስቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር ከምስረታው ዕለት ጀምሮ ለ10 ተከታታይ ወራት ተጋድሉ ሲያደርግ ቆይቶ ጣሊያን ኢትዮጵያን ይዛ በቆየችባቸው አምስት ዓመታት ውስጥ ይፋ እንቅስቃሴው ተቋርጧል።[15]

ይሁን እንጂ በ1933 ዓ.ም በኢትዮጵያ ህዝብ ተጋድሎና በአርበኞች ጥረት ጣሊያን ከሀገራችን ሲባረርና ነፃነት ሲመለስ በወረራው ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር "የወጣቶች ምንጭ የሀገር ፍቅር ማህበር" በሚል ስያሜ ሚያዚያ 5 ቀን 1933 ዓ.ም በአቶ መንግሻ ከፈላ መሪነት እንደገና ተቋቋመ።

የሀገር ፍቅር የወጣቶች ምንጭ የህዝብ ሠበካ ማህበር ሥራውን ሲያካሂድ ቆይቶ አቶ መኮንን ሀብተወልድ ከፈረንሳይ ሀገር ሲመለሱ በ1933 ዓ.ም ማህበሩን ይመሩ ከነበሩት አቶ መንግሻ ከፈላና ከአጋሮቻቸው ጋር ቅራኔ ውስጥ ወደቁ። በወቅቱ ቅራኔው ለንጉሠ ነገሥቱ ደርሶ ተሰማምታችሁ ሥሩ የሚል መልስ በመስጠቱ ሥራው በአቶ መኮንን ሀብተወልድ መሪነት ቀጠለ። አቶ መንግሻ ከፈላም ሥራቸውን ወጣቶችን በማስተማር ብቻ በመወሰን ከሀገር ፍቅር ማህበር አፈገፈጉ።... አቶ መኮንን ሀብተወልድ በእርሳቸው መሪነት በለውል መኮንን ኃይለሥላሴ የበላይ ጠባቂነት የጣሊያኖች የነበረውንና የዛሬውን የሀገር ፍቅር

[15]ሀገር ፍቅር (ልዩ መጽሄት)፣ 1991 ዓ.ም፣ ገፅ 5

ቴአትር የመለማመጃ ትንሽ አዳራሽ ከንጉሱ አስፈቅደው የማህበሩ ፅህፈት ቤትና የሰብከት ቦታ በማድረግ ሥራውን ያራምዱ ጀመር፡፡[16]

ከጣሊያን ወረራ በኋላ በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ቀርበው ተወደጅነትን ካተረፉት ቴአትርቶች መካከል "አፋጀሽኝ" የተሰኘው የቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሴ ድርሰት አንዱ ሲሆን፣ ይዘቱም ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ከመውደቋ በፊት በሽተኛ ሆና፣ ሐይለልዑል የተባው ልጇ ከተበጣባጭ ልጆቿና ከሀሰተኛ የባዕድ ልዑካን ለማዳን የሚያደርገውን ጥረት የተመለከተ ነው፡፡

የሀገር ፍቅር ቴአትር (በቀድሞ ስሙ የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር) ተቀባይነትን እያገኘ ሲሄድ በ1948 ዓ.ም አሁን ቴአትር የሚቀርብበት ትልቅ አዳራሽ ተሠራና አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡ ቀደም ሲል በ1939 ዓ.ም ተጀምሮ የነበረው የአርቲስቶች ቅጥርም ቀጥሎ በርካታ የቴአትርና የሙዚቃ ባለሙያዎችን ለማሰባሰብ ተቻለ፡፡

በ1948 ዓ.ም ሌላኛው በኢትዮጵያ የቴአትር ዕድገት ውስጥ ትልቅ ሥፍሪ ይዞ የሚገኘው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር ግንባታ ተጠናቆ በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ተመርቆ ተከፈተ፡፡ ይህ ቴአትር ቤት በቀድሞው የትምህርትና ሥነ-ጥበብ ሚኒስቴር ሥር ይተዳደር የነበረ ሲሆን፣ ከ1954 ዓ.ም ጀምሮ በማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ከ1966ቱ ህዝባዊ አብዮት በኋላ ደግሞ በባህል ሚኒስቴር ሥር እንዲሆን ተደርጓል፡፡[17] የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ተዋንያን ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ስር ለፋንፋር ሙዚቃ (የሰልፍ ሙዚቃ) እና ለቴአትር ተመልምለው የነበሩት አባላት ሲሆኑ እነዚህም ስመ ጥር ከነበሩት ሰዎች መካከል፣ አውላቸው ደጀኔ፣ ተስፋዬ ሳህሉ፣ ተስፋዬ ተሰማና ጌታቸው ደባልቄ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር በቴአትር ደራሲነት፣ አዘጋጅነትና ተዋናይነት ስመ ጥር ከነበሩት ሠዎች መካከል፣ፀጋዬ ገብረመድህን፣ ተስፋዬ ገሠሠ፣ ጌታቸው አብዲ ማንያዘዋል እንደሻው፣ጌትነት እንየው፣ ከሴቶችም፣ አስናቀች ወርቁ፣ አስካለ አመንሸዋ፣ አለምፀሀይ ወዳጆ ይገኙበታል፡፡

---

[16]ሀገር ፍቅር (ልዩ መጽሄት)፣ 1991 ዓ.ም፣ ገፅ 6

[17]የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር በአሁኑ ጊዜ በባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ስር ይገኛል፡፡

ከ1966 ዓ.ም በኋላ ሌሎች ተጨማሪ ቴአትር ቤቶች ማለትም፣ (ራስ ቴአትር፣ የአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ እና የህፃናትና ወጣቶች ቴአትር) ፣ ተከፍተው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ በዚህ ወቅት ይቀርቡ የነበሩ ቴአትሮችም፣ በአብዛኛው፣ አብዮቱን እና አብዮቱ ያስገኛቸውን ትሩፋቶችን የተመለከቱ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ይዘት የነበራቸው ቴአትሮች ነበሩ፡፡[18]

1.2 የጥናቱ መነሻ

ፎክሎር ከተለያዩ የጥናት መስኮች ጋር የሚዛመድ ብዘሃ ትምህርት እንደመሆኑ፤ ከሚያጠናቸው የትምህርት መስኮች መካከል ቴአትር አንዱ ነው፡፡ ይሁንና በሀገራችን ፎክሎርና ቴአትርን በተመለከተ የተደረጉ ጥናትና ምርምሮች፣ በተለይ በድህረ ምረቃ ደረጃ የሚገኙት፣ ቁጥራቸው እጅግ ዝቅተኛ ከመሆኑ አንፃር ጨርሶ የሉም ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይህም በአንድ በኩል በዘርፉ የእውቀት ክፍተት እንዳለ የሚያመለክት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ክፍተቱን ለመሙላት ከፎክለርና ከቴአትር ጋር የተያያዙ በርካታ ጥናትና ምርምሮችን ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ነው፡፡ ለዚህ ጥናት መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች መካከልም አንዱ ይኸው ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የፎክሎር ፋይዳ በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ ምን ይመስላል የሚለዉ በጥናትና ምርምር አለመታወቁም እነዲሁ እዚህ ላይ የሚጠቀስ ሌላዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ የሀገራችን ፀሐፌ-ተውኔቶች በስራዎቻቸው ያነሷቸውን ፎክሎርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ከ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች ፋይዳዎች አንፃር በማጥናት፣ በሌሎች ሀገሮች እንደተደረገዉ ሁሉ በሐገራችንም ፎክሎርን ለተለያዩ ግልጋሎቶች መጠቀም ሲቻል፣ እስካሁን ይህ ሲሆን አልተስተዋለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ የተነሱ ስነ ቃላዊ ጉዳዮችን ፋይዳ በማጥናት ጥቅም ላይ የሚውለበትን መንገድ ለማሳዬት ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡

[18]Zelalem Getahun. “Amharic Political Plays (1974-81) A Contextual Study” MA. Thesis School of Graduate Studies, Addis Ababa University. 1997.

ሌላዉ የዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት የአጥኝዉን የአካዳሚና የግል ተሰጥኦ መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ በተፈጥሮ ለቴአትር ያለኝ ቅርበትና በዘርፉ ተማሪ ሆኜ ማለፌ ፎክሎርን በቴአትር ዉስጥ ማጥናት ብችል የተሻለ የምርምር ስራ ማቅረብ እችላለሁ የሚል እምነት እንዲያድርብኝ አድርጎኛል፡፡ለዚህም ይመስለኛል ገና ከጅምሩ የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከበርካታ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል መርጦ በዚህ ዙሪያ እንዳጠና የፈቀደልኝ፡፡

1.3 የምርምር ጥያቄዎች

በኢትዮጵያ ቴአትር ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ገዳዮች ምን ፋይዳ አላቸዉ ? የሚለው በዚህ ጥናት የሚመለስ አቢይ ጥያቄ ሲሆን፣ ሌሎች ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ዝርዝር ጥያቄዎች ደግሞ ፡-

1. በኢትዮጵያ ቴአትር ለማሳያ በተመረጡ ተዉኔቶች ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘት ምን ይመስላል?
2. በአንዳንድ ተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከዘመን አንጻር ምን የሚገልፁት ነገር አለ?
3. ከጭብጥ (ፍሬ ሀሳብ) አንፃር ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ምን የሚስተላልፉት ነገር አለ?
4. ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከተግባራዊ ፎክሎር አኳያ በምን በምን መሰኮች ላይ ዉለዉ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ? የሚሉት ሲሆኑ፣ በጥናቱ መልስ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

1.4 የጥናቱ ዓላማ

1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ፋይዳ በተመረጡ ተዉኔቶች አስረጅነት ማሳየት ሲሆን በዚህ ዋና አላማ ስር የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ተነድፈዋል፡፡

1.4.2 ዝርዝር ዓላማዎች

1. የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዘት መግለፅ፣
2. በአንዳንድ ተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከዘመን አንጻር ምን የሚገልጹት ነገር አለ? የሚለዉን ማወቅ፣
3. ስነ ቃላዊ ጉዳዮቹ ከቀረበው ተውኔት ጭብጥ (ፍሬ ሀሳብ) ጋር እንዴት መስተጋብር እንደፈጠሩ ተንትኖ ማሳየት፣
4. በተውኔቶቹ ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን መንገድ መግለጽ።

1.5 የጥናቱ ፋይዳ

ፎክሎርን በመሰብሰብና በማጥናት ጥቅምላይ ማዋል እንደሚቻል የተለያዩ ሀገራት ልምድና ተሞክሮዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ፣ ስዊዲን ረጅም ታሪክና ባህል ያላት ሀገር መሆኗን ለሌሎች ተቀናቃኞቹዋ የአዉሮፓ ሀገሮች ለማሳየት፣ ፊንላንድ በታላቁ የሰሜን ጦርነት ምክንያት ከደረሰባት ጉዳት ለማንሰራራት ይረዳት ዘንድ የነደፈችዉን የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራም ለማስፈጸም፣ ጀርመን ጠንካራ ብሄርተኝነትን ለመፍጠር፣ አሜሪካ ለትምህርትና ለቱሪዝም መስህብነት ፎክሎርን ተጠቅመዉበታል። [19] ይህም የሚያሳየዉ ፎክሎር እንደየሀገሩ ነባራዊ ሁኔታ የተለያዩ አገልግሎቶች መስጠት የሚችል መሆኑን ነዉ። ከዚህ አንጻር ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ቴአትር ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ፋይዳ በማጥናትና ጥቅም ላይ የሚዉሉበትን መንገድ በማሳየት ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲሁም ጥናቱ የፎክሎር ትምህርት ከቴአትር ሙያ ጋር የሚተሳሰርበትንና በባለሙያዎች መካከል የእውቀት ሽግግር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ከማሳየት አንጻር ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል። በተጨማሪም ወደፊት በቴአትርና በፎክሎር ዙሪያ የተለያዩ ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎችና ሌሎች ባለሙያዎች እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

---

[19] ፈቃደ አዘዘ (አርታኢ ሺፈራው በቀለ) *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ ቁዘማ፣ ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ* (በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች)፣ ኤክሊፕስ ማተሚያ ቤት፣ 2004 ዓ.ም ገጽ 117-122።

1.6 የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰን ከቴአትርና ከፎክሎር (ከሁለቱም) አንጻር የሚታይ ነዉ። ከቴአትር አንጻር ያለዉ የጥናቱ ወሰን ከጥናቱ ዓላማ ይመነጫል። የጥናቱ ዓላማ በኢትዮጵ ቴአትር ውስጥ የተነሱ ስነ ቃላዊ ጉዳዮችን ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች አስርጅነት ማሳየት እንደመሆኑ፣ ወነኛ ትኩረቱ ፎክሎራዊ እንጂ ቴአትር ነክ ጉዳች ላይ አይደለም። በመሆኑም ከገፀባህርያት አሳሳል፣ ከሴራ አነዳደፍ፣ ከታሪክ አወቃቀር፣ ከመቼት (setting) አጠቃቀምና ሌሎች ከቴአትር ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ አላባዉያንን በጥልቀት አይመለከትም። ይህ ማለት ግን ከፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና ጋር በተያያዘ አይነሱም ማለት አይደለም።

ከፎክሎር አንጻር ይህ ጥናት ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች መካከል በተዉኔቶቹ ዉስጥ የተነሱትን ስነ ቃላዊና ሐገረ ሰባዊ ጉዳችን በማጥናት ላይ ብቻ የተገደበ ነዉ። ምክንያቱም የምርምር ስራ ጊዜና ገንዘብን ባገናዘበ ሁኔታ የሚሰራ በመሆኑነዉ።

ይህ ማለት ግን በፍክሎር ጥናት ዘርፎች ውስጥ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ የልዩነት መስመር አለ ማለት አይደለም። ይልቁንም እርስ በርስ የተሳሰሩ በመሆናቸዉ አንዱን ስናነሳ ምናልባት ሌላዉን መንካታችን አይቀር ይሆናል። ለምሳሌ በዚህ ጥናት በተዉኔቶቹ ዉስጥ ስለተገለጹት የስነ ቃላዊ ጉዳዮችን ክዋኔ ስናነሳ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስላለዉ ፣ ስለ ገፀ ባህርያት ባህላዊ አለባበስ፣ ስለሚገለገለባቸዉ ባህላዊ ቁሶች ወዘተ. መጥቀሳችን አይቀር ይሆናል። ይህም ቀደም ሲል እንደተገለጸዉ የፎክሎር ዘርፎች አንዳቸዉ በአንዳቸዉ ዉስጥ የሚገቡ መሆናቸዉን የሚያመለክት ነዉ።

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ፅንሰ ሀሳባዊና እንዲሁም ተዛማጅ ጥናቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች የተቃኙበት ነው። እነዚህም በአንድም በሌላም መንገድ ከዚህ ጥናታዊ ምርምር ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች የተዳሰሱበት ናቸው። የፅንሰ ሀሳብ ዳሰሳን አስመልክቶ ስለ ፎክሎር ምንነትና ሚና ፣ ሰለ ተግባራዊ ፎክሎር ፣ ስለ ስነ ቃል ምንነትና ፋይዳዉ በዝርዝር የቀረበበት ነው። የተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት በተመለከተ ቴአትርና ፎክሎርን አስመልክቶ በአገር ዉስጥ እና በዉጭ አገሮች የተሠሩ ተዛማጅ ጥናቶች የታዩበት ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች የተዳሰሱበትነው።

2.1. ጽንሰ ሐሳባዊ ጽሁፎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የተካተቱት ጉዳዮች ጥናቱ የሚከናወንበትን ዲሲፒሊን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን ከጻፏቸው ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ጽንሰ ሀሳቦች ምንነትና ጠቀሜታ ላይ ያተኮሩ ናቸው። በመሆኑም ስለፎክሎር ምንንትና ፋይዳ፣ ስለ ፎክሎር ምደባ፣ ስለ ተግባራዊ ፎክሎር፣ ስለ ስነቃል ምንነትና ፋይዳ፣ ስለ ሀገረሰባዊ ለማድና ስለ ሀገረሰባዊ እምነት ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር የምንመለከት ይሆናል፡፡

2.1.1 የፎክሎር ምንነትና ፋይዳ

ፎክሎር[20] የሚለው ቃል ህዝብና ልማድ የሚሉ የሁለት ጽንሰ ሃሳባዊ ቃላት ውህድ ነው (Schoemaker 1990፡3)። ህዝባዊ የሚለው ቃል ቡድናዊ የሆኑ ሰዎችን የያዘ

[20] ፎክሎር የሚለዉን ቃል ለመጀመሪያ የተጠቀመዉ Willan John Thoms የተባለ እንግሊዛዊ ሲሆን ይኽዉም እ.ኤ.አ በ1846 The Atheneaum ለተባለዉ ጆርናል በጻፈዉ ደብዳቤ ነበር፡፡ በወቅቱ የ Willian ዓላማ በእንግሊዝ ሀገር አሮጌ ጥናቶች (Antiquarian) በሚል ስም ይጠሩ የነበሩትን የአሮጌ ህንጻ፣ የአሮጊት ተረት፣የአሮጌ ባህል፣የአሮጌ ዘፈን የአሮጌ መዝገበ ጥናቶች ወዘተ. በአዲሱ ሰም(ፎክሎር) ለመተካት በማሰብ ሲሆን በዚህ ርዕስ ይጠሩ የነበሩትም ጥንታዊ ህይዎትን የሚገልጹ ነበሩ(ፈቃደ፣1991፣ Shoemaker, 1990).

አካል ሲሆን ልማድ ደግሞ በባህል ክፍል ውስጥ የሚመደብ ነው። የሰው ልጅ ማህበራዊ በመሆኑ እንደ ሰው ልጅነታችን ሁላችንም በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተሳታፊዎች እንደሆን፤ ከዚህም የተነሳ አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባትና ግንኙነት መፍጠር እንደሚችል ተጽፏል። ከዚህ አገላለጽ ጋር በሚስማማ ሁኔታ ፈቃደ (1998፡2) "ፎክሎር ህይወት ስለሆነ" በግለሰብም ይሁን በማህበረሰብ ደረጃ የእለት ተእለት አኗኗር ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም ነገር እንደሚያጠቃልል ያስረዳል። ከዚህ ገለፃ መነሻነት ፎክሎር የሚለው ቃል ማንኛውንም የሕዝብ ቡድን የሚመለከት ሆኖ ቢያንስ አንድ በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ያላቸውን የጎብረተሰብ ክፍል የሚገልጽ መሆን እንዳለበት እንረዳለን፡፡

በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ትምህርት፣ ሥራ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣...ወዘተ ሊሆን ይችላል (Dndes, 1965)። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፎክሎር ማለት ጥበባዊ ተግባቦት ያላቸው የጎብረተሰብ ቡድን መሆኑንና በቡድኑ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ሰዎቹ የሚናገሩትን፣ የሚያደርጉትን፣ የሚሠሩትን ...ወዘተ ጉዳዮች የተመለከተ መሆኑን Ben-Amos (1971:13) ይገልጻል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ፎክሎር የሚለውን ቃል ፈቃደ አዘዘ (2003) ለማስተማሪያነት መርጦ ባደራጀው ማቴሪያል ውስጥ (Steiner Mathisen, 1999:35) Dundesን ጠቅሶ፣ ፎክ እና ሎር በማለት ቃሉን ለሁለት በመክፈል ብያኔ ይሰጣል። ይሄም "ፎክ (folk) አንድ የጋራ ነገር ያላቸው የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ይመለከታል። "በማለት ሎር (lore)ን ደግሞ "የጋራ የሆነውና ያ የሚያገናኛቸዉ እውቀት ነው፤ የጋራ እውቀቱ ምንም ይሁን ምን ሎር ይባላል።" በማለት የሚያገናኛቸው ዋናው ነገር የጋራ ልማድ (tradition) መሆኑን ይገልጻል። ባጭሩ ፍክሎርን የሁለት ክዋኔዎች መግለጫ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፤ ሰዎች በዘልማድ የሚናገሩት እና ሰዎች በዘልማድ የሚተገብሩት የሰዎች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ባህል ነው ማለትም ይቻላል (ፍቃደ አዘዘ፣ 1996፡ v)። ከዚህ የምንረዳው ፎክሎር ከሰዉ ልጅ ሕይወት ጋር የተያያዘ የዕለት ተዕለት ባህላዊ ጉዳዮች የሚንጸባረቅበት መሆኑን ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን እሳቤዎች በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) እኤአ 2010 “Basic Texts of the 2003 Convention for the Safeguarding of the Intangible Cultural Heritage” በማለት አንድ ሰነድ አውጥቷል። በሰነዱ ውስጥ “Intangible Cultural Heritage” ተብሎ የቀረበው ጽንሰ ሀሳብ የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ የያዘ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/92 የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ ግዙፍነት ከሌለው የሰው ልጅ እውቀት አንጻር ይመለከተዋል። “ግዙፍነት የሌለው ቅርስ ማለት በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን በዓይን ለማየት፣ በጆሮ ለመስማት የሚቻል ቅርስ ሲሆን የብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርዒትና ጨዋታ፣ ሥነ ቃል፣ የሃይማኖት፣ የእምነት፣ የጋብቻ፣ የሐዘን ሥነ-ስርዓት፣ ሙዚቃ፣ ድራማና ሌሎች ተመሳሳይ ባህላዊ እሴቶች፣ ወግና ልማድን ይጨምራል” በማለት ይተረጉመዋል። በዚህ ትርጉም መሠረት ኢንታንጅብል ባህላዊ ቅርስ የማይዳሰስ የሰው ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ ክዋኔ ውጤት መሆኑን እንረዳለን።

ፎክሎር አንድ ሕዝብ በማህበራዊና ባህላዊ ሕይወቱ ውስጥ ማሕበረሰቡ የሚገኝበትን ሁኔታ በማንጸባረቁ ረገድ የተለየ ሚና እንዳለው በርካታ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከእነዚህም መረጃዎች ውስጥ Dundes, (1965) ፎክሎር ያለፈውን የሚያወሳ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ የእውቀት ምንጭ በመሆኑ በዕለታዊ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ውስጥ ወቅታዊ የትኩረት ጉዳዮችን በማሳየት ባህላዊና ሥነልቦናዊ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በጭንቀት ምክንያት ድብቅ የሆኑ ጉዳዮችን ሳይቀር ይፋ የማድረግ አቅም እንዳለው በፎክሎር ትንተናው ላይ ያብራራል።

በሌላ አገላለጽ Ben-Amos, (1979) ፎክሎር ማህበረሰቡ በቋንቋው አማካይነት ባህላዊ እሴቶቹን የሚገልጽበት መስታወት ከመሆኑ አንጻር የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫና በውስጡም በርካታ እሴቶችን ያካተተ መሆኑን ይናገራል። በመሆኑም ፎክሎር አገልግሎት ለሚሰጥበት ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ንብረቱ እንደመሆኑ መጠን የሕዝቦችን ልማድ፣ ወግ፣ እምነት እና ጥበቦችን ያካተተ የባህል ዘርፍ መሆኑን ገልጿል።

2.1.2 የፎክሎር ምደባ

የፎክሎር ምደባን በተመለከተ Dorson “በመስኩ የሚደረግ ምርምርን ስርዓት ለማስያዝና... መልክ ለመስጠት ሲል...” ፎክሎርን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈለው መሆኑን ፈቃደ (1991፣ 2-4) ይገልጻል። እነርሱም ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል ናቸው። ዩኔስኮ ደግሞ ይህን ምደባ እንዳለ ይወስድና ሀገረሰባዊ ልማድን ለሁለት በመክፈል “Intangible Cultural Heritage” የሚለውን ጨምሮ በአምስት መድቧቸዋል። አምስተኛው “የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ” ይለዋል። ነገር ግን የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ ራሱን ችሎ የሚወጣ ሳይሆን በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘ ነው። በዚህ ጥናት ፎክሎርን በአራት አበይት ዘርፎች ከፍሎ ማየት የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በፈቃደ (1991) አራቱ አበይት የፎክሎር ዘርፎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሀ/ ስነቃል፡- በዚህ ምድብ የሚካተቱት የፎክሎር ዓይነቶች የሰው ልጅ ምኞቱን፣ ፍላጎቱን፣ ችግሩን፣ ደስታውን፣ ሐዘኑን፣ ደግነቱን፣ ተግባሩን ወዘተ... ሁሉ በቃሉ የሚገልጽባቸው ናቸው። እነዚህም ቃል-ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ቀልዶች፣ አፈታሪኮች እና ሌሎችም በቃል የሚከወኑ ናቸው።

ለ/ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፡- ይህ የፎክሎር ዘርፍ ሀገረሰባዊ ሙዚቃን፣ ዳንስንና ድራማን የሚያቅፍ ነው። ሀገረሰባዊ ሙዚቃ በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በትንፋሽ ወይም በምት አማካይነት ድምፅ የሚሰማበት የሙዚቃ አይነት ነው። ዳንስ ደግሞ የተለያዩ የሰውነት አካላትን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሞዴራ፣ እስክስታ፣ ዳንኪራ ወዘተ...ነው። ሀገረሰባዊ ድራማ ወይም ቴአትር በሰው ልጅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ የሚያተኩሩ ትዕይንቶችና ትረካዎች የሚታዩበት ነው። ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ዳንስና ድራማ ሦስቱ ብቻቸውን የቆሙ ሳይሆኑ በተግባር አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው።

ሐ/ ሀገረሰባዊ ልማድ፡- በዚህ የፎክሎር ዘርፍ የሚጠቃለሉት የሰው ልጅ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም ፍላጎቶቹን ለማሟላት በግልና በጋራ የሚያከናውናቸው ድርጊቶች ናቸው። እነዚህም የሰው ልጅ የህይወት-ዑደት (ልደት፣

ጋብቻ፣ ሞት)፣ የእምነት፣ የማህበራዊ ደረጃና ክብር መገለጫ፣ የሥርዓተ ፆታ፣ የስም አወጣጥ፣ የሰውነት አጋጌጥ፣ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት፤ ሥነ ስርዓቶች፣ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች፣ ስፖርት ወዘተ ... ናቸው።

መ/ ቁሳዊ ባህል፡- በዚህ ውስጥ የሚካተቱት የሰው ልጅ በመደበኛ ትምህርት ሳይሆን በምልከታና በተግባር በሚያገኘው ልምድ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ማተሪያሎችን የሚሰራበት ክህሎት ነው። ይህም የእንጨት፣ የቆዳ፣ የሸክላ፣ የሳር፣ የብረት እና ሌሎችም የእደ ጥበብ ውጤቶችንና የአሰራር ጥበባቸውን የሚያጠቃልል ነው።

2.1.3 ተግባራዊ ፎክሎር

*Studie*s in African applied folklore በሚለዉ መፀሐፉ Hurreiz(2006,12) "ተግባራዊ" (Applied) የሚለውን ቃል እንዲህ በማለት ይበይነዋል፡፡ " The term applied is used in a general sense meaning to put to practical use and in a specific sense which means, concerned with concrete problems rather than with fundamental principles."

ሲተረጎም ፡-

"ተግባራዊ የሚለው ቃል በጥቅሉ ሲታይ አንድን ነገር ለሆነ ተግባር ማዋል (መገልገል) ወይም መጠቀም የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን፣ በዋናነት ደግሞ መሠረታዊና ቁልፍ ለሆኑ መርሆች ትኩረት መስጠት ማለት ነወ፡፡ "

በሌላ በኩል ደግሞ Hurreiz "ፎክሎር" የሚለውን ቃል Dorson (ን) በመጥቀስ፣ አራት የጥናት ዘርፎችን ማለትም፣(ስነ ቃልን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ ሐገረሰባዊ ልማድን፣ እና ሐገረሰባዊ ትውን ጥበባትን) የሚያጠቃልል መሆኑን ይገልፃል ፡፡ "... in the following studies the term folklore incorporates the four sectors proposed by Richard Dorson, namely oral literature, material culture, folk custom (and belief) and performing folk arts" (2006,12).

ከዚህ የ Hurreiz ብያኔ በመነሳት፣ ተግባራዊ ፎክሎር ማለት በጥቅል በስማቸው ፎክሎር ተብለው የሚጠሩት (ስነ-ቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና እምነት እና

የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት) ግልጋሎት (ጥቅም) የሚሰጡበትን መንገድ የሚመለከት ነው ብሎ መዉሰድ ይቻላል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ(Toelken, In Hurriz, 12) ፎክሎር ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የሚችልባቸውን ሦስት መንገዶች እንዳለ ይዘረዝራል ። ይኸዉም፣ በተለያዩ የትምህርት አይነቶች ውስጥ ለምሳሌ፣ በ (ታሪክ፣ ሂሳብ፣ ስነ ጽሑፍ፣ ሥነ-ልሳን ... በመሳሰሉት) ፣ በልዩ ልዩ ሁነቶች ወቅት ለምሳሌ፣ (በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት፣ በሠፈራ ፕሮግራሞች ወዘተ.)፣ እና ለህዝብ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት መሆኑን ይጠቅሳል።

“ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች” (2004 ዓ.ም)፣ በተባለዉ መጽሐፍ ውስጥ ፈቃደ አዘዘ Antonio Gramisci እና Michael Owens Jones የተባሉ የፎክሎር ምሁራን ስለ ተግባራዊ ፎክሎር ያቀረቡትን ምርምር በተመለከተ(Dundes, 1995) ዋቢ በማድረግ በዝርዝር ፅፏል። እንደ ፈቃደ፣Gramisci ካደረጋቸው አስተዋፅኦች አንዱ፣ የፎክሎር ጥናት በዘመናዊ አስተሳሰብ እና ትምህርት ያልተጠኑትን ማህበራዊ ቡድኖች ርዕዮተ አለም ለማጥናት ይጠቅማል ያለው ነው። ፎክሎር መጠናት ያለበት ዘመናዊ አስተሳሰብ እና ትምህርት ያልደረሰባቸው ማህበራዊ መደቦች፣ ወገኖች፣ ቡድኖች፣ አለምን የቀረፁበት፣ የገለፁበት፣ የሳሉበት፣ የተመለከቱበት እና ዛሬም የሚያዩበት መንገድ (ርዕዮተ ዓለማቸው) ደርጐ ነው (ፈቃደ፣ በሸፈራዉ ዉስጥ፣ 2004፡115)

ሌላው በፈቃደ የተጠቀሰው Michael Owen Jones,(Putting Folklore to Use, 1994) በሚለው መፅሀፉ ስለተግባራዊ ፎክሎር ባቀረባቸው የምርምር ሥራዎቹ ውስጥ ፎክሎርን ሰብስቦ፣ በስብሰቡ አንድ ማህበራዊ ፋይዳ መስራት ረጅም ታሪክ እንዳለው ለማሳየት የስዊዲን፣ ፊንላንድ፣ ጀርመን እና አሜሪካን ተሞክሮ እንደ ምሳሌ ይጠቅሳል። ስዊዲን ረጅም ታሪክና ባህል ያላት ሀገር መሆኗን ለሌሎች ተቀናቃኞቹዋ የአዉሮፓ ሀገራት ለማሳየት፣ፊንላንድ በታላቁ የሰሜን ጦርነት ምክንያት ከደረሰባት ጉዳት ለማንሰራራት በማሰብ ለነደፈችዉ የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራሚያ ማስፈጸሚያ፣ጀርመን ጠንካራ ብሄርተኝነት ለመፍጠር፣አሜሪካ ወታደሮች በጠላት ባህል ዉስጥ መኖርን እንዲለምዱ ለማድረግ፣የዘርና የሰራተኛ

አመፅን ለማብረድ፣ ትምህርትን ለማስፈፈትና ለቱሪዝም መስህብነት ተጠቀመዉበታል።

አፍሪካውያን እንዲሁ ከቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ባደረጓቸው ቀደምት (Primary) በሚባሉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ፎክሎር ጥቅም ላይ ውሏል። በመላው አፍሪካ በተለያዩ ቦታዎች በተካሄዱ የፀረ-ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴዎች፣ ጀግናን የሚያወድሱ አባባሎች፣ ተራኪ ቃል-ግጥሞች፣ ተረቶች፣ሚቶሎጂዎች፣ ገድሎች፣ የሀገረሰብ ሙዚቃዎች (ቀረርቶዎች፣ ሽለላዎች፣ ፉከራዎች፣ የእረኛ ዘፈኖች)፣ እንቆቅልሾች እና ሌሎችም የፎክሎር አይነቶች የትግሉ ማነቃቂያ እና ማቀጣጠያ መሳሪያዎች ነበሩ። ይህንን በተመለከተ Hurreiz የሚከተለዉን ጽፏል።

*Throughout Africa there are numerous primary resistance movements that lean heavily on traditional cultural heritage. Social institutions such as ages sets, secret societies and initiation ceremonies were adapted and utilized for political purpose. Heroic traditions, mythologies and other religious repertories were employed in order to give political movements a sense of conviction and spiritual perspectives. Moreover, folksongs, riddles, legends and other genres became instruments of political mobilization and resistance (*2006,12).

ፎክሎር ጥቅም ላይ ከዋለባቸው ቀደምት የአፍሪካ የነፃነት የትግል እንቅስቃሴዎች መካከል፣ በምስራቅ እና መካከለኛው አፍሪካ የተደረጉትን፣ የኔድቤሌ፣ የሾና፣ የማኡ-ማኡ፣ የማጂ-ማጂ፣ የዲንካ እና የማህዲስቶችን እንቅስቃሴዎችን መጥቀስ የሚቻል ሲሆን፣ ዋናዋና መሪዎቹ ደግሞ፣ Dengkur, Aterwol, Dhiew Alam እና Ariandhit ነበሩ። ከነዚህ መካከል በደቡብ ሱዳን የዲንካ ህዝቦችን ተቃውሞ ይመራ የነበረው Dengkur ህዝቡ እና ተከታዮቹ በወቅቱ በነበሩት ቅኝ ገዢዎች (እንግሊዞች) ላይ የትጥቅ ትግል እንዲያካሂዱ ለማነሳሳት ሲል ከጠላት ወገን የሚተኮሰው ጥይት እሱን እንደማይመታውና ልክ እንደውሃ አቅዝቅዞ የሚያስቀርበት አንዳች ምትሃታዊ ሀይል እንዳለው አድርጎ ያወራላቸው ነበር (Hurriez,132-144)። ከዚህም መረዳት የሚቻለዉ ፎክሎር የሰዎችን አስተሳሰብ እስከ መቀየር ድረስ ምን ያህል ጠቀሜታ ያለዉ መሆኑን ነዉ።

ይህ ጥናት ከፎክሎር ዘርፎች መካከል በዋናነት በሥነ ቃልና ሀገረሰባዊ ልማዶች ላይ ያተኮረ እንደ መሆኑ ስለ ስነ ቃል እና ሀገረሰባዊ ልማዶች የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረን ስለ ምንነታቸዉ እና ፋይዳቸዉ በምሁራን የተገለጹትን እንዲሁም የተከናወኑትን ጥናቶች ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

2.1.4 የስነ ቃል ምንነትና ፋይዳ

ሥነቃል በጥናትና ምርምር ውስጥ የማህበረሰቡ ባህላዊ ልዩ ልዩ ገፅታዎች አንጸባራቂ፣ የማህበረሰቡ ምኞትና ፍላጎት የሚገለጽበት እንዲሁም ሥነ ውበታዊና መዋቅራዊ የሆኑ ጉዳዮች የሚረወዳሰስበት እና የማህበረሰቡን አጠቃላይ አመለካከት ያካተተ መሆኑን Brunvand (1979)፣ Wilson (1979) እና Austin (1994) ያብራራሉ። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፈቃደ አዘዘ፣ (1991፡ 11) ሥነቃል ማለት በቃላት አማካይነት የሚፈጠሩትን በተረት፣ በቀልድ፣ በሌጀንድ፣ በሚት፣ በዘፈን ወይም በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ በእንቆቅልሽ፣ በእንኪያስለንቲያ እና በመሳሰሉት እንዲሁም ወደዚህ የሚቀርቡትን የምንጠራበት የጥቅል ስም መሆኑን ይገልጻል ።

በማያያዝም ዘሪሁን (1992፡20) ሲያብራራ “ስነቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በማዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነጥበብ ነው” ይላል።

የስነቃልን ስያሜ በሚመለከት ተረታ-ተረቶችን፣ ሚቶችን፣ አፈታሪኮች፣ ምሳሌዎች፣ እንቆቅልሽ እና ቃልግጥምን፣ ዝማሬዎችን የመሳሰሉ በቋንቋ የሚገለጹ ጥበባትን ሁሉ ጥቅል የመጠሪያ ሆኖ እንደሚያገለግልና ትርጉሙም ስነቃሉ ከሚከወንበት ዓላማና ከሚያበረክተው አገልግሎት የሚመነጭ መሆኑን ብርሃኑ (1995: 2-9) ያብራራል። በተመሳሳይ ሁኔታ ማህበረሰቡ ስለራሱ ማንነት፣ የህይወት ፍልስፍና ማህበራዊ ግንኙነት፣ ጥላቻና ፍቅሩን የሚገልጸው በሥነቃል ዓይነቶች አማካይነት መሆኑን አሰፋ ቶሌራ (2004) ይገልጻል።

ሥነቃል የማህበረሰቡ እውቀት መገለጫ እንደመሆኑ መጠን ከአንዱ የማህበረሰብ አባል በመማር ለሌሎችም የምናስተምርበት የእውቀት ዘርፍም በመሆን ያገለግላሉ።

ከዚህም ስነቃል የመሰራጨት አድማሱ ሰፊና ፈጣን እንዲሁም በየትኛውም ባህል ውስጥ በተነገረበት ቅጽበት ወደ ሌሎች የመሸጋገር ሀይል ያለው መሆኑን እንገነዘባለን። ለምሳሌ ያህል ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን እና ቀልዶችን ከታላላቆቻችን እንማራለን፤ ሌሎችንም እናስተምርበታለን። በዚህ መልኩ ሥነቃል ከአንዱ ትውልድ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ የማስተማር ሚናም አለዉ (Finnegan, 1970; Mieder, 1993; Egbe, 2000; Okpewho, 2004)።

እነዚህም ተግባራት የሥነቃል ባህሪያት መሆናቸውን በመግለጽ የሥነቃልን የማስተማር ሚና አስመልክቶ የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች እምቅ በሆነ ትርጉማቸው መልዕክት የማስተላለፍ ሚናቸው የጎላ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን Finnegan፣ (1970) እና Okpewho (2004፡226) ያስረዳሉ። ስለሆነም የማህበረሰቡን አባላት የማስተማር፣ የመለወጥና የተበላሸ ባህሪይን የማስተካከል ፋይዳ አላቸው። የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች የማህበረሰቡን ሥነ-ምግባራዊ ተግባራት እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ውጤታማ ናቸው (Bascom,1954)።

ሌላው የሥነቃል ፋይዳ ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊናሥነልቡናዊ ጉዳዮችን ግልፅ ማድረጉ ነዉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሥነቃል ማህበረሰቡን በሚመለከት የማይዳሰሰው የሕይወት ዘርፍ አለመኖሩን ነው። በመሆኑም በኢትዮያ ቴአትር ዉስጥ ስራዎቻቸዉን ለህዝብ አቅርበዉ ተቀባይነትን ያገኙ ፀሀፊ-ተዉኔቶች በሥነቃል የማህበረሰቡን ልዩልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነልቦናዊ ጉዳዮችን የገለፁበትን መንገድ በማጥናት የኑሮ መማሪያ ማድረግ ይቻላል። የማህበረሰቡን ችግሮች ለመፍታትም እንዲሁ በዚሁ ላይ ትኩረት ማድረጉ በተለይ አሁን በአለዉ የአገራችን ተጨባጭ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁናቴ ዉስጥ በአዎንታዊ መልኩ አጋዥነት ይኖረዋል ፡፡

2.1.5 የሀገረሰባዊ ልማድ ምንነትና ፋይዳ

ሀገረሰባዊ ልማድ ከአራቱ የፎክሎር የጥናት መስኮች አንዱ እንደሆነ Dorsen (1972, 51) እና ፈቃደ (1991፣10-15) ገልጻሉ፡፡

“ሰዎች አጥብቀዉ የያዟቸዉ እምነቶችናልማዶች መነሻ ምንጫቸዉ ምንድነዉ? የተወሰኑ ስርዓቶችንና አምነቶችንስ ለምን ይከተላሉ? እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በተለይ ፈላስፎች፣ ደራሲያን፣ ስነ ሰበኞችና ፎክሎረኞች ጊዜ ወስደዉ የተመራመሩባቸዉና ዛሬም የሚመራመሩባቸዉ ጥያቄዎች ናቸዉ ”(ፈቃደ፣ 1991፣13)። ከላይ ከቀረበዉ ሀሳብ ለመገንዘብ እንደሚቻለዉ ሀገረሰባዊ ልማዶች ሰዎች በዘመናቸዉ አጥብቀዉ የያዟቸዉ ፣ ለመከታተላቸዉም ምክንያታዊ ፋይዳ ያላቸዉ የአመለካከት አይነቶች ናቸዉ ማለት ይቻላል። ፈቃደ አክለዉም Dorson በ (1972) መጽሀፉ “ሀገረባዊ ልማድ ” በሚለዉ ክፍል ካካከታተቸዉ አራት መጣጥፎች መካከል አንዱ ሀገረሰባዊ ሀይማኖት (Folk relligion) እንደሆነ ይገልጻለ። የሀገረሰባዊ ሀይማኖት ምርምር በልዩ ልዩ በዓላት ፣በመንደር፣ በቤተሰብ ፣በቤተሀይማኖት የሚካሄዱትን ክዋኔዎች፣በልደት፣በክርስትና በመሳሰሉት ክዋኔዎች ዉስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን የሚያጤን ሲሆን የጥናቱ ትኩረት ግን ከዚያጋር አያይዞ ማህበረሰቡ የሚፈጽማቸዉ ሀገረሰባዊ ልማዶችና ስርዓቶች (አምነታዊ ድርጊቶች) እና ሌሎች በሀይማኖታዊ መጻህፍት የማይመረመሩ እምነት ነክ ጉዳዮች(በግራጎን መነሳት ፣የቅንድብ ማርገብገብ...) እና ለእምነቶቹ የሚሰጠዉን ትርጉምና ፋይዳ መመርመር ላይ እንደሆነ ፈቃደ (1991፣14) ያስረዳሉ።

2.1.5.1 ሐገረሰባዊ አምነት

የሀገረሰብ እምነት በሰለጠነዉ ዓለም ግልጽ መለኪያ ያልተቀመጠለት በሙከራ ያልተረጋገጠ፣እራሱን የቻለ እዉቀት ሳይሆን እንደ አመለካከት ሂደትና የእዉቀት መንገድ የሚቆጠር ፣ ተቀባይነቱም እምነቱ ባለበትና በሚፈጸምበት አካባቢ የሆነ፣በዚያዉ አካባባቢ ማህበረሰብም እዉነት ሆነዉ የሚቆጠሩ እምነታዊ አባባሎችና ድርጊቶችን ያካተተ አመለካከት እንደሆነ Mullen (1969:225) እና Motz (1998:340) ይገልጻሉ። የሀገረሰብ እምነት በፎክሎር ጥናት ዉስጥ ያለዉን ቦታ አስመልክቶም Motz የሚከተለዉን ይላል። “The concept of folk belief is so central to the discipline that is hard to talk about folklore with out talking about belief” (የሀገረሰብ እምነት በፎክሎር ጥናት ዉስጥ ማዕከላዊ (ዋና ጉዳይ) ሲሆን የሀገረሰብ እምነትን ሳያካትቱ ማዉራትም አስቸጋሪ ነዉ።)፣ (Motz,1998፣140)። የዚህ ጥናት አንዱ ትኩረትም በፎክሎር ጥናት ዉስጥ ማዕከላዊ

ጉዳይ በሆኑትና በሰለጠነዉ አስተሳሰብ መለኪያ በሙከራ ያልተረጋገጡ፣ በሚነገሩበትና በሚፈጸሙበት ማህበረሰብ እንደ እዉነት ተወስደዉ የሚታመኑ፣ እምነታዊ አባባሎች፣ አመለካከቶች፣ ድርጊቶችና ስርዓቶች ላይ ነዉ፡፡ Mulen አክሎም የፎክሎረኞችን ትኩረት ከሌሎች ትምህርት መስኮች ተመራማሪዎች ጋር በማነጻጸር፣ ዋና ትኩረታቸዉ የህገረሰብ እምነቶችን ከመተንተን ይልቅ ጥሬ መረጃዎችን ሰበስቦ በማስቀመጡ ላይ እንደሆነና የስነሰብ ተመራማሪዎች ትኩረት ደግሞ በአንጻሩ ጥሬ መረጃዎችን ከአገልግሎታቸዉና ትርጓሜያቸዉ አንጻር መተንተኑ ላይ እንደሆነ በመግለጽ፣ እነዚህን የፎክለረኞችንና የስነ ሰብእ ተመራማሪዎችን የአጠናን መንገዶች በጥምረት መጠቀምም ስለአንድ ማህበረሰብ አዉዳዊ መረጃ ለማግኘት እንደሚያስችል ያስረዳል፡፡ የእነዚህን ዘዴዎች ትግበራም አስመልክቶ Mullen የሚከተለዉን ይመክራል፡፡

“The most fruitful way to applay this approach is to use a group that has strong tradition of folk belief to question the members of the group as to their attitude toward their magical practiices (1969: 214) .”

ሲተረጎም፡-

“እነዚህን ዘዴዎች በጋራ ተጠቅሞ ህገረሰባዊ እምነቶችን የመሰብሰቡና የመተንተኑ ተግባር የበለጠ ፍሬ ያፈራ ዘንድ እምነቶችን በመከተልና በመፈጸም ረገድ የዳበረ ልምድ ያላቸዉ ቡድኖችን ወስዶ ስለሚፈጽሟቸዉ የህገረሰብ እምነታዊ ድርጊቶች ያላቸዉን አመለካከት መጠየቅ ጠቃሚ ነዉ፡ ”

በዚህ ጥናት በተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱ ህገረሰብ እምነትን የተመለከቱ ጉዳዮች እስካሁን ከቀረበዉ አንጻር ለማየት ተሞክሮአል፡፡

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

2.2.1 በዉጭ ሀገር የተሰሩ ጥናቶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ በቅድሚያ የዳሰስኩት *Religion and Drama in Early Modern England* (Janehwang Degenhardt and Elizabeth Williams,2006) የተባለውን

መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል በድራማና በሐይማኖት መካከል ስላለው ግንኙት፣ ድራማ ሐይማኖታዊ እሳቤዎችን (Religious Elements) እንደሚይዝ ለመረዳት በክዋኔ (Performance) እና በቁስ (Material) ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ የሚያብራሩ የተለያዩ መጣጥፎች (essays) ተካተውበታል፡፡ በሁለተኛው ክፍል በቀረቡ በርካታ የንባብ አሃዶች (Set of Readings) በ17ኛው ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ የቴአትር እድገትና ዘናዊነትን ተከትሎ የሐይማኖታዊ ምስጢራትን የመተርጎም እና የመረዳት ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር፣ ታዳሚ (Audience) በቴአትር ውስጥ የሚነሱ ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን ቀደም ሲል ስለ ሐይማኖት ከነበረው እውቀት (Religious Experience) አንፃር እንዴት ይመለከታቸው እንደነበር፣ በድራማ መልክ በሚቀርበው ሐይማኖታዊ ርዕስ (Religious Issues) እና ከዚያ ውጭ ባለው ሃይማኖታዊ ትችት (Religious Discourse) መካከል ስላለው ግንኙነት፣ በቴአትር ክውኖች(Theatre Performance) እና በሐይማኖታዊ ከበራዎች (Religious Celebrations) መካከል ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር ስላለው ተመሳስሎ ወዘተ. የመሳሰሉ ሐሳቦች ተነስተዋል፡፡

መጽሐፉ በቴአትርና ሀይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሁም ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር ያላቸውን ሚና የሚያነሳ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ያዛምደዋል፡፡ ልዩነት ብዬ በዋናነት የምጠቅሰው ጉዳይ የእኔ ጥናት በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ በተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በመሆኑና ፋይዳውን ከማህበራዊ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች የፎክሎር ብዝሃ-አገልግሎቶች (Folklore multi functional role) አንፃር ጭምር የሚመለከት በመሆኑ ነው፡፡

በመቀጠል የተመለከትኩት “Theatrical Aesthetics and Functional Values of Ekuechi Masquerade Ensemble of The Ebira People” የሚለውን ጆርናል ሲሆን፣ ጸሐፊዋ Sendey Ododo (Professor) ናቸው፡፡ ይህ ጆርናል በናይጀሪያ የኤብራ (Ebirra) ማህበረሰብ ዘንድ አሮጌውን ዓመት ለመሸኘትና አዲሱን ለመቀበል በየአመቱ የሚዘጋጀውን ኢኩቺ (Ekuechi) የባህል ፌስቲቫል የተመለከተ ነው ፡፡ “Ekuechi festival is a ritualistic enactment of myth, legend and traditional social events meant to mark the end of the year and usher in a new

one. The Ebira people of kogi state in Nigeria cellerate it annually" (Ododo, 2001:2).

ጸሐፊዋ በዋናነት በፌስቲቫሉ ድራማዊ አላባዎችና ማህበራዊ ፋይዳዎች ላይ ትኩረት አድርገዋል። ድራማዊ አላባዎችን በተመለከቱበት ክፍል የፌስቲቫሉን አቀራረብ ከቦታ፣ ከተመልካች፣ ከቁሳቁስ፣ ከሚካኘ፣ ከመብራትና ከድምጽ አንጻር ለመተንተን ሞክረዋል። ማህበራዊ ፋይዳውን አስመልክቶ ፌስቲቫሉ የኢብራን ማህበረሰብ ታሪክ፣ ባህል፣ እምነት፣ ማንነት፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ጠብቆ በማስቀጠል ረገድ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ገልፀዋል። በመደምደሚያቸው ላይም ፌስቲቫሉ ለበርከታ ዓመታት ትኩረት ሳይሰጠው መቆየቱን እንደ ችግር በመጥቀስ፣ ሆኖም ወደ ቱሪስት መስህብነት በመቀየር ለኤብራ(Ebirra) ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ መስጠት የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል ይላሉ። ይሄ ሐሳባቸው ደግሞ Ododo ከእኔ ጥናት ጋር ያዛምዳቸዋል።

2.2.2 በሀገር ዉስጥ የተሰሩ ጥናቶች

በዚህ ክፍል የቃኘሁአቸው ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ቤት እና የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጸሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ለዲግሪ ማሟያ ያቀረቧቸውን ጥናታዊ ጽሑፎች፣ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የትውፊታዊ ቴአትር ትውን ጥበባትና ምርምር ክፍል የተሠሩ ጥናታዊ ሥራዎችን ነው።ከዚህ እንደሚከተለዉ ይቀርባሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ቤት እና የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ካቀረቧቸው ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል፣ ማርታ ንጉሴ፣ "የሰላሌ አካባቢ የጉማ ሥርዓት ክዋኔዎችና ተውኔታዊ አላባዎች" (1998 ዓ.ም)፣ ተመስገን ፋናዬ፣ "የዛር ትውፊትና በውስጡ የሚገኙ የቴአትራዊ አላባውያን በራያና ቆቦ አካባቢ" (1995 ዓ.ም)፣ እንግዳ ሐብቴ፣ "የሶዶ ብሄረሰብ ትውፊታዊ ድራማ" (1984 ዓ.ም)፣ እና በላይ መኮንን፣ "የደቡብ ንግስት ተውኔት ከአፈ-ታሪኩ አንፃር" (1999 ዓ.ም) ይገኙበታል። የማርታ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ በሁለተኛው

ምዕራፍ፣ የተዛማጅ መፃህፍት ቅኝት፣ በሦስተኛው ምዕራፍ፣ የጉማ የግጭት መፍቻ ትውፊታዊና ተውኔታዊ አለባዎች፣ በአራተኛው ምዕራፍ፣ ማጠቃለያ ቀርቧል። ማርታ፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን አስፈላጊነት ስትገልጽ፡- "በማህበረሰቡ ዘንድ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የሚከሰቱትን ማህበራዊም ሆነ ሥነ ልቦናዊ ግጭቶች ለመፍታት የሚጠቀሙበትን የአሠራር ዘዴ ለመገንዘብ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ ህዝቡ ያለውን አመለካከት ለማወቅ ይረዳል" ትላለች።

የጉማን ትውፊታዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ማህበራዊ ጉዳይ ወይም አገልግሎት በጠቀሠችበት፣ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ፣ የጉማ ግጭት አፈታት ለማህበረሰቡ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ጠቅሳለች፡- "የአገር ሽማግሌዎችን ማክበር አካባቢን ለማስተዳደርና ሠላምን በማስፈን ረገድ ትልቅ ጠቀሜታ አለው የማህበረሰቡን ባህልና ልማድ በወጉ ጠንቅቀው በሚያውቁ ሽማግሌዎች መዳኘት፣ ምክራቸውን ወይንም ቃላቸውን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረጉ የጉማ ሥርአት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ልማድ ጥሩ የሆነ የሚያስማማ ስልት በመሆኑ የሠላሌ አካባቢ ኦሮሞ በነፍስ ግድያ የሚያደርገውን የጉማ እርቅ ብዙ ገንዘብ ሳያስወጣ ወይም ሌላ ግድያ ሳያስከትል በሠላም ስለሚያልቅ መደበኛ ፍርድ ቤት እንዳይጉላሉና ለከፍተኛ ወጪ እንዳይዳረጉ ያደርጋቸዋል።" ይህ ነጥብ የፎክሎርን ማህበራዊ ፋይዳ የሚያሳይ እንደመሆኑ፣ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያለው ሲሆን፣ የእሷ ጥናት በዋናነት በጉማ የግጭት አፈታት ስርአት ላይ ብቻ ማተኮሩና ሌሎች ፎክሎራዊ የሆኑ ጉዳዮችን መዳሰስ አለመቻሉ ከዚህ ጥናት ይለየዋል።

የተመስገን ፋናዬ ጥናት በሦስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ ዳራዊ ገለፃና በአካባቢው የሚዘወተሩ ሌሎች ተዛማጅ ትውፊታዊ ክንውኖችን የያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምዕራፍ የዛር ትውፊት በራያና ቆቦ፣ ሦስተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ የዛር ትውፊት ይዘት የሚሉትን ያጠቃልላል፡

ጥናቱ በዋናነት ያተኮረው የቴአትርና የዛር ትውፊታዊ ክንዋኔን በማዛመድ፣ በዛር ትውፊት ክንዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተውኔታዊ አላባዎችን ነቅሦ በማውጣት የሁለቱን ዝምድና ባህርያት ማመላከት ላይ ነው።

ይህንኑ ዝምድና ጠቅለለ ባለመልኩ ሲገልፀውም፣ ቴአትር ከአምልኳዊ ሥርዓት ቀስበቀስ ወደ ድራማ ከዚያም ወደ ቴአትር ያለው ሽግግር ደረጃውን ጠብቆ ያደረገ መሆኑንና የአምልኳዊ ሥርዓት በድራማ አማካኝነት ወደ ቴአትር መሸጋገር የረጅም ጊዜ ሂደትን የወሰደና የተወሰኑ አላባውያን፣ እንደ፡- የሚና ክፍልል፣ ድባብ፣ ቃላዊና አካላዊ ምላሽ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ቀስበቀስ እየተሻሻሉ የመጡ ሲሆን፣ ሌሎች ባህርያት ደግሞ በተቃራኒው እየጠፉ መሆኑን ያብራራል፡፡

ተመስገን፣ የቴአትርና የሥርዓተ አምልኮን ዝምድና የገለፀበት ሐሳብ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ የእሱ ጥናት በራያና ቆቦ አካባቢ ብቻ መወሰኑ፣ ዓላማው በዛር ትውፊት ክንዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተውኔታዊ አላባዎችን ነቅሦ አውጥቶ የሁለቱን ዝምድና ባህርያት ማመላከት መሆኑና፣ የዚህ ጥናት ዓላማ ደግሞ በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ፋይዳ ማሳየት መሆኑ፣ በልዩነት የሚጠቀስ ነው፡፡

እንግዳ ሐብቴ፣ ጥናታዊ ጽሑፉን በአራት አበይት ክፍሎች መድቧቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል፣ አጠር ባለ መልኩ ስለ ጉራጌ ታሪካዊ አመጣጥና ጠቅለል ባለ መልኩ ስለ ሶዶ ብሂረሰብ፣ በጨረፍታም ቢሆን፣ ለማሳወቅ ሞክሯል፡፡ በክፍል ሁለትና ሦስት ከጋብቻ ምርጫ እስከ መልስ ድረስ የሚከወኑ የተለያዩ ሥርዓተ ልማዶችን ከነድርጊታቸው ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ አስፍሯል፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍም በትውፊቱ ውስጥ ከሚገኙ በርካታ የድራማ አላባውያን መካከል አበይት ያላቸውን አትቷል፡፡

እንግዳ በጥናቱ፣ ትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ከአንድ ማህበረሰብ ወደ ሌላ ማህበረሰብ በቁስና በአካል እንቅስቃሴ፣ የህዝብ ዳንሶች፣ እስክስታዎች፣ የገና ጨዋታዎች፣ የገበጣ ጨዋታዎች ... ወዘተ. የሚተላለፍ የእውቀት ዘርፍ ነው ይላል፡፡ ነገር ግን በማለትም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ህልውናው የሚኖረው ከሚያበረክተው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ አስተዋጽኦ አኳያ ብቻ እንደሆነና አለዚያ ግን በሌላ እውቀት እንደሚተካ ይገልፃል፡፡ ይህም ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ በሌላ በኩል በሶዶ ማህበረሰብ ወግ መሠረት የጋብቻ ምርጫ መመዘኛዎች፣ የአመራረጥ ስልትና የጋብቻ አይነቶች፣ የቀለበት፣ የጥፍር

ቀፈፋ፣ የአደብና፣ የሠርግ፣ የጫጉላ፣ የመልስ ወዘተ. ሥነ-ሥርዓቶችና በውስጡ የሚገኙ አበይት የድራማ አላባውያን ክንውኖችን በመጥቀስ፣ ከነኚህ ጋር በተያያዘ ጐጂና ኋላቀር ልማዶች ስለሆኑ መሻሻል ወይም መወገድ አለባቸው የሚላቸውን ሌሎች ባህላዊ ጉዳዮች ደግሞ ዘርዝሯል።

ይህ ደግሞ ፎክሎርን አገልግሎት (ጥቅም) ላይ ማዋል ከሚለው ከእኔ ጥናት ሃሳብ ጋር ስለሚጋጭ በልዩነት የሚታይ ነው።

በላይ መኮንን፣ የደቡብ ንግስት ተውኔትን ከአፈ-ታሪክ አንፃር በተመለከተበት ጥናታዊ ጽሑፉ፣ ስለ አፈ-ታሪክ ምንነትና ጠቀሜታ የተወሰኑ ነጥቦችን አንስቷል። “አፈታሪክ የአንድ ሰው ታላቅነት፣ ለታላቅነቱ ያበቁት የህይወቱ ዘመኑን ተግባራት፣ ያሳለፋቸውን ከባድና አስጨናቂ ውጣ ውረዶች ለመቋቋም ያስቻለውን መለኮታዊና ልዩ ሀይል፣ ከተራው ሰው የሚለይበትን ልዩ ተሰጥኦ የሚያወሳ፣ የመጠሪያ ዘመኑ በክፍለ ዘመናት ወደ ኋላ የሚቆጠር፣ ደቂቅነት አስቸጋሪነት ያለው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እንዲሁም እንደየአካባቢው ሁኔታ በጽሑፍ የሚተላለፍ የሥነ ቀል ዘርፍ ነው” (ገጽ 8)።

ጥቅሙን አስመልክቶ፣ አፈታሪክ የሚነገረው ለተዝናኖት ሳይሆን፣ ሠዎችን ለማስተማር፣ አንድ አስፈላጊ ጉዳይ እንዲያውቁ ለማድረግና በባህላቸው የሚደርስባቸውን አደጋ ለመከላከል፣ ዝግጁ እንዲሆኑ ለማስጠንቀቅ እንደሆነ ገልጿል።

ይህም በአንድ በኩል የፎክሎርን ፋይዳ የሚያሳይ ሲሆን፣ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያዛምደው ነው።

የበላይ ጥናት በዋናነት ከእኔ ጥናት የሚለየው፣ በአፈታሪክ ላይ ብቻ ያተኮረና ሌሎች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የማይዳሰስ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ጥናቱ ከፎክሎር እሳቤዎች ይልቅ በተውኔት አላባውያን ላይ ማተኮሩ ሌላው ልዩነታችን ነው።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የትውፊታዊ ቴአትር ትውን ጥበባት ጥናትና ምርምር ክፍል ከተሰሩ ጥናትና ምርምሮች መካከል የጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ እና ደስታ ለሬንሶ የጋራ ጥናት የሆነው የቃቄ ወርዶዎት ይገኝበታል። ይህ ጥናት ሁለት ዋናዋና ክፍሎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያ ክፍል፣ "የቃቄ ወርዶወት ትውፊታዊ የጥናት ውጤቶችና አንትሮፖሎጂያዊ ትንተና" የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል፣ "የቃቄ ወርዶወት ታሪክና የጉራጌ ብሔረሰብ ባህል ሥነ-ቃልና ትውፊታዊ ትውን ጥበባት" ይሠኛል።

አጥኚዎቹ፣ በጥናታቸው፣ በ1860ዎቹ አካባቢ ቃቄ ወርዶወት የተባለች ሴት በጉራጌ ባህልና ታሪክ ውስጥ ተጽእኖ መፍጠሯንና አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከቷን ጠቅሰዋል።

ቃቄ ወርዶወት በወቅቱ አለም ገና ያላነሳውን የሴቶች የእኩልነትና የመብት ጥያቄ ይዛ በመነሳት በኢትዮጵያ ጉራጌ ህዝቦች ውስጥ ዘመናዊ አስተሳሰብ እንዲስፋፋ ማድረጓን በጥናታቸው ከሠበሠቧቸው አፈታሪኮች፣ ሥነ-ቃሎች፣ ግጥሞችና ዘፈኖች መረዳታቸውን አብራርተዋል።

ይህም፣ የፎክሎር ፋይዳ የሚያሳይ በመሆኑ የእነሱን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ ልዩነቱ የእነሱ ጥናት ዋና ዓላማ ለትውፊታዊ ቴአትር ግብአት የሚሆን መረጃ መሰብሰብ ሲሆን፣ የእኔ ጥናት ደግሞ፣ አስቀድመው ከተፃፉ (ከቀረቡ) ተውኔቶች ውስጥ ፎክሎርን ሰብስቦ ከፋይዳው አንፃር ማጥናት መሆኑ ነው።

ምዕራፍ ሶስት

3. የጥናቱ ስልትና ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዓይነት፣የመረጃ ምንጮች፣ የናሙና አመራረጥ ስልት፣ የመረጃ አሰበሰብ ዘዴዎችና የመረጃ መተንተኛ ቲዎሪዎችን የተመለከቱ ርዕሰ-ጉዳዮች ይቀርባሉ፡፡

3.1 የጥናቱ አይነት

አንድ አጥኝ የጥናትና ምርምር ስልተ ቅየሳ /ዲዛይን/ ሲሰራ በቅድሚያ መወሰን ያለበት ምን አይነት የጥናትና ምርምር ስትራቴጂ መከተል አለብኝ የሚለውን እንደሆነ Kothari (2004: 5) እና ያዴሳ ቶሎሳ (2008፡63) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ጥናት የተከተለው ገለጻ ተኮር (Disciptive) እና ማብራሪያ ተኮር (Explanatory) የጥናትና ምርምር ዘዴዎችን ሲሆን፣ ይህም ለጥናቱ በተመረጡት ተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ከተለያዩ ቲዎሪዎች አንጻር የተገለጸበትና የተብራራበት መንገድ ነው፡፡

3.2 የመረጃ ምንጮች

በጥናትና ምርምር ሂደት ውስጥ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ይሰበሰባሉ፡፡ እነዚህም በልዩ ልዩ የመረጃ መሠብሰቢያ ዘደዎች ከመስክ የሚሰበሰቡ እና ከቤተ መጽሐፍት፣ ከድረ ገፅ እንዲሁም ከተለያዩ ጽሁፎች ለንባብ የተጠናቀሩ የመረጃ ምንጮችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ዚህ ጥናት በዝርዝር የምንመለከታቸዉ ሰባት ተውኔቶች ከተለያዩ ቴአትር ቤቶች የተገኙ ሲሆን፣ በእነዚህ ተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱ አንዳንድ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አካባቢያዊናባህላዊ ትርጉም በተሟላ ሁኔታ ለመረዳት የሚጠቅሙ ተጨማሪ መጀዎች ደግሞ ከተለያዩ ግለሰቦች በቃለ-መጠይቅ የተሰበሰቡ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መጽሐፍት፣ ጥናታዊ ስራዎች፣ መጽሔቶች እና አርቲክሎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኬነዲ ላይብረሪ እና የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ ከብሔራዊ ቤተ መጻህፍትና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ እና ከድረ-ገጾች የተሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው፡፡

3.3 የመረጃ ናሙና አመራረጥ ስልት

3.3.1 የዒላማ ናሙና

የኢላማ ናሙና (Purposive Sampling) አጥኚው አንዳንድ ግለሰቦች ወይም ነገሮች በጥናቱ ቢካተቱ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ያስችላል ብሎ ሲገምት ስራ ላይ የሚውል ዘዴ ሲሆን በናሙናው ውስጥ የሚገቡት ሆን ተብሎ በአጥኚው የሚመረጡት ሰዎች ወይም ነገሮች መሆናቸውን ያዲሳ ቶሎሳ (2007፣77-79) ያብራራል። ከዚሁ አንጻር በዚህ ጥናት ውስጥ የፎክሎርን ፋይዳ በተሻለ መልኩ ሊያሳዩ ይችላሉ ተብሎ በአጥኚው የታመነባቸው ሰባት ተውኔቶች ተመርጠዋል። እነዚህን ተውኔቶች ለመምረጥም በፎክሎርና በቴአትር ዙሪያ እውቀትና ልምዱ ያላቸውን የተለያዩ ሰዎች ጥቆማ መሠረት በማድረግ ወደ ሃያ በሚጠጉ ተውኔቶች ላይ በቅድሚያ የዳሰሳ ንባብ ተደርጎአል። በተጨማሪም አጥኝው በዚሁ የተውኔት መረጣ ሂደት ሌሎች የተለያዩ መስፈርችን ከግምት ውስጥ ለማስገበት የሞከረ ሲሆን ከነዚህ መካከልም ከዘመን እና ከፀሀፌ-ተውኔት አንጻር የሚነሱ ጉዳዮች ዋናዋናዎቹ ናቸው። ፎክሎር በአንድ ዘመን/ወቅት የነበረን ማህበረሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች[21] መሰል ጉዳዮች ወደ ኋላ መለስብለን የምናጠበት የዕውቀት አካል እንደመሆኑ (Benamos, 1995 ; Dorson, 1963) በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ ተውኔቶችን ሰበባስቦ ከፎክሎር አንጻር የተነሱ ጉዳዮችን ማጥናት ከዚህ አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

ከፀሀፌ- ተውኔት አንጻር ለተውኔት መረጣው በአጥኚው የተወሰደዉ ሌለው ግንዛቤ፣ ስራዎቻቸው በዚህ ጥናት የተካተቱላቸው አብዛኞቹ ፀሀፊዎች የቋንቋ፣ የስነ ጽሁፍ፣ የቴአትር፣የባህልና የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶችን በዩንቨርሲቲ ደረጃ ቆምር ያጠኑ[22] ከመሆናቸው አኳያ ስራዎቻቸው (የጻፉዋቸው ተውኔቶች) ለዚህ ጥናት ቢመረጡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይረዳል የሚል ነው።

[21] ስነ ልቡናዊ፣ ሞራላዊ ፣ መንፈሳዊ ፣ ስነ አእምሮአዊ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

[22] ለምሳሌ፡- አያልነህ መላኩ (ቴአትር፣ስነ-ጽሁፍና ባህል)፣ ፍስሀ በላይ ይማም (ቋንቋና ስነ ጽሁፍ)፣ መንግስቱ ለማ (ቴአትር)፣ አስታጥቃቸው ይሁን (ቴአትር፣ ቋንቋና ስነ ጽሁፍ)፣ ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ (ቴአትር፣ ቋንቋና ስነ ጽሁፍ) ።

3.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

በአንድ ጥናት ውስጥ የምርምር ችግሮችን መሠረት ያደረጉ የምርምር ጥያቄዎችን በመመለስ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ እንደ ጥናቱ ባህርይ ልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል (Marshal & Rossman, 2006:111)። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውሰጥ ሥራ ላይ የዋለ ሁለት ዘዴዎች ሲሆኑ እነሱም ሰነድ ዳሰሳና ቃለ መጠይቅ ናቸዉ።

3.4.1. ሰነድ ዳሰሳ፡- ሰነድ ዳሰሳ ማለት ከጥናቱ ርዕሰ -ጉዳይ ጋር ተዛማጅ የሆኑናመረጃ ሊሰጡ የሚችሉትን የተለያዩ መጻህፍት፣መጣጥፎችን፣የግልናየድርጅት ማህደራትን፣ብሮሸሮሸሮችን፣በራሪወረቀቶችን፣ፖምፍሌቶች፣ፖስተሮች፣ጥራዞች፣የተማሪ መጽሀፍት፣የስራማኑዋሎች፣መመሪያዎች፣ማዕቀፎች፣ፖሊሲዎች፣ስትራቴጅዎች፣ጋዜጦ ች፣መጽሄቶች፣ የጥናትና ምርምር ጽሁፎች ወዘተ. ፍተሻ ማድረግ ማለት ነዉ ሲል (ያዴሳ ቶሎሳ፣2007፡108) ያብራራል። በተያያዘ Goldstien የሰነድ ዳሰሳ ሊሰራ ከታሰበበትጊዜ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ፍጻሜ ድረስ ባሉት ተግባራት ሁሉ የሚከወን የጥናትናምርምር ሂደትናተግባር መሆኑን ይገልጻል (Goldestein 1964:110)። በዚህ ጥናት የሰነድ ዳሰሳ ተግባራዊ የተደረገበት ሂደትም ይህን የተከተለ ነዉ።

3.4.2 ቃለ-መጠይቅ፡- በፎክሎር ጥናት ውስጥ ከአውድ ውጪ መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች አንዱ በሆነው ቃለ-መጠይቅ ወቅት መረጃ አቀባዮች ስለተጠየቁት ጉዳዮች እንደማህበረሰቡ አባልነታቸው ከውስጣቸው የሚገልጹበት እና የሚያስረዱበት መሆኑን Goldstien ሲገልጽ እንዲህ ይላል። “This method used by field worker to obtain data about ideas or events outside the context of the interview itself through questioning persons believed or known to have that info rmation. During the interview, the informants describe situations, materials, attitudes, or ideas from the advantage point of the insider (Goldstein, 1964፡ 77-78).” ይህ ማለት በዚህ ዘዴ የመስክ ሠራተኛው ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ከአውዱ ውጭ መረጃዎችን የሚያገኝበት መንገድ ነው። በዚህ ጥናትም ቃለ-መጠይቅን ተጠቅሜ መረጃ ለመሰብሰብ መሞከሬ በተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አካባቢያዊና ባህላዊ ትርጉም በተሟላ ሁኔታ ተገንዝቤ ለመግለጽ፣ለመተርጎምናለመተንተን ስለሚረዳኝ ነዉ። ከዚሁ አኳያ በዚህ ጥናት

የተገደበ እና ያልተገደበ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒኮች[23] እንደ ሁኔታው በማመጣጠንና በማሰባጠር ተግባራዊ ሆነዋል።

3.5 የመረጃ መተንተኛ ቲዎሪዎች

ይህ ክፍል የጥናቱ መረጃ መተንተኛ ቲዎሪዎች ንድፈ ሀሳባዊ ዳሰሳ የተደረገበት ነዉ። ከዚህ እንደሚከተለዉ ይቀርባሉ።

3.5.1 ተግባራዊ ቲዎሪ

ተግባራዊ ቲዎሪ በማህበራዊ ህይወትና በስነ-ተፈጥሯዊ ህይወት ውስጥ ያለውን ተመሳሳይነት ያንፀባርቃል ። የአንድ ፍጡር መላ አካላት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ተደምረው ፍጡሩን ሙሉና ህያው የሚያደርጉት ከሆነ የፎክሎር ክዋኔዎችም ተደምረው የከዋኙን ማህበረሰብ ህልውና ሙሉ የሚያደርጉ ተግባራዊ ፋይዳዎች አሏቸው (Radcliffe-Brown 1935: 394-397)። ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው Bascom (1954፡344-346) ያስረዳል። ከዚያም በላይ የተግባራዊ ቲዮሪ እሳቤን ማወቅ አንድ የሰዎች ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰራ እንደሆነ ለመረዳት ያግዘናል። ተግባራዊ ቲዮሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል (Okpewho (1992:173)። እዚህ ላይ ማንኛውንም የሚለው አባባል ተግባራዊ ቲዮሪ በማህበረሰቡ ውስጥ በግንባታ ሚና ብቻ ሳይሆን በአፍራሽ ሚናም የሚገለጽ መሆኑን ነው። የፎክሎር ተግባር የማህበረሰቡን ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ በማሸጋገር ሚና እንዳለው ሁሉ በተቃራኒም ያለውን

[23] ያልተገደበ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒክ በአጥኚውና በመረጃ ሰጪው መካከል የሚካሔድ ያልተገደበ ውይይትን ሲሆን፣ በሌላ በኩል የተገደበ የቃለ-መጠይቅ ይህን ቴክኒክ የጥያቄና መልሱ በአጥኚው የሚመራ ሆኖ አጥኚው ቀድመው የተዘጋጁና ተከታታይ ጥያቄዎችን ይጠይቃል።ቴክኒኩ አገልግሎት ላይ የሚውለው የሚፈለገውን የመረጃ አይነት መሰረት በማድረግ ነው። መረጃ ሰጪው በሚፈልገዉ መረጃዎች ላይ ብቻ አተኩሮ ያለውን እውቀት እንዲያካፍል በመደረጉ ይህ ቴክኒክ ጊዜ ከመቆጠብ አንፃር ጠቃሚ ነው (Goldestein 1964:109)።

አፍራሽ ገጽታ በሚመለከት ከድረገጽ የተገኘ የBascom (1954) ሥራ እንደሚከተለው ተገልጿል።

> *The functions of folklore can be classified differently, …. Folklore operates within a society to insure conformity to the accepted cultural norms, and continuity from generation to generation through its role in education and the extent to which it mirrors culture. To the extent inwhich folklore contrasts with the accepted norms and offers socially acceptable forms of release through amusement or humor and through creative imagination and fantasy, it tends to preserve the institutions from direct attack and change. (http://www.jstor.org Fri Apr 13 , 2017).*

ከዚህ የምንገነዘበው ይህ ቲዮሪ የማህበረሰቡ ባህላዊ ጉዳዮች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ፋይዳቸውን የሚመለከት ቢሆንም ከጠቃሚ ባህላዊ እሴት በተቃራኒ ያሉትን ጉዳዮችም የሚተነትንበት መንገድ መሆኑን ነው።

በሌላ መልኩ እያንዳንዱ የፎክሎር ቅንጣት ዘውግ (genre) ለሰው ልጆች ትርጉምና አገልግሎት አላቸው። ይህም ማለት ዘውጉ ለምን ዓላማ እንደሚነገር፣ እንደሚከወንና ምን አገልገሎት እንዳለው አውድን መሠረት አድርጎ የሚገለጽበትና የሚተነትንበት መሆኑን Malinowski (1946 [1923]) ይገልጻል ። ከዚሁ አኳያ የዚህ ቲዮሪ ዋና ዓላማ አንድ ሥነቃል የተለያየ አገልግሎት እንዳለው የሚያሳይ ነው። በዚሁ ቲዮሪ መሰረትም ሥነቃል፤ የማስተማር፣ የማዝናናት፣ ባህልን የመጠበቅ፣ የመቆጣጠርና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ባህላዊ ወጎቹን የሚጠብቅበትና ማህበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበት ነው (Bauman, 1977)።

ከዚህ አንጻር ሲታይ ተግባራዊ ቲዮሪ በልዩ ልዩ መልኮች (ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ተምሳሌታዊ ወዘተ …) የሚገለጽ በመሆኑ የማይደሰሳቸው መስኮች የሉም። ይህም ማለት በማህበረሰቡ ውስጥ የሥነቃል ሚና በልዩ ልዩ መስኮች ከሚገለጽባቸው ጉዳዮች አንዱ ፋይዳውን ማሳየት ነው። ስለዚህ

ተግባራዊ ቲዎሪ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ተግባራትንና ፋይዳዎችን ለማብራራት ምቹ በመሆኑ ለዚህ ጥናት ለመተንተኛነት ተመርጧል።

3.5.2 ተምሳሌታዊ ቲዎሪ

በ Dorson (1972) አከፋፈል ተምሳሌት በቁሳዊ ባሕል የፎክሎር ዘውግ ሥር የሚካተት ነው ሲል፣ Vitor Turner (1961) ደግሞ የማህበረሰብን እውቀት በውስጣቸው ያቀፉ ነገሮች መኖራቸውን ይጠቁማል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተምሳሌት ገላጭ የሚሆነው በቅርፁም ይሁን በይዘቱ ባዘለው ማህበረ ባህላዊ ፍቺ ጭምር እንዳለውና ቁሳዊ ብቻም ሳይሆን ረቂቅ ነገርም (Physical and Abstract) ተምሳሌትነት ሊኖራቸው እንደሚችል ጠቅሰው ተጨባጭና ረቂቅ በማለት በሁለት ይከፍላሉ። ረቂቅ ከሆኑት ቀለማት፣ ድምፆች፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ክስተቶች፣ ወዘተ... ሊጠቀሱ እንደሚችሉ Eahleman, J. Ross, Barbara G. Cashion, Laurence A. Basirico: (1993) ያስረዳሉ።

በአፍሪካ በተለይም በዛምቢያ ማህበረሰብ ላይ ጥናት ያደረገው Vitor Turner (1967:19) የተምሳሌት አይነቶች ውጫዊ በሆኑ ወይም ግዑዝ ነገር ብቻ እንዳልሆኑ ጠቅሶ በሰዎች ተግባራት ውስጥም ተምሳሌታዊ ጉዳዮች እንዳሉ በመግለጽ በተመለከተበት የመስክ አውድ ቁሳዊ የሆኑ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ ድርጊቶች፣ የማህበራዊ ግንኙነት መስመሮች፣ ክስተቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሥፍራዎች ጭምር ተምሳሌታዊ አገልግሎት ይዘው እንደሚገኙ ይዘረዝራል።

ከእነዚህ ከተዘረዘሩ የተምሳሌት ዓይነቶች የምንገነዘበው፣ የነባርም ይሁን የሌሎች ፍቺዎች ስፋትና ጥልቀት ጎልቶ የሚታየው የሚነገረውና የሚከወነው የሥነቃል ዓይነት በአውድ ውስጥ ማህበራዊ እውቀቱ ያለውን ድርሻ ማሳየቱ (ማጉላቱ) ላይ ነው።

በመሆኑም የሥነቃል ተምሳሌት በቁጥሮች፣ በስሞች፣ በቀለሞች፣ በአቅጣጫዎች፣ በክስተቶች እና በቦታዎች የሚገለጽ አውዳዊ ትርጉም አላቸው። ተምሳሌታዊ ትርጉሙ እንደየ ባህሉ ስለሚለያይ ላንዱ ተምሳሌት የሆነ ለሌላው ተራ ሊሆን እንደሚችል Gusfield and Jerz (1984) ይገልጻሉ። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር

ተምሳሌት በወካይና ተወካይ መካከል ያለውን ዝምድና የሚገልጽ ሲሆን መገለጫው በቋንቋ፣ በቁሳቁስና በክዋኔ ሆኖ በውስጡም በርካታ ትርጉሞችን የያዘ ነው (Dundes, 1989:112-114)።

በማህበረሰቡ ፎክሎራዊ እውቀት ውስጥ አብዛኞቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወክሉት ነገር ይኖራል። እነዚህ የውክልና ሁኔታዎችም በአብዛኛዉ ሜታፈሮች (Metaphors) መሆናቸውን Mills (2008) እና ባይለየኝ ጣሰዉ (2009) ይገልጻሉ። ሌሎችም የሥነቃል ዓይነቶች ማህበረሰቡ እንደየሚገለገልበት ሁኔታ የሚወክሉት ጉዳይና የየራሳቸው ማህበረሰባዊ ትርጉም አላቸዉ። ከዚህ የምንገነዘበው አንድን ነገር በተምሳሌታዊ ንጽጽር ለመግለጽ የሜታፈር አገልግሎት የጎላ መሆኑን ነው።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ከተምሳሌት ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ መሰል ጉዳዮችን ለመተንተን ይህ ቲዎሪ ተመራጭ ሆኗል።

3.5.3 አውዳዊ ቲዎሪ

የዚህ ቲዮሪ አቀንቃኞች (Bascom 1954 እና Ben Amos 1993) ዋነኛ ትኩረት አንድ ፎክሎር ዘውግ የተከናወነበትን አውድ ማጉላት ነው። ቀደምት የBascom (1954) እሳቤዎችን መሰረት በማድረግ ምሁራን እንዳመለከቱት ማንኛውም ክዋኔ ሲተነተን የክዋኔው ዓውድ መገለጽ አለበት (Okpewho 1992:10፤ Ben Amos 1993:1፤ ፈቃደ 1991:37)። Jackson (1986፡4) ዓውድ በስነ ሰብእ (Anthropology) ጥናት ውስጥ ላሉ ሁሉም ተመራማሪዎች ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ለሁሉም ግን ዓውድ ወሳኝ እና በተመሳሳይ መንገድ የሚያገለግል አይደለም። እንደዚሁም Sims and Stephens (2005፡137) ዓውድ የፎክሎር አንድ ቅንጣት የሚከወንበት ውስን ማህበራዊ ሁነት መሆኑን ገልጿል።

ስለዚህ የፎክሎር ጥናትና ምርምር አውድን መሠረት ያደረገ ነው ሲባል የሥነቃሉ ዓይነት (ምሳሌያዊ ንግግር፣ ቀልድ ተረት ዘፈን ወዘተ ... (Text)፣ የዓይነቱ ውስጣዊ ሁኔታ ወይም የቋንቋው ሳህይ (Texture) እና ሥነቃሉ የተነገረበት (የተከወነበት)

አውድ (Context) ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (Dundes, 1980:20-32; Ben-Amos, 1993:210)።

ከዚሁ አንጻር የዓውዳዊ ቲዮሪ ዋና ትኩረት ክዋኔን ማዕከል ያደረጉ ሁሉን አቀፍ መረጃዎች ከባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች አኳያ የከዋኙን አከዋወን ሁኔታ ከጊዜና ቦታ አንጻር የሚገለጽበት መንገድ ነው (Dorson, 1972)። በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ማለት በስፋት ሲታይ ስለ አንድ ድርጊት ክንውን የሚገልጽ ሲሆን በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ቲዮሪዎችና ዘዴዎችን የሚመለከት መሆኑን Ben-Amos (2006) እና Goldstein (2004) ይገልጻሉ። ይህም ተናጋሪው ሥነቃሉን በሚናገርበት ጊዜ የአቀራረብ ሁኔታ፣ የሚከውኗቸውን ድርጊቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴና የከዋኙን ልዩ ችሎታ፣ እንዲሁም የአድማጭ ተመልካቹን ግብረመልስና ስሜት የሚመለከት በአጠቃላይ በሰዎች የርስ በእርስ ግንኙነት ውስጥ የሚታዩ ጥበባዊ መገለጫዎች መሆኑን Bauman (1977) ያብራራል። በማያያዝ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአውድ ግንዛቤ ያለውንና የታየውን መረጃ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አካቶ መተርጎምንና መተንተንን የሚያካትት መሆኑን Ben-Amos (1993፡ 210-211) ያስረዳል።

ይህንኑ በማጠናከር አውድን ከሥነቃል አንጻር ሲገልጽ ከሦስት ቁልፍ ጉዳዮች ማለትም ከከዋኙ ሰብእና፣ ከመከወኛው ድባብ፣ ከማህበራዊና ባህላዊ አውድ አኳያ ይመለከታል (Okepewho, 1992: 105)። እንደ እርሱ አገላለጽ የከዋኙ ሰብእና የሚላቸው ግለሰቡ ይዞት የሚቀርበውን ማንኛውንም ነገር የሚያመለክት ሲሆን እነዚህም ኪናዊ ዝንባሌውን፣ ቤተሰባዊ ዳራውን፣ ግላዊ ተመክሮዎቹን እና የተከታተላቸውን ሥልጠናዎች የሚመለከቱ ናቸው። የክዋኔው ድባብ ማለት ከከዋኙ አንደበት የሚወጡትን ቴክስቶች (የሥነቃል ዓይነቶች)፣ ቴክስቱን ለመግለጽ የተጠቀማቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ከዋኙን ከበው ያሉ ታዳሚዎችና ተጽዕኗቸውን እንዲሁም በከዋኙ ስኬት ወይም ውድቀት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ያካትታል።

ለአውድ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ብያኔ ሰጥተዋል። ለምሳሌ Sims & Stephens አውድ አንድ ድርጊት የሚከወንበት ጊዜና ቦታ እንደሆነ በአጭሩ አስቀምጠዋል። ስለዚህ የአንድ ፎክ ቡድን አባላት ፎክሎርን የሚጋሩት አካላዊ

መቼቶችና ማህበራዊ ሁነቶች እንዲሁም የታዳሚዎችና ከዋኞች ግንኙነት አውድን ይመሰርታሉ። በመሆኑም አውድ የሚያመለክተው በቴክስትና ክዋኔ ዙሪያ የሚገኙ ማንኛውንም የክዋኔ፣ እውነታ፣ ቁሳቁስ፣ ሁነቶችና ክስተቶችን ጭምር ነው (Sims & Stephens,2005:138)። የተለያዩ የአውድ ዓይነቶች አሉ። እነዚህን ለይቶ ማወቁ ለሚካሄደው ፎክሎራዊ ትንታኔ ወሳኝ ሚና አለው። ስለዚህ የአውድ ዓይነቶች መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል።

የአውድ ዓይነቶች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም ማህበራዊ አውድ እና ባህላዊ አውድ ይባላሉ። መማህበራዊ አውድ የሚባለው የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ባህላዊ አውድ ደግሞ በውስጡ የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚቀርብበት ሰፊ ገጽታ ሲሆን፤ ክዋኔው በውስጡ የሚወክላቸውን ነገሮች፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የሚመራበት ማህበራዊ ደንብ፣ የተሳታፊዎች የእምነት ስርዓት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኙ የታሪክ ዕውቀትና የስነ-ምግባር ህግጋትን ሁሉ ያጠቃልላል (Ben-Amos,1993፡216)።

አንድ ፎክሎረኛ መረጃ ለመተንተን ሲያደራጅ አውድን በተመለከተ ሊያተኮርባቸው የሚገባ ስድስት ነጥቦች እንዳሉ Bauman ያስረዳል። እነሱም፡- ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ ይባላሉ (Bauman,1983፡367)። የእነዚህን አውድ ትኩረት እንደሚከተለው እንመልከታለን።

ፍቻዊ አውድ፡- የዚህ አውድ ትኩረት የሚያጠነጥነው ፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ላይ ነው። ይኸውም ማህበረሰቡ ስለሚከውናቸው ፎክሎሮች (የሥነቃል ዓይነቶች) ያለው ግንዛቤ፣ አረዳዱ፣ ለመከወን ያነሳሳው ጉዳይና የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳዩ ለመረዳት ያስችለናል።

ተቋማዊ አውድ፡- በአውድ ተኮር ጥናት ሊተኮርበት ከሚገባው ውስጥ ተቋማዊ አውድ ሌላኛው ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። ጉዳዩ የሚከወንበት በባህሉ ውስጥ የት ቦታ ላይ

እንደሆነ ለይተን ማስቀመጥ እንዳለብን የሚያስገነዝበን አውድ ነው። ይኸውም የሚከወኑት የት እንደሆነ ከማስገንዘቡም በላይ ፎክሎራዊ ጉዳዩ መከወናቸው የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ለመመርመር ያግዛል።

የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፡- በአውድ ተኮር ጥናት ውስጥ የሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሻ ነው። ይሄም የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ ምንነት፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድና አንዱን ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀምበትን ዘዴ በውስጡ ያካትታል።

ማህበራዊ መሰረት፡- ማህበራዊ መሰረት የሚባለው የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት የሚያመለክተን ነው። ይሄ ማለት የሚጠናው ፎክሎር የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፣ የትኛውን ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይ፣ በክዋኔው ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረዳት የተሻለ አውዳዊ ትንታኔ መስጠት ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት አባላት በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሙያ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉ ቡድኖች ይከፈላሉ።

ግለሰባዊ አውድ፡- ግለሰባዊ አውድ የሚመለከተው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የግለሰቡን ሕይወት ምን እንደሚመስል ከማወቅ ላይ ነው። በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከግለሰቡ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር እንዴት ይያያዛል? ለሚል ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ላይ የሚያጠነጥን ነው። በዚህ አውድ ውስጥ የግለሰቡን የመከወን ችሎታና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለግለሰቡ የሚሰጠውን ስሜት ሊጤን ይገባል። ይህም ከግለሰቡ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊ እና ባህላዊ ማንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል።

ሁኔታዊ አውድ፡- በመጨረሻ በአውዳዊ ትንተና ውስጥ የሚነሳው ጉዳይ ሁኔታዊ አውድ ሲሆን፣ ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚከውነው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? ለሚለውና በማህበራዊ ሁኔታ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ምላሽ የሚሰጥ ነው። ሁኔታዊ አውድ ሲባል በባህሉ የተወሰነ የአንድ ገጠመኝ መግለጫ አንድ

ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው። በዚህ ውስጥ አካላዊ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገነዘቡባቸው የተለያዩ ህግጋት፣ በክዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓጎም የሚከናወንበት መመሪያ፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት፣ ቅደም ተከተላቸውን ጭምር ያካትታል።

3.5.4 የክዋኔ ቲዎሪ

ፎክሎርን ለሚያጠና ሰው ክዋኔን መመልከት ማለት ሰዎች አንድን ድርጊት እንዴት እንደሚፈጥሩ፣ እንደሚለዋወጡ እና ከድርጊቱ መልእክት ጋር እንዴት እንደሚተዋወቁ መገንዘብ ማለት ነው። የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔ ለማጥናት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁለት መሰረታዊ አተያዮች እንዳሉ እና የሚከተሉት እንደሆኑ Bauman, (1992፡ 5) በአርትኡቱ ውስጥ ጠቁመዋል። የመጀመሪያው ማህበረሰቡ ጉዳዩን የሚያከናውነው ተስማምቶ ባዋቀረው ስርዓትና ደንብ መሰረት በመሆኑ ታዳሚው አዳዲስ ፎክሎሮችን የመፍጠር እድል ሊኖረው እንደሚችል የሚያመለክት ሀሳብ ሲኖረው፣ ሁለተኛው ደግሞ ከዋኙ በተሳታፊዎች ብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጠቀመው ቋንቋ፣ የአነጋገር ለዛ እና የአከዋወን ሂደት የሚያመለክት ሀሳብ አለው።

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ አቀራረብ በሚከውነው ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች እንዲሁም እንደ ከዋኙና ተሳታፊው አቅም ይለያያል። በዚህ ምክንያት መልዕክቱም ስለሚለያይ የክዋኔው ደረጃ በሚቀርብበት አጋጣሚ ይወሰናል። በሌላ በኩል የከዋኙና የተሳታፊው ጾታ፣ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፣ ክዋኔውን ለመከወን የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ ጉዳዩ የሚቀርብበት ወቅትና ጊዜ እንዲሁም የፎክሎራዊ ጉዳዩ ዓይነት፣ ጭብጥና የአቀራረብ ስልት ሁሉ በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ በመሆናቸው ለሚከወኑበት አጋጣሚ የሚመጥኑ ሆነው መቅረብ አለባቸው።

በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ ጽንሰ ሀሳብ ወደ ማህበራዊ ዓውዶችና ግንኙነቶች እየሰፋ በመምጣቱ፤ የከዋኞችንና የታዳሚዎችን ሚና የክዋኔው ፋይዳና የሰው ልጅ የህይወት ተሞክሮዎች እንዴት እርስ በርስ እንደሚደጋገፉ ይመረምራል። ስለዚህ

ክዋኔ ሰዎች አንድን ፎክሎር ቅንጣት የሚፈጥሩበት፣ የሚጋሩበትና ከቅንጣቱ ጋር የሚዛመዱበት ስልት በመሆኑ ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ህይወትና ከትርጉም የሚነጠል ጉዳይ አይደለም። ክዋኔም በሥነቃል ውስጥ ሁሉም የጥበቡ አላባውያንን ያማክላል (Finnegan 1992)። ፎክሎር ከዋኞችንና ታዳሚዎችን የሚያካትትና በክዋኔ ውስጥ ያለው የፉክክር ጉዳይም መመዝገብና መተንተን ያለበት ባህርይ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል (Dundes 2005፡389፣ Sims and Stephens 2005፡128)።

በመሆኑም በዚህ ጥናት የፎክሎራዊ ጉዳችን ክዋኔ በተዉኔቶች ዉስጥ ለመተንተን የክዋኔ ቲዎሪ ተመርጧል፡፡

3.5.5 የፎክሎር ዳያክሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ

በዳይክሮኒክ እሳቤ መሰረት አንድ በንግግር የሚከወን የፎክሎር ዓይነት የታሪክና የማህበራዊ ድርጊቶች ውጤት ነው (Bauman & Brigges 1992)፡፡ አንድ የስነ ቃል አይነት በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች ውስጥ የነበረውን ቀጣይነት ለማየት፣ የማህበረሰቡን ህይወት ከማንጸባረቅ አኳያ የተጫወተውን ሚናና የነበረውን ተግባር ለመመርመር ይህ ቲዮሪ ይረዳል፡፡ ከሲንክሮኒክ አቅጣጫም ስነ ቃሎች ይተነተናሉ፡፡ ይህ አቅጣጫ በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ ስነ ቃሎች መካከል ያለውን የይዘት ገጽታዎች (Textual Features) ስምረት ለመፈተሽ ይረዳል፡፡ እነዚህ የይዘት ገጽታዎች በስነ ቃሎች አማካይነት የተላለፉት መልዕክቶች ምን ያህል ጥምረትና ስምረት እንደነበራቸው ለመግለጽ ያገለግላሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ ስነቃሎችን ለመተንተን የመሰኩ ምሁራን ዳያክሮኒክና ሲንክሮኒክ ብለው የሚጠሩት ይህ ቲዎሪ ተመርጧል፡፡

3.5.6 የፌሚኒዝም ቲዎሪ

የፌሚኒዝም ቲዎሪ በተለያዩ ንዑስ ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋሉት ራዲካል ፌሚኒዝም እና የባህል ፌሚኒዝም የተባሉት ናቸዉ፡፡

ራዲካል ፌሚኒዝም፡ - የዚህ ጽንሰ ሀሳብ አራማጆች በጾታዎች መካከል እስካሁን እኩልነት የለም ፣በዓለም ሁሉም ማህበረሰብ ዉስጥ የሴቶች የበታችነት

ይንጸባረቃል፤የወንዶች የበላይነት አለማቀፋዊ እስከመሆን ደርሷል ብለዉ ያምናሉ (Pine, 1996)፡፡ በመሆኑም ሴቶች በጸታቸዉ የተነሳ የሚደርሰዉንን በደል በመቃወም በማህበራዊ፣ኢኮኖሚዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከወንዶች እኩል መብት ሊኖራቸዉ ይገባል ይላሉ፡፡

የባህል ፌሚኒዝም ፡- የባህል ፌሚኒዝም አቀንቃኞች ሴቶች ተሸለዉ የሚገኙባቸዉና ትኩረት ሊደረግባቸዉ የሚገቡ አስፈላጊ ጉዳዮች ስላሉ በእነዚህ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ይላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ሴቶች በተፈጥሯቸዉ ደግ፣ርህሩህና ጨዋ ስለሆኑ በዚህ አንጻር ዓለማችን በሴቶች ብትመራ ጦርነት የሚባል ነገር በምድራችን ባልነበር ብለዉ ያምናሉ፡፡ስለ ሴቶች ሲታሰብም በተፈጥሮ ስለታደሉት የተለየ ችሎታና አቅም ላይ ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ይገልጻሉ (http:/www.amazoncastle.com /feminism/eco cult.shtm.14/11/2017)፡፡ Fredel እና Lampher በአለም አቀፍ ደረጃ የሴቶች የበታችነትና በወንዶች ተጽእኖ ስር መሆን የሚታወቅ ቢሆንም አንዳንድ ሴቶች በአካባቢያቸዉ ጉዳይ ላይ ትልቅ ሀይልና ስልጣና ሊይዙ የሚችሉበት አቅዋም እንዳለ በአንዳንድ ባህሎች ዉስጥ መታየቱን ይገልጻሉ(1979፡252)፡፡ ከዚሁጋር በተያያዘ ሁኔታ በአንድ ማህበራዊ አዉድ ዉስጥ አንድ የተለየ ስብዕና እንዴት ያድጋል፣ ይወጣል የሚለዉን ያጠኑ ተመራማሪዎች አሉ፡፡ከእነዚህ መካከል Diboyes እንደምትለዉ በአንድ ማህበረሰብ መዋቅር ዉስጥ ከአብዛኛዉ የጋራ ስርዓት ወጣ ያለ ልዩ ግለሰቦች በአንድ በባህል ዉስጥ ይፈጠራሉ፡፡ የእነዚህ ግለሰቦች ማንነት በህብረተሰቡ ዉስጥ ተጽእኖ ይፈጥራል (Diboyes in Myrphy, 2004)፡፡ የ Diboyes ን ሀሳብ በሚጠናክር መልኩ Nahomi እና Klawdiya በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ ግለሰቦች ከሚኖሩበት ባህላዊ አስተሳሰብ ወጣ ያለ ፈጠራ ፣ተቃዉሞና አለመግባባት የታከለበት አስተሳሰብ ይይዛሉ፤አእምሯቸዉ አዲስ አመለካከት በመያዝ የቀድሞዉን የማስተካከል ስራ ይሰራል፤እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ለባህርይ ለዉጥ ይጋብዛል፤ ያደፋፍራል ይላሉ(Nahomi and Klawdiya in Kottak,1994:410) ::

በዚህ ጥናት አንዳንድ ተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱ ፎከሎራዊ ጉዳዮች አስካሁን ከቀረበዉ አኳያ መተንተን የሚገባቸዉ ናቸዉ፡፡ በመሆኑም የራዲካልና የባህል

ፌሚኒዝም ቲዎሪን በመጠቀም ከዚህ አንጻር ያሉትን መረጃዎችን ለመተንተን ተሞክሯል።

3.5.7 የሐይማኖት ቲዎሪ

ሃይማኖትና እምነት በራሱ አንድ የጥናት መስክ ቢሆንም በፎክሎር ጥናት በተለይም በሚቶሎጂ መስክ ከሚጠኑት አንዱና ዐቢይ ጉዳይ ነው። የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በህገረ-ሰባዊ ልማድና በሃይማኖት መካከል ቁርኝት በመኖሩ "ሃይማኖትና ፎክሎር የለየላቸው ተቃራኒ ሀሳቦች ናቸው" ማለት ስህተት መሆኑን በአፀንኦት ይናገራል (Larry 1986, in Fekade 2003:53)። ስለሃይማኖት ምንነት የተለያዩ ጸሀፍት በተለያየ መልኩ፣ ነገር ግን ተቀራራቢ ይዘት ባላቸው አገላለጽ ለማስረዳት ሞክረዋል። ለአብነት ያህል O'Neil ሃይማኖት ማለት ሰዎች ዘወትር በልዕለ ተፈጥሮ (supernatural being) ኃያልነት የማመን ስርዓት እንደሆነ ይገልጻል (O'Neil, 2009)። Schoemaker ደግሞ የሃይማኖት ብያኔ መታየት ያለበት ከመንፈሳዊ ለማዶች አንጻር እንደሆነ ያስረዳል። ይኸውም እነዚህን በሚመስል የሕይወት ልምዶች ስርዓት የተደራጀ ሲሆን፣ ሃይማኖቶች በቅርጻቸውና በይዘታቸው ሊለያዩ ይችላሉ። በሌላ በኩል ሃይማኖት የእምነት ስርዓት ሆኖ በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ፈጣሪያቸውን ለማግባባት የሚከወኑ ከበራዎች አሉ (Schoemaker, 1990፡238)። እነ Peoples, J. ይህንኑ ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

"The three components of all religions, then are (1) belifes about the existence and nature of supernatural powers, (2) mythologies about the historical deeds of these powers, and (3) rituals intended to influence these powers to intervene favorably on behalf of the performances" (Peoples, J. and Bailey, G. 1991:293).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሃይማኖት በውስጡ እምነቶች (belifes)፣ ሚቶች (mythologies) እና ከበራዎች (rituals) እርስ በርስ የሚደጋገፉ ጽንሰ ሀሰቦችን እንደሚያካትት ነው።

ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሃይማኖት ዓለምን በፈጠረና ተፈጥሮን በበላይነት ይቆጣጠራል ተብሎ በሚታመንበት ልዕለ ተፈጥሮ (supernatural being) ልዩ ኃይል በእምነት መቀበል፣ ስለልዕለ ተፈጥሮው እውነትነትና ሀያልነት የሚያስረግጡ ሚቶች ያላቸውና ሃይማኖታዊ ድርጊቶቹ ያዘሉትን እሴቶች የሚገልጹ ከበራዎች ውጤት እንደሆነ ከተለያዩ ብያኔዎች ለመረዳት እንችላለን፡፡

በዚህ ጥናት ከሃይማኖት ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለመተንተን የሀይማኖት ቲዎሪ ተመራጭ ሆኖአል፡፡

3.5.8 የማህበረሰብ እዉቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ

ይህ ንድፈ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ገኖ የወጣው እ.አ.አ. በ1966 በእነ Berger,P. & Luckman T. ካሳተሙት "The Social Construction of Reality" ከሚለዉ መጽሀፋቸው በኋላ እንደሆነ ይገለጻል፡፡ የማህበረሰብ የውቀት አዋቃሪያን ንድፈ-ሀሳብ ማህበረሰቡ ከሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት በሂደት ልማድን እየፈጠሩ፤ በመቀጠል ተቋማትን እየገነቡ ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ ተቋማቱ ቅደም ተከተላዊ ተግባራትን በመጀመሪያ ደረጃ ያዋቅራሉ የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ ይህ የጋራ ዕውቀትም እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ካለው ዕውቀት ተጠራቅሞ የተገነባ እንደሆነ Berger & Luckman እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

“The primary knowledge about the institutional order is knowledge on the pretheoretical level. It is the sum total of ’what everybody knows’ about a social world, an assemblage of maxims, morals, proverbial nuggets of wisdom, values & beliefs’, myth, and soforth… “ (Berger and Luckman,1966:83).

በመሆኑም ከዚህ ንድፈ -ሀሳብ አተያይ ዕውቀት ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ማህበራዊ ውቅር መሆኑን ነው፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ማህበረሰቡ በጋራ ያዋቀሩት ዕውቀት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ በእኩል የሚሰራ ድንጋጌ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ግለሰቦች ማህበረሰቡ ባኖሯቸው ድንጋጌዎች ይገለገላል፤ ይመራል፤ ይቀጣል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ዕውቀቱ በሂደት ባዋቀሯቸው የጋራ ጉዳዮች ውስጥ በግለሰብ ደረጃና በማህበረሰብ ደረጃ ትርጉም አዘል ሆኖ ሊሰራ እንደሚችል ያወሳል፡፡ ሆኖም

በግለሰብ ደረጃ ያለው ዕውቀት ከግለሰብ ግለሰብ ሲለያይ፤ ተቋማትም ባላቸው ሚናና አግባብነት ያለው የግንኙነት ህግ የተነሳ በየደረጃው ይለያያል ፡፡

በዚህ ጥናት አንዳንድ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ከማህበረሰብ እዉቀት አኳያ ማየት የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህ ቲዎሪ ሊመረጥ ችሏል፡፡

ምዕራፍ አራት

4. በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት

ይህ ምዕራፍ ለጥናቱ በተመረጡት ተውኔቶች፣ ማለትም፣ (**ፋቡላ፣ ያላቻ ጋብቻ፣ አልቃሸና ዘፋኝ፣ ሾተላይ፣ የቴዎድሮስ ራዕይ፣ የቃቄ ወርዶወት እና የአሻልጅ**) ዉስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና የቀረበበት ነው። ትንተናው የተደረገው በዋናነት ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲሆን፣ አውዳዊ ቲዎሪ፣ የክዋኔ ቲዎሪ፣ ተምሳሌታዊ ቲዎሪ፣ የዳይከሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ፣ የፌሚኒዝም ቲዎሪ፣ የሐይማኖት ቲዎሪ እና የማህበረሰብ አዋቃሪያን ቲዎሪ እንደ አስፈላጊነቱ ደጋፊ የመተንተኛ ቲዎሪዎች በመሆን አገልግለዋል። በተጨማሪም በአንዳንድ ተዉኔቶች ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አካባቢያዊና ባህላዊ ትርጉም በተሟላ ሁኔታ ተገንዝቦ ለመተንተን በቃለ-መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ጥቅም ላይ ውሏል። እያንዳንዱን ተውኔት በተናጠል ወስዶ በማየት በውስጡ የተነሱትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለመተንተን የተሞከረ ሲሆን፣ ለትንተና አመቺነት ሲባል በአንዳንድ ተዉኔቶች ዉስጥ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች አንድ ላይ እንዲመደቡ ተደርጓል። ትንተናዉ የሚጀምረዉ የተውኔቶቹን ታሪክ አስቀድሞ በማቅረብ ሲሆን እንደሚከተለዉ ይቀርባል።

4.1. ያላቻ ጋብቻ

ያላቻ ጋብቻ ታሪክ የተመሠረተው በወይዘሮ አልጋነሽ ዱብዳ እና በወንድማቸው ልጅ በባህሩ አዳሸነህ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ላይ ነው። የሁለቱም አለመግባባት ጉልቶ የታየው ባህሩ አክስቱ ያጨለትን የባላባት ልጅ እኩያውን ቢቢታ ጋሻው በዛን ንቆ አቻው ያልሆነችውን ገረዱ በለጤን ባገባ ጊዜ ነበር።

ወይዘሮ አልጋሽ ኮከብ ቆጣሪ፣ ጠጠር ጣይ አማክረው ቢቢታን ለባህሩ ለመዳር እየተዘጋጁ ባለበት ጊዜ በለጤን እንዳገባ ከሁለቱ ሽማግሌዎች አለቃና ሐጂ ሲሰሙ፣ በኋላም ከራሱ ከባህሩ አንደበት ሲያረጋግጡ የሚይዙት የሚጨብጡት አጥተው ይቆጣሉ። እውነታውን አሜን ብለው መቀበል ስላዳገታቸውም፣ “በለጤ

መተት አድርጋበት ነው፤ ያሰርኩሽ- ተበተብኩሽ አስደግማበት ነው" በማለት ድግምቱን ለማስፈታት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ስራውንም ለደብተራ ልዝቡ ይሰጣሉ፡፡

ደብተራ ልዝቡም ምንም እንኳን በለጌ ባህሩ ላይ መተት አስደርጋበታለች ብሎ ለማመን ቢከብደውም፣ አንድም የወይዘሮ አልጋነሽን ትእዛዝ ለመፈፀም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቃል የገቡለት የሃምሳ ብር ድርጐ እንዳትቀርበት በማሰብ በለጌን "ኮከባችሁ አይገጥምም፤ እሳትና ውሃ አጥፊና ጠፊ ናችሁ፤ ካልተለያያችሁ ከሁለት አንዳችሁ ይሞታል" በማለት አስፈራርቶ ከባህሩ ቤት እንድትወጣ ያደርጋታል፡፡ ነገር ግን እስከመጨረሻው አይሳካለትም፤ በአባ ማሚቶ (ጠጠር ጣዩ ጠንቋይ) እርዳታ ወደ ቤቷ ትመለሳለች፡፡ የወይዘሮ አልጋነሽ ሁሉ ልፋትና ባህሩን ለ ቢቢታ ለመዳር የነበራቸው ተስፋም በዚሁ ያበቃል፡፡

4.1.1. ያላቻ ጋብቻ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተዉኔት ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች፣ ኮከብ ቆጠራን፣ ጠጠር መጣልን እና የሐይማኖት መቻቻል ባህልን የሚመለከቱ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸዉን በዝርዝር የምንመለከታቸዉ ይሆናል፡፡

4.1.1.1 ኮከብ ቆጠራን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ሰው የተፈጠረው ከአራቱ ባህርያተ ስጋ ማለትም፣ (ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃ፣ መሬት) እና ከሶስቱ ባህርያተ ነፍስ ማለትም፣ (ልባዊት፣ ህያዊት፣ ነባቢት) ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ (ሞገስ፣ 1957፣ 66-72)፡፡ ከነዚህም መካከል ሰውን በስጋ ከፈጠሩት አራቱ ባህርያት (ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃ እና መሬት) በመነሳት ሰዉ ኮከቡን መቁጠር (ስለኮከቡ መናገር) ይቻላል ይባላል፡፡ ይህን አስመልክቶ ለዚህ ጥናት መረጃ የሰጡት ሊባኖስ መንክር (መሪ ጌታ) እነዚህ አራቱ ባህርያተ ስጋ በሰው ልጅ እድሜ ውስጥ እያንዳንዳቸው ሃያ ሃያ ዘመን ይገዛሉ ይላሉ፡፡[24]

[24] ሊባኖስ የተመኝ (መሪ ጌታ)፣ ቃል - መጠይቅ፣ደብረ ማርቆስ፣ መጋቢት፣2008ዓ.ም

መሪ ጌታ ሊባኖስ እንደሚሉት፣በመጀመሪያ ከአንድ እስከ ሃያ ዓመት ያለውን ነፋስ ይገዛል ተብሎ ይታመናል። ይህ ወቅት የሰው ልጅ የልጅነት ጊዜ ስለሆነ ፈጣን ነው። እዚህም እዚያም እንደ ነፋስ " ሽዉ ሽዉ" ማለት ያበዛል። ሲጠሩት አቤት፣ ሲልኩት ወዴት ለማለት አይታክትም። እዚህ ታይቶ እዚያ ነው። ነፋስ ፈጣን እንደሆነ ሁሉ፣ የሰው ልጅም በዚህ የልጅነት እድሜው ከወዲያ ወዲህ ማለት ያበዛል በማለት ይገልጻሉ።

ቀጣዩን ከሃያ ዓመት እስከ አርባ ዓመት ያለውን ዘመን የሚገዛው ደሞ እሳት ነው ይባላል። የሰው ልጅ በዚህ ዘመኑ ሀይሉ ይጨምራል፤ ወኔው እንደ እሳት ይንቀላቀላል፤ አነጋገሩ ያስፈራል ፤ ጡንቻው ይፈረጥማል፤ ጉልበተኛ ይሆናል። በዚህ ዘመን የሚፈራውም ሆነ የሚያሰጋው ነገር የለም። ስለዚህ ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም፤ ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ አንድን በሃያዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ወጣት በተለምዶ "እከሌ'ኮ እሳትነው" የሚሉት።

ሦስተኛው ዘመን፣ ከአርባ እስከ ስልሳ ዓመት ያለው የሰው ልጅ እድሜ ሲሆን፣ ሰው በዚህ ዘመኑ የውሃ ባህርይ ያሳያል ተብሎ ይገመታል፤ ልክ እንደ ውሃ ይቀዘቅዛል፤ አእምሮው ማገናዘብ ይጀምራል፤ ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገንም ይመለከታል። ቀልቡን መሰብሰብ፣ አደቡን መግዛት ይጀምራል። ለዚህም ነው "...ልብ በአርባ ዓመት" የሚባለው።

አራተኛውን ዘመን፣ ከስልሳ እስከ ሰማንያ ዓመት ያለውን የሰው ልጅ እድሜ የሚገዛው መሬት እንደሆነ ይገልጻሉ። በዚህ ዘመን የሰው ልጅ የመሬት ባህርይን ይወርሳል። ልክ እንደ መሬት ሁሉን ይችላል፤ ሁሉን ይሸከማል፤ አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ ይሆናል። እያንዳንዷ እንቅስቃሴው በእርጋታ የተሞላች ትሆናለች። በሌሎች ዘንድ የታፈረና የተከበረ በመሆኑም፣ የተጣላ ያስታርቃል፤ ያጠፋን ይመክራል፤ ከህይዎት ልምዱ በመነሳት ማህበረሰቡን ያስተምራል ተብሎ ይታመናል።

እነዚህ አራቱ ባህሪያት በሰዉ ልጅ ዕድሜ ዉስጥ ተፈራርቀዉ ሲያልቁ ወይም በሌላ አገላለጽ አንድ ሰው እድሜው ከሰማንያ ዓመት በላይ ሲሆነዉ፣ በመጀመሪያዎቹ ዘመን የነበሩት የነፋስ ባህርያት ተመልሰው እንደሚገዙ

ይገልጻለ።።[25] በመሆኑም የሰው ልጅ በዚህ የእድሜ ዘመኑ ቀድሞ በነፋስ ዘመን እንደነበረዉ የልጅ ባህርይ ማሳየት ይጀምራል።። ህፃን ይመስል በትንሽ በትልቁ ማኩረፍ ያበሳል፤ አሁን የተናገረውን አሁን ይረሳዋል፤ ባጠቃላይ ተለዋዋጭ ባህርይ ይኖረዋል ።። ለዚህም ነው "ዕድሜዉ የገፋ ሰዉና ህጻን ልጅ አንድ ናቸዉ" እየተባለ ሲነገር የምንሰማዉ።።[26]

እስካሁን የተመለከትናቸዉ አራቱ ባህሪያት በአስራ ሁለት ክዋክብት ውስጥ በቁጥር ተዘርዝረው እና በባህሪ ተለይተው ይገኛሉ።።

ሰንጠረዥ 1. አስራሁለቱ ከዋክብትና የባህርያቸዉ ምሳሌ [27]

ተ.ቁ	የኮከቡ ስም	የኮከቡ ባህርይ [28]
1	ሐመል እሳት	(ድብ)፣ በባህርይው ውስድ ምልስ የሚያደርገው አይነት ሰው ነው።።
2	ሰውር መሬት	(ዝንጀሮ)፣ ድብቅ ነው፤ የሚሰራው አይታወቅበትም።።
3	ገውዝ ነፋስ	(አጋዘን)፣ ብዙ ነገር መቋቋም የሚችል ጠንካራ ነው።። ለምሳሌ ወታደር ቢሆን ይሳካለታል።።
4	ሸርጣን ውሃ	(ቀበሮና ዋላ)፣ ነገረ ሰይጣን ነው፤ የሚናገረውን ሁሉ ሰው አይቀበለውም።።
5	አሰድ እሳት	(አንበሳ)፣ ቀማኛ ነው፤ ሙግት የሚችለው የለም።።
6	ሰንቡላ መሬት	(ጉጉት አሞራ)፣ ገንዘብ ይገባለታል፤ የሰው ገንዘብ ክፍሉ ነው፤ ከነተረቱ እንኳ "ስንቡላ የሰው ይበላ" ይባላል።።
7	ሚዛን ነፋስ	(ተኩላ)፣ የጨበጠው ሁሉ ይሳካለታል።። ለምሳሌ፣ ደብተራ ከሆነ የቆረጠው ሁሉ ይነግስለታል (የቆረጠው እፅ ሁሉ መድሃኒት ነው።።)
8	ዓቅራብ ውሃ	(ነብር)፣ የዘመድ መመኪያና ኩራት ይሆናል።። በተለይ ወደ ኋላ ጊዜ ዘመዶቹን የሚጠቅም ሀብታም ይሆናል።።
9	ቀውስ እሳት	(ጅብ)፣ ብስጭታም (ቁጭታም) ነው
10	ጀዲ መሬት	(ንስር)፣ የሚይዘው ሁሉ ይሳካለታል።። ለምሳሌ፡- አትክልትና እርሻ ይሆንለታል፤ የተማረ ከሆነ ጽህፈት ክፍሉ ነው።።
11	ደለዊ ነፋስ	(በሬ)፣ ሁሉ የተደላደለለት ነው፤ ሀብታም ነው።።
12	ሁትውሃ	(ከይሲ)፣ ጠብ ጫሪ (ነገር ኮትኳች) ነው፤ "ሁት፣ ነገር ይኮትኩት ነው።።"

[25]ዝኒከማሁ

[26] ዝኒ ከማሁ

[27] መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኝ ፣ደብተራ አዕምሮ መንገሻ(ቃል-መጠይቅ)

[28] በእያንዳንዱ ኮከብ ስር የተዘረዘሩት ባህርያት እንደ ምሳሌ የቀረቡ እንጂ እነዚህ ብቻ አለመሆናቸዉን ይገነዘቧል።።

የአንድን ሰው ኮከብ በመቁጠር የሚገኘዉን ቁጥር ይዞ የኮከቡ መገለጫ ከሆኑ ባህርያት ጋር በማመሳከር በማመሳከር ስለዚያሰዉ ባህርይና ከህይዎቱ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ጉዮች ማወቅ ወይም "ያ ሰዉ እንደዚህ ነዉ.. ወደፊት እንደዚህ አይነት ነገር ያጋጥመዋል " ወዘተ... ብሎ መናገር/ መተንበይ ይቻላል ተብሎ ይታመናል።[29] ቆጠራው የሚሰራው የባለቤቱን (ኮከብ የሚቆጠርለትን ሰው) እና የእናቱን ስም በመፃፍና በመጽሀፉ መዝገብ[30] የፊደላት አቆጣጠር አዋጅና ህግ መሠረት[31] ቁጥር ከሠጡ በኋላ በመደዳ በአስራ ሁለት እየገደፉ[32] የሚገኘውን ቀሪ ይዞ በመደመር እያሰሉ በመሄድ ነው።[33] ይህም ከማህበረሰብ ዕዉቀት አዋቃሪያን እና ከ ሐይማኖት ቲዎሪ አንጻር የሚታይ ነዉ።

ሰንጠረዥ 2. የፊደላት አቆጣጠር አዋጅና ህግ[34]

ፊደል	ቁጥር	በ 7 ሲገደፍ	በ 9 ሲገደፍ	በ12 ሲገደፍ
ሀ	1	-	-	-
ለ	2	-	-	-
ሐ	3	-	-	-
መ	4	-	-	-
ሠ	5	-	-	-
ረ	6	-	-	-
ሰ	7	-	-	-

[29] መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኝ ፣ደብተራ አእምሮ መንገሻ(ቃል መጠይቅ)

[30] ስለ ፊደላት አቆጣጠር የሚገልጽ ሀይማኖታዊ መጽሀፍ

[31] በሰንጠረዥ 2 ዉስጥ ይመለከቷል።

[32]በአስራ ሁለት መግደፍ ማለት ከቁጥሩን ላይ አስራ ሁለት በመቀነስ ቀሪውን መያዝ ማለት ነው።

[33] አዕምሮ መንገሻ (ደብተራ)፣ቃለ -መጠይቅ፣ደብረማርቆስ፣መጋቢት ፣ 2008 ዓ.ም

[34] *አዉደ ነገስት ፍካሬ ክዋክብት ሰነ ምርምር፣* (1953)፣ በጥንታዊያን ኢትዮጵያ ሊቃዉንትና ጠበብቶች የተዘጋጀ (በ1983ዓ.ም ተሻሽሎ በድጋሚ የታተመ።)

ቀ	8	1	-	-
በ	9	2	-	-
ተ	10	3	1	-
ጎ	20	6	2	8
ነ	30	2	3	6
አ	40	5	4	4
ከ	50	1	5	2
ወ	80	4	6	-
ዐ	70	-	7	10
ዘ	80	3	8	8
የ	90	6	-	6
ደ	100	2	1	4
ገ	200	4	2	8
ጠ	300	6	3	-
ጰ	400	1	4	4
ጸ	500	3	5	8
ፀ	600	5	6	-
ፈ	700	-	7	4
ፐ	800	2	8	8

ለምሳሌ፣ በዚህ ያላች ጋብቻ ተውኔት ውስጥ በደብተራ ልዝቡ ኮከቧ የሚቆጠርላት ቢቢታ ጋሻዉበዛ ስትሆን፣ የእናቷ ስም ወርቃፈራሁ ነው። በመሆኑም የቢቢታን ኮከብ ለማወቅ የእሷን እና የእናቷን ስም ጽፈን በሚከተለው መልኩ እንቆጥራለን ማለት ነው።

በመጀመሪያ፣ በሰንጠረዥ 2. በቀረበዉ መሰረት ለፊደላት በመጽሀፍ መዝገብ ዉስጥ ያላቸዉን አቆጣጠር መሰረት በማድረግ በ 12 ሲገደፍ የሚገኘኘውን ቁጥር መስጠት[35]። ይኸውም፡-

ተ.ቁ	ስማቸው	የስሙ ሆሄያት ወደ ቁጥር ተቀይረው							
1	ቢቢታ	ቢ	ቢ	ታ					
		9	9	10					
2	ወርቅአፈራሁ	ወ	ር	ቅ	አ	ፈ	ራ	ሁ	
		0	6	8	4	4	2	1	

ቀጥሎም ከቢቢታ በመጀመር ቀጥሎም የእናቷን ስም እያንዳንዱን የፊደሉን ቁጥር እየደመሩና እየቀነሱ እንደሚከተለዉ በመደዳ ማስላት፡-



[35] የ 12 አገዳደፍ ከ ጎ ጀምሮ እስከ ፐ ሲሆን፣ሌሎች ማለትም ከ ሀ አስከ ተ ያሉት በቆጠራ ወቅት ቁጥራቸው እንዳለ ይወሰዳል(ዝኒ ከማሁ)።

ከ ቢቢታ የተገኘው ቀሪ ቁጥር (4) + የ እናቷ ወርቅአፈራሁን (5) = 9 ፡፡ ይህን ቁጥር ደግሞ በአስራ ሁለቱ በኮኮቦች ዝርዝር ውስጥ ስንመለከተው “ቀውስ እሳት” ነው፡፡ ስለዚህ በእሳትነቷ ቀውስ እሳት ናት ማለት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም በባህርይዋ ቁጡ (ተበሳጭ) ናት ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

ከፍ ብሎ የቀረበውን ዝርዝር የኮከብ አቆጣጠር በተውኔቱ ውስጥ ሲፈፅሙ እንመለከተውም፡፡ ይህ ማለት ግን ደብተራ ልዝቡ የቢቢታን ኮከብ ሲቆጥር በዚህ ሂደት አላለፈም ማለት አይደለም፡፡ ተውኔት ከጊዜና ከቦታ አንፃር የሚገደብ በመሆኑ፣ ፀሀፊው መንግስቱ ለማ ሆን ብለው የደብተራ ልዝቡ የኮከብ ቆጠራ ሂደት ከመጋረጃ በስተጀርባ (በቤቱ) እንዲጠናቀቅ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው የተውኔቱ ክፍል የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡

ልዝቡ፡- ትናንት ማታ እሜትዬን እጅ ነስቼ እንደ ሄድኩ፤ እጮጆዬ ስደርስ ወዲያውኑ ኩራዜን አብርቼ ስራ ጀመርኩ፡፡ ሞላ ሌሊቱን ቁጭ በዪ ኮከቧን ስቆጥር ነው ያደርኩት፡፡ እንቅልፍ የሚሉት እንኳ በአይኔ ዝር አላለም፡፡

(ከኪሱ ትንሽ ደብተር ያወጣና ይገልጣል) ሁሉንም ጽፌዋለሁ፡፡

እሜቴ፡- እሺ፤ እኮ በል፡፡ ዎ ክርስቶስ -

ልዝቡ፡- እመቤቴ እንዳዘዙት በሐሳብ ሀብቷ ጀመርኩና፣ ሐሳብ ጋብቻዋን፣ ሐሳብ ጽንሷን፣ ሐሳብ ወሊዷን፣ ሐሳበ እህል ውሃውን፣ ሐሳበ ክርክር ሙግቷ ሳይቀር ልቅም አድርጌ ቆጥሬላታለሁ፡፡ ሐሳበ ፍቅሩ ትርፍ ነው አያስፈልግም ስላሉኝ፣ ዘልየዋለሁ፡፡

እሜቴ፡- እህ፣ ታዲያስ?

ልዝቡ፡- የልጅቷ ስም ቢቢታ፤ያባቷ ስም ጋሻው በዛ፤ የእናቷ ስም ወርቃፈራሁ፡፡ ያያቷ ስም ግድየለም፤ አያስፈልግም፡፡

እሜቴ፡- ዋናው የአያቷ ስም! አውራሪስ ጐሹን ያህል ስም እኮ ነው አያስፈልግልም የሚለው! ያሁሉ አላድ፣ ያሁሉ ሜትር ካሬ ከየት

መሰለህ የተገኘው? ካውራሪስ ጐሹ ነው። በጄ፤ ዎ ክርስቶስ- ዎ ክርስቶስ-

ልዝቡ፡- የለም እሜትዬ፤ የነገሬን አርፍተነገር እለተከተሉልኝም። ያያት ስም አያስፈልግም ማለቴ ለሐሳብ ጋብቻ ለማለት ነው እንጅ ለሌላ አይደለም ።

(ገቢ.1፤ ትዕ.2)

ከላይ በቀረበው የደብተራ ልዝቡ ንግግር ውስጥ ሐሳብ ጋብቻዋን ሲል፣ ጋብቻዋ ይሰምራል ወይስ አይሰምርም የሚለውን ማለቱ ሲሆን፣ ሐሳበ ጽንሷ የሚለው ደግሞ ፅንሱ ወንድ ነው ወይስ ሴት ማለቱ ነው።

ሐሳበ መውለዷ ሲል ትውልዳለች ወይስ አትወልድም (መካንናት ወይስ አይደለችም) ለማለት ሲሆን፣ ሐሳብ እህል ውሃዋ ሲል ካገባችው ሰው ጋር ሊያኖራት ወይም ሊያለያያት የሚችለውን ሰበበ ምክንያት ማለቱ ነው። እንዲሁም ሐሳበ ፍቅሯ ሲል፣ ከምታገባው ሰው ጋር ተግባብታና ተስማምታ ትኖራለች ወይ... የሚለውን ለማት ሲሆን፣ ሐሳበ እድሜዋን ማንሳቱ፣ ምን ያህል ዕድሜ ይኖራታል የሚለውን ለማወቅ በመፈለጉ ነው። ይሁንና የደብተራ ልዝቡ ኮከብ ቆጠራ በማጭበርበር የተሞላ ነው። ለዚህ ትልቁ ማሳያ በለጤን ከባህሩ ቤት ለማባረር የሚቆጥረው ነው፡-

ልዝቡ፡- መጽሐፉ የሚለው የታወቀ ነው። (ከጐን ኪሱ መጽሐፍ ያወጣል) ሁሉም ተጽፏል። ሐሳብ እህል ውሃውን ለንብብልህ "የወንድ ኮከብ እሳት ሆኖ ሴት ውሃ ብትሆን፣ አጥፊው ናት። የእሳትና ውሃ ተጋብቶ ባልና ሚስት መሆነ አደጋን ያመጣል፤ እሳቱ አመድ ውሃው ላቦት ይሆናልና። ነፋስ መዓት ይበታትናቸዋል፤ ይለያያቸዋል። ነፋሱም የመልዓክ ሞት ምሳሌ ነው። እድሜአቸው አጭር ይሆናል፤ ገና በለጋቸው ይቀጫሉ፤ በጮርቃቸው አንጓቸው ይሰበራል፤ አንዳቸው ላንዳቸው ገፊ ናቸው። ካልተለያዩ፣ እምቢ ብለው አብረው ከኖሩ፣ ከሁለቱ አንዱ ይሞታል፤ ውሃው እሳቱን ያጠፋዋል" መጸሐፉ የሚለው ያውልህ።

ባህሩ፡- ለጊዜው ተለያይተው፣ በኋላ ቆይቶ፣ የኮከቦቹ መአት ካለፈ በኋላ እንደገና ሊታረቁ ይችላሉ አይችሉም?

ልዝቡ፡- አይሆንም፡፡ አንዴ ከተለያዩ በኋላ እንደገና ቢታረቁ፣ ጥንቱኑ ቀድሞ ቤቱን ለቆ የወጣው ደፍሮ በመመለሱ ይሞታል፤ ቁርጥ ነው፡፡ ይልቅስ መጽሐፉ የሚለውን ስማ፤ አላለቀም፡፡“እሳትና ውሃ ኮከብ የሆኑ ወንድና ሴት እሳትና ውሃነታቸውን ሳያውቁ፣ በቁርባን በሰማኒያ ወይም በሌላ ዘዴ ቢጋቡና አብረው ቢቆዩ፣ አጥፊና ጠፊ መሆናቸውን ግን ከተጋቡ በኋላ ቢያውቁት፣ ጥቁር በግ መድረክ ላይ አርደው ደሙን ረግጠው ከቤታቸው ይውጡና ይለያዩ” (የመጽሐፉን ቅጥል ይገለብጣል) በጀ፡፡“ሴቲቱ በቅጥር ወይም በግርድና የገባች ብትሆን፣ ደሙን ተራምዳ መድረኩን ዘላ ከዚያ ቤት እንደወጣች ሰባት ወንዝ ተሻግራ አገር ጥላ ትጥፋ፡፡ ዘወር ገልመጥ ብላ ብታይ፣ እንደሎጥ ሚስት የጨው ሃውልት ትሆናለች፡፡ ሃውልት እንዳትሆን ቀይ ዶሮ አርዳ፣ አልጫ ሠርታ፣ መቋደሻውን ትብላና፣ የተረፈውን ከነጭ ጤፍ እንጀራና የዶሮውን አይን ከመሰለ የገብስ ጠላ ጋር ለመጽሐፍ ገላጭ ወይንም ለኮከብ ቆጠራ ደብተራ ካህን እግዚአብሔር ትመግብ፡፡” ይላል፡፡

(ገቢ. 2፣ ትዕ. 2)

ደብተራ ልዝቡ ትክክል ይሆን የነበረው በለጤ ከባህሩ ቤት እንደወጣች ቀርታ ቢሆን ነው፡፡ ነገር ግን በተውኔቱ ታሪክ የመጨረሻ ክፍል እንደተገለፀው በለጤ ምንም እንኳ መጀመሪያ ላይ የደብተራ ልዝቡን ማስፈራሪያ ሥምታ የባህሩን ቤት ጥላ ብትጠፋም የኋላ ኋላ ግን ተመልሳ አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው የደብተራ ልዝቡን አጭበርባሪነት ነው፡፡

4.1.1.2 ጠጠር መጣልን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ይህን አስመልክቶ መረጃ የሰጡኝ አባ አእምሮ መንገሻ (ደብተራ) እንደሚሉት ብዙ ጊዜ ሰዎች ወደ አዋቂ (ጠንቋይ ወይም ደብተራ) ዘንድ ሂደዉ ጠጠር የሚያስጥሉት

በሁለት ምክንያቶች ሲሆን፣ እነሱም **“ሐራ ዘመን”** እና **“ሐሳበ ህመም”** በመባል ይታወቃሉ።።[36]

“ሐራ ዘመን” ማለት አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ የሚገጥሙትን ክፉም ሆነ ደግ አጋጣሚዎቹን (ዕድሎቹን) ለምሳሌ፣ በዚህ ጊዜ ይህን ታገኛለህ (ገንዘብ፣ ሹመት፣ ልጅ፣ ወዘተ... ሊሆን ይችላል)፣ እንደዚህ ትሆናለህ፤ በዚህ ወቅት እንዲህ ያለ ነገር ይገጥምሃል፤ ይህ ያሠጋህል ወዘተ... የመሳሰሉትን ለማወቅ ሲያስፈልግ ወደ አዋቂ ዘንድ በመሄድ ጠጠር እየተጣለ የዚያ ሰዉ እጣፈንታ የሚታወቅበት ነው።።

በሌላ በኩል ለ **“ሐሐሳበ ህመም ”** የሚጣልበት/የሚታይበት ዋና አላማ አንድን በጠና የታመመ ሰው ወይም የአልጋ ቁራኛ የሆነ በሽተኛ ይድናል ወይም አይድንም የሚለውን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ለማወቅ ነው።። አንድ በጠና የታመመ በሽተኛ ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ አስታመው ሲሰለቹና ከህመሙ ማገገም ሲሳነው፣ መጨረሻውን ለማወቅ ወደ አዋቂ ዘንድ ሄደው ጠጠር እንዲጣልላት ያደርጋሉ።። የሚገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግም ቀጣይ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።። ጠጠር ጣዩ ይድናል ካለ ማስታመማቸውን ይቀጥላሉ።። ያድነዋል ያሉትን ማንኛውም ነገር ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አይሉም።። ነገር ግን አይተርፍም ይሞታል ከተባሉ ለማይድን በሽተኛ ከመልፋት ይልቅ ሲሞት ስለሚደረገው ነገር ማሰብና መዘጋጀት ይጀምራሉ።።

ከላይ ከቀረቡት ሁለት የጠጠር መጣል አይነቶች (**“ህራ ዘመን”** እና **“ሐሳበ ህመም”**) መካከል ያላቸ ጋብቻ ውስጥ የቀረበዉ **“ህራ ዘመን”**ን ይመለከታል።።

በተውኔቱ ውስጥ (ገፀ. 2፣ ትዕ.1) አባ ማሚቶ ጠጠር እየጣለ/እያየ ወይዘሪት ቢቢታ ጋሻዉ በዛ “ሹመት አላት፤ ንዘብ አላት፤ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤” እያለ ሲናገር ይስተዋላል።።ለቢቢታ ጠጠር እንዲጣልላት ያስደረጉት ወይዘሮ አልጋነሽ ዱብዳም አባ ማሚቶ የሚናገረዉ ሁሉ እውነት ነው ብለው ስላመኑ “እልልል!” እያሉ እንደሚከተለዉ ይቀበላሉ።።

[36] አባ አእምሮ መንገሻ (ደብተራ) ፣ (ቃለ-መጠይቅ)፣ደብረ ማርቆስ፣መጋቢት 13፣ 2008 ዓ.ም።።

አባ ማሚቶ፡- (ጠጠሮቹን አተኩሮ ይመለከታል) ባመቱ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ዱብ ነው፡፡

እሜቴ፡- እንዲህ ነዋ በጀ

አባ ማሚቶ፡- ባመቱ ትደግማለች፡፡

እሜቴ፡- እሰይ፡፡ ደሞሳ?

አባ ማሚቶ፡- ባመቱ መንታ ትደግማለች፡፡

እሜቴ፡- እልልልል! እኔም ብያለሁ፤ የወላድ ዘር ነች፡፡

አባማሚቶ፡- ገንዘብ አለ፤ ገንዘብ አለ፡፡

እሜቴ፡- ሳይታለም የተፈታውን! የጌታ ዘር ነች፤ ዘረ ጌታ፡፡

አባ ማሚቶ፡- ሹመት አለ፡፡

እሜቴ፡- እሺ እስቲ እንዲህ እንዲህ አምጣው!

አባማሚቶ፡- ሹመት አለ፡፡

(ገቢ.2፣ ትዕ.1)

የተወኔቱ ፀሀፊ ፣መንግስቱ ለማ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ እምነቱን ብቻ ሳይሆን ክዋኔውንም ይገለፀልናል፡፡ ስለ አባማሚቶ አለባበስ፣ የሚገለገልባቸው ቁሶች፣ ጠጠሮቹን ስለሚመድብበት ሁኔታ፣ ስለሚያሳዬው የሰውነተ እንቅስቃሴ ወዘተ. በግልጽ ያሳዩናል፡-

(ከእሜቴ ግርጌ እመሬቱ ላይ በስተግራ አነድ አጠር ያለ ደልዳላ ሰው በጉልበቱ ተምበርክኮ በክንዱ መሬቱን ተደግፎ እፊቱ የተዘረገፉትን ጠጠሮች ይቆጥራል፡፡ ሽምልምል ሽመሉ ባጠገቡ ተጋድሟል፡፡ ... አባማሚቶ ጫት በመቃም ላይ ስለሆነ፣ ግራ ጉንጩ እንደ ዝንጀሮ ጉንጭ ተወጥሮ አፍጥጧል፡፡ ይህ ግን ከመናገር አያግደውም፡፡ ... አባ ማሚቶ የወርቅ ሎቲውን አንጠልጥሎ በርጋታ ጠጠሮቹን አፍሶ እንደገና ይበትንና በሦስት በሦስት እየከፈለ ይመድባቸዋል፡፡ አንድ ጠጠር ትተርፋለች፤ አንስቶ አተኩሮ ያስተውላትና ለብቻዋ ያስቀምጣታል፡፡ በትካዜ ራሱን ይወዘውዛል፡፡)

(ገቢ.2፣ ትዕ.1)

ወይዘሮ አልጋነሽ ዱብዳ ጠጠር ያስጣለብት ዋና ዓላማ ለወንድማቸው ልጅ ባህሩ አዳሽነህ ጋብቻ ያጨዋት ቢቢታ ጋሻው በዛ ዕጣ ክፍሏ ምንድነው የሚለውን ለማወቅ ነው። ይህንንም የሚያደርጉት ያገር ልማድ ስለሆነና እሳቸውም ስለሚያምኑበት ነው። ... "ምን ይደረግ? ያገርልማድ ነው፤ አዋቂ ሳይጠየቅ ሠርግ አይደገስ፣ ልጅ አይዳር! ዎ አምላክ፤" እንዳሉት እሳቸዉም (ገቢ.2፣ ትዕ.1)።

ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ጠቅለል አድርገን ፋዳቸውን ስንመለከተዉ፣ **"ኮክብ ቆጠራ"** እና፣**"ጠጠር መጣል"** የእነዚህ ሐገረሰባዊ አምነቶች ተከታይ ለሆኑ ሰዎች ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችን እና ተግዳሮቶችን አስቀድሞ ከማሳወቅ አንጻር ፋይዳ አላቸዉ ብሎ መውሰድ ይቻላል።

4.1.1.3 የሐይማኖት መቻቻል[37] ባህልን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

መንግስቱ ለማ በዚህ ተውኔት ውስጥ በሀገራችን ሲወርድና ሲወራረድ የኖረውን በክርስትና እምነት እና በእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል ያለውን መቻቻልና ተከባብሮ የመኖር የቆየ ባህል ለማሳየት ሁለት ደጋግ ሽማግሌዎችን ሀጂና አለቃን አስተዋውቀውናል።

ሀጂና አለቃ ምንም እንኳ የተለያየ እምነት ተከታዮች ቢሆኑም፣ እንደታናሽና ታላቅ ወንድም የሚተያዩ፣ እርስ በእርስ የሚዋደዱና የሚከባበሩ የፍቅርና የመቻቻል ተምሳሌት የሆኑ ጓደኛማቾች ናቸው። ስለዚህም ሁለቱም በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ቦታ አላቸው። የተጣላን ያስታርቃሉ፣ ያጠፉን ይገስፃሉ። እርስ በእርስ ያላቸው

---

[37] በተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ያሉ የመቻቻል ግንኙነቶች የፎክሎር ትኩረቶች ሆነው ይገኛሉ። የመቻቻል ተግባራዊነት ከእምነት ሥርዓቶች ጋር ቁርኝት ያለው የፎክሎር አንዱ ገጽታ ነው (Mathisen, 1993, in Fekade 2003; Linda Degh 1972: 56)። ተቻችሎ፣ ተከባብሮና አብሮ ተሳስቦ መኖር በአጠቃላይም መቻቻል በታሪክ ሂደት ሰዎች በጋራ የሚፈጥሯቸው ዋነኛ የፎክሎር የትኩረት ነጥቦች መሆናቸውን ነው። ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ማህበራዊ ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን ይልቁንም በፎክሎር አማካይነት በአጥጋቢ ደረጃ የሚጠና መስክ ነው።

መካባበርና መተሳሰብ ሌሎችም በዚህ አይን እንዲያዩዋቸው አስችሏቸዋል። ለምሳሌ ባህሩ በለጤን ሲያገባት ቤቱ እንዲገኙለት የጋበዛቸው እንግዶች ሁለቱ ብቻ ነበሩ። ሌላ ተጨማሪ ሰው መጥራት አላስፈለገውም። እንዲሁም አንዳቸውን ከአንዳቸው አላበላለጣቸውም። ወይዘሮ አልጋነሽ ዱብዳም ቢሆኑ ለእነዚህ የሐይማኖት አባቶች ያላቸው ስሜት ተመሳሳይ ነው። ወደ ቅላዳቸው (እርስታቸው) በሚመጡበት ጊዜ ሳያገኟቸው አይመለሱም።

ፀሐፌ-ተውኔት መንግስቱ ለማ በቀላል ቋንቋና ዘና በሚያደርጉ ምልልሶች (humorous dialogues) በእነዚህ ሁለት ሰዎች ገፀባህሪያት በሀገራችን በርካታ ተከታይ (አማኝ) ባላቸው ሁለቱ ታላላቅ ሐይማኖቶች (በእስልምና እና ክርስትና) መካከል ያለውን/የነበረውን ተቻችሎ እና ተከባብሮ የመኖር ብሂል ለማሳየት ሞክረዋል። ለአብነት ከዚህ በታች የቀረበዉን ቃለ-ተውኔት እንመልከት።

ባህሩ፡ - ይቀመጡ ሐጂ፤ አለቃ -አረፍ አትሉም?

ሐጂ፡- እንሂዳለን፤ አፈርሳታ አለብን። (ይቀመጣሉ)

አለቃ፡- አንቆይም፤ (ይቀመጣሉ) የመንደር ሽማግሌነትስ አንድ ሥራ አይደለም ልጅ ባህሩ

ባህሩ፡ - (በእምብርክኩ ይነሳል) የአባ ማሚቶ ፍየል ያቺ ባለ ቃጭል-ጠፍታለች አሉ። የሰረቃት ታውቋል?

አለቃ፡- አፈርሳታው ለዚያው አይደል?

ሐጂ፡- አባ ማሚቶ ወፍ ነገረችኝ፤ ልዝቡ ነው ይለናል። እኛ ግን ሐሜቱን ቢሙሉ አልተቀበልነውም።

አለቃ፡- ይልቅስ ልጅ ባህሩ እንኳን ደስ ያለህ ቸሩን ወሬ ከእሜቴ ስምተነዋል። ሚስት የማጨትህን ጭምጭምታ። እንግዲህ ተፍተፍ ነው! ሙሽርነት ቀላል ነገር አይደለም።

ሐጂ፡- (በቀልድ) ያንዱን ድግስ በልተናል፤ የሁለተኛዋን ደሞ እንበላለን-ምናለ-ረጅም እድሜ ለልጅ ባህሩ እያልን! (ይስቃሉ)

አለቃ፡- (በቀልድ) ሐጂ ትሳሳታለህ፡፡ ልጅ ባህሩ ክርስቲያን መሆኑን ዘነጋኸው ልበል?

ባህሩ፡- (በችኮላ) እምዬ (ወ/ሮ አልጋነሽን) አንዴ ይቅርታሽን ተማሪዎቼ ይጠብቁኛል፡፡ የሚታረም ደብተራቸውን ይዘው መጥተዋል፤ አንዳፍታ ልሂድና ልቀበላቸው፡፡ አሁን መጣሁ አልቆይም፡፡ እስከዚያ እነ ሐጂ ያጫውቱሻል፡፡

እሜቴ፡- እንዳትቆይ፤ መነሻዬ ደርሷል፡፡

ባህሩ፡- አምስት ደቂቃ አይወስድብኝም፡፡ (ወደ በሩ ያመራል)

ሐጂ (እጁን በሰላምታ ይጨብጡና አልለቅህም ይሉታል) አለቃን አትስማው፣ ያጣ ወሬ ነው፡፡ አንድ ሚስት ማግባት መልካም፡፡ ሁለት ይበልጣል፡፡ ሦስት ሚስት ሰባት እጅ ያመጣል፡፡ አራት ሚስት ማግባት የደስታ ድምበር ነው! (ይስቃሉ)፡፡

(ገቢ.2፣ ትዕ.1)

ከላይ በቀረበው ቃለ ተውኔት ማየት እንደሚቻለዉ፣ ሀጂ እና አለቃ የሚያደርጓቸው የቃላት ምልልሶች፣ አንዱ ስለሌላው ሀይማኖት እያነሳ የሚናጋራቸው ከደግነት የመነጩ ቀልድ አዘል ጨዋታዎች... እነዚህ ሁሉ በተለይ በሀገራችን በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አካባቢዎች “በውሃ ቀጠነ” ምክንያት ከሚነሱ ሐይማኖታዊ ግጭቶች አንፃር ሲታዩ፣ በቀደሙት ጊዚያት በእያንዳንዱ ማህበራዊ እንቅስቃሴያቸዉ ዉስጥ የሐይማኖት መቻቻል/መከባበር የቱን ያህል ትልቅ ስፍራ እንደነበረዉ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ከየትም ሳይሆን ማህበረሰቡ ለሚኖርበት ባህላዊና ማህበራዊ ስርአት ተገቢዉን ትኩረት ከመስጠት የሚመጣ ነው፡፡ ደራሲው/ፀሐፊው ለማሳየት የፈለገዉም ይህንኑ ይመስላል፡፡

ከተግባር አንጻር ፣ በተለያዩ ሐይማኖት ተከታዮች መካከል የመቻቻልና የመከባበር ባህል መኖር ዘላቂ ሰላምን ከማስገኘትና ማህበራዊ ትስስርን በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና አለዉ፡፡

4.2. ሾተላይ[38]

የተዉኔቱ ታሪክ እንደሚያሳየዉ በርካታ ልጆቿን ቀብራ ሁለት ከሞት የተረፉ ልጆቿን ያለ አባት የምታሳድግ "ሾተላይ" እናት አለች፡፡ ወንድሟ የእህቱንና የእናቱን ፈቃድ ሳይጠይቅ እህቱን አስገድዶ ቀደም ሲል "ወሮታ" ለዋለለት ጓደኛው ያስጠልፋታል፡፡ ከዚያም እናቱን "ልጅሽ ወንድ ተክትላ ጠፋች፡፡" ብሎ ዋሸቶ ያሳምናታል፡፡ ልጅቷ ከጠለፋት የወንድሟ ጓደኛ ጠፍታ ወደ እናቷ ስትመለስ፣ ጠላፊዋ ከእሷ ቀድሞ ደርሶ "ሚስቴን ከእናቷ ከሚደርሳት ሀብት ጋር ስጡኝ" ብሎ ካስጠለፋት ወንድሟ ጋራ ጦርነት ገጥሞ ከባድ እልቂት ሆኖ እናት በሬሳ ተከባ ትደርሳለች፡፡ ከዚያም እናት የልጅቷን፣ የአስጠላፊ ወንድሟንና የጠላፊዋን ክርክር ካደመጠች በኋላ ውሳኔ ትሰጣለች፡፡ "ከአሁን በኋላ እያንዳንዱ ልጅ በወደፊት አዲስ ህይወቱ ላይ ግልፅ የሆነ የራሱ ውሳኔ መውሰድ አለበት፡፡ ዛሬ ያለንባት ህይወት ወሳኝ ናት፡፡ ወደኋላ ተጐትታ ከትላንቷ ጋር አትደባለቅም፡፡ ወደፊት ገስግሳ ነገን መረበሽ የለባትም፡፡ እኔም ቀሪ ዘመኔን በረጋ ህይወት ውስጥ ማሳለፍ እፈልጋለሁ፡፡ በልጅ ትርምስ ውስጥ ህይወቴን ማጣት... ክብሬን... ታሪኬን... ስሜቴን ማስደፈር አልፈልግም፡፡..." ትላለች-ሾተላይዋ እናት፡፡[39]

[38]የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት (1993፡ 39) ሾተላይ የሚለውን ቃል የወንድና የሴት የደም አይነት ቅንጅት ተስማሚ ባለመሆኑ ሽሉ እንደተፀነሰ ወይም ህፃኑ እንደተወለደ እንደሚሞት የሚታመንበት... ይለዋል፡፡

[39]የተውኔቱ ፀሀፊ፣ አያልነህ ሙላቱ ራሱ በተወኔቱ መግቢያ እንደጠቀሰው፣ ይህን ተውኔት ለመድረክ ጽፎ ለማዘጋጀት የቅርብ ሰበበ ምክንያት (Immidiate cause) የሆነው በ1990 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ተከስቶ የነበረው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ነው፡፡ በመሆኑም፣ አያልነህ በተውኔቱ ውስጥ በአንዳንድ ቦታዎች ሆን ብሎ ተምሳሌታዊ (symbolic) የአፃፃፍ ስልት መከተሉንና የተውኔቱን ታሪክም ከዚህ አንፃር ጭምር መረዳት እንደሚገባ ይገነዘባል፡፡

4.2.1. ሾተላይ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

4.2.1.1 ሾተላይን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በተደጋጋሚ እየጸነሰች የሚያስወርዳት ወይም ህጻኑ እንደተወለደ የሚሞትባት ሴት በዘልማድ "ሾተላይ"ተብላ ትጠራለች ይላሉ።[40] "ሾተላይ እስማንዲዎስ በተባለ የጭን ጋኔ ምክንያት የሚፈጠር ነዉ። ይህ ጋኔን በሴቷ ማህጸን አድሮ እንደወንድ እየሆነ ይገናኛታል፤ ስለዚህ ከወንድ ጋር በምትገናኝበት ጊዜ ይቀናል። በዚህ የተነሳም ህፃኑን ገና እንደተፀነሰ ወይም ከተወለደ በኋላ ይገድለዋል። የህጻኑ አባት የሚሞትበት አጋጣሚም እንደዚሁ ሊፈጠር ይችላል።"[41]

ከዚሁ ጋራ ተመሳሳይነት ያለው ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ እንደሚከተለዉ ተጽፎ እናገኛለን፡፡

> ***ያምልጅ መለአኩን አለው፤ "አንተ ወንድሜ አዛርያ! ያቺን ልጅ ሰባት ወንዶች እንዳገቧት እኔ ሰምቻለሁ፤ ሁሉም በሠርጉ ጊዜ ሞቱ። አሁንም እኔ ለአባቴ ብቸኛ ነኝ፤ ወደ እርሷም በገባሁ ጊዜ እንዳልሞት፤ የአባቴን የእናቴንም ህይወት በእኔ ምክንያት በጭንቅ ወደ መቃብር እንዳላወርድ እፈራለሁ፤ የሚቀርባቸውም ሌላ ልጅ የላቸውም። ያም መላክ አለው፤ ከዘመዶችህ ሚሰት ታገባ ዘንድ አባትህ ያዘዘህን ቃል አታስብምን? አሁንም አንተ ወንድሜ ስማኝ፤ የጋኔኑ ነገርስ አያሳዝንህ፤ በዚች ሌሊት ከዘመዶችህ ወገን እርሷ ሚሰት ሆና ትሰጥህለችና፤ ወደ ጫጉላ ቤትም በገባህ ጊዜ የእጣን እራሪ ውሰድ፤ ከዚያም ዓሳ ከጉበቱና ከልቡ ጨምረህ አጢሰበት። ጋኔኑም በሸተተው ጊዜ ይሸሻል፤ ለዘለዓለሙም አይመለስም (ጦቢ. 6፤13-17፤ 8 ፤1-3) ።***

ከላይ በቀረበው ታሪክ ልጁ ሰባት ጊዜ አግብታ ሰባቱም ባሎቿ የሞቱባትን ሴት ለማግባት ቢፈልግም እሞታለሁ ብሎ እንደፈራ፣ መልአኩም ጋኔኑን የሚያሸሽበትን መድሃኒት እንደነገረው ተገልጿል። ከዚህ ገለጻም በሴቷ ማህፀን ያደረና

---

[40] መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኘ (ቃል -መጠይቅ)

[41]ቀሲስ ዘላለም አዱኛ (ቃል -መጠይቅ)፣ ሚያዚያ፣ 2008 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

የተገናኙዋትን ወንዶች ሁሉ የገደላቸዉ የሆነ ጋኔን ያለ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህም ከሐይማኖት ቲዎሪ አኳያ ሲታይ " ሾተላይ ሴቶችን እንደ ወንድ እየሆነ በሚገናኛቸዉ የሴን ጋኔን የተነሳ የሚከሰት ነዉ" የሚለዉን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ ከዚሁ በተመሳሳይ መልአኩ ለልጁ **"ጋኔኑ ሴቷን እንዲሸሻት የእጣን ዕራሪ ከዓሳ ጉበትና ልብ ጋራ አጢስባት"** እንዳለው ሁሉ በሀገራችንም በተለይ በገጠሩ አካባቢ አንዲት ሴት ሾተላይ መሆኗ ከታወቀ ከእፅዋት የተቀመመ ባህላዊ መድሃኒት በማር ወይም በሰመሬታ በሶ ተለዉሶ እነደሚሰጣትና በጊዜ ሂደትም ሾተላይነቷ እንደሚቀር ይታመናል[42]፡፡ ከማህበረሰብ ዕዉቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ አንጻር ባህላዊ መድሀኒቱ ማህበረሰቡ ተፈጥሮአዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቀምበትን ጥበብ ያሳል፡፡

በተውኔቱ ውስጥ ፀሐፊው፣ አያልነህ ሙላቱ "ሾተላይ"ን ተምሳሌታዊ በሆነ አገላለጽ በተለየ ሁኔታ ከሀገር ጉዳይ ጋራ አያይዞ ያነሳዋል፡፡ ንጽጽራዊ በሚመስል መልኩም፣ ከማህፀኗ ተጣብቆ ልጆቿን እየገደለ በሚያስቸግራት ጋኔን (ሰይጣን) ምክንያት ስቃይ ውስጥ እንደምትገኝ እናት ሁሉ፣ ኢትዮጵያ ሀገራችንም የውጭ ጠላቶቿ በየጊዜዉ በሚሰሩባት ደባ ልጆቿ ፍቅር አጥተዉ እርስ በርስ እየተጫረሱ ተቸግራለች ይለናል፡፡

ደቀቁ... ከዚያም በኋላ... አለቁ....

ተላለቁ፡፡ የወላድ መሽን ሆነች አገር...

ምድር አፈራች ደም መጣጭ መሸገር፡፡

በሬሳ ላይ ቆመች እናት... ወንድ ወልዳ

ወንድ አጥታ ካናት...

ይህን ከምር ከምር የሚመክር፣ በፅናት...

ኧረ አንተ ፈጣሪ አጽናት... ይቺን አገር ተማፀናት...

ይቅር ብለህ አፅናናት፡፡

ወልዳ -አሳድጋ! ለአፈር....

[42] ደብተራ አእምሮ መንግሻ(ቃለ- መጠይቅ)

ልጅ ገባሪ ለቸነፈር... ለእረስ በእርስ ጦርነት ለሰፈር፡፡

ይች! ቀዬ... ይች! ደጅ... ከአሁን ወዲያ የላት ልጅ...

ዘመድ አዝማድ ወዳጅ... የወላጅ ሾተላይ ናት እንጅ፡፡

(ገቢ. 1፣ ትዕ. 3)

በዚህ ቃለ ተዊኔት ዉስጥ የተጠቀሱት " ደቀቁ ... አለቁ... ተላለቁ" ፤" የወላድ መኻን ሆነች አገር..."፤ " ወልዳ -አሳድጋ! ለአፈር....፣ ለእረስ በእርስ ጦርነት ለ ሰፈር "፤እና " የወላጅ ሾተላይ ናት እንጅ..." የሚሉት አገላለጾች ኢትዮጵያ ከሾተላይ እናት ጋር በደራሲዉ የተነጻጸረችባቸዉ ሀሳቦች ናቸዉ፡፡ ከተምሳሌታዊ ቲዎሪ አንጻር ኢትዮጵያ በሾተላይ እናት ተወክላ ቀርባለች፡፡ ከተግባር አንጻር ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ ሾተላይ እናት ልጆቿን በሞት እየተነጠቀች መኖሩ ይብቃት፣ የእርስ በእርስ ጦርነት ይቁም የሚል ይዘት ያለዉ እንደመሆኑ ሰላምን ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ይሰብካል፡፡

4.2.1.2 የሙት መንፈስን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (ገጽ፣ 38) "*መናፍስት ጠሪ*" የሚለውን ቃል "ርኩስ መናፍስትንና የሞቱ ሰዎች መናፍስትን በድግምት የሚጠራና የሚጠይቅ" ይለዋል፡፡ ከዚህ ትርጉም በመነሳት የሙት መንፈስን "የሞቱ ሰዎች መንፈስ/መናፍስት/" ብሎ መጥራት ይቻላል፡፡[43] በተለምዶ የሙት መንፈስ ሰዎች በቁመናቸው ለሠሩት ክፉ ሥራ ነፍሳቸው ወደ ሰማይ በመሄድ ፈንታ በምድር ቀርታ የሚደርስባት ቅጣት ተደርጐ ይወሰዳል፡፡[44]

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እምነት አጥብቆ ይቃወማል፡፡ "ለሰው አንድ ጊዜ ሞት፣ ከዚያም በኋላ ፍርድ እንደሚጠብቀው እንዲሁ ክርስቶስም የብዙዎችን ሐጢአት ያስተሰርይ ዘንድ ራሱን አንድ ጊዜ ሰዋ፤ በኋላ ግን ያድናቸው ዘንድ ተስፋ የሚያደርጉበት ያለ ሀጢአት ይገለጥላቸዋል" ይላል (ዕብ. 9፣ 27)፡፡ ይህም

---

[43]"የሙት መንፈስ" በተዘዋወሪ ለመተርጐም የሞከርኩት የተያዩ መዝገበ ቃላትን ተመልክቼ ቃሉን በቀጥታ ሊተረጉምልኝ የሚችል በማጣቴ ነው፡፡

[44] Ghost- Wikipedia the free encyclopedia. Retrived April 15,2016.

የሚገልፀው አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ነፍሱ በምድር የምትቀር ሳትሆን ወደ ሰማይ ሄዳ ፍርድ የምታገኝ መሆኗን ነው፡፡ ፍርዱም በምድር መልካም ለሠራ መንግስተ ሰማያት (ቆሮ. 5፣ 6-8፤ ፊሊ. 1፣ 23)፤ ክፉ ላደረገ ገሃነመ እሳት (ማቲ. 25፣ 46፤ ሉቃ. 16፣ 22) ነው፡፡

ስለዚህ፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በምድር ላይ የሚቀር ወይም ከሞተ በኋላ ተመልሶ የሚመጣ መንፈስ የለም ማለት ነው፡፡[45] ይሁንና እንደ ፎክሎር፣ ሚቶሎጂና ስነ-ጽሑፍ ባሉ ትምህርቶች የሙት መንፈስ (ጣዕረሞት) የሚባለው በአካል ወይም በሌላ (በድምፅ፣ በጠረን፣ በንክኪ፣ ወይም “sense” በማድረግ)፣ ለአንድ በህይወት ላለሰው ሊከሰት (ሊገለጥ) የሚችል የሞተ ሰው መንፈስ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡[46]

በዚህ ሾተላይ ተዉኔት ውስጥ የተጠቀሰው የሙት መንፈስ በጦርነት የሞቱ የኢትዮጵያ ወታደሮች መንፈስ ሲሆን፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች በአካልና በድምፅ እየተገለጠ በህይወት ያሉ ሠዎችን ሲያነጋግር ይስተዋላል፡፡ ለአብነት ያህል በመንፈሱ እና በአሮጊቷ መካከል የተደረገውን ቃለ-ምልልስ ቀጥሎ እንመልከት፡፡

መንፈስ፡- እናት

አሮጊቷ፡- አቤት

መንፈስ፡- እያንዳንዱ የሰው ልጅ ቀስት--- በሰው ልጅ አምሳል ላይ የታለመ መሆኑን ትረጃለሽ...

አሮጊቷ፡- እረዳለሁ... የእኛው ግን በዛ... በአምሳሉ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን ወንድም በወንድሙላይ የታለመ ነው፡፡

መንፈስ፡- ልጆችሽ ለሠላም... ለመልካም ነገር ጥበበኞች አይደሉም፡፡

አሮጊቷ፡- አዎ አይደሉም፡፡

---

[45]በእርግጥ መጽሐፈ ቅዱስ በምድር ላይ አሉ የሚላቸው መንፈሶች አሉ፡፡ እነሱም፡- መላዕክትና ሰይጣን (እርኩስ መናፍስት) ናቸው፡፡ መላዕክት የሚባሉት እግዚአብሔርን ሌት ተቀን በታማኝነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ፣ ሰይጣን (እርኩስ መናፍስት)በአንድ ወቅት በመላዕክት ደረጃ የነበሩ ነገር ግን ለእግዚአብሐር አልገዛም በማለታቸው ስልጣናቸው ተገፎ የወረዱ ናቸው(ዝኒ ከማሁ)፡፡

[46]Ghot-Wikipedia the free encyclopedia.Rerived April 15,2016

መንፈስ፡- ሠላም ለሚፈልጉ ህዝቦች ግን ፈጣሪ የሰላም ዋስትና ይሰጣቸዋል... ሠላማቸውንም ይጠብቅላቸዋል፡፡

አሮጊቷ፡- ይሆናል፡፡ ለኛ ግን ሠላም ምን እንደምትመስል አይገባንም፡፡ አይተናትም አናውቅም፡፡

መንፈስ፡- እናት! እንደዚህ አትበይ! ህይወትን የሰጠ አምላክ ነፃነትና ሠላምን አብሮ አድሏል፡፡

አሮጊቷ፡- ታዲያ እኛ ዘንድ የት አሉ? የከበበኝ ሬሳ ነው፡፡ ያንጃበበው ሠላም ሳይሆን ጦርነት ነው፡፡ ህይወትና ሠላም የት አሉ? ወይስ ፈጣሪ ሰላምን ለእኛ ለማስፈን ፈቃደኛ አልሆኑም!

መንፈስ፡- የሰው ልጅ የተፈጠረው ለችግርና ለችግር መሆኑን አስታውሺ... ለፈተና መሆኑንም አትርሺ፡፡

(ገቢ.1፣ ትዕ.4)

ከላይ በቀረበው ቃለ- ምልልስ አሮጊቷ የሙት መንፈሱን ድምፅ ይሰሙታል እንጂ በአካል አያዩትም፡፡ በሌላ በኩል ግን፣ ለምሳሌ፣ በ (ገቢ.1፣ ትዕ.5) የሙት መንፈሱ በአካል ተገልፆ ለአሮጊቷ ልጅ መልዕክት ሲያስተላልፍ እንደሚከተለዉ እንመለከተዋለን፡፡

የሙት መንፈስ ነኝ ገራገር፣ የምጓዝ ከአገር አገር፡፡

ከእናት ጋር ባለምሳለሁ፣ ለአንድነት፣ ለፍትህ ቁሚያለሁ፡፡

ብርቅ ህይወቴንም ሠዋኋት፣ ሐቅም ላነሳቸው ሰጠኋት፡፡

ዛሬም እሻለሁ ተከታይ፣ የእኔን ችቦ አቀጣጣይ፡፡

ለአንድ አገር ለአንድ ህዝብ ቋሚ፣ ለዲሞክራሲ ተፋላሚ፡፡

እናም አንቺ ልጅ ስሚ...

(ገቢ.1፣ ትዕ.5)

እዚህ ላይ ፀሐፌ-ተውኔት አያልነህ ሙላቱ፣ የሙት መንፈሱን በአካል ለማሳየት የተጠቀመበት መንገድ የሞቱ ወታደሮች ከወደቁበት ተነስተው የኮረስ ዘማርያን እንዲሆኑና ከመዝሙሩ በኋላ ተመልሰው ሬሳ እንዲሆኑ በማድረግ ነው። አላማዉም በገሃዱ ዓለም የሙት መንፈስን አስመልክቶ ያለዉን አመለካከት በቴአትር ለመግለጽ የተጠቀመበት ቴክኒክ ነዉ። ከተምሳሌታዊ ቲዎሪ ፣ ከአውድና ፍች አንጻር፣አሮጊቷ ተብለዉ የተጠቀሱት ኢትዮጵያን፣ መንፈስ የተባሉት ደግሞ በኢትዮጵ እና ኤርትራ ጦርነት (1991-1993) የሞቱ የኢትዮጵያ ወታደሮችን ይወክላሉ። ከተግባራዊ ቲዎሪ አንጻር ፋይዳዉን በተዉኔቱ ዉስጥ መመልከት የሚቻል ሲሆን፣ ይኸዉም ፀሀፊዉ የሙት መንፈስን እንደ አንድ ሚት[47] ተጠቅሞ ከመልዕክት አንጻር ማስተላለፍ የፈለገዉን **“ወንድማማች በሆኑት የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች መካከል ሁል ጊዜ ሰላም ይስፈን፤ ጦርነት መቼም እንዳይኖር...”** የሚል ይዘት ያለዉ መልዕክት ለማስተላለፍ ችሏል የሚል እምነት አለኝ ።

4.2.1.3 ጸሎትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ጸሎት፣ ልመና ወይም ደግሞ በልመና የሚገኝ ማለት እንደሆነ፣ ካህሳይ (2008፡ 300) ይገልፃል ። በዚህ ተውኔት ውስጥ የምናገኘዉ ፀሎት በመጽሐፍ ቅዱስ (መዝ. 66፣ 31) የተጠቀሰው **“ኢትዮጵያ ታበጽህ አድዊሃ ሃበ እግዚአብሔር” (ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ፈጣሪ ትዘረጋለች)** የሚለው ነው። ይህ ጸሎት (ተማፅኖ) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዘንድ በተለይ ሀገሪቱ ላይ አንዳች ሰው ሠራሽ ወይም ተፈጥሯዊ አደጋ (ለምሳሌ-፡ ድርቅ፣ ርሃብ፣ ጦርነት፣ ስደት ወዘተ.) ተከስቷል ተብሎ ሲታሰብ ተደጋግሞ እንደሚጸለይ ይገልጻሉ።።[48] የፀሎቱ አንድምታ፣ ኢትዮጵያ ከመጣባት ችግርና ፈተና መዳን የምትችለው

---

[47] Bascom ሚት ስለነገሮች አፈጣጠር የሚተርክ ፣ በአማኞች ዘንድ የተቀደሰ ተብሎ የሚታመንበት ሰነድ መሆኑን ይገልጻል (Bascom, 1965:5) ። Oring ደግሞ ሚት እዉነትነቱ መረጋገጥ የማይችል ፣ ዓለምን ማን ፈጠረዉ ለሚለዉ ምላሽ የሚሠጥ፣ የተቀደሰ ፣ ስነ ፍጥረታትንና ፈጣሪን የሚያዋጋ፣ገፀ ባህርያቱ ልዕለ ሰብ የሆኑ ፣ ፍፁም መንፈሳዊነት የሚንፀባረቅበት ፣ የሚታመን፣የመክፈቻና መዝጊያ ስርዓት የሌለዉ ወይም ያልተወሰነ እንደሆነ ያስረዳል (Oring,1986:124) ::

[48] ቀሲስ ዘላለም፤ መሪ ጌታ ሊባኖስ(ቃለ-መጠይቅ)

ፈጣሪዋን በፀሎት በመለመን በእሱ አርዳታ ብቻ መሆኑን የሚያመለክት ነው።።[49] ከሐይማኖት ቲዎሪ አንጻር ስንመለከተው ሐይማኖት ማለት ሰዎች ዘወትር በልዕለ ተፈጥሮ (Spritual being) ጎያልነት የማመን ስርዓት ነው ከሚለዉ የ Oneil (2009:11) እሳቤ አኳያ የሚታይ ነው።።

በተውኔቱ ውስጥ ለመመልከት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ የተወከለችና አሮጊቷ በሚል የገፀ በህርይ ስም የተሰጣቸዉ እናት ኢትዮጵያ ሀገራቸው በድንገት ከመጣባት መዓት፣ በልጆቿ መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ካንጥበበዉ ጦርነት ፈጣሪ እንዲታደጋት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ፀሎት ለፈጣሪያቸዉ ያቀርባሉ።።

መጥኔስ ቢሰጠን ማንነቃ...

ግፍ ተውሎብን መሰንቃ...

ይህ መጥፎ ቀን በምን ያብቃ...

እንዴት ይለፍ ይህ ደቂቃ...

የውጭ እጅ ሥራ ሆነን እቃ...

ለመሙላት... የነጭ ቡሃቃ...

እርስ በርሳችን ስንዋቃ...

በሬሳ መሐል ገብቼ...

ልቤ በሀዘን ተጠቃ...

እባክህ ፈጣሪ ማረን! የእርስ በእርስ ፍጅቱ ያብቃ!

ለማን ብሎ ማንይደፋ... ለማን ተብሎ ህይወት ይጥፋ...

ወንድም ወንድሙን ይግደል! ምድር በሬሳ ይከርፋ!...

የወንድማማቾች ቀይ ደም! የሚፈሰው በበረሃ...

የአንድ እናት ዘር ስለሆነ፣ ይወፍራልና ከውሃ...

የፍጥረት አምላክ አንተ እርዳን፣ ከአልቂት አውጣው ይህን ድሃ....

“ኢትዮጵያ ታበጽህ አድዊሃ ሃበ እግዝአብሔር”...

(ገቢ. 2፣ ትዕ.3)

[49] ዝኒ ከማሁ

የጸሎቱ ክዋኔ በተዉኔቱ ዉስጥ የተገለጸበትን መንገድ ስንመለከተው ፣ አሮጊቷ ይህን ፀሎት ሲያቀርቡ በጉልበታቸዉ ተንበርክከው፣ እጆቻቸውን ወደሰማይ ዘርግተውና በሀዘን ስሜት ውስጥ ሆነው ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ካህሳይ ሲያብራራ “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች በቤተክርስቲያንም ሆነ በቤታቸው ሆነው ፀሎት በሚያደርሱበት ጊዜ እጆቻቸውን ዘርግተው፣ ዓይኖቻቸውን ወደላይ አቅንተው ነው፡፡ የዚህ ዋናው ምክንያት ሰማይ የእግዚብሔር የክብሩ ዙፋን መገለጫ በመሆኑ ነው” (ካህሳይ፣2008፡313) ይላል፡፡ በተጨማሪም ካህሳይ የዚህ አይነቱ የፀሎት ስርዓት ከብሉይ ዘመን ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ ከመሆኑም በላይ በዘመነ ሐዲስም ራሱ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ በፀሎት ጊዜ የሚጠቀሙበት ዘዴ እንደነበር ይገልጻል፡፡ Shomaker(1990:238) ሐይማኖት የእምነት ስርዓት ሆኖ በተከታዮቹ (እንደፈጣሪያቸዉ ከሚያምኑት ጋራ አብሮ በማስገባት) የሚከበሩ ከበራዎች አሉ በማለት የገለጸው ይህን የካሳይን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ ከተግባራዊ ቲዎሪ አንጻር በአጠቃላይ የጸሎት ፋይዳ በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ የሚከወን ማንኛዉንም ነገር ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል ከሚለዉ የ Okepwho (1992:173) እሳቤ አኳያ የሚታይ ሲሆን፣ በዚህ ተዉኔት በዋናነት የተነሳዉ **“ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ሐበ እግዚአብሔር” (“ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ፈጣሪ ትዘረጋለች”)** የሚለው ጸሎት ከሀይማኖታዊና መንፈሳዊነቱ ባሻገር ውስጡ ያለውን የ ሀገር ፍቅርና መልካም ምኞት ይመለከታል፡፡

4.2.1.4 ቆሌን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ሌላው ሾተላይ ውስጥ የተነሳው ፎክሎራዊ ጉዳይ ቆሌን የተመለከተ ሲሆን በዋናነት የአባይ ቆሌ ላይ ያተኩራል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም መዝገበ ቃላት ቆሌ ማለት የአንድን ሰው ወይም አካባቢ ደህንነት ይጠብቃል ወይም ግርማ ሞገስ ይሰጣል ተብሎ የሚታሰብ እንደ ውቃቢ፣ ዛር፣ ከራማ፣ አድባር... ያለ የባዕድ አምልኮ መንፈስ ነዉ (የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም መዝገበ ቃላት፣1993፡ 203)፡፡ በተውኔቱ ዉስጥ የተጠቀሰው የአባይ ቆሌ በተለይ የወንዙ መነሻ በሆነችው ባህርዳርና አካባቢዋ በሚገኙ ማህበረሰቦች ዘንድ ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በጥብቅ ይታመንበታል፣ የተለያዩ የአምልኮ

ስርዓቶችም ይፈጸሙበታል።[50]፣[51] የአካባቢው ነዋሪዎች ጤናቸውን እንዲሰጣቸው፤ በታመሙ ጊዜ ከበሽታቸው እንዲፈውሳቸው፤ ልጆቻቸውን፣ ከብቶቻቸውን እንዲጠብቅላቸው፤ አገር ሠላም ውለ ሠላም እንዲያድር፤ አውድማ ጐተራው የሞላ እንዲሆን ወዘተ... የአባይን ቆሌ (አድባር) ዘወትር ይለማመናሉ። "... ተአምር እንደሚያደርግላቸው ስለሚያምኑ በተለያዬ ጊዜ እየሄዱ፣ 'ጊዎን አንተ ታውቃለህ' እያሉ ይሳሉለታል። በተለይ በየዓመቱ የጥር ወር ሲገባ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ የመሳሰሉትን እያረዱ ከስጋው የተወሰነውን በልተው ሌላውን ቆዳውን ጨምሮ እዚያው ይጥሉለታል፤ ይህን የሚያደርጉት ሰዎች ከባህዳር ብቻ ሳይሆን አርባና ስልሳ ኪ.ሜ፣ ተጉዘው ከአዴትና ኮጉንጅ ድረስ ጭምር በመምጣት ነው"[52]

ከሀገረሰባዊ እምነት አንጻር እንደ ሂደትና የእቀት መንገድ የሚቆጠር፣ ተቀባይነቱም እምነቱ ባለበትና በሚፈጸምበት አካባቢ የሆነ ፣ በማህበረሰቡም ዘንድ እንደ እውነት ሆነ የሚቆጠሩ እምነታዊ አባባሎችና ድርጊቶችን ያካተተ ነዉ ከሚለዉ የ Mullen (1969:215) እና Motz (1998:340) እሳቤ አኳያ የሚታይነዉ። የአባይ ቆሌ የወንዙን መነሻ ተከትለዉ በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ እንድ ልዕለ ተፈጥሮ ሐይል (Superstiton being) ተቆጥሮ ይታመንበታል። **'ጊዎን አንተ ታውቃለህ'** የሚለዉ አባባል የዚህ መገለጫ ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ በወንዙ ላይ የሚፈፀመው የእንስሳት እርድና ሌሎች ተያያዥ ሰርዓቶች እምነታዊ ድርጊቶች ኖቸዉ።

---

[50] ጊዜነዉ አዲስ (ቃለ -መጠይቅ)፣ ባህርዳር፣የካቲት፣2008 ዓ.ም።

[51]ጎጃምና ሸዋን በሚያናንዉ ትልቅ ድልድይ(ሚሊኒየም ድልድይ) አካባቢም እንዲሁ የተለያዩ የአምልኮ ስረዓቶች ይፈጸማሉ። እኔ እራሴ ወደጎጃምና ከጎጃም አዲስ አበባ በአዉቶብስ በተመላለስኩባቸዉ በርካታ ጊዚያት አንዳንድ ተሳፋሪዎች " በቸር አድርሰን " እያሉ ወደ ወንዙ ሎሚ ሲወረዉሩ ተመልክቻለሁ። በዚሁ አጋጣሚ የተዋወቅሁዋቸዉና ከድልድዩ በቅርብ እርቀት ላይ በምትገኘዉ ደጀን ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ አበረ ስማቸዉ እንደገለጹልኝ ደግሞ በየዓመቱ ጳጉሜ ሩፋኤል (ጳጉሜ 3) በአባይ ድልድይና አካባቢዉ የሚኖሩ ሰዎች የወንዙን ወሃ እንደ ፈዋሽ ጠበል ስለሚቆጥሩት ይጠመቁበታል፤ይጠጡታል፤ እነዲሁም ቀድተዉ ወደቤታቸዉ ይወስዱለታል።(አቶ አበረ ስማቸዉ፣ የካቲት፣2008 ዓ.ም)።

[52]ጊዜነው አዲስ (ቃለ -መጠይቅ)፣ ባህዳር፣ የካቲት 2008 ዓ.ም።

የአባይ ቆሌ፣ በዚህ ተውኔት ውስጥ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ሰዎች ሲለማመኑት ወይም “ወንዛችን” እያሉ ሲያሞግሱትና ሲዘምሩለት አንመለከትም፡፡ ይልቁንም ከዚህ በተፃራሪ ተወቃሽ ተነቃሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምለም አፈር ተሸክሞ ለባዕድ እየወሰደ ከመገበሩም በላይ ለኢትዮጵያ ጠላት በማፍራቱ፣ ከውስጥ ሆነ ከውጭ ለሚነሱ ጦርነቶች፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የእሱ አስተዋፅኦ ያለበት በመሆኑ፣ የአባይ ቆሌ ክፉኛ ወቀሳ ይደርስበታል፡፡

የእኛ ጠብ ጫሪ ደባይ፣ የእኛን ውሃ አፈር አቀባይ፣

እርሃብ ቸነፈር ለኛ አዳይ፣ ለእኛ ጠላቶች ሲሳይ፣

ትንላንትም ዛሬም አባይ፡፡

እኛን በእኛ... የሚወጋ፣ እኛን በእኛ የሚያዋጋ፣

የውጭ አልጋ የውስጥ ቀጋ፣ ለኛ ጭንቀት ለባዕድ ፀጋ፣

ቋሚ ችግር በእኛ ሠፈር፣ አንተ ያባይ ውሃ ያባይ አፈር

የእኛነታችን አጥፊ ጠላት፣

ያባይ ወንዝነህ፣ ያባይ አፈር፡፡

(ገቢ. 1፣ ትዕ. 5)

የአባይ ቆሌ ግን ይህን ወቀሳ አይቀበለውም፤ “**ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እናንተ ኢትዮጵያውያን ናችሁ እንጅ እኔ አይደለሁም** ” ሲል እንደሚከተለዉ ይሞግታል፡፡

እናት ችግሩ... አንች ቤት ነው ያለው... ልጆችሽ አልተባበሩም...

ልጆችሽ አልጠነከሩም... በእኔ ለመልማት አልጣሩም...

እኔን ለማውጣት አልሞከሩም... አንድ መስመር ቦይ አልቆፈሩም፡፡

... እኔን በግድብ ገድባችሁ... ከጉድጓዴ አውጥታችሁ

ለመብራት ኃይል ስባችሁ... አትክልት አዝርእት አብቅላችሁ...

ዛፎች አሳድጋችሁ የተነሳባችሁ ጠላት...

የወጋችሁ በደም ፍሰት

ካለ በግልጽ ተናገሪ... ሥጋትሽን ብቻ አታውሪ...

ፍራትሽን ለእኔ አትናገሪ፡፡

(ገቢ. 1፣ ትዕ. 5)

ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለዉ በዚህ ቴአትር ፀሀፌ ተዉኔቱ በአባይ ቆሌ አማካኝነት ኢትዮጵያዉያን አባይን እየወቀሱ ከመኖር ባለፈ ለብዙ ዘመናት ወንዙንና ገባሮቹን አልምቶ በመጠቀም ረገድ ያሳዩትን ዳተኝነት[53] መግለጹን ነዉ፡፡ ይህም ከፀሀፌ ተዉኔት አንጻር አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ተጠቅሞ ሀሰቡን ለመግለጽ የሞከረበት ዘዴ (Technique) ሲሆን ከተግባር ቲዎሪ አንጻር ሲታይ ደግሞ አገር ለማሳደግ የሚቻለዉ ከወቀሳና ትችት በዘለለ ጠንክሮ በመስራት እንደሆነና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰዉ ልጅ ተፈጥሮ የለገሰችዉን ሐብት በአግባቡ ሊጠቀምበት እንደሚገባ የመከረበትና ያስተማረበት ነዉ ብሎ መዉሰድ ይቻላል፡፡

4.3 አልቃሽና ዘፋኝ

የአልቃሽና ዘፋኝ ታሪክ የሚያተኩረው አስጋርጅው እና ማሩ በተባሉ አንዲት ትንሽ ክፍል ቤት በጋራ ተከራይተው በሚኖሩ ሰዎች ላይ ነው፡፡ አስጋርጅው የታወቀች አስለቃሽ (ሙሾ አውራጅ) ስትሆን፣ ማሩ ደግሞ አዝማሪ ነው፡፡ የሁለቱ ሰዎች ሙያ ከሙያም በላይ የህልውና ጉዳይ ጭምር ነው፡፡ ይህም በተውኔቱ ታሪክ ውስጥ ጎልቶ የሚወጣው ደጃዝማች አለሜ የተባሉ ሐብታም ሰው የልጅ ልጃቸውን እንደሚድሩ በታወቀ ጊዜ ነው፡፡ ሁለቱም የቤት ኪራይ የሚከፍሉት አጥተው በአከራይአቸው ጉሮሮአቸውን ታንቀው ባሉበት በዚህ ጊዜ ይህ የደጃዝማች አለሜ ሰርግ ምንም እንኳ ለማሩ የምስራቹ ቢሆንም፣ ለአስጋርጅው ግን ፋይዳው ምንም ነው፡፡ ስለሆነም፣ አስጋርጅው በጊዮርጊስ ስዕል ፊት ሻማ አብርታ፣ “. . . ጊዮርጊስ እባክህ

[53] የአባይ(ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ) ግንባታ የተጀመረዉ በ 2003 ዓ.ም መሆኑን ያስታዉሷል፡፡

ትልቅ ትልቁን ገንድስልኝ" በማለት ትለምናለች፡፡ ታቦቱ ልመናዋን እንዲሰማትም ደጋግማ ስዕለት ትሳላለች፡፡ ማሩ በበኩሉ ከደጃዝማች አለሜ ዳጎስ ያለ ገንዘብ እንደሚያገኝ ተስፋ በማድረግ ጋሻ ሲሳይ ከሚባሉ ሰው ብር በአራጣ ተበድሮ ሱሪና እጅ-ጠባብ አሰፍቶ፣ መጫሚያ ገዝቶ፣ ማሲንቆውን ወልውሎ ለሠርጉ ዝግጅት ማድረግ ይጀምራል፡፡ ሆኖም የአስጋርጅው ፀሎትና ልመና "ጊዎርጊስ ገንድስልኝ" የሚለው የዕለት ተዕለት "ሚርት" በደጃዝማች አለሜ ሰርግ ላይ አንዳች የከፋ ነገር እንዳይፈጠር ስለሰጋ "ሚርትሽን አቁሚ" በሚል ከአስጋርጅው ጋር የመረረ ፀብ ውስጥ ይገባል፡፡ በዚህ ሁናቴ ውስጥ እንዳሉም የሰርጉ ቀን ይቃረብና በደጃዝማች አለሜ ግቢ ውስጥ ዳስ መጣል ይጀመራል፡፡ ነገር ግን ብዙም አይቆይም፤ አንድ ያልታሰበ ዱብ-ዕዳ ነገር ይፈጠራል፡፡ ሙሽራዋ የደጃዝማች አለሜ የልጅ ልጅ ቀደም ሲል ሲያሰቃያት የነበረው ህመሟ ድንገት አገርሽቶባት በጠና ትታመምና ወደ ሀኪም ትወሰዳለች፡፡ ይሁንና ህይወቷን ማትረፍ ባለመቻሉ ትሞታለች፡፡ ሰርጉም ወደ ሐዘን ይቀየራል፡፡ ይህ አጋጣሚ በአንድ በኩል ከሠርጉ ብዙ አተርፋለሁ ብሎ አቅዶ በነበረው አዝማሪው ማሩ ላይ መሪር ሀዘን ሲፈጥር በሌላ በኩል ደግሞ ሠው እንዲሞትላት ስትመኝ ለነበረችው አስጋርጅው ደስታንና ገንዘብን ያመጣል፡፡ የታሪኩ ፍፃሜም ሁለቱን ተቃራኒ ሠዎች በስመተጨረሻ በትዳር በማጣመር ይጠናቀቃል፡፡

4.3.1. አልቃሽና ዘፋኝ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተውኔት ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሙሾ እና የአዝማሪ ግጥሞችን የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

4.3.1.1 የሙሾ ግጥሞችን[54] የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

1. አየጉድ አየጉድ
   አለሁ ማለት ከንቱ
   የሞት እንግድነት መምጫው አይታወቅ
   በቁስ አይመለስ በጉቦ አይታረቅ

(ትዕ. "ሀ"፣12)

የዚህ ግጥም አጠቃላይ ይዘት ሞት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የማይቀርና በማንኛውም የህይወት ዘመኑ ሁሉ ድንገት ሊከሰት የሚችል መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ እንደዚሁም ሞት ከሰው ልጅ አቅም በላይ የሆነና በምንም አይነት መልኩ ሊቋቋመው የማይችል ተፈጥሯዊ ህይል ያለመኖሩን ያመለክታል፡፡

ግጥሙ የቀረበበትን አውድ በተውኔቱ ውስጥ ስንመለከተው፣ ግጥሙ የተገጠመው የደጃዝማች አለሜ የልጅ ልጅ የሆነችው ወጣት ሙሽራ ሰርጓ አንድ ቀን ሲቀረው ድንገት ሳትታሰብ በመሞቷ ነው፡፡

"**. . . የሞት እንግድነት መምጫው አይታወቅ**" የሚለውም ሙሾ አውራጇ (አስጋርጅው) ክስተቱን ለመግለፅ የተጠቀመችበት ነው፡፡ ከተግባር ቲዎሪ አንፃር የሙሾ ግጥሙ የመምከርና የማስጠንቀቅ ፋይዳ አለው፡፡ የሰው ልጅ ሞት አይቀሬ መሆኑን ዘንግቶ በትዕቢት እንዳይኩራራና ከሚኖርበት ማህበረሰብ ባህልና ወግ

---

[54] እንደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት ምርምር ተቋም መዝገበ ቃላት (ገፅ 68) "ሙሾ" ሰው በሞተ ጊዜ በአውራጅና በተቀባይ አማካይነት በግጥምና በዜማ እየታጀበ የሚካሄድ ለቅሶ ማለት ሲሆን፣ "ሙሾ አውራጅ" የለቅሶ ግጥምን በዜማ እያሰማ የሚያለቅስ ሰው ማለት ነው፡፡ የሙሾ ግጥሞች ረጅም ታሪክ ያላቸው ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ካህሳይ(2008፣48) "ከብሉይ ዘመን አንስቶ እስካለንበት ጊዜ ድረስ እየተሰራባቸው ካሉ የለቅሶ ልማዶች አንዱ የሙሾ ግጥም ወይም የሀዘን እንጉርጉሮ ነው፡፡ የሙሾ ግጥሞችን (ቅኔዎችንም) በመደርደር በኩል ዳዊት ተጠቃሽ ነው፡፡ ዳዊት ሳኦልና ልጁ ዮናታን በሞቱ ጊዜ ረዘም ያለ የሀዘን እንጉርጉሮ (የሀዘን ቅኔ) አሰምቶአል" በማለት የጊዜዉን ርዝመት ይገልጻል፡፡

ባፈነገጠ መልኩ ያልተገባ ተግባር እንዳይፈፅም ይህ ግጥም ይመክራል፣ ያስጠነቅቃል፡፡

2. ዋዋ !አየ እህል ውሃ
   ኧረ ወየው ወየው!
   ኧረ ወየው ወየው!
   በቀዬ ተከብራ ትኖር የነበረች
   ሰፈፍ የሌላት ማር ዛሬ ተቆረጠች
   ዋ እኔን ደፋ ያርገኝ፡፡

(ትዕ. "ሀ"፣15)

3. በእናቷ በአባቷ የጠራች እመቤት
   ደፋ ብላ ቀረች ሊበላት ነው መሬት

   እኔን እኔን ወይ አንቺ ሙሽራ

   ጋብቻው አነሰኝ ማለትሽ ነው ወይ

   ጫጉላ አፈራርሰሽ ከአፈሩ የምትውይ፡፡

(ትዕ. "ሀ"፣20)

ከላይ በተራ ቁጥር 2 እና 3 የቀረቡት ሁለት የሙሾ ግጥሞች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ይዘት አላቸው፡፡ ከመተንተኛ ቲዎሪ አንፃር በአውዳዊ ቲዎሪ/ማህበራዊ አውድ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚታዩ ናቸው፡፡ ይህም በዋናነት አውድ የስነቃል አይነቶች ከግለሰብ ህይወትና የኑሮ መሰረት ጋር የሚገናኙበት መንገድ ሆኖ በውስጡ የተካተቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከት እንደሆነ Bauman (1977), Okepeho (1992) እና Ben Amos (1993) ከገለጹት ሀሳብ ጋር ይያያዛል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር እነዚህን የሙሾ ግጥሞች ስንመረምራቸው ሚች ከዕድሜ እና ከፆታ አንፃር በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ እንስት መሆኗ እንረዳለን፡፡

እንደዚሁም ከ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ አንጻር ከሀብታም ቤተሰብ ተወልዳ "በጨዋ ደንብ" እና በእንክብካቤ ያደገች እንደሆነች እንገነዘባለን፡፡

ከተግባር ቲዎሪ አኳያ ስንመለከታቸው እነዚህ የሙሾ ግጥሞች የአንድ ሰው የህይወትና የኑሮ መሰረት ይገልጻሉ፡፡

4. ዋይ ዋይ የት ትሄጃለሽ?
   ዋይ ዋይ የት ትሄጃልሽ ?
   እህት የሞተሽ ወንድም የሞተሽ
   ዋይ ዋይ የት ትሄጃልሽ?
   እናት የሞተሽ አባት የሞተሽ
   ዋይ ዋይ የት ትሄጃልሽ?
   ያዥ ይህን ጊዜ እንዲያ ይውጣልሽ፡፡

(ትዕ. “ለ”፣25)

በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰዉ የሙሾ ግጥም ከ ክዋኔ ቲዎሪ አኳያ በሙሾ ግጥሞች ክዋኔ ወቅት በከዋኙ (Performer)) እና በተሳታፊዎች (Observers) መካከል ያለዉን ኪናዊ መስተጋብር ያሳያል፡፡ ይህም መስተጋብር በመልዕክት (Texture) እና በከዋኔ (performance) የሚገለፅ ነው፡፡ **እናት፣ አባት፣ እህት ወይም ወንድም የሞተብሽ በዚህ አጋጣሚ በደንብ አልቅሽና ይውጣልሽ** . . . የሚለው የሙሾ አውራጅ መልዕክት በከባድ ደረት ድቂ ታጅቦ ሲቀርብ፣ እናትና አባት ወይም እህትና ወንድሞቻቸውን በሞት በአጡ የለቅሶው ተሳታፊዎች ላይ የሚፈጥረው የሀዘን ስሜት ከፍተኛ ነዉ፡፡፡፡ ይህም በሌላ በኩል ከተግባር ቲዎሪ አንፃር ሲታይ የሙሾ ግጥሙ የማህበረሰቡን የሀዘን ስሜት በጋራ የመካፈል ፋይዳ ያመለክታል፡፡

ለማጠቃለልያህል እስካሁን የተመለከትናቸው የሙሾ ግጥሞች የሚችን ማንነት፣ የአስተዳደግና የኑሮ ሁኔታ፣ ቤተሰባዊ ዳራ ወዘተ. እያነሱ የሀዘኑን ተካፋዮች በተለይም ደግሞ ቤተሰብን ያጽናሉ፡፡

4.3.1.2 የአዝማሪ ግጥሞችን[55] የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

1. ደጃዝማች አለሜ ይበልህ ደስ ደስ
   ፈረስ ያስጋልባል የሰራኸው ዳስ፡፡
   አዲሱ ሙሽራ ዕድለኛ ነህ
   የደጃዝማች ቀኝ ዕጅ አማቻቸው ሆንህ፡፡

   (ትዕ. "ለ"፣30)

2. የኛ ሙሽራ ኩሪ ኩሪ
   በእንግሊዝ ተናገሪ፡፡

   (ትዕ."ለ"፣35)

   3.ሙሽሪት በአንድ አልጋ
   ሙሽራው በአንድ አልጋ
   መልአክ ይመስላሉ ክንፉን የዘረጋ፡፡

   (ትዕ."ለ"፣32)

የእነዚህን የአዝማሪ ግጥሞች ይዘት ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው በውዳሴ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከሚከውኑበት አውድ አንፃር ደግሞ ሠርግ ቤት የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ከተውኔቱ ታሪክ ጋር በማያያዝ እያንዳንዳቸውን በዝርዝር ስንመለከታቸው፣ በተራ ቁጥር 1 ላይ አዝማሪው ማሩ". . . **ፈረስ ያስጋልባል-የሰራኸው ዳስ**" በማለት ግጥሙን ከውዳሴ ባለፈ የደጃዝማች አለሜን የኢኮኖሚ ደረጃ ለማሳየት ተጠቅሞበታል፡፡

---

[55] አዝማሪነት በሀገራችን መቼና እንዴት እንደተጀመረ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፣ ሙያው ረዥም ዕድሜ ያስቆጠረ ስለመሆኑ ግን አንዳንድ ጥናትና ምርምሮች ይጠቁማሉ፡፡ ካህሳይ (2008፣187-188) "በጥንት ጊዜ አዝማሪ እንደ መለከት ነፊና በገና ደርዳሪ ዋና ተግባሩ ታቦት ዑደት(እርገት) ሲወጣ መሠንቆ እየመታ በእንጉርጉሮ ዜማ እግዚአብሔርን ማመስገን ነበር፡፡ ለዚሁ አገልግሎቱም እንደ አገልጋይ ካህናት ተቆጥሮ መሬት ይሰጠው ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ግን ነገስታትና መኳንንት ራሳቸውን ለማዝናናት ሲሉ በየቤታቸው (በግል) አዝማሪ በቋሚነት ማስቀመጥ ጀመሩ፡፡" ይላል፡፡ አልማዝ (1974፣4) በበኩሏ፣ አዝማሪነት በሰፊው በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፍቶ የታየው በ19ኛው ክፍለ ዘመን በተለይም በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት እንደነበር ትገልፃለች፡፡

በተመሳሳይ መልኩ **“አዲሱ ሙሽራ እድለኛ ነህ፣የደጃዝማች ቀኝ እጅ አማቻቸው ሆንህ”**

ብሎ በመቀኘት ደጃዝማች የልጅ ልጃቸውን የሚያገባው ሙሽራ ከእርሳቸው ጋር በጋብቻ በመዛመዱ ብቻ ዕድለኛ መሆኑን በመጥቀስ አሁንም በተዘዋዋሪ መንገድ ደጃዝማቹን ያሞግሳቸዋል፡፡

ይህ ውዳሴ ከአውዳዊ ቲዎሪ/ማህበራዊ አውድ አኳያ የደጃዝማቹን የኑሮ ደረጃና ማህበረሰቡ የሰጣቸዉን የተለየ ስፍራ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል፣ ከተግባር ቲዎሪ አንጻር፣ ግለሰቡ ሙገሳውን ከአዝማሪው ሲሰሙ የሚሰማቸውን እርካታና የደስታ ስሜት ከግምት ውስጥ በማስገባት ግጥሙ በግለሰብ ደረጃ ደስታ እና እርካታን በማስገኘት ረገድ ያለውን ፋይዳ መረዳት ይቻላል፡፡

በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው **“የኛ ሙሽራ ኩሪ ኩሪ በእንግሊዝ ተናገሪ”** የሚለው ግጥም በዚህ ጥናት (በምዕ.3) ከቀረበዉ “የስነ ቃልን ክዋኔ ፋይዳ ከዘመን ፍላጎት አንጻር ያለበትን ሁኔታ መተንተን . . .” ከሚለው የእነ Bauman (1992) ሀሳብ አኳያ ሲታይ፣ በአንድ ወቅት እንግሊዝኛ ቋንቋን አስመልክቶ በሀገራችን የነበረውን ከፍተኛ ግምት ያሳያል፡፡

በ1960ዎቹና 70ዎቹ አካባቢ እንግሊዝኛና አማርኛን እየቀላቀሉ መናገር በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ የክብርና የኩራት መገለጫ ተደርጎ ይታይ እንደነበር ይነገራል፡፡[56]

ስለሆነም የአዝማሪ ግጥሙ በእንግሊዝኛ መናገር መቻልን አስመልክቶ በአንድ በተወሰነ ዘመን የነበረን ማህበረሰባዊ አመለካከት ያሳያል፡፡

በተራ ቁጥር 3 ላይ ያለው ከተምሳሌታዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ በነገሮች መካከል ያለውን ተምሳሌታዊ ውክልና ያመለክታል፡፡ አዝማሪው፣ **“ሙሽሪት በአንድ አልጋ፣ ሙሽራው በአንድ አልጋ፣ መላክ ይመስላሉ ክንፉን የዘረጋ”** በማለት የሙሽሮችን (ረቂቅ ያልሆኑ ፍጥረታትን) ውበት ከመልአኩ (ረቂቅ ከሆነው ፍጥረት) ክንፎች ጋር አመሳስሎታል፡፡

[56] አልቃሽና ዘፋኝ ተውኔት የተጻፈው በ1973 ዓ.ም መሆኑንና ታሪኩ የተፈፀመበት ዘመን ደግሞ (እንደ ፀሀፌ-ተውኔቱ ገለጻ) ቅድመ የኢትዮጵያ አብዮት ዘመን መሆኑን ይገነዘባል፡፡

ከተግባር ቲዎሪ አንፃር ስናየው ይህ ግጥም የሰውን ልጅ ውበት በረቀቀ መንገድ ይገልጻል፡፡

አልቃሸና ዘፋኝ ወስጥ በቁንጽል የተመለከትናቸው የአዝማሪ ግጥሞች በግለሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የማወደስ፣ የማዝናናትና ደስታ የመፍጠር ፋይዳ እንደአላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

4.4. የቴዎድሮስ ራዕይ

የቴዎድሮስ ራዕይ ታሪክ በዋናነት በካሳ (በኋላም አፄ ቴዎድሮስ) አነሳስና “ውድቀት” ላይ የሚያተኩር ሆኖ በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮችን ያነሳል፡፡

ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመን አንድነቷ ተጠብቆ የኖረች ጥንታዊት ሀገር ናት ይሁን እንጂ ለዘመናት የኖረው ይህን የሀገሪቱን አንድነት መፈታተን ጀምሮአል-ዘመነ መሳፍንት :: በዚህ ዘመን እዚያም እዚህም ብቅ ያለ ጎጠኛና አምባገነን ባላባቶች በእኔ እነግስ እኔ እነግስ ሽኩቻ ተጠምደዋል፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅት ነበር ካሳ ሀይሉ (ከቋራ)፣ ገብርዬ (ከጋይንት)፣ አለሜና ገልሞ (ከሞጁልጋ)፣ በገዛ ሀገራቸው የደረሰባቸውን በደል በመቃወም የሸፈቱት፡፡

ለካሳ በኋላም ቴዎድሮስ መሸፈት የመጀመሪያው ምክንያት ተዋበች አለ ናት፡፡ ገና በጠዋቱ በተዋበች ፍቅር የተነደፈው ካሳ ሕይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ ተዋበችን ከቱርክ ምርኮ አዳናት፡፡ ነገር ግን ለአባቷ ለራስ ኃይሉ ዋጋ የሚሰጠው አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ (በእነሱ እይታ) ካሳ ከመሳፍንት ወገን የሚቆጠር ዘር የለውም፡፡ ምንም እንኳ ኋላ ላይ ካሳ ስሙ በአቁራና አካባቢው እየገነነ አስፈሪነቱም እየጨመረ ሲመጣ ተዋበችን እንዲያገባ ቢፈቅዱለትም ጋብቻው ካሳን በዝምድና ለማሰር ብቻ የታቀደ በመሆኑ የእቴጌ መነን ንቀት ቀጠለ፡፡ በተለይ በአንድ ወቅት ካሳ ታሞ እቴጌዋ አንድ ንቅል የበሬ ስጋ ለመጠየቂያ ከላኩለት በኋላ “ደሞ ለአንድ ፍየል ጠባቂ እረኛ አንድ ንቅል ስጋ አነሰው በሉኛ . . .” በማለት የሠደቡት አንገበገበው፡፡ እናም በሚስቱ በተዋበች አነሳሽነት ደግሞ በእቴጌ መነን ላይ ሸፍቶ በጦር ሜዳ ተፋለማቸው፡፡

ደምቢያ በተባለች ቦታ እቴጌዋን ማረከና አሰራቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ዝናው ከበፊቱ የበለጠ እየገነነ የመጣው ካሳ የዘመኑን መሳፍንት ሁሉ አንድ በአንድ በጦር ሜዳ አሸንፎ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ ለመሆን በቃ፡፡ ንግስናውን ተከትሎ ሀገሪቱን አንድ አድርጎ ለመግዛትና ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን የተለያዩ የለውጥ እርምጃዎችን መውሰድ የመጀረው ቴዎድሮስ ከተለያየ አቅጣጫ ራዕዩን የሚቃወሙ ጠላቶች ይነሱበት ጀመር፡፡ በዚህ የተበሳጨው ካሳም ጠላቶቹን እያሳደደ መቅጣቱን ቀጠለ፡፡ በተለይ እጅግ የሚወዳት ሚስቱ ተዋበች አሊ ከሞተች በኋላ ቅጣቱ በሌላውም ላይ ጭምር በረታ፡፡ ሆኖም በዚህ ሁኔታ ውስጥም ሆኖ፣ ሀገሪቱን አንድ ለማድረግና ለማዘመን የነበረውን ጥረት ግን አላቆመም ነበር፡፡ ከተለያዩ የውጭ ሀገራት በተለይ ከእንግሊዝ መንግስት ጋር ወዳጅነት መሠረተ፡፡ ነገር ግን ከእንግሊዞች የሚጠብቀውን ያህል መሳሪያና የባለሙያዎች ድጋፍ ባለማግኘቱ ተበሳጭቶ ቆንስል ካሜሩን እና ሌሎች እንግሊዛውያንን አሰረ፡፡ በሌሎች የአውሮፓ ዜግነት ባላቸው ሠዎች ላይም ተመሳሳይ ድርጊት ከፈፀመ በኋላ ወደ ጋፋት በመላክ የጦር መሳሪያ እንዲሰሩለት አስገደዳቸው፡፡ እስረኞችም ከብዙ ድካምና ተደጋጋሚ ሙከራ በኋላ “ሲባስቶፖል” የተባለውን መድፍ ለመስራት ቻሉ፡፡ ነገር ግን ካሳ ገና ደስታውን ማጣጣም ከመጀመሩ መድፉ በራሱ ጦር መሀል ፈነዳ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም ይባሱኑ የእንግሊዝ መንግስት የታሰሩ ዜጎቿን በሀይል አስፈታለሁ በማለት በካሳ ላይ ጦሩን አዘመተ፡፡ በጄነራል ናፒየር የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ማረፊያውን ምፅዋ ወደብ ካደረገ በኋላ ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል ገሠገሠ፡፡ አምስት ወር ከፈጀ አድካሚ ጉዞ በኋላም ወደ ቴዎድሮስ ምሽግ መቅደላ አምባ ተቃረበ፡፡ ካሳ ተከታዮቹን አስተባብሮ፣ ገብርዬ፣ ገልሞን እና አለሜን የጦሩ መሪ አድርጎ ለአይቀሬው ጦርነት ተዘጋጀ፡፡ ድሉ የእሱ እንደሚሆንም በፈጣሪው ላይ እምነቱን ጣለ፡፡ ነገር ግን ጦርነቱ በተጀመረ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሠራዊቱ ቁጥር ሲመናመን ተመለከተ፡፡ በተለይ በጦር ጀብዱ የሚመካበት ገብርዬ መገደሉን ሲሰማ ሁሉ ነገር እንዳበቃለት ተረዳ፡፡ በስተመጨረሻም ጄነራል ናፒየር ያቀረበለትን “በክብር እጅህን ስጥ” ጥያቄ ውድቅ አድርጎ በገዛ ሽጉጡ ራሱን በራሱ አጠፋ፡፡

4.4.1. የቴዎድሮስ ራዕይ ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

የቴዎድሮስ ራዕይ ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች በ ተራኪ- ቃል-ግጥሞች፣ ባህላዊ ዘፈኖች፣ ቀረርቶና ፉከራዎች እና እረኛ ዘፈኖች ላይ ያተኩራሉ፡፡ በመሆኑም እያንዳንዳቸውን ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

4.4.1.1 ተራኪ ቃል ግጥሞችን[57]የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

1. . . . አዎ፣ ሩቅ - ሩቅ - ሩቅ ነው፡፡ይህች የተፈጥሮ ረቂቅ አሻራ መሬት፣ ይህች የሰው ዘር ምንጭ መፍለቂያ ምድር፣ . . . ከትናንቱ የጎንደር ንጉስ ተክለጊዮርጊስ፣ እስከ ሸዋው ንጉስ ሚናስ . . . ከሰለሞናዊው ይኩኖ አምላክ፣ እስከዛጉዌአዊው ይትባረክ . . . ከላስታው መራ ተክለሀይማኖት፣ እስከ ንግስት ሳባ አክሱማዊት፣ ያለው የታሪኳ ክሯ እንኳ ሲመዘዝ፣ . . . ይህች ሀገር፣ ይህች ኢትዮጵያ፣ ሩቅ ነው ስር መሰረቱዋ! ሩቅ ነው ወርድ ስፋቱዋ! . . . አዎ፣ በምስራቅ፣ እስከ ማዳጋስካር፣ . . . በደቡብ፣ እስከ ኒያንዛ ባህር፣ . . . በምዕራብ እስከ ኑቢያ፣ በሰሜን እስከ ምስር ምድር፣ . . . የተዘረጋ ቁመትዋ፣ የተንጣለለ ደረቱዋ፣ . . . ይህቺ ባለጥንተ ታሪክ፣ ይህቺ ባለቀደምት ስልጣኔ፣ ይህች ባለድንቅ እደጥበባት ሀገር፣ . . . ሩቅ ነው ስርዋ ግንድዋ! ጥብቅ ነው ዘር ሀገረግ ውሎዋ! ጥልቅ ነው መሰረት ስርዋ!! . . .

(ገቢ 1.፣ት፬.1፣1)

ከላይ የቀረበዉን ተራኪ ቃል ግጥም ይዘት ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፣ ኢትዮጵያ ረዥም ታሪክ ያላት፣ የሰው ዘር መፍለቂያና የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት መሆኗን ይገልጻል፡፡ እንደዚሁም በተለያየ ጊዜ ሀገሪቷን ስለመሩት ነገስታትና ስርወ

[57] ተራኪ ቃል-ግጥሞች ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ግጥሞች ታሪካዊ ድፍረት ፈፃሚዎችን፣ ድርጊቱ የተፈፀመባቸውን ቦታዎችና ዘመኑን፣ ማህበረሰቡ ያለፈበትን የታሪክ ጉዞ፣ የገጠመውን ውጣ ውረድ፣ ሀዘኑን፣ ደስታውን ሁሉ ይተርካሉ፡፡

መንግስታቸው ይተርካል፡፡ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ ቀደምት ምድር ስለመሆኗ ከ 4 ሚሊዮን ዓመት በፊት በምድር እንደኖረች በሳይንቲስቶች የተረጋገጠው ሉሲ-ድንቅነሽ ወይም በሳይንሳዊ አጠራር “Australo Pithecus Afarnessis” ምስክር ናት ፡፡ ከዚህ አንጻር በተራኪ ቃል ግጥሙ **“ይህቺ የሰው ዘር ምንጭ መፍለቂያ ምድር”** ተብሎ የተገለፀው ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የኖረባት ሀገር እንደሆነች ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ **“ይህች ባለ ጥንት ታሪክ፣ ይህች ባለ ቀደምት ስልጣኔ፣ ይህች ባለድንቅ ዕደ ጥበባት ሀገር . . .”** የሚለው ትረካ ሀገሪቱ በአንድ ወቅት በስልጣኔ ደርሳበት የነበረዉን ደረጃ ያመለክታል፡፡ በ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ፀሀፊዎች ለምሳሌ፣ (ጳዉሎስ፣1991፤ ተክለጻዲቅ፣1969፤ Harold,1994) ተጽፎ እንደሚገኘው፣ ጥንታዊ አክሱማውያን የውብ ኪነ-ህንፃዎች መሀንዲሶች ነበሩ፡፡ የተለያዩ የወርቅ ሳንቲሞች አስቀርፀው ለገበያ ማዋል ችለውም ነበር፡፡ በተመሳሳይ የዛጉዌ ስርወ መንግስት ወራሽ የሆኑት ላስታዎቹ በንጉሳቸው ላሊበላ እየተመሩ በአሁኑ ጊዜ በ UNESCO የዓለም ቅርስ ተመዝግበው የሚገኙትን የላሊበላ አቢያተ ውቅር ቤተ ክርስትያናት ማነጽ ችለው ነበር፡፡

በተራኪ ቃል-ግጥሙ የተገለፀው ከላይ የቀረበው የዚህ ታሪክ እውነታ ነፀብራቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከተግባር ቲዎሪ አኳያ ሲታይ ፣ ግጥሙ ታሪክን በመተረክና በአንድ በተወሰነ ዘመን የነበረው የሀገራችን የዕድገትና የስልጣኔ ደረጃ እንዲታወቅ በማድረግ ረገድ ያለዉን ፋይዳ መመልከት ይቻላል፡፡

1.2.1. . . . . **አዎ፣ ያስፈራል፣ ያሳፍራልም . . . ከአክሱም ፅዮን-ሮሃ ላሊበላ . . . ከላሊበላ ላስታ፣ ሸዋ፣ ደብረ ኤባ፣ ኤፍራታ፤ . . . ከመሃል ሸዋ አንኮበር ሰሜን፣ በጌምድር፣ ጎንደር፤ . . . በዘመንና በትውልድ ከአንዱ ወደ አንዱ ሲሸጋገር ሲወርድ ሲዋረድ የኖረ፣ ተቀጣጥሎ በታሪክ ክር፣ ተቀባብሎ የዘለቀ፣ አንድ ማዕከላዊ ስርዓት፣ አንድ ኢትዮጵያዊ ሀርነት፣ . . . በ”እኔ አነግስ፣ እኔ እነግስ” ጉጉት፣ በ”እኔ እጎርስ፣ እኔ እጎርስ” ስስት፣ ተበጣጥቆ፣ ተቦጫጭቆ፣ ተፍረክርኮ የታየበት፣ . . . አንድ ትልቅ የነበረች ሀገር፣ በየወንዙ ተሸንሽና፣ በየሰላሳው ሹም ስር፣ ሰላሳ ትንንሽ ሆና፤ ቁልቁል የወደቀችበት፣ ህዝቧ እርስ በእርስ ፍትጊያ፣ . . . አሳሩን የሚያይባት የግብግብ፣**

> የትንቅንቅ፣ የትልቅልቅ ዘመን፣ ዘመነ መሳፍንት፡፡ . . . አዎ፣ ያስፈራል፣ ያሳፍራል ያስቆጣል፣ ያስቆጫል፣ “ኧረ ያገር ያለህ! ኧረ የሰው ያለህ! ኧረ የወንድ ያለህ! . . .” ያሰኛል!! . . .
>
> (ትዕ.1፣3)

ከሁኔታው አውድ አንጻር ይህ ተራኪ-ቃል ግጥም በኢትዮጵያ ታሪክ ዘመነ መሳፍንት በመባል የሚታወቀውን ጊዜ ይገልፃል፡፡ የግጥሙን ይዘት በዝርዝር ለማየት ያህል፣ ዘመነ መሳፍንት የኢትዮጵያ አንድነት የተሸረሸረበትና አሻንጉሊት ነገስታት የበዙበት ጊዜ እንደነበር ይገልጻል ፡፡

ከተራኪ ግጥሙ መረዳት የሚቻለው ሌላው፣ ዘመነ መሳፍንት በጎጥ የተከፋፈሉ ገገርዎች የበዙበት ብቻ ሳይሆን “እኔ እነግስ እኔ እነግስ” በሚል ሽኩቻ እዚያም እዚህም አታካች ጦርነቶች የተደረጉበት፣ ከነዚህም መሀል አንዳንዶቹ በሚያስገርም ሁኔታ በአባትና በልጅ መካከል ጭምር የተደረጉ ነበሩ፡፡ “. . . ደጃች ጎሹ ዘውዴ በሰሜን ኢትዮጵያ ለበላይነት ከሚፋለሙ መሳፍንት አንዱ ለመሆን መጠነኛ ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ በዘመነ መሳፍንት ማንም ለማን የማይተኛ ነበርና ከባላንጣዎቹ አንዱና ዋነኛው የገዛ ልጁ ብሩ ጎሹ ነበር፡፡ በ1834 ባደረጉት ውጊያም ብሩ አባቱን አሸነፈው” (ባህሩ፣2007፣12-13)፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተራኪ ግጥሙ በዘመነ መሳፍንት የነበረውን ነባራዊ ሁኔታ ለማሳየት ያለዉን ፋዳ ሲሆን ከዚሁጋር በተያያዘ ስለ መተባበርና አንድ ጠንካራ ሀገር ስለመፍጠር ያለዉን አስተምሮት መመልከት ይቻላል፡፡

4.4.1.2 ባህላዊ ዘፈኖችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

1. <u>ወንድ አቀንቃኝ</u>

ታሪካዊት መነሻዬ
ሀገራዊት መድረሻዬ
የዘር ሀረግ ማሰሪያዬ
አክሱማዊት ሀበሻዬ
<u>ሴት አቀንቃኝ</u>

ሙዳዬ ነሽ ገመናዬ

አምባሬ ነሽ ማጌጫዬ

ቀለሜነሽ መለያዬ

አክሱማዊት ኢትዮጵያዬ

<u>ወንድና ሴት አቀንቃኞች (በህብረት)</u>

መፈጠሪያ መብቀያችን

መደገፊያ ምርኩዛችን

የዘር ሀረግ ቋጠሯችን

አክሱማዊት ኢናታችን . . .

(ገቢ.2 ፣ት፡1፣ 2)

ከስነፍቺ አንጻር ይህ ባህላዊ ዘፈን ጥንታዊት አክሱም እና ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ እና ሀበሻ ተነጣጥለው የማይታዩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው የሚል ትርጉም አለው፡፡ ከተምሳሌታዊ ቲዎሪ አንጻር "ሀበሻ" እና "አክሱማዊት" የሚሉት ቃላት ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይወክላሉ ፡፡ ከዚህ አንጻር ዘፈኑ አክሱም ለአበሾቹ ኢትዮጵያውያን ጥንተ መሰረት ናት የሚል መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

ከተግባር ቲዎሪ አኳያ ይህ ባህላዊ ዘፈን ማንነትን የመግለጽና ታሪክን የማስተላለፍ ሚና አለዉ፡፡

2. **ማን እንበልህ**

   ምን እንበልህ

   የጀግኖች ጀግና፣ ማን ብለን እንጥራህ?

   እስከ ባህር ማዶ፣ ግዛት ታሰፋለህ

   ሰላምና ሰርዓት፣ በአገር ታሰፍናለህ

   አንተ ዳግማዊ ካሌብ፣ ስምህን ማን እንበልህ?

   ማን እንበል?

   ምን እንበልህ?

(ት፡2፣28)

በተራ ቁጥር 2. ላይ የቀረበዉ ይህ ባህላዊ ዘፈን ከ ሁኔታዊ አዉድና የፎክሎር ዳይክሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ፣ በ6ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሰ-ነገስት የነበሩት አፄ ካሌብ ቀይ ባህርን ተሻግረው በሰሜን እስከ ኑቢያ (የአሁኗ የመን)፣ በደቡብ እስከ ሳውዲአረቢያ ማስገበር (መግዛት) እንደቻሉ ሁሉ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ባለታሪክ የሆነው ካሳም (በኋላ አፄ ቴዎድሮስ) የኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ግዛቷን ያሰፋል የሚል ጥቁምት አለው፡፡

ከተግባር ቲዎሪ አንፃር ደግሞ ዘፈኑ የጀግናን ታሪክ እያወሳ ያወድሳል፡፡ እንዲሁም አንድ ትዉልድ ከሌላዉ ጀግንነትን መውረስ፣ ለሀገር ጥቅም መቆምን መማር እንዳለበት ይገልጻል፡፡

4.4.1.3 ቀረርቶና ፉከራን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

1. ኧረ የወንድ ያለህ! . . .
   ኧረ የሰው! . . .
   ኧረ ያገር ያለህ ይላል የጨነቀው
   በአገር ተቀምጠ፣ . . .
   የገዛ ሀገሩ፣ መሬቱ እየራቀው! . . .
   (ገቢ 2.፣ትዕ. 1፣4)

2. ወይ አገሬ! . . . ኧረ አገሬ! . . .
   ወይ አገሬ! ጋይንት፣ አገሬ ፎገራ
   ወልቃይት ጠገዴ፣ ሰሜን፣ ጃናሞራ!
   ኧረ አገሬ! . . .
   አገሬ በለሳ፣ ቋራና ደንበያ
   ደብረ ታቦር፣ ጎንደር፣ አገሬ ኢትዮጵያ
   ተለያየንና . . .
   ተጠፋፋንና . . .
   እኛም ቀረን ወዲህ፣ አንቺም ቀረሽ ወዲያ
   (ገቢ.2፣ ትዕ. 1፣5)

የእነዚህን ሁለት ቀረርቶዎች ይዘት ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የካሳን አነሳስ ያሳያሉ፡፡ ፀሀፌ-ተዉኔቱ በተዉኔቱ ዉስጥ ቀረርቶዉ የሚከወንበትን አውድ ሲገልጽ፣ “ በዚህ ጊዜ ከመድረክ በስተቀኝ ጥግ የሚነድ እሳት ፈካ ማለት ይጀምራል፡፡ እየቆየ እሳቱ እየደመቀ ሲሄድ፣ በእሳቱ ዙሪያ ያሉ ሽፍቶች በወጋገኑ መታየት ይጀምራሉ፡፡ ሶስቱ (ካሳ፣ ገብርዬ እና ገልሞ) ተቀምጠው፣ አራተኛው (አለሜ) እየተንጎራደደ ቀረርቶውን ይቀጥላል” ይላል (ትዕ.1፣5)፡፡ ይህ ማለት ደግሞ፣ ከ ክዋኔ ቲዎሪ አኳያ፣ ቀረርቶው ከዋኙን (አለሜን)፣ የአከዋወኑን ሁኔታ (አለሜ እየተንጎራደደ የሚያቅራራዉ)፣ ተሳታፊዎችን (እነ ካሳን)፣ እና ቀርቶዉ ሲከወን በአካባቢዉ የነበረውን ድባብ (የሚነደው እሳት) እነዚህን ሁሉ አካቶ ይዟል ማለት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለውም ክዋኔ የስነ ቃል ዋና ጉዳይ መሆኑን ነዉ፡፡

ከተግባር ቲዎሪ አንጻር ሲታይ ደግሞ ስነ-ቃል ህዝቦች ህዘን ደስታቸውን፣ ምኞት ተስፋቸውን፣ ፍቅር ጥላቻቸውን፣ ድል ሽንፈታቸውን፣ ድጋፍ ተቃውሟቸውን የሚያንፀባርቁበት እንደመሆኑ፣ ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱት ቀረርቶዎችም ብሶት እና ተቃውሞን የመግለጽ ተግባር አላቸዉ ፡፡

3. **ገብርዬን የሚያህል ብርቱ ጦር ጨብጠህ**
   አለሜን የሚያህል ስል ጎራዴ ታጥቀህ
   ተዋበችን ያህል ጋሻ ተመርኩዘህ
   ተነስ እንጂ ታጠቅ ምን ትጠብቃለህ?

   (ገቢ. 2፣ትዕ.2፣ 26)

4. **አለሜ እሳቱ!**
   አለሜ እሳቱ!
   መገፋት ሞቱ ጥቃት ሬቱ!
   ልበ ተራራ አለሜ ኩሩ!
   እንኳን ሊወጉ ሳይሰነዝሩ
   ንግስት ማራኪ ጭሮ በጦሩ
   የካሳ ወንድም አለሜ ነበሩ፡፡

   (ገቢ. 2፣ትዕ. 2 ፣26)

በተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ቀረርቶ ይዘት ከሁኔታዊ አውድ አንጻር ካሳ በራስ አለ እናት እቴጌ መነን ሊበን ላይ ጦር እንዲያዘምት ያነሳሳል፡፡ የገብርዬን እና የአለሜን ጀብደኝነት፣ የሚስቱን የተዋበችን የኋላ ደጀንነት፣ በመጥቀስ የካሳን ወኔ ይቀሰቅሳል ፡፡ ይህም ስነ ቃል አንድን ማህበረሰብ (ወይም ግለሰብ ሊሆን ይችላል) ለአንድ ለተወሰነ ዓላማ በማነሳሳት ረገድ ያለውን ሚና ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር 4 ላይ ያለው ፉከራ በተራ ቁጥር 3 የቀረበውን ቀረርቶ ተከትሎ የሚመጣ ነው፡ አለሜ ቀረርቶው በፈጠረበት ልዩ ስሜት ተነሳስቶ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ይፎክራል፡፡ ይህም ከፎክሎር ዳይክሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ አንጻር ሲታይ የስነ-ቃሎችን ተለጣጣቂነትና ስምረት ያሳያል፡፡

ከተግባር ቲዎሪ አኳያ የፉከራው ፉይዳ ከቀረርቶው ብዙ የተለየ አይደለም፡፡ ከዚህ ላይ የሚታየው ዋናው ልዩነት ፉከራው ከቀረርቶው በበለጠ የማነሳሳትና የማደፋፈር ኃይል ያለው መሆኑ በቻ ነው፡፡

4.4.1.4 የእረኛ ዘፈኖችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፍይዳ ትንተና

1. ወንድ እረኛ፡ - ከቋራ ምድጃ፣ . . .የተጫረች እሳት

ሴት እረኛ፡ - እንኳን እፍ ብለው ፣...እንኳን ቆስቁሰዋት

ወንድ እረኛ፡ - ታልጋ ትወጣለች ፣ ..ለመደብ ሲንቋት፡፡

ሴት እረኛ፡ - እታታ አትጠግብ ፣...እንዳጠፋች አውቃ

ወንድ እረኛ፡ - የጌታ ሀይሉን ዘር በቅምባ ደብቃ

ሴት እረኛ፡ - ካሳ አቆይታለች ለአገር የሚበቃ፡፡

ወንድ እረኛ፡ - የምጥዋ አሻቦ ሳይነሰነስ

ሴት እረኛ፡ - ሰርዶ አልግጥም አለ የካሳ ፈረስ ፡፡

(ገበ. 3፣ትዕ. 1፣16)

ከላይ ቀረበውን የእረኛ ዘፈን ይዘትና ፋይዳ በብዙ መልኩ ተንትኖ ማየት ይቻላል፡፡ **“ከቋራ ምድጃ የተጫረች እሳት”** የሚለው፣ ቋራ በቴዎድሮስ ሕይወት ውስጥ የነበራትን አስተዋፅኦ ያሳያል፡፡ “ቋራ ለቴዎድሮስ የስልጣኑ መቆናጠጫና የዘመኑ ፖለቲካ መለማመጃ ትምህርት ነበረች” እንዳለዉ (ባህሩ፣ 2007፣ 28)፣ ቋራ ከልጅነት እስከ ዕውቀት በካሳ ሕይወት ዉስጥ ትልቅ ስፍራ ነበራት ፡፡ በቋራ አድጓል፤ በቋራ ተምሮአል፤በቋራ ሽፈፍቶአል፤ በቋራ የወደፊት ስልጣኑን አደላድሏል፡፡

“እንኳን እፍ ብለው እንኳን ቆስቁሰዋት” ካሳ በእቴጌ መነን ላይ የሸፈተበትን ሁኔታ ይገልጻል፡፡ እቴጌ መነን ምንም እንኳ የልጃቸውን የራስ አሊን ልጅ ተዋበችን ለካሳ ቢድሩለትም ዓላማው የካሳን የስልጣን ሩጫ በጋብቻ አስሮ ለማቆም የታቀደ ብቻ በመሆኑ ለእሱ ቅንጣት ታህል ክብር አልነበራቸውም፡፡ ይልቁንም፣ በአንፃሩ፣ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ንቀታቸውን ይገልጹለት እንደነበር ይነገራል፡፡ “. . . ለአንድ ፍየል ጠባቂ እረኛ፣ አንድ ብልት ስጋ አነሰው በለኛ፣ . . . ይልቅ ያ ኮሶ የለመደ አንጀቱ ላይ ታች እያለ እንዳያውከው መጀመሪያ ተልባ ፈልጎ ሆዱን ያውሣው” (ሙሉቀን፣ 2008፣ 8፣ ጳውሎስ፣ 1994፣ 24) በማለት ካሳን መሳደብና መዝለፋቸውም ለዚህ ይመስላል፡፡ **“እታታ አትጠገብ እንዳጠፋች አውቃ . . .”** የሚለው የካሳ እናት (አትጠገብ) ልጇን የወለደችው ከአባቱ ራስ ሀይሉ ጋር በድብቅ ተገናኝታ ነው እየተባለ የሚነገረውን አፈ-ታሪክ ለመግለጽ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ **“የጌታ ኃይሉን ዘር በቅምባ ደብቃ . . .”** የሚለው አትጠገብ ካሳን በህፃንነቱ ቋራ ለሚገኙት ታላቅ ወንድሙ ደጃች ክንፉ ወስዳ መስጠቷን እና ካሳም ያደገው ደጃች ክንፉ ቤት መሆኑን ያመለክታል፡፡

“ታልጋ ትወጣለች ለመደብ ሲንቋት” የሚለው የካሳን ንጉሰ ነገስት መሆን አይቀሬነት ያመለክታል፡፡ ስነ ቃል አንድ ማህበረሰብ ያለፈውን ታሪክ የሚዘክርበት ወደፊት ይመጣል ብሎ የሚያስበውን የሚተነብይበት ሀብቱ እንደመሆኑ ይህ አባባል በኋላ በተግባር የሆነውን የአፄ ቴዎድሮስ ንግስና አስቀድሞ ይተነብይልናል፡፡

“የምጥዋ አሻቦ ሳይነሰነስ፣ ሰርዶ አልግጥም አለ የካሳ ፈረስ” የሚለው አፄ ቴዎድሮስ በንግስና ዘመኑ የምዕዋን ወደብ ከግብፆች) ለማስለቀቅ የነበረውን እልህ ያመለክታል፡፡

በስተመጨረሻም በዚህ ተውኔት ውስጥ የተነሱትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ አጠቃሎ ባጭሩ ለመግለጽ ያህል፣ ማንነትን ከማሳወቅ፣ ታሪክን ከማቆየትና ከማስተላለፍ እንዲሁም ከግለሰብ ከማህበረሰብና ከሀገር ዕድገትና ለውጥ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

4.5. የቃቄ ወርዶወት[58]

የቃቄ ውርዶወት የዛሬ አንድ መቶ ሃምሳ ዓመት አካባቢ (በ1850ዎቹ) ማለትም በአፄ ቴዎድሮስ የንግስና ዘመን (1845-1860 ዓ.ም) በጉራጌ ህብረተሰብ መካከል የሴቶች በደል ቆርቁሯት የተነሳች ሴት ናት፡፡ በቀድሞው የጉራጌ ህብረተሰብ የስም አጠራር ከታዋቂ (የሚከበር) አባት የተወለደ ልጅ የአባቱ ስም ቀድሞ የልጁ ተከትሎ የመጥራት ባህል መሰረት ውርዶወት የሚለው ስሟ ከአባቷ ከቃቄ ስም ቀጥሎ ነውና የሚጠራው የቃቄ ውርዶወት በመባል ትታወቃለች፡፡ ወርዶዎት እጅግ ሐብታም ከሆነ ቤተሰብ ትወለዳለች ፡፡በጉራጌ፣ በምሑርና አክሊል ወረዳ፣ ቆረር ቀበሌ፣ ዠርመኘ ተብሎ በሚጠራው መንደር በሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች፣ ሰፊ የእንሰት ተክል፣ በጣም ሰፊ ቦታን የያዘ መሬት ያላቸውና በምሑር ቤቴ-ጉራጌ አንቱ የተባሉ ባላባትና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ከሆኑት ዳሞ ቃቄ ወራቦ እና በጥብቅ የእስልምና እምነት ተከታይነታቸው ከሚታወቁት የወለኔ ቤተ-ጉራጌ ተወላጅ ከሆኑት አጅየት አሚና ትወለዳለች፡፡ የመጨረሻ (አራተኛዋ) ልጅ የሆነችው ውርዶወት ከመጀመሪያው (የበኩር ልጅ ከሆነው) ሴራሞ እና ከሁለት ታላላቅ እህቶቿ (ኮርወት እና ፎርወት) በላይ በቤተሰቦቿ ዘንድ ተወዳጅና የልጅነት ዘመኗን አክብሮትና አድናቆት እየተቸረች ያደገች መሆኑ በሰፊው ይነገራል-እልኸኛነቷም፡፡ ሰዎች ቁንጅናዋን ሲመሰክሩ “ተወዳዳሪ የማይገኝላት የውበት ዳርቻ እሷ ብቅ ስትል አካባቢው የሚደምቅ ውብ ብርሃን የቆንጆዎች ቁንጮ” ይሏታል፡፡

[58] **ይህ ቴአትር በእዉነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰርቶ የተጻፈ መሆኑን ይገነዘቧል፡፡**

ቃቄ ውርዶወት ከሁሉ በላይ ጀግንነትን በጣም ትወደዋለች ፣ዝናን ትናፍቀዋለች፡፡ በኋላም ይህቺ ውብ ጀግንነት ወዳድ ልጃገረድ ለታዋቂው የእጣ ጀግና ለአጋዝ (አበጋዝ) ፋርችየ ላምቢየ ትዳራለች፡፡ የጀግና ገድል ልቧን ትርክክ የሚያደርገው ውርዶ በመጀመሪያ ለአጋዝ ፋርችየ መዳሯ አላስከፋትም፡፡ እንዲያውም የጀግናውን ክንድ ተንተርሳ፣ በእቅፉ ውስጥ ሆና ዝናውን ለመስማት የዓመታት ምኞቷ ስለነበረ ስመጥር ከሆነው ፋርችየ ላምቢየ ጋር ትዳር መመሥረቷን ወዳዋለች፡፡ ነገር ግን ያላሰበችው የቅሬታ ስሜት ቀስ እያለ ይነተርካት ጀምር፡፡ ለካስ ይኼ ጀግና የአንዲት ሴት ብቻ ባል አልነበረም፡፡ በአብዛኛው የቤተ-ጉራጌ የጋብቻ ልማድ መሠረት ሌሎችም ሚስቶች አሉት፡፡ ታዲያ እስዋም ከሌሎቹ ሴቶች ጋር ጀግናዋን መጋራት አልሆን አላት፣ የፍቅር ስሜትዋን አቀዘቀዘባት፡፡ ብቻዋን በምታድርባቸው ሌሊቶች ሴት ሆኖ መፈጠርዋን ከወንዶች መረን ያለፈ ነፃነት ጋር ስታብላላው ስሜትዋ እንቢ ብሎ ይሸፍትባት ጀመር፡፡ ከልጅነትዋ ጀምሮ በደልን የማትቀበለው ውርዶወት ይሄን ጉዳይ በየዕለቱ ታብሰለስል ገባች፡፡ ወንዶችን ስትታዘብ ቀን ቀን በጀፎረ /በቤተ ጉራጌ አውራ መንገዶች ላይ በሚኙ ዋርካዎች/ ሥር ሆነው በገበጣና በተለያዩ ጨዋታዎች እየተዝናኑ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ የፊለጋቸውን ያህል ሴት ያገባሉ - ንብረታቸው (ሐብታቸው) ሚፈቅደውን ያህል፡፡ እዚህ ላይ “ለምን” አለች ውርዶወት፡፡ ንብረት እንደሆነ የፊለገችውን መጠን ያህል ሊሠጣት የሚችል ሃብታም አባት አላት፡፡ ታዲያ እንደወንዶቹ የሐብትዋ መጠን የሚፈቅድላትን ያህል ባል ባታገኝ እንዴት አንዱን እንኳን በወጉ የራሷ ብቻ ማድረግ ይሳናታል?

ቀኖች እያለፉ ወሮች እየተደጋገሙ ሲሄዱ ውርዶወት ይኸን ጉዳይ ለሴቶች ለማማከር ተነሳች፡፡ እናም እንዲህ አለቻቸው፡፡ “እኛ በቤት ውስጥ እንለፋለን፣ እንደክማለን፡፡ ወንዶቹ እንደልብ የመዝናኛ ጊዜ አላቸው፡፡ ታዲያ ይኸን ዝም ብንላቸው ለምን ሁለት፣ ሶስት፣ አራት ያገባሉ? በአንድ ሚስት ተወሰኑ እንበላቸው፡፡ እንቢ ካሉ ለእኛም ከአንድ በላይ ባል ማግባት ይፈቀድልን” አለች በጀፎረ የሴቶችን መሰብሰብ የሚከለክለውን ባህላዊ ህግ ለመጀመሪያ ጊዜ አፍርሳ፡፡ በመጀመሪያ ተሰሚነት ያላቸውን የባላባት ሚስቶችን በመሰብሰብ ጉዳዩን ጀመረች፡፡ ሴቶቹም አዲስና የሚነቀንቅ ሃሳብ ስላገኙ ደገፏት፡፡ ሰብሰባው ሲደጋገም የአካባቢው

ሴቶች መገናኘት ጀመሩ። ሃሣቦችም እየዳበሩ መሄድ ቀጠሉ። እዚህ ላይ ወንዶች ግራ መጋባት ጀመሩ። ተገረሙም። ሴት በጀፎረ እንድትሰበሰብ ቀርቶ በስብሰባው ላይ እንድትቆም እንኳን የተወገዘ ነውር ነው። እነዚህ ሴቶች ግን ይሽን ነውር መደጋገም ያዙ። ስለዚህ ወንዶች ተሰባሰቡና ሰብሳቢያቸውን ጀግናውን ፋርችየን "ምንድነው ይሽ ጉዳይ?" አሉት። ጀግናው ፋርችየ እዚህ ላይ ፈተና ገጠመው። የሚወዳትን ያቺን እልሽኛ ውብ ሚስቱንና ሌሎች የባላባት ሚስቶችን ጨምሮ የአካባቢውን ሴቶች ሁሉ መከራከር አልፈለገም። በእርጋታ ለወደፊቱ የሚታይ ጉዳይ ይሆናል። አገር ከተስማማበትም የሚበጀውን ይወስናል። "እሺ ለጊዜው ይሁን። ግን አሁን ምንድነው ጉዳያችሁ?" አላቸው። ጉዳያቸውን በዝርዝር ነገሩት። "ዋናውና የመጀመሪያው - እናንት ወንዶች ብዙ የመዝናኛ ጊዜ አላችሁ። እኛ የልጅን፣ የማድቤትን ጉዳይ ለማቃናት ደፋ ቀና እያልን በሥራ ስንባትል እንውላለን፣ እናመሻለን። ነገር ግን እናንተ በአንዲት ሴት ላይ ሌሎች ብዙ ሚስቶች ታገባላችሁ። ስለዚህ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ብቻ ባል ይሁን፣ ትብቃው። አይሆንም ካላችሁ እኛም ሴቶች ከአንድ በላይ ወንድ እንድናጋባ ይፈቀድልን። ሁለተኛ - አንዲት ሴት በባልዋ በደል ሲደርስባት ፍቺ ለማስፈፀም እጅግ ብዙ ልፋት አለባት። እንዲያውም ይሄን ልፋት አልፋ ማስፈጸም ስለማትችል ምንም በደል ቢበዛባት ችላ ነው የምትቀመጠው። ምክንያቱም መጨረሻ እራሱ ባልየው እሺ እፈታለሁ ብሎ ካልተስማማ ፍቺ አይፈጸምም። ስለዚህ ሴት ልጅ በቃኝ፣ ፍታኝ ስትል ባሏ እንዲፈታት ፍቺ በሚስት ጥያቄና ውሳኔ እንዲፈጸም ይደረግ። "ሶስተኛ - ሴቶችም ጉዳይ ሲገጥማቸው በጀፎረ መሰብሰብ ይገባቸዋልና መከልከሉ እንዲቆም" ወዘተ ...። ጀግናው ፋርችየ ይሽን ሚገርም እንግዳ ሃሳብ ይዞ ወደ ወንዶች ሸንጎ ይመለሳል። ሴቶቹ እየተበራከቱ ሲሄዱ ጉዳዩ የባሰ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷልና መከሩበት። በተለይም "አንድ ወንድ አንዲት ሚስት ብቻ ትብቃው" የሚለው እጅግ ከባድ አስቸጋሪና የያንዳንዱን ቤት የሚያናጋ ነጥብ ሆነ። ንብረት ኖሮት ሁለትና ሶስት ሚስት ያላገባ የለም። ከየሴቶቹም ወልዷል። ታዲያ የትኛዋን ሊፈታ ነው? ከየሴቶቹ የተወለዱት ልጆችስ ጉዳይ? ደግሞም ፍቺ በሴት ጥያቄ ብቻ የሚፈፀም ከሆነ ያ ሁሉ እንደልቡ መኖር የለመደ ወንድ ሚስቱ 'ሥራ በዛብኝ፣ በደል ተዋለብኝ ' እያለች እየፈታችው ብትሄድ ምን ሊውጠው ነው ማድቤት ገብቶ ቆሎ ሊጋግር?

አሁን የሴቶች ህብረት እየተጠናከረ ስለሄደ በጉልበት ወይም በሃይል ጉዳዩን ለመጨረስ እምብዛም የሚያስኬድ መስሎ አልታየም፡፡ ጥያቄው እየተስፋፋ ሄዶ በርካታ የሰባት ቤት ጉራጌ ሴቶች ተካፋይ ሆነውበታል፡፡ ወንድ በአንድ ሚስት ይወሰን የሚለው ጥያቄ ፈፅሞ የማይቻል መሆኑ በወንዶች ጉባዔ ተበይኖበታል የስንቱን ቤት ሚያፈርስ ነውና፡፡ ለሴቶችም ከአንድ በላይ ባል ይፈቀድ የሚለው ጥያቄም አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡‘ አንዲት ሴት ሶስት አራት ባል ብታገባና ልጅ ብትወልድ የልጁ አባት ማነው ሊባል ነው? ስለዚህ ልጅን ያለ አባት የሚያስቀር አደጋ ነው’ ተባለ፡፡ ቤተ - ጉራጌ አንድ ችግር ሲገጥመው ጉዳዩን በጋራ ለመፍታት ምክክር ማድረግ የተለመደ፣ እስከአሁንም ድረስ በጠንካራ የአደረጃጀት ሰንሰለት የተዋቀረ ባህላዊ ምክር ቤት ያለው ህብተሰብ ነው፡፡ የአካባቢው ሽማግሌዎች ጉዳዩን አይተው መፍታት ካቃታቸው ከፍ ላለው የጎሣ ጠቅላላ ጉባዔ፣ እዛም ካልተፈታ የኩታገጠም ጎሣዎች ጉባዔ፣ በዚያም ማለቅ ካልቻለ የጠቅላላው ቤተ - ጉራጌ ሸንጎ የእጅካ ሸንጎ የሚሰኝ ምክርና ውሳኔ ሰጪ ባህላዊ ምክር ቤት አላቸው፡፡ በወርዶወት የሚመራው የሴቶች ህብረት ከሰባት በላይ ግዙፍ የሚባሉ ዖታዊ ተጽዕኖን የሚያፈራርሱና የሴትን ልጅ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የትዳር (የቤተሰብ) ስር ነቀል ጥያቄዎችን በማንሳት በተለይም በዋናነት አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ብቻ ባል መሆንን የሚጠይቅ ፈተና ይዞ የዛሬ አንድ መቶ ሃምሳ ዓመት አካባቢ እነዚህን ጉባዔዎች ደረጃ በደረጃ እየተሻገረ ወደጠቅላላው የቤተ - ጉራጌ ሸንጎ ደረሰ፡፡

በበሳል አባቶች የሚመራው፣ መላና ፍትህ በእጁ ነው የሚባልለት ታላቁ የእጅካ ሸንጎ ይኼ ፈተና ሲገጥመው ከፍተኛ አድናቆትም፣ የአደጋ ስጋትም ስላደረበት ትልቅ ጥንቃቄና ምክር አደረገ፡፡ ይሄን ፈታኝ እንቆቅልሽ ለመፍታት ከሁለት ሶስት ጊዜ በላይ ቀጠሮ እየተሰጠ መፍትሔ ታሰሰ፡፡ አንዳች መላ ማግኘት ግን አልተቻለም፡፡ የሴቶቹ ጥያቄ ተጋግሎ ውሳኔ የሚሰጥበት “ቁርጥ ቀን ይሰጠን” ብለው ስላስቸገሩ ለውሳኔ የቀጠሮ ቀን ተያዘላቸው፡፡ በመሐለ ምሑር ወዳሉት ወደ አባቷ ወደ ዳሞ ቃቄ የአገር ሽማግሌዎችና የሐይማኖት አባቶች የአደራ ትልቅ መልእክት ተላከ ፡፡ ነገር ግን ውርደወትን መክረው ከዚህ አመፅ እንድትወጣ ይመክሩና ይማፀኑ ዘንድ የተደረገው ጥረት በወርዶወት እንቢታ ከሸፈ፡፡

የእጆካ ሽንጎ አደጋ አንጥበበት፡፡ ከቀጠሮው ቀን በፊት የጉዳዩ መሪ የሆኑትን ሴቶች በግል ድርድርና ሽምግልና በመደለል ጉዳዩን እንዲተውት ለማድረግ ተሞከረ፡፡ አልተቻለም፡፡ በተለይ የሴቶቹን ስሜት እንደ እሣት የሚያንገበግበውን የውርዶን አንደበት መግታት አልተቻለም፡፡ ክርክሩንም የሚያሸንፍ ሃሳብ ለማቅረብ የሚቻል አልሆነም፡፡ ጥያቄዋ እንኳን ሴቶችን ወንዶችን ማርኮአል፡፡ ደግሞም የውርዶወት እልህ ከፍተኛ ስለሆነ ሞት ይመጣል እንጂ የምትመራውን ትግል ትታ ወይም ከድታ ለመውጣት የማይታሰብ ነው፡፡

የእጆካ ሽንጎ በዝግ መከረ፡፡ በመጨረሻም ብልህና መለኛነታቸው በድፍን ሰባት ቤት ጉራጌ የሚታወቁት የመቆርቆር ቤተ-ጉራጌ ባላባት የነበሩት ባሼ ኤጋኖ “የዚህ እድማ አስተባባሪ ውርዶወት ስለሆነች እርስዋን መነጠል የሚቻልበት ዘዴ ይፈለግ፣ እስዋን መነጠል ከተቻለ ሌሎቹን ለማሸነፍ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ለእርስዋ ብቻ አንቂት ይነሳላት” በማለት ምክር አቀረቡ፡፡ ግማሾቹ ተቀበሉት ግሚሶቹ ደግሞ ጀግናው ፋርችየን በማክበርና በመፍራት “እንዴት ይሆናል?” በማለት ስጋታቸውን ገለፁ፡፡ በመጨረሻም “አጋዝ ፋርችየን እንጥራውና ከእሱው ጋር እንምከር፣ እሱኑ እንለምነው ” ብለው ተስማሙ፡፡

አጋዝ ፋርችየን ሸንጎው በዝግ ስብሰባ ጠርቶ ‘ይሄን የጉራጌ ሴቶች አመፅ ለማስቆም እንችል ዘንድ ለውርዶወት አንቂት ማንሳት ግድ ሆኖ አግኝተነዋልና እባክህ የኛን የሽማግሌዎችን ቃል ስማ፣ አንቂቱን አንሳላት፡፡’ አሉት፡፡

“እኔስ?” አለ ፋርችየ፡፡ “ከአገር ተለይቼ ለምን ሚስቴን አጣለሁ?” ‘በኛ ይሁንብህ እሺ በለን፡፡ አንተ ተስማማና አንቂት አንሳላት፡፡ ከዚያም እንደገና ያንተው ሚስት እንድትሆን እንለምናታለን፡፡ እሷም ብትሆን ከኛ ከሽማግሌዎች ቃል አትወጣም፡፡ እንለምናለታለን-እሺ እናሰኛታለን፡፡ አንተ ብቻ ተስማማና እሺ በለን፡፡ ያለበለዚያ የዚህን ሁሉ ሴት አመፅ ማቆም አይቻለንም፡፡ ደግሞም የአገሬው ሁሉ ቤት ከሚፈርስ የአንድ ሰው ሚስት ፍቺ ይቀላል፡፡ አንተም ታላቅ ጀግናችን ነህ፡፡ ከዚህም በፊት ጠላት በመጣ ቁጥር ስታስከብረን የኖርክ መመኪያችን ነህ፡፡ አላሳፈርከንም፡፡ አሁንም አታሳፍረን፡፡ እሺ በለንና እንመርቅህ” አሉትና ተነስተው ቆሙ፡፡ እሺ ካላለ ላይቀመጡ፡፡ በመጨረሻም ጀግናው ፋርችየ ለአገር ሽማግሌዎች ተሸነፈ፡፡ “እሺ አባቶቼ፣ ከቃላችሁ አልወጣም” አለ፡፡ ምርቃት ጎረፈለት፡፡

ከእምድብር ከተማ አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ በምትገኘው ሞጨ በምትባለዋ ስፍራ የተሰበሰበው የእጆካ ሸንጎ እፎይ አለ፡፡ እርግጥ ውርዶወትን በተደጋጋሚ ይሄን ጉዳይ እንድትተው ለምነዋት አሻፈረኝ በማለቷ አሁንም ፉርችየ ከፈታት በኋላ ተመልሳ ሚስት እንድትሆነው ቢለምኗት አሻፈረኝ ልትል እንደምትችል ጠርጥረዋል፡፡ ቢሆንም መጀመሪያ ይሄን የብዙ ሴቶች አመፅ ካስቆሙ በኋላ በግለሰብ ጉዳይ መምከሩ የተሻለ እንደሚሆን ተረድተዋል፡፡

በመቀጠል ሸንጎው ወንዶችን ብቻ ጠርቶ ሚስጥራዊ ምክክርና ውሳኔ አስተላለፈ፡፡ የመጨረሻው የሴቶቹ ጉዳይ የሚቆረጥበት ቀን ታውቋል፡፡ ስለዚህ በዕለቱ እያንዳንዱ ወንድ ሚስቱን በተቻለው ሁሉ አባብሎ ጉቦም ሰጥቶ ቢሆን እንዲያስቀር ተወሰነ፡፡ ውሳኔው ሙሉ ስምምነት አገኘ፡፡

የጉራጌ ባል በዛች ሰሞን ለሚስቶቹ ፈቃድ ትህትናውን አሳየ፡፡ ስብሰባው አንድ ቀን ሲቀረው ደግሞ ሁሉም በየፊናው በነጋታው ማለትም በውሳኔው ዕለት እቤት እንዲውሉ ማባበያ እየሰጠ ይለምን ገባ፡፡ የእንሰት ተክሎች፣ ላሞች፣ በግና ፍየሎች በጉቦነት ለሚስቶች ሽልማት እየተባሉ ተሰጡ፡፡ አንዳንዶቹ ሴቶች ተሰማሙ፡፡ ነገም ሌላ ቀን ነው፡፡ ስብሰባው ሌላም ጊዜ መቀጠል ይችላል በሚል ሃሳብና እንቢ ቢሉ ሊገጥማቸው የሚችለውን ዱላ በመፍራት፡፡ እንቢ ያሉት ሴቶች ግን ሌሊቱን ሲገረፉ አደሩ - ተዛተባቸው፡፡ 'አስቲ ከዚች ደጅ ዝር ትይና! በምን እግሬን ተሰበርኩ እንዳትይ! እውነትም እኔ ወንድ አይደለሁማ!' ተባሉ፡፡

የውሳኔው ዕለት ጠዋት የእጆካ ሽማግሌዎች ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይጠብቃሉ፡፡ ውርዶወት በበቅሎዋ ሆና ከጃንጥላዋ ሥር በድል አድራጊነት ስሜት እንደፀሐይ ደሞቃ እያበራች ከተፍ አለች፡፡ ነገር ግን ባለጉዳዮች እንዲቀርቡ ቢጠበቅ ብቅ የምትል አንዲት ሴት ሳትኖር ቀረች፡፡ የቀጠሮው ሰዓት ማለፍ ጀመረ፡፡ ውርዶ ተናደደች፡፡ እንደዚህ ከተማማሉት ሴቶች መካከል እንዴት አንዲ እንኳን ሳትመጣ ትቀራለች? በቅሎዋን እያሰገረች በአራቱም አቅጣጫ ኩረብታ ላይ እየወጣች ብትመለከት ብቅ ያለች አንዲትም ሴት የለችም፡፡

"እህሳ ውርዶወት ምን ተሻለ" አልዋት ሽማግሌዎች፡፡

“እንዴት ምን ተሻለ? በኸጆካ ቂጫ መሰረት ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጥ እንጂ” አለች ተበሳጭታ።

“አይሆንም። በተደጋጋሚ ይሄ ሽንጎ በዚሁ ጉዳይ ላይ ተሰብስቧል። ዛሬ የቁርጥ ቀን መሆኑንም ቀደም ብለን ለሴቶቹ በሙሉ ገልፀናል። እንደምታይው ሴቶቹ ሁሉ ትዳራቸውን መርጠዋል። ማንም ጥያቄውን የሚያቀርብ ሴት የለም። ስለዚህ ውሳኔውን ልንሰጥ ነው።” አሏት።

“እኔ ቀርቤአለሁ።”

“ብቻሽን አንቺ ተለይተሽ?”

“አዎን፣ ብቻዬን ለውሳኔ ቀርቤአለሁ።”

“እንግዲያው ለሁለተኛ ይኼንን ጉዳይ አንመለከተውም፤ አንቺም ከዛሬ ጀምሮ ሌሎቹን ሴቶች ማነሳሳት እንድታቆሚ። ሴቶቹ በጊዜያዊ ሆያ ሆዬ ነው እንጂ ነገሩን ውለው አድረው በእርጋታ ሲያዩት እንደማይበጃቸው ውስጥ ለውስጥ ተማክረው ነው እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሱት። ስለዚህ ሁለተኛ የሌሎቹን ሴቶች ትዳር ላትበጠብጪ ቃል ግቢልን።” አሏት።

“ለኔስ አበቱታ ምን መልስ አላችሁ?”

“ለየቱ? የግልሽ ጥያቄ ነው?”

“አዎን - አንቂት ይነሳልኝ፤ በራሴ ፈቃድ ይሁን ትዳር መያዝና መፍታት የምወስነው - ይሄን ወስኑልኝ።”

“ወስነናል። አንቂት አይኑርብሽ። የፈቀድሽውን አግቢ! በፈቀድሽ ጊዜ ፍቺ! መርቀናል። በሌላ ቤት ግን አትግቢ።” አሏት ሽማግሌዎች።

“እሺ። በሌላው ጉዳይ አልገባም” ብላ ተሰናበተች። ስትመራው የነበረውና ተቀጣጥሎ ጫፍ የደረሰው የተበደለ ፍትህ ጠያቂ ሴቶች ትግል በወንዶች ሴራ በሴቶች መፍረክረክና ከመድረኩ መገለል ስለከሸፈ ውርዶ በጣም አዘነች። በግልዋ ግን አግባብ ያልሆነው የወንዶችና ሴቶች የትዳር ግንኙነት አልቀበልም ብላ

አሸቀንጥራ ጣለችው፡፡ ከማህበረሰቡ ህግ ሸፈተች፡፡ ዝናዋ በመላው የጉራጌ ምድር አስተጋባ፡፡ እጅግ ቆንጆ አንደበተ ርቱዕዋ፣ ዶታዊ በደልን አልቀበልም ብላ የተነሳችው ቃቄ በህዝብ መሀከል ሸፈተች፡፡ ያያትን ሁሉ የምታማልል ቆንጆ ሸፍታ - ውርዶወት ቃቄ፡፡[59]

4.5.1. የቃቄ ወርዶወት ውስጥ የተነሱ ፎክሎረዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተወኔት ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ጀፎረን፣የእጅካ ባህላዊ ሽንጎን፣ አንቂትን፣ምርቃትን፣ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ባህላዊ የማዕረግ ስሞችን፣ ቄግ እና ባህላዊ ዘፈኖችን የተመለከቱ ናችዉ፡፡ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸዉን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

4.5.1.1 ጀፎረን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ጀፎረ የጉራጌ መገለጫ ከሆኑ የባህልና የቱሪስት መስህቦች ውስጥ በመጀመሪያው መስመር ላይ ይቀመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ጀፎረ ማለት ጥሬ ትርጉሙ በመንደርና በመንደር መካከል የሚገኝ ባህላዊ አዉራ ጐዳና ወይም የጋራ ባህላዊ አደባባይ ማለት እንደሆነ የዚህ ጥናት መረጃ ሰጪ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ጐይቴ ገልጸዋል፡፡[60] ባህላዊ የሚያስብሉትን ምክንየቶች ሲጠቅሱም-፡ “ጀፎረ በኢትዮጵያ ምድር ከጉራጌ ውጭ በየትኛውም ቦታ የማናገኘው ከዛሬ ሁለት መቶና ሶስት መቶ ዓመት በፊት ዘመናዊ ትምህርት ባልቀሰሙ የጉራጌ ጥንታዊ አባቶች የተሰራ፣ በግራም በቀኝም እንዳይነካ በ ጐርዳ[61] ተጠብቆ የሚኖር ነው፡፡” ይላሉ፡፡ በጀፎረ መሀል በበቀሉ ሰፋፊና ትላልቅ እድሜ ጠገብ ዝግባዎችና ዋርካዎች ስር ባህላዊ የእርቅና የዳኝነት ስርዓቶች፣ ሽምግልናዎችና ግልግሎች ይካሄዳሉ፡፡ በሠርግና በለቅሶ ወቅት የአካባቢዉ ማህበረሰብ ከጫካ ቅጠል ቆርጦ በማምጣትና ዳስ (ባህላዊ ድንኳን ወይም አዳራሽ) በመስራት ሠርግ ይደግሱበታል፣ ሀዘናቸዉን

---

[59] የታሪኩን ክፍል ሁለት በአባሪ ሶስት ይመለከቷል፡፡

[60] አቶ ተስይዬ ጐይቴ፣ የጉራጌ ባህልና ልማት ማህበር ዋና ዳይሬክተር (ቃለ መጠይቅ)፣ መስከረም፣ 2010 ዓ.ም፡፡

[61] ጐርዳ በጉራጌ መሐላ ወይም ቃል-ኪዳን ማለት ነው፡፡

ይወጡበታል፡፡ ከሩቅና ከቅርብ የሚመጡ እንግዶችም እንደዚሁ ይስተናገዱበታል፡፡ በተጨማሪም በጀፎር የመንደር ሠዎች ተሰብስበው ስለ አካባቢያቸው ጉዳይ በጋራ ይመክሩበታል፡፡ በተለያዩ የበዓላት ቀናት ባህላዊ የፊረስ ግልቢያ፣ ትግልና ይህን መሰል ክዋኔዎች ይካሄዱበታል ፡፡ ለዚህም ይመስላል በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ የተቀደሰ ስፍራ እንደሆነ የሚታመንበት፡፡ በጀፎረ ላይ ያልተገባ ድርጊት የፈፀመ አንድ ሰው ቤተሰቡ ላይ ችግርና መከራ ይደርስበታል እየተባለ ይነገራል ፡፡ ይሄን በመፍራትም ቀደም ሲል እንደተገለጸዉ ማንም ሰዉ ባህሉ ከሚፈቅደዉ ዉጭ ጀፎረን የመድፈር ወኔዉ የለዉም [62] ፡፡

በጉራጌ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎችና የገጠር ቀበሌዎች አሁንም ድረስ ባህላዊ ይዘታቸው ተጠብቆ ከሚገኙ ጥንታዊ ጀፎረዎች መካከል በዚህ የቃቄ ውርዶወት ተውኔት ውስጥ የምናገኘው የዴሰነ ጀፎረ ነው፡፡[63] ይሄ ጀፎረ ከመሪ ገፀ- ባህርይዋ ቃቄ ውርዶወት እና ተከታይዎቹዋ የጉራጌ ሴቶች የመብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ በተዉኔቱ ዉስጥ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይነሳል ፡፡ እነ ቃቄ ውርዶወት በወንዶች ይፈፅሙብናል ያሉዋቸውን በደሎችና በጓላም ለእጅካ ባህላዊ ሸንጎ/ፍርድ ቤት ያቀረቧቸውን የመብት ጥያቄዎች[64] አስመልክቶ በዴሰነ ጀፎረ በተደጋጋሚ እየተገናኙ መክረዋል፡፡

ቀስ በቀስም ከዚህ የዴስነ ጀፎረ የተነሳው የመብት ጥያቄ ድፍን ጉራጌን ሲያጥለቀልቅና በጊዜው የነበሩትን ወንዶችና የእጅካን ባህላዊ ሸንጎ/ፍርድ ቤት ሲያስጨንቀዉ እንደሚከተለዉ እንመለከተዋለን፡፡

---

[62] ጌታቸዉ ደቄ (ዶ/ር)፣(ቃል- መጠይቅ)፣ ምስከረም፣2010 ዓ.ም ፡፡

[63] ዴሰነ በጉራጌ ዞን፣ እጎ ወረዳ የሚገኝ የገጠር ቀበሌ ነው፡፡

[64] እነ ቃቄ ወርዶወት ያነሷቸዉ ዋናዋና የመብዕት ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

ሀ. አንድ አባወራ አንድ ሚስት ትብቃዉ፡፡

ለ. በሴቶች ላይ የተጣለዉ እርግማን (አንቂት) ይነሳልን፡፡

ሐ. ሴት ልጅ እንደ ወንድ ልጅ የአባቷን መሬት ትዉረስ፡፡

መ. ሴት ልጅ የመረጠችዉን ታግባ፡፡

አጋዝ ሲቆራ፡- እንግዲህ ልናገረው እንጂ... አባቶቼ፤ "በዶሮ ቅልጥም አፈር ይሰረሰራል" እንዳሉት አበው አሁን ሴቶች ይ በልጥ በርክተዋል፡፡ ምን ዴሰነና እሣ ብቻ በችሃ፣ በምሁር፣በጉመር ፣በአክሊል፣ በጌቶ፣ እንዳገኝ ድረስ ሁሉ ያሉ ሴቶች በየገበያው እየተገናኙ፣ በመልዕክተኛ እየተላላኩ፣ በየጆፎረው ሳይቀር እየተሰባሰቡ እየተማማሉ ነዉ፡፡

አባገዳ ጅባቦ፡- ምን... በጆፎረ?

አጋዝ ዳርሳሞ፡- ሴት በጀፎረ? ሴት ለሽምግልና? የሴት የሸንጐ መካሪ? የሸንጐ ዳኛ?

ባሼ ኤጋኖ፡- አጋዝ ዳርሳሞ ልክ ጠየቁ፡፡ ጀፎረ ከጥንት ከአባቶቻችን ጀምሮ የአገር ሽማግሌዎች የአገር ጉዳይ የሚመክሩበት የፈጣሪ ምህረትና በረከት የሚጠይቁበት የተከበረ ቅዱስ ቦታ ነው፡፡

አጋዝ ዳንቃሞ፡- ቀድሞ ነገር ሴት የጀፎረ መርገጥ እርኩሰት ነው! መርገምት ያመጣል! ሚስቶቻችንን እንዴት መያዝ ያቅተናል? ሴት በዴሰነ ጀፎረ?

(ገቢ 2፣ ትዕ. 1፣ 28-29)

ከላይ ከቀረበው ቃለ ተውኔት መረዳት የሚቻለው ሌላው ጉዳይ ጀፎረ በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ከጥንት ጀምሮ የክብርና የቅድስና ቦታ የነበረዉ መሆኑን ነው፡፡ የባሼ ኤጋኖ "... ጀፎረ ከጥንት ከአባቶቻችን ጀምሮ የአገር ሽማግሌዎች የአገር ጉዳይ የሚመክሩበት፣ የፈጣሪ ምህረትና በረከት የሚጠይቁበት ቅዱስ ቦታ ነው" የሚለው ንግግር የሚገልጸዉም ይህንኑ ነው፡፡

ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ ጀፎረ ከጥንት ጀምሮ የጉራጌ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች (ባህላዊ ዳኝነቱ፣ እርቁ፣ ሽምግልናው፣ ሠርጉ፣ ሀዘኑ፣ ባህላዊ ፈረስ ግልቢያው ወዘተ.) የሚከናወኑበትና ማህበረሰቡን እርስ በርስ የሚያገናኝ ባህላዊ ቦታ በመሆኑ ፋይዳው የጐላ ነው ብሎ ሊወሠድ ይቻላል፡፡

4.5.1.2 የእጅካ ባህላዊ ሸንጎ/ፍርድቤትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

የእጅካ ባህላዊ ሸንጎ/ፍርድቤት የምዕራቡ ጉራጌ ማህበረሰብ[65] የሚተዳደርበት ባህላዊ የዳኝነትና የእርቅ ስርዓት (በብሔረሰቡ አጠራር ቂጫ) የሚታይበት የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጪ ባህላዊ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ የዛሬ ሶስት መቶ ዓመት አካባቢ ማለት በአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ እንደተመሰረተ የሚነገረዉ የሰባት ቤት ጉራጌ ህብረት፣ በየቤተ ጉራጌው የሚመነጩ የአስተዳደር ሕጎችን በህብረተሰቡ መካከል የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮችን በጋራ ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበት የባህላዊ አስተዳደር ማዕከሎችን ፈጥሮ መተዳደር ጀመረ፡፡ ስለዚህም የእጅካ ሸንጎ የተመሠረተው የመላው ሰባት ቤት ጉራጌ የአስተዳደር ማዕከል በመሆን ሕግ ለማመንጨትና በወጣውም ህግ መሠረት ሰባት ቤት ጉራጌን ለመምራት ነው፡፡

“የሰባት ቤት ጉራጌ ህብረት አባሎች በአንድ ህብረት ሥር ተጠቃለው በጋራ ባህላዊ መተዳደሪያ ደንቦች ቢጠቀሙም፣ ከህብረቱ በፊት እያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሆኑ መተዳደሪያ ደንቦች ነበሩዋቸው፡፡ ከህብረቱ በኋላም እስከ ዛሬ የዘለቀ የየአካባቢያቸው ህዝብ የሚተዳደርባቸው ባህላዊ ደንቦች አሉአቸው፡፡ እነዚህ ደንቦች የእጅ”ካ ቂጫ አካል ሆነው ሊጠቀሱ ይችላሉ ፡፡” [66]

የሰባት ቤት ህብረት አባል ቤተ ጉራጌዎች በየራሳቸው ቀበሌዎች በሚያካሂዱዋቸው የባህላዊ አስተዳደር ሸንጎ ጉባኤዎች ላይ በሕዝባቸው መሐከል የተፈጠሩትን ችግሮች አቅርበው ይወያዩባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጅካ ባህላዊ አስተዳደር ሸንጎ የሚያሳልፋቸውና የሚቀርጻቸው ባህላዊ ደንቦች ወደ ሕዝቡ የሚደርሱትና ተፈፃሚ የሚሆኑት በእነዚህ በየቤተ ጉራጌው ባህላዊ አስተዳደር ሸንጎዎች አማካኝነት ነው፡፡ የጅካ ሸንጎ አባላት የሚመረጡትም በየሕብረቱ አባላት ቤት ጉራጌዎች ሸንጎ ጉባኤ ላይ ነው፡፡ በአካባቢያቸው ማህበረሰብ ዘንድ ባላቸው የላቀ ከበሬታ፣ በብልህነታቸው፣ በነገር አዋቂነታቸውና ሚዛናዊ አተያያቸው ተመርጠው ለእጅካ ሸንጐ ይላካሉ፡፡

[65] ሰባት ቤት ጉራጌ እየተባለ የሚጠራዉ ማለትነዉ፡፡

[66] አቶ ተስፋየ ጐይቴ(ቃል -መጠይቅ)

የሸንጎዉ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ (በመደበኛነት) ይካሄዳል፡፡ አስፈላጊና አስቸኳይ የሆነ ጉዳዮች ሲገጥሙ ከዚያም በበለጠ ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፡፡ ጉባኤው የሚካሄደው የህብረቱ አባል በሆነ አንድ ቤት ጉራጌ ሸንጎ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በይግባኝ ሊታይ ካስፈለገ፣ ወይም ደግሞ በመተዳደሪያ ደንቦች ላይ ማሻሻያ ለማድረግና አዳዲስ ደንቦችን ለመቅረጽ ካስፈለገ ብቻ ይሆናል፡፡፡

የእጆካ ባህላዊ ሸንጐ እነ ቃቄ ውርዶወት አለን ያሉዋቸዉን የመብት ጥያቄዎች ይዘው ለመጨረሻ ጊዜ ከእነ አጋዝ ፉርችየ እና አጋዝ ሲቆራ ጋር የተሟገቱበት፣ ጓላ ላይም ወርዶወት በግሏም ቢሆን ድል የነሳችበትና “አንቂቷን” (እርግማኗን) ያስነሳችበት ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህንም በተውኔቱ ውስጥ በሚከተለው መልኩ ተገልጸ እናገኘዋለን፡፡

ወርዶወት፡- ...ይህ የግሌም ጥያቄ ነው፡፡

አባገዳ ጅባቦ፡- የግል ጥያቄሽ ነው?

ወርዶወት፡- አዎ የጆካን ሸንጐ በግሌ ከዚህ በጓላ እንቂት እንዳይኖርብኝ፣ ከዚህ በጓላ ያሻኝን ላገባ፣ በቃኝ ስል ባሻኝ ጊዜ ልፈታ እንቂት እስከ መጨረሻው ይነሳልኝ ዘንድ ፍርድ ይሰጠኝ ዘንድ ቀርቤአለሁ፡፡

አባ ገዳ ጅባቦ፡- እንግዲያው የግልሽ ጉዳይ ከሆነ፣ የግልሽ ጥያቄ ከሆነ ሸንጐው በዚህም ጉዳይ ላይ በበቂ መክሮ የጨረሰ ስለሆነ የመጨረሻ ፍርዱን ላንቺ እንሰጣለን፡፡ እሺ ሁላችሁም የሸንጐው አባላት ቁሙና ውሳኔውን እንስጣት፡፡ (ሁሉም ይቆማሉ፡፡) የቃቄ ውርዶወት ከዛሬ ጀምሮ ዳግመኛ በሌላው ትዳር አትግቢ፡፡ የሌሎቹን ሴቶች ሰላማዊና ንፁህ ህሊና በነገር አትበጥብጪ፣ አገር አታምሺ፣ በጉራጌ ላይ መዓት አትጥሪ፡፡ ይሄ የጆካ ሸንጐ ይሄን ውሳኔ በቅድሚያ ሰጥቷል፡፡ ፍርዱን ሰምተሻል?

ወርዶወት፡- ሰምቻለሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ ዳግመኛ በሌሎች ሴቶች ትዳር ጉዳይ አልገባም፤ (ከእንባዋ እየታገለች) አላይም፣ አልሰማም፡፡ የራሴን ጥያቄ ፍርድ ስጡኝ፡፡

አባገዳ ጅባቦ፡- ያንቺን ጥያቄ የእጆካ ሽንጮ በትኩረት አውጥቶ አውርዶ ይሁንልኝ ያልሽውን ተቀብሎ ወስኗል። የቃቄ ውርዶወት፣ ከእንግዲህ ወዲያ እስከ መጨረሻው አንቂት አይኑርብሽ። የወደድሽውን አግቢ፣ በወደድሽ ጊዜ ፍቺ፣ የወላጆችሽን ንብረት ፈቅደው ያወረሱሽን ያህል ውረሽ ብለን ወስነናል። በተቀር የጉራጌ ህዝብ ግን ከአባቶቹ የወረሰውን በስራ ታታሪነትና በፍቅር በጨዋ ተሳስቦ፣ ተጋግዞ ሰምና ወርቅ ሆኖ የመኖር ያለውን ትልቅ ባህሉን አክብሮ ጠብቆ ይኖራል። ችሎቱ አብቅቷል።

(ገቢ. 4፣ ትዕ .4፣ 77-78)

በዚህ ዉሳኔ የእጆካ ሽንጎ በወርዶዎት የተበለጠ ቢመስልም ሴቶችን ከወርዶወት በመነጠል ብልጠት የተመላበት ፍርድ ማስተላለፉን መገንዘብ ግን ይቻላል። በቀጣዩ የተውኔቱ ክፍል ደግሞ የጆካ ሽንጮ የሚያስተላልፈው ማንኛውንም ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ግለሰብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና ከበሬታ እንመለከትበታለን።

አጋዝ ፋርችየ፡- የእጆካ ሽንጮ ለሚስትህ አንቂት እንሳላት፣ ሚስትህን ፍታ አለኝ።

ወርዶወት፡- አዎ አንቂቱን አንሳልኝ፣ የእኔ አንቂት ሲነሳ የጉራጌ ሴት አንቂት ሁሉ የእኔን ተከትሎ ይነሳና የሴቱ እንባ፣ በሴቱ ግፍ መዋል ይቆማል።

አጋዝ ፋርችየ፡- በቃ ይሄዉ ነዉ?

ወርዶዎት፡- የመሃላ ቃሌ ነዉ።

አጋዝ ፋርችየ፡- ታላቁ የእጆካ ሽንጮ ግድ አለኝ እንጂ፣ የአገር አድባር የሆኑ ሽማግሌዎችን አከበርኩኝ እንጂ ... እኔማ ጦር ገጥሜም ቢሆን አስቀርሽ ነበር።

(ገቢ፣ 3፣ ትዕ.2፣ 69-70)

በሠር ሜዳ ጀብዱ የሚታወቀውና በሚኖርበት ማህበረሰብ ዘንድ የጀግኖች ጀግና ተደርጐ የሚቆጠረው አጋዝ ፍርችየ ለእጆካ ፍርድ ቤት ውሳኔ መግዛት ስላለበት ብቻ የማያምንበትን ነገር ሲፈፅምና በጣም የሚወዳት ሚስቱን የፈለግሽውን አግቢ ብሎ ሲፈቅድላት ይታያል። ይህም እጆካ በየትኛውም ደረጀ የሚገኝ የማህበረሰብ ዘንድ ያለውን ክብርና ተቀባይነት ያሳያል።

ፋይዳውን ለመግለጽ ያህል ፣የእጆካ ባህላዊ ሽንገሎ ማህበረሰቡ ኑሮውን በሰላማዊ መንገድ እንዲመራ በማስቻል፣ የጉራጌ ህዝብ ጥንታዊ የባህል እሴቶች ተጠብቀው እንዲቆዩና ለወደፊቱ እንዲቀጥሉ በማድረግ፣ የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን ስራ በማቃለል፣ ከነዚህና ከመሳሰሉት አንጻር ጉልህ ሚና አለው።

4.5.1.3 አንቂትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

አንቂት በጉራጌ ጥንታዊ ባህልና እምነት መሠረት ሴት ልጅ ባሏ እስካልፈቀደ ድረስ ፍቺ መፈፀም እንዳትችል የሚከለክል እርግማን ነው።[67] በዚህ የጉራጌ ጥንት አባቶች እንደተደነገገ በሚነገረው እርግማን ህግ መሠረት ሴት ልጅ አንድ ጊዜ ከአገባች በኋላ የቱንም ያህል በደል ቢፈፀምባት ችላው ትኖራለች እንጅ ከባሉ ፈቃድ ውጭ ፍቺ መፈፀም ቤቷን ጥላ መሄድ ፈጽሞ አይፈቀድላትም።

ይህን ፈጽማ የተገኘች ሴት ብትኖር የተለያዩ ችግሮች ይደርስባታል ተብሎ ይታመናል። ለምሳለ፡- ጨርቅን ጥሎ ማበድ፣ በጠና መታመምና የአልጋ ቁራኛ መሆን ወዘተ... ሊሆን ይችላል። ይሄ አስተሳሰብ በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ተአምኖትን አግኝቶ ለብዙ ዘመናት ከአንዱ ወደ ሌላው ሲርድ ሲወራረድ እንደኖረ ይነገራል። የቃቄ ውርዶወት ተውኔት ውስጥ ከተነሱት አንኳር ጉዳዬች ውስጥ አንዱ ይኸው ሲሆን፣ ቃቄ ወርዶወትና አጋሮቹዋ አንቂት ይነሳልን በማለት የእጆካን ሽንጎ የሞግታሉ። “በባሏ በደልና እንግልት የተማረረች ሴት ትዳር በቃኝ ብላ ፍቺ እፈልጋለሁ ብትል ጥፋቷ የቱ ላይ ነው” በማለት ጠንከር ያለ መከራከሪያ ያቀርባሉ። በአንጻሩ የወንድን ወገን ወክለው የቆሙት እነ አጋዝ ሲፋኑ ይህን የእነ

[67] አቶ ተስፋየ ነይቱ(ቃል -መጠይ)

ወርዶወትን አመክኖአዊ ሀሳብ ባለ በሌለ ሀይላቸው ተጠቅመው ሲያጣጥሉት ይስተዋላሉ፡-

አጋር ሴት 1፡- ለጆካ ሽንጮ የምናቀርበው ዋና በደላችን ይሔ ነው፡፡ ሴት በደል ቢበዛባትም አንገቷን ሰብራ እንዳትቀመጥ እንባዋን በጓዳ እያፈሰሰች ግድ መኖር ይብቃት፡፡

ወርዶወት፡- ጉዳዩ ባጭሩ፣ የግል ፈቃድና የፍቺ ምርቃት ሳትቀበል ለሄደች ሴት የሚረግመው የሽማግሌዎች የቃል እስር አንቂት ይነሳልን ብላው የአገሩ ሴቶች ለጆካ ሽንጮ አጠንክረው ጠይቀዋል፡፡

አባገዳ ጅባቦ፡- ወርድወት እስቲ ስታስቡት ፍቺንስ እግዜር ይወደዋል? በደልስ ቢኖር ይቅር ለግዜር መባባሉ አይበልጥም?

አጋዝ ሲፋኖ፡- ነፍስ ፈጣሪዋ ይቅርታ ነው የሚወድ፡፡ እንዲያው ምን አይነት በደል ነው የፈጣሪ ይቅርታ የሚያስንቅ?

ወርዶወት፡- ጥያቄ አችን አንቂት ይነሳልን የሚል ነው፡፡

አጋዝ ሲቆራ፡- ምን? ማንያብላ ያጠጣት ድንገት ባልትታ ሄዳ? እታጠን ብላ ተቃጠለች አሉ፡፡

ወርዶወት፡- ለምን? በእርግማን ይከለከላል? በደልና ግፍ እንጅ መረገም ያለበት ግፍን ሸሽቶ መሄድ ለምን ይረገማል?

አጋዝ ሲቆራ፡- በጠቅላላ ጉራጌ የተረገመ እርግማን ነዋ! ከዚህ በላይ መርገምት ከየት ይምጣ?

አጋዝ ሲፋኖ፡- አሁንም ሴቶች ስሙ! ባሏ የፍቺ ምርቃት ያልሰጣት ሴት በራሷ ፈቃድ ትዳሯን ተታ ብትሔድ መጥፎ እርግማን ያለባት ሴት ናት፡፡ በእሷም በዘሮቹዋም ሁሉ ጥፋት ይወርዳል፡፡

አጋዝ ሲቆራ፡- እንዲህ ያለች ሴት ባል እንዳታገባ፣ ብታገባም የተረገመ ሀጢያት ነውና ትዳሯም ዘርዘሯም በበሽታ ይለቅ ተብሎ በሬ ታርዶ ደም ተረጭቶ ተረግሟል፡፡

(ገቢ 2፣ትዕ፣2 ፣42-43)

ከ ራዲካል ፌሚኒዝም ቲዎሪ አኳያ ስንመለከተው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶች የበታችነትና በወንዶች ተፅዕኖ ስር መሆን የሚታወቅ ቢሆንም አንዳንድ ሴቶች በአካባቢያቸው ጉዳይ ላይ ትልቅ ሐይልና ስልጣን ሊያሳዩ የሚችሉበት አቅም እንዳለ በአንዳንድ ባህል ውስጥ መኖሩን ያረጋግጣሉ ከሚለው የ Fried እና Lamphere (1979፡ 246) እሳቤ አኳያ የሚታይ ነው፡፡ አጋዝ ሲፋኖ እና የአጋዝ ሲቆራ ለሴቶች የነበራቸው ዝቅተኛ ግምትና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚናገሩት ንቀት የተመላ ንግግር በአንድ በኩል ፣ የእነቃቄ ወርዶወት ቅፅበታዊ ምላሽና አልሸነፍ በይነት በሌላ በኩል፣ እዚህ ላይ ከሚነሱ ጉዳዮች ዋና ዋና ዎቹ ናቸዉ፡፡

ከዚህ በታች በቀረበው የተውኔቱ ክፍል ደግሞ የአንቂት (የሴት ልጅ እርግማን) አነሳስ ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመሰል እንመለከታለን፡፡

(ሶሶት የአካባቢው ሽማግሌዎተ በዝምታና በእርጋታ ይገባሉ፡፡ ፍርችየ አየት አርጓቸው መልስ መሬቱን አጐንብሶ ያያል፡፡ አንደኛው ሽማግሌ የያዙትን አንድ ጭብጥ ለምለም ሳር ለፍርችየ ሲዘረጉለት ተቀብሎ በጐጆ ቤቱ ግራ ጐን ወደ መሐል ፊት መድረክ የተጋደመው ትልቅ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ይቆማል፡፡ ሌላው ሽማግለ ወተት የያዘ የተጌጠ የጮጮ ቅል አምጥተው ለፍርችየ ያቀብሉታል፡፡ ወርዶወት በዝግታ ሄዳ ክፍርችየ ፊት ለፊት እገዣን ሰብራ ትቆማለች፡፡ ፍርችየ በእርጋታ የያዘውን ለምለም ሳር ቅሉ ውስጥ ይነክረዋል፡፡ ቀና ብሎ ሽማግሌዎችን ካየ በኋላ ምርቃት ሊሰጣት ይዘጋጃል፡፡)

ፉርችየ ፡- ፈትቸሻለሁ ፡- የወደደ ያግባሽ፡- (ሳሩን ድጋሚ ወደ ቅሉ ከቶ ያወጣና አናትዋ ላይ ያስቀምጣል፡፡)

ፋርችየ፡- ፈትቼሻለሁ- የወደደ ያግባሽ ፡፡ (ከጥቂት ዝምታ በኋላ አጋዝ ፋርችየ የመረቀበትን ለምለሙን ሳር ለወርዶ ለመስጠት እጁን ይዘረጋል፡፡)

ፋርችየ፡- ለምለም ሁኚ፡፡

(ገቢ፣ 3 ፣ትዕ. 2፣79)

ከላይ እንደተመለከትነው አንቂት በቃል “ፈትቼሻለሁ” ተብሎ የሚነሳ ብቻ ሳይሆን ራሱን የቻለ የፍቺ ስርዓት መፈፀም አለበት፡፡ ሶስቱ ሽማግሌዎች ለምለም ሳር እና ወተት ይዘው በመምጣት ለፋርችዬ የሚሰጡት፣ ከዚያም ፈርችዬ ሳሩን ቅሉ ውስጠ ደጋግሞ እየነከረ በማውጣት ወርድወት አናት ላይ ካስቀመጠ በኋላ “ፈትቸሻለሁ የወደደ ያግባሽ” ወዘተ. እያለ የሚመርቃት ... እነዚህ ሁሉ የአንቂት አነሳስ የራሱ የሆነ ባህላዊ ስርዓትና ደንብ ያለው ስለመሆኑ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ከተግባራዊ ቲዎሪ አንፃር ሲታይ፣ አንቂትን አስመልክቶ የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ የሆኑትን ሥናይ ባህላዊ እሴቶች ጠብቆና ተንከባክቦ ማቆየት እንደሚገባ ሁሉ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ የቆሙትን ማውገዝና ማስቀረት እንደሚያስፈልግ ያስተምራል፡፡

4.5.1.4 ምርቃትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ምርቃትና ጉራጌ ደምና ስር ናቸው ይባላል፡፡ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው መረጃ አቀባይ አቶ ተስፋዬ ጐይቴ ይህን አስመልክቶ ሲናገሩ፡- “ምርቃት በጉራጌ የተለየ የሚያደርገው ህብረተሰቡ የቱንም ያህል ጠንክሮ ቢሰራ የእናት የአባት የሽማግሌ ምርቃት ከሌለኝ የያዝኩት አይበረክትም፤ ማደግ መለወጥም አልችልም ብሎ ስለሚያምንበት ነው፡፡ ለዚህም ነው የጉራጌ ልጅ ምርቃት ፍለጋ ያለ የሌለውን አገር ቤት ላለ ዘመድ አዝማድ የሚልከው፡፡ በአካባቢ ልማት፣ ትምህርት ቤት በመስራት ወዘተ. የሚሳተፈው” ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተውኔቱ ውስጥ የምርቃት ይዘትና ፋይዳ ምን እንደሚመስል ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

አባገዳ ጅባቦ፡- እርሶ ይመርቁና እንጀምር፡፡ ጋሼ ኤጋኖ ከሁላችን በእድሜ ከፍ ይላሉ፡፡ ይመርቁ፡፡

ጋሼ ኤጋኖ፡- ካላችሁኝ እሺ፡፡ ምድር ሰላም ይሁን ፡፡

ሁሉም፡- አሜን

ጋሼ ኤጋኖ፡- ልጆች ይደጉ፡፡

ሁሉም፡- አሜን

ጋሼ ኤጋኖ፡- ሽማግሌዎች ይሰንብቱ፡፡

ሁሉም፡- አሜን ፡፡

ጋሼ ኤጋኖ፡- እናንተም ለዚህ የእጅካ ሽንጐ መልዕክት ለማድረስ ላይ ታች በማለት የደከማችሁ ወንድሞቻችን ልፋታችሁን ፈጣሪ ይካሳችሁ፡፡

ሁሉም፡- አሜን፡፡

(ገቢ.2 ፣ ትዕ.2 ፣ 67)

ከዚህ ምርቃት ለመረዳት የሚቻለው ምርቃቱ የእድሜ ተዋረድን መሠረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ በአድሜ ከፍ ያሉ ሽማግሌዎች ምርቃቱን እንዲሰጡ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ እነሱም ከላይ እንደተመለከትነው ምድር ሰላም ትሁን፣ ልጆች ይደጉ፣ ሽማግሌዎች ይሰንብቱ ወዘተ. በማለት ይመርቃሉ፡፡ ታዳሚዎችም “አሜን” በማለት ምርቃቱን ይቀበላሉ፡፡ ከማህበራዊ አውድ አኳያ ሲታይ ምርቃት በጉራጌ በዋናነት የእድሜ ተዋረድን መሰረት አድርጎ የሚከወን መሆኑን ያመለክታል፡፡ የምርቃቱን ፋይዳ ከተግባራዊ ቲዎሪ አንጻር ስንመለከተዉ ደግሞ ለተመራቂው የስነ ልቡና እርካታ ያስገኛል፡፡ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ መከባበርን ይፈጥራል፤ አንድነትን ያጠናክራል፡፡

4.5.1.5 ምሳሌያዊ ንግግሮችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተውኔት ውስጥ የምናገኛቸው ምሳሌያዊ ንግግሮች በአማርኛና በጉራጌኛ ቋንቋ የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም በጉራጌኛ ለቀረቡት በዚህ ጥናት አቻ የአማርኛ ትርጉም ተሰጥቶአቸዋል። ምሳሌያዊ ንግግሮችን በማስቀደም ትንተናው እንደሚከተለው ይቀርባል።

ጐራግኛ	የአማርኛ ትርጉም
1. በዝራ ወረጀ ጠ አጉጅም	ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል
2. በሰብጌንዞ እምር ፍቃ	በሰው ጠገራ ብር ድንጋይ ፍለጥ

(ገቢ.2 ፣ ትዕ.1 ፣ 28-36)

በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ሞኝነትነ ያመላክታል። አንድ ሰው አጠገቡ ተቀምጦ በቀላሉ ሊያገኘዉ የሚችለውን ነገር ሞኝ በመሆኑ ብቻ ከሩቅ የመጣ ሌላ ብልጥ ሰው ይወስድበታል የሚል ይዘት አለው። ከተግባር አኳያ ብልሀትን ማስተዋልን ያስተምራል። በተራ ቁጥር 2 የቀረበው ምሳሌያዊ ንግግር አንተ ምን ችግረህ በሌላ ሰው ገንዘብ እንደፈለክ ትሆናለህ የሚል ይዘት አለው። ንግግሩ የሌላ ሠው የሆነን ንብረት እንደራሳችን ቆጥረን ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግለት እንደሚገባ ይመክራል። ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ፣ ምሳሌያዊ ንግግሩ ሞራልና ስነ ምግባርን ያስተምራል።

ጉራግኛ	የአማርኛ ትርጉም
3.ድንቻ ሁዳ በእጀሻ ተንኪያ ሰበረችን	በእጅ የተተከለ ድንች መደቅደቂ ሰበረ
4.እታእ ባረቸ ተቃጠለቸ	እታጠን ብላ ተቃጠለች
5.እሶ እታኬ ባርታ ማሚታ አኘ	ጨው አታጠን ብሎ ሚሙቶ ቀረ

(ገቢ.2 ፣ ትዕ.2 ፣ 45-56)

በተራ ቁጥር 3 ላይ ያለው በአንድ ወቅት ቀላል ነው ብለው የናቁት ነገር አንድ ቀን ያልተጠበቀ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ያሳያል፡፡ አንድን ነገር ገና ከጅምሩ አሳንሶ ከማየት ይልቅ ለዚያ ነገር በወቅቱ ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ይመክራል፡፡

በተራ ቁጥር 4 እና 5 ላይ የቀረቡት ምሳሌያዊ ንግግሮች ተመሳሳይ ይዘት አላቸው፡፡ የሰው ልጅ የማይገባውን ነገር ለማግኘት የሚያደርገው አንገብጋቢ ሩጫና አቅምን ያላገናዘበ መፍጨርጨር መጨረሻው ውድቀት እንደሆነ ያስረዳሉ፡

ማንም ሰው ማግኘት የሚችለው አቅሙ በሚፈቅደውና በሠራው ልክ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

4.5.1.6 ባህላዊ የማዕረግ ስሞችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ጉራጌ በባህሉ ከጥንት ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ባህላዊ የማዕረግ ስሞች አሉት፡፡ እነዚህ የማዕረግ ስሞች በሁለት መልኩ እንደሚገኙ ይነገራል፡፡ ይኸውም አንደኛው ከቤተሰብ በውርስ ሲሆን ሁለተኛው ማህበረሰቡ ለአንድ ሰው የሠራውን ትልቅ ሰራ፣ ባህርይውን፣ የኑሮ ደረጃውን ወዘተ. አይቶና መዝኖ የሚሰጠው ነው፡፡ ከቤተሰብ በውርስ የሚገኘው “አዝማች” ይባላል፡፡ ትርጉሙም ንጉስ እንደ ማለት ነው፡፡ አባት በሚሞትበት ጊዜ ከወለደችው ልጆች ውስጥ በዕድሜ አንጋፋው ወይመ የተመረጠው ንግስናውን ይረከባል፡፡ ንጉስ የሚያስብለው በዕጅ ላይ የሚያጠልቀው ባህላዊ አምባር በጉራግኛ “ጐንደር” ነው፡፡[68]

በማህበረሰቡ ተቀባይነት አግኝቶ የሚሰጠው የማዕረግ ስም ቀደም ሲል እንደተገለፀው የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የወርዶወት አባት ቃቄ በሀብታቸው ብዛትና በለጋስነታቸው “ዳሞ” የሚል ስም ተሰጥቶአቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተውኔቱ ውስጥ የተነሱትን ሌሎች ባህላዊ የማዕረግ ስሞች ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

[68] አቶ ተስፋየ ነይቱ (ቃል- መጠየቅ)

አሲህ አርብ ፡- የማይፈራ፣ በውጊያ ወቅት ከጦር ሜዳ የማይሸሽ ማለት ነው።

አባ ገዳ ፡- ነገር አዋቂ፣ ብልህ፣ አስተዋይ፣ ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ የመመልከት ችሎታ ያለው ሰው ማለት ነው።

አጀት ፡- ለሴቶች የሚሰጥ የማዕረግ ስም ሲሆን፣ የላቀች ባለሙያ፣ ለጋስ፣ ርህሩህ እንደማለት ነው።

አጋዝ፡- እጅግ በጣም የሚፈራ ጦረኛ፣ ገና ሲያዩት የሚያስደነግጥ ትልቅ ግርማ ሞገስ ያለው ጀግና ማለት ነው።

ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታዩ እነዚህ ባህላዊ የማዕረግ ስሞች ሠዎች ለስራቸው እውቅናን የሚሰጡና ክብርን የሚያጐናጽፉ በመሆናቸው ማህበራዊ ፋይዳቸው የጐላ ነው።

4.5.1.6.7 ቄግን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ቄግ በጉራጌ የጀግና ማወደሻ ዘፈን ነው። የተለየ ታሪክ ያላቸው ከጠላትና ወራሪ ጋር ተዋግተው በጦር ሜዳ ጀብዱ የፈፀሙ፣ ማህበረሰባቸውን ከሸፍታና ሌባ ተከላክለው የኖሩ፣ አደን ወጥተው ትልቅ አውሬ (ለምሳሌ፡- አንበሳ ወይም ነብር) የገደሉ አንተ እንደዚህ አይደለህም ወይ፣ ይህን አልሠራህም ወይ እየተባሉ ታሪካቸው እየተነሳ በቄግ ይሞካሻሉ። አንዳንድ ቄጮች ከግለሠብ ባለፈ ጐሳንም ያነሳሉ።

አንድ ግለሰብ ወይም አንድ ጐሳ ከአንድ በላይ ቄግ ሊኖረው ይችላል። ቄግ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይዘፈናል። ለምሳሌ፡- አንድ ቤት ሠርግ ካለና የሙሽራው/የሙሽራዋ እናት አባት፣ አያት ቅድመ አያት ወይም ጐሳ ከላይ የተጠቀሱት ታሪክ ካላቸው ይኸው እየተነሳ ይዘፈናል። ሠርጉ ሊደረግ የሳምንት ጊዜ ሲቀረው ጀምሮ የሠፈር ሠዎችና ዘመድ አዝማድ ማታ ማቱ በሠርጉ ቤት እየተሰባሰቡ በቄጋማው[69] መሪነት ይዘፍናሉ። አንዳንድ ሞቅ ያሉ ቄጮች ከበሮ እየተመታ፣ ተቀባይዎች

[69] ቄጋማ ቄግ የሚዘፍን ሰው ማለት ሲሆን ተቀባይ ይኖረዋል። ተቀባዩ በዋናነት የአድማቂነትን ሚና ይጫወታል።

ከበው ሰውነታቸውን በስሜት እየነቀነቁ ይዘፈናሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ያለከበሮ ዉዝዋዜ ይዘፈናሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው የክዋኔው አይነት ከዌግ ዌግ የሚለያየ መሆኑን ነው፡፡ በተውኔቱ ውስጥ ወደ ስድስት የሚጠጉ ዌጐች የቀረቡ ሲሆን በዚህ ጥናት ሁለቱን ብቻ ለአብነት ያህል ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

1. ኢዬ ኢዬ ኢዬ (2)

ወርዶወት፣ ወርዶወት

ተፈጠርሒም፣ በውርየ

ተፈጥረሻል፣ ከውድ ማጠር

ተፈጥረሻል፣ ከቅራዕት

ተወልደሻል፣ ከለጋስቸር

ከትላልቅ፣ ከሻኛ ነሽ

ከጀግኖቹ፣ ከምሁር ነሽ

ሽቦታ ነው፣ ጀግና አጐትሽ

የአንበሳ ዘር፣ አንበሳ ነሽ

ወገን አለሽ ሒጂ ኬርሴ

ከነቤንጌ፣ ከነቶትየ፣

ኧረ ስንቱን፣ ልቁጠርልሽ

ከጀግኖቹ፣ ከምሁርነሽ

ተወልደሻል፣ ከለጋስቸር

ደሞ ቃቄ፣ ቆረር ምሁር

(ገቢ 1፣ ትዕ. 1፣ 5-6)

ይሄ ዜግ የቃቄ ውርዶወትን ያሞግሳል። ሙገሳው በዋናነት በሶስት ጉዳዬች ላይ ያተኩራል። የውርድወት ጐሳ፣ ቤተሰባዊ የዘር ግንድ ዋና የተወለደችበት ቦታ የትኩረቱ ማጠንጠኛዎች ናቸው።

“ተፈጥረሻል ከውድማጠር” የሚለው ውድማጠር ከሚባል ጐሳ የተገኘች መሆኗን ለመግለጽ ሲሆን **“ከጀግኖቹ ከምሁር ነሽ”** የሚለው በጉራጌ አካባቢ ምሁር በተባለ ቦታ መወለድዋን ለማመልከት ነው።

በሌላ በኩል “ሽቦታ ነው ጀግና አገኙሽ” **“ከዳወቶ አሲህ አርቡ”፣ ከጥራ ጫሙስ ከጠረኛው”፣ “ካባ ገደ ሔጀ ከርሴ”፣ “ከእነ፣ ቤንጌ ከእነ ቆትየ”** እና **“ዳሞ ቃቄ ቆረር ምሁር”** የሚሉት በቤተሰብ የዘር ግንድዋ የሚነገር ታሪክ ካላቸው ታላላቅ ሠዎች የተገኘች መሆኗን ይጠቅሳል።

ከአውድ አንጻር ለዚህ ዜግ መነሻ ተደርገው የሚወሰዱ ምክንያቶች ወርዶወት ለራሷና ለጉራጌ ሴቶች መብት መከበር በጽንአት መቆሙዋ፣ ትኖርበት በነበረው ባህላዊና ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ የማይደፈሩ የነበሩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጥያቄዎችን አንስታ መታገሉዋ፣ በስተመጨረሻም(ለግሉዋም ቢሆን) ማሸነፍ በመቻሉዋ ነው።

2. **ብዙ ሰምቻለሁ፤ ብዙ አይቻለሁ**

   እኔ በዘመኔ ብዙ መስክሬአለሁ

   ከቶ አልገጠመኝም ሳተና ቆፍጣና

   አቤት! አቤት! ኤችሁ! አውጣን!

   ያነጩ ፈረስ ለምነው የተጫነው?

   ወራሪ ጦር ደርሷል ፈጥነህ ታጠቅ በሉት

   ፎክሮ ተነሳ፤ የቁርጥ ቀን ደራሽ የችሀው አንበሳ

   ጐራዴውን በወገቡ ሻጥ አድርጐ ታጥቆ

ጠሩን ያን ረጅሙን በአየር ላይ ነቅንቆ

ፈረሱን ያን ነጩን ያን እልኸኛውን

አስከትሎ እነዚያን ተናዳፊዎችን

ተነሳ አንበሳው ጋለበቼ አለው ፈረሱን

ከሩቅ የሚሰማ የሚያቋጭ ቃጭሉ

ጠላት ብርክ የሚያሲዝ ገና ከሩቅ ሳሉ

ቼ! አለው ፈረሱን

ቼ! ቼ! አለው

(ገቢ 5፣ ትዕ. 2፣ 90)

በተራ ቁጥር 2 ላይ በቀረበዉ ቄግ ሲወደስ የምናየው ደግሞ የቸሃው ጀግና አሲህ አርብ ፉጋ ነው፡፡ አሲህ አርብ የማዕረግ ስሙ ሲሆን፣ ከዛሬ 150 ዓመት በፊት በጉራጌ ምድር ከታዩት ስመጥር ጀግኖች መካከል አንዱ እንደነበርና ከአጋዝ ፉርችየ በኋላ ቃቄ ወርዶወትን ማግባት የቻለ ሰዉ እንደነበር ይነገራል፡፡[70] በመሆኑም ይሄን ጀግና ከላይ በቀረበው መልኩ በቄጉ አማካኝነት ታሪኩ እየተነሳ ተወድሶአል፡፡ ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ፣ ቄግ ታሪክን እያነሳ የታሪኩ ባለቤት የሆኑትን ጀግኖች የሚያወድስ እንደ መሆኑ ታሪክን የማስተላለፍ ባህልን የማስቀጠል ፋይዳ አለው፡፡

4.5.1.6.8 ባህላዊ ዘፈኖችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተውኔት ውስጥ በዋናነት የቀረቡት ባህላዊ ዘፈኖች በጉራጌ ማህበረሰበ ዘንድ በስፋት የሚታወቁት “ግቻምቄ” እና “መራራ ሽሚሮ” የተባሉት ናቸው፡፡ ሁለቱንም ጠቀለል አድርገን ከተግባር ቲዎሪ አንጻር ስንመለከታቸው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛዉም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመረመር ይረዳል ከሚለው የ Okephwo (1992,173) እሳቤ አኳያ የሚታዩ ናቸዉ፡፡

[70] ዝርዝሩን በአባሪ 2 (የቃቄ ወርዶወት ታሪክ ክፍል ሁለት) ይመለከቷል፡፡

ስለዘፈኖቹ ይዘትና በተውኔቱ ውስጥ የተነሱበትን መንገድ አስመልክቶ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>ግቻምቄ</u>

ግቻምቄ .... ገቺ

ግቻምቄ... ገቺ

ገረ ... ገቺ

የምበኽር .. ገቺ

ወርድወት .... ገቺ

ይብቃሽ .... ገቺ

ከእናትሽ ... ገቺ

ይብቃሽ .... ገቺ

ከአባትሽ ... ገቺ

ዛሬስ ... ገቺ

ይብቃሽ ... ገቺ

ዛሬስ ... ገቺ

በኬር .... ገቺ

ያግባሽ ... ገቺ

ግቻምቄ... ገቺ

(ገቢ. 1፣ ትዕ. 1: 10)

ግቻምዌ... ገቺ፣ አንተ እንደዚህ አይደለህም ወይ፣ አንቺ እንደዚህ አይደለሽም ወይ፣ እየተባባሉ እያወደሱና እየነቀፉ የሚዘፍኑት የዘፈን አይነት ነው።[71] በባህሉ መሠረት ብዙ ጊዜ የሴቶች ዘፈን ቢሆንም አሁን አሁን ወንዶችም እየዘፈኑት ይገኛሉ።[72]ግቻምዌ ከሚዘፈንባቸዉ አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ሰርግ ላይ ሲሆን፣ በአብዛኛዉ በዕድሜ ትላላቅ የሆኑ ሴቶች(እናቶች) ተሰባስበዉ ይጫወቱታል። በተውኔቱ ውስጥ የተነሳበት መንገድም ከዚሁ ጋር ይያያዛል። በወርዶወት ሠርግ ላይ የተገኙት የምሁር አካባቢ ሴቶች "ወርዶወት ከእናትና አባትሽ ጋር መኖሩ አበቃ አሁን ልታገቢ ነው" እያሉ ሲጨፍሩ ይስተዋላሉ። ከጭፈራው አይነት በመነሳት በጋራ የሚከወን በርካታ ተሳታፎች ያሉት ዘፈን መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ ግቻምዌ የማዝናናት፣ የማስደሰትና ሠርግን የማድመቅ ፋይዳ አለው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

2. <u>መራራ ሽሚሮ</u>

ወርዶወት ወርዶወት፣ ክፉ አያግኛት

በሄደችበት፣ እግሯ አይቆርቁራት- ጅካ አንጥፉላት

በሄደችበት፣ ፀሀይ አይንካት- ጃንጥላ ዘርጉላት

አደራ አጋዘ ፋርችየ- አደራ

አደራ የቤት ቅንጡን - አደራ

አደራ ልዕልታችንን አደራ

(ገቢ. 1፣ ትዕ. 1: 10)

መራራ ሽሚሮ እንደ ግቻምዌ ሁሉ በሠርግ ላይ ይዘፈናል። እዚህ ላይ ዋናው ልዩነት ሆኖ የሚታየው ዘፈኑን የሚጫወቱት ልጃገረዶች ብቻ መሆናቸዉ ነዉ። በተውኔቱ ውስጥ እንደተገለጸው ከወገብ በላይ ከቆዳ፣ ከወገብ በታች ከቃጫ የተሠራ ባህላዊ ልብስ የለበሱ ወጣት ልጃገረዶች ከላይ የቀረበውን መረራ ሽሚሮ

[71] አቶ ተስፋየ ጎይቴ (ቃል-መጠይቅ)

[72] ለምሳሌ፣ ድምፃዊ ሀይሉ ፈረጃን እና ድምፃዊ ደምሴ ተካን መጥቀስ ይቻላል።

ይዘፍናሉ፡፡ ይህም ከክዋኔ ቲዎሪ አንጻር ሲታይ ዘፈኑ ከአልባሳት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ቅድመ ዝግጅት የሚደረግበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ፋይዳውን በተመለከተ ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ ከቀረበዉ ግቻምዌ ብዙ የተለየ ባይሆንም፣ በልጃገረዶች ሚቀርብ መሆኑ ሲታይ ግን ዘፈኑን የበለጠ ሳቢና ማራኪ ያደርገዋል፡፡

4.6. የአሻ ልጅ

ይሄ ተውኔት በደቡብ ብሄር በሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ዉስጥ ከሚገኙት እንዱ በሆነው የመኢኔት ብሔረሰብ ትውፊታዊ /ባህላዊ/ የክዋኔ ስርዓቶች ላይ ያተኩራል፡፡ የዚህ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑት አቶ ሙርዴች እና ወ/ሮ ሞርደሊን፣ ኮሮይ፣ ጊብዚኒ እና ኢፋይ የተባሉ ሶስት ልጆች አሏቸው፡፡ ኮሮይ የበኩር ልጅ ሲሆን ጊብዚኒ ተከትላለች፡፡ ኢፋይ ደግሞ የመጨረሻ ልጅ ነው፡፡ ኮሮይ የበኩር ልጅ እንደመሆኑ እስካሁን ማግባት የሚገባው የነበር ቢሆንም በመኢኔት ብሔረሰብ የጋብቻ ባህል መሠረት ለጥሎሽ የሚከፍለዉ ከ 4-8 ሺህ ብር፣ ከ5-15 የቀንድ ከብትና የጦር መሳሪያ የሌለው በመሆኑ፣ ይህን ማሳካት አልቻለም፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ “ሾሽ”[73] እየተባለ እንዳይጠራ ይሰጋል፡፡ ያምቢሆን፣ ታናሽ እህቱ ጊብዚኒ ተድራ ቤተሰቡ በሚያገኘው ጥሎሽ እሱም አንድ ቀን የወደዳትን አግብቶ እንደሚኖር ተስፋ ያደርጋል፡፡ ጊብዚኒ ባርኮሞይ የተባለ እጮኛ ቢኖራትም በቅርቡ የጀመረችውን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (Elementary school Education) እስክታጠናቅቅ ለጊዜውም ቢሆን ጋብቻ ላለመፈፀም ወስናለች፡፡ ኢፋይ በበኩሉ ውሸኔ የተባለች የከንፈር ወዳጅ አለቸው፡፡ ሆኖም እሱም እንደ ታላቅ ወንድሙ ካሮይ ለጥሎሽ የሚከፍለው በቂ ሀብት የሌለው በመሆኑ የከንፈር ወዳጁን “አንድ ቀን ተሳክቶልኝ አገባሻለሁ” እያለ የተስፋ ቃል ከመስጠት በስተቀር ሌላ ማድረግ የሚችለው አልነበረዉም፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀጠለው የኢፋይ እና የውሸኔ ፍቅር ከዕለታት በአንዱ ቀን ያልታሰበ ችግር ገጠመው፡፡ ጸሎጋ የተባለ የመንደሩ ወጣት በአሳቻ ጊዜ ጠብቆ ውሸኔን ከጠለፋት በኋላ በብሔረሰቡ ባህል መሠረት ለቤተሰቦች ማድረግ የሚገባውን አድርጎ የራሱ አደረጋት፡፡ በዚህ የተበሳጨውና በቀልን

[73] “ ሾሽ” በመኢኔት ፣ ስራፊት፣ዋልጌ፣ ቦዘኔ፣ለትዳር ያልተመረጠ ማለት ሲሆን ፣በዚህ ጥናት ወደፊት በስፋት የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡

የቋጠረው ኢፋይም ጳሎጋን ገድሎ ተበቀለው፡፡ እንግዲህ የ"አሻ"[74]ዉ ጉዳይ ከዚህ ክስተት በኋላ ይጀምራል፡፡ ልጃቸው የሰው ነፍስ ማጥፋቱን የሰሙት አቶ ሙርዴች ጊዜ ሳያጠፉ የተፈጠረውን አቅራቢያቸው ላለ የጦሳ መሪ አሳወቁ፡፡ የጦሳ መሪውም በመኢኔት ባህል መሠረት የሀገር ሽማግሌዎችን መርጠው ወደ ሟች ቤተሰብ "በቀል እንዳይኖር፣ እርቅ ይውረድ" ሲሉ ላኩዋቸው፡፡ ለእርቅ የተላኩት ሽማግሌዎችም በባህሉ መሠረት የገዳይ እህት (ጊብዚኒ) ለሟች (ጳሎጋ) ቤተሰቦች በ "አሻ" (የደም ካሳ) እንድትሰጥ፣ በተጨማሪም የገዳይ ቤተሰብ ለቀብር ማስፈፀሚያ የሚውል ሁለት ሺ ብር እና፣ አራት ከብቶች በስጦታ እንዲከፍሉ ፈርደው፤ እርቁ ስርዓት በሌላ ጊዜ እና ቦታ እንዲፈፀም ተአስማምተው ተለያዩ፡፡ ይህን ያወቀችዉ "አሻዋ ለጅ"፣ የወንድሟ ዕደ ከፋይ ትሆን ዘንድ የተፈረደባት ጊብዚኒ አምርራ አለቀሰች፡፡ የምትውደውን ሰው በፈቃዷ ለማግባት ካለመቻሏም በላይ ምኑንም የማታውቀውን ሰው አግብታ፣ ወደፊት ልጆች ወልዳ እንዴት መኖር እንደምትችል ስታስብ ሀዘኗ የበለጠ በረታ ፡፡ በሌላ በኩል እህቱ ተድራ በሚገኘው ጥሎሽ አሱ እንደሚያገባ ተስፋ ያደርግ የነበረውና አሁን ሁሉም ነገር ከንቱ የቀረበት ኮሮይ የዚህ ሁሉ "ጦስ" ነው ያለውን ወንድሙን አፋይ መቼ አግኝቼ እኔዉ እራሴ በገደልኩት እያለ ይዝት ያዘ፡፡ ከሟች (ጳሎጋ) ቤተሠቦች ሸሽቶ አጦቱ ዘንድ የተሸሸገው አፋይ፣ እህቱ ጊብዚኒ በእሱ የተነሳ ለ "አሻ" ልትሰጥ መሆኑን ሲረዳ ህሊናው በፀፀት እረፍት ስላጣ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ብሎ አሰበ፡ እናም የእሱን ዕዳ እህቱ መከፈል እንደሌለባት እራሱን አሳምኖ ወደ ጳሎጋ ቤተሰቦችአመራ፡፡ እነሱም ጊዜ አላጠፉም፤ የልጃቸውን ገዳይ እንዳዩት ወዲያው ተረባርበው ገደሉት፡፡ በስተመጨረሻም ጊብዚኒ በኢፋ ሞት ለ "ኧሻ" ተላልፋ ከመሠጠት ተረፈች ደም - በደም ጠራ፡፡

[74] " አሻ" በመኢነት ባህል መሰረት ሴት ልጅ ለደምካሳነት የምትሰጥበት ስርዓት ሲሆን በዚህ ጥናት ወደፊት በዝርዝር የምንመለከተዉ ይሆናል፡፡

4.6.1. የአሻ ልጅ ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተዉኔት ዉስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች በዋናነት በመኢኔት ብሄረሰብ ጋብቻና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ክዋኔዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸውን በዝርዝር የምንመለከታቸው ይሆናል፡፡

4.6.1.1 ጋብቻን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በመኢኔት ብሔረሰብ ጋብቻ የተለየ ቦታ እንዳለዉ ይነገራል፡፡ ብሔረሰቡ ጋብቻን ከሚፈለግባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ዘርን የመተካትና በቁጥር ከፍ ብሎ የመገኘት ፍላጐት ነው፡፡[75] እንደማንኛውም ብሔረሰብ መኢኔቶች አይናቸውን በአይናቸው የማየት፣ በቤተሰብም ሆነ በጐሳና በብሔረሰብ ደረጃ ቁጥራቸውን የማሳደግ፣ ማሳዋቻቸውን በሰው ሀይል ለማሳደግ ያላቸዉ ፍላጐት ሳይነጋገሩ የሚግባቡበት፣ ልዩነት የማይታይበት፣ የማህበረሰቡ የጋራ ስምምነት ነው፡፡ በእነሱ እምነት ለቁጥር ማነስ በጠላት በቀላሉ ከመጠቃት ጀምሮ ለበርካታ ችግሮች መንስኤ ነው፡፡

ሌላው ብሔረሰቡ ጋብቻን አጥብቆ የሚፈልግበት ምክንያት የቅድመ ጋብቻ ወሲብ ክልከላ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ባህል መሰረት ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ ተደርጐ ቢገኝ እንኳ የተቀመጠው የብሔረሰቡ የቅጣት ህግ ከበድ ያለ ነው፡፡ አንዲት ሴት ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሟ ከተረጋገጠ በቤተሠቧ አባላት አማካኝነት ታስራ ከባድ ግርፋት ይደርስባታል፡፡ ለምን ይህን ተግባር እንደፈፀመችና ከማንስ ጋር እንደፈፀመች እውነቱን ካላወጣች በስተቀርም ግርፋቱ አይቆምም፡፡ በመሆኑም ሴቷ ከግርፋቱ ስቃይ ለመገላገል እውነቱን ትናገራለች፤ ፈፃሚውም ይታወቃል፡፡ ይህን በማህበረሰቡ ክልክል የሆነ ነገር በመፈፀሟ እንደረከሰች ስለምትቆጠርም በሬ ተቀጥቅጦ በደም በመታጠብ የመፅዳት ስርዓት መፈፀም አለባት፡፡

[75] አስታጥቃቸው ይሁን (ቃል-መጠይቅ)፣ አዲስ አበባ፣ ጥቅምት፣ 2010 ዓ.ም

ይህን እስክትፈፀምም ማንም ሰው ከእጇ ተቀብሎ አይበላም፤ ከማህበረሰቡ ጋርም መቀላቀል አትችልም፡፡ ከዚህ ሂደት በኋላ የሴት ወገኖች ቤተሰቡን የደፈረውን፣ የማህበረሰቡን ህግ የጣሰውን፣ የልጃቸውን ክብር ያረከሰውን ጐረምሳ በጦር መሳሪያ ማሳደዱን ይቀጥላሉ፡፡ ተፈላጊው እራሱን ካልጠበቀና ማህበረሰቡ ለዚህ አይነቱ ችግር ማርከሻ ያስቀመጠውን ሥርዓት በቶሎ ካልፈፀመ አንድም እንደአውሬ ዱር አደር ይሆናል፤ አንድም ነፍሱን ለጦር ወይም ለመሳሪያ አሳልፎ ይሰጣል፡፡ ታዲያ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ማህበረሰቡም ሆነ ቤተሰብ እጁን አጣጥፎ አይቀመጥም፡፡ የልጁ ቤተሠብ ከተለመደው የጋበቻ ጥሎሽ የበለጠ ጥሎሽ አዘጋጅቶ፣ እጅግ የተከበሩና የታፈሩ ሽማግሌዎችን መርጦ በመለማመን ወደ ህጋዊ ጋብቻ ይገባል፡፡ የሴቷን ወገን አሳምኖ ጋብቻውን ለመፈፀም የሚደረገው ሂደትም እጅግ አስቸጋሪና እልህ አስጨራሽ ይሆናል፡፡ ታዲያ ማህበረሰቡ ከተፈጥሯዊው የዝሙት ጠስም ሆነ የማህበረሰቡ ስሪተ ካስቀመጠው ሰው ሰራሽ ጦር ለመዳንና ከአላስፈላጊ ግጭቶች ለመራቅ በዘላቂ መፍትሄነት ጋብቻን አጥብቆ ይፈልገዋል፡፡

በተውኔቱ ውስጥ ሻምባይ የተባለች ወጣት ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማ በመገኘቷ በብሄርሰቡ ባህል መሠረት ከላይ የተጠቀሱት የቅጣት ህጐች ተፈፃሚ የሆኑባት መሆኑን ከዚህ በታች ከቀረበው ቃለ-ተውኔት እንረዳለን፡፡

ሻምባይ፡- /ጊቢዚኒን ተጠግታ አቅፋት እያለቀሰች/ ሌሊቱን ሙሉ ስገረፍ አደርኩ፡፡ ማን ከጋብቻ በፊት ክብረ ንፅህናዬን እንደገሰሰ እንድነግራቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ እየተፈራረቁ ክንዳቸው እስኪዝል ገረፉኝ፡፡

ጊበዚኒ፡- /ለቅሶዋ ይበረታል/

ሻምባይ፡- እስኪነጋ ድረስ ዱላውን ችየ ማን እንደሆነ አልተናገርኩም ነበር፡፡ ዱላው ሲያይልብኝ ግን ተናገርኩ፡፡ /ታለቅሳለች/

ጊብዚኒ፡- ለምን? ለምን?... ለምን...? በገዛ ልጃቸው በገዛ ስጋቸው ላይ እንዲህ ይጨከናሉ?

ሻምባይ፡- የመኢኔት ከጥንት የመጣ ባህል አይደል?

ጊብዚኒ፡ - እንዲህ ዓይነት ባህል... ለምን? ... ለምን?

ሻምባይ፡- አንዲት ሴት ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሟ ከተረጋገጠ በቤተሰቧ አባላት አማካይነት ታስራ ከባድ ግርፋት ይደርስባታል፡፡ ከማን ጋር እንደፈፀመች እውነቷን ካላወጣች ግርፋቱ አይቆምም፡፡

ጊብዚኒ፡- እኮ ለምን? ... ድንገት ተሳስተሽ በተፈጠረ ነገር... ለምን እንዲህ ይጨክኑብሻል? ... ለምን.... ለምን ... ለምን ... ለምን ...?

/ለጥቂት ተቃቅፈው ዝም ይላሉ፡፡ ወጣቶቹ ለጭፈራ ይዘጋጃሉ፡፡/
ጊብዚኒ፡- እና... ወደ ጭፈራው አንቀላቀልም?
ሻምባይ፡- እኔማ አልችልም፡፡ በማህበረሰባችን ክልክል የሆነ ነገር በመፈፀሜ እንደ ርኩስ ስለምቆጠር በሬ ተቀጥቅጦ በደም ታጥቤ እስክነፃ ከማህበረሰቡ ጋ መቀላቀል አልችልም፡፡

(ገቢ 1፣ ትዕ.1፣ 11)

ከዚህ ቃለ ተዉኔት መረዳት እንደሚቻለዉ ሻምባይ ከጋብቻ በፊት ወሲብ በመፈጸሟ በቤተሰቦቿ ከባድ ግርፋት ደርሶበባታል ፡፡ በተጨማሪም የመንጻት ስርዓት ገና ስላልፈጸመች “ጉሌ ” ተብሎ ከሚጠራዉ የወጣቶች ጭፈራ ተገላለች፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በዚህ ብሄረሰብ ቅድመ ጋብቻ ወሲብ በጥብቅ የተከለከለ በመሆኑ የሚበጀዉ በጊዜ የትዳር አጋርን ፈልጎ በጋብቻ መተሳሰር መሆኑን ነዉ፡፡ ከተግባራዊ ቲዎሪ አንጻር ሲታይ የቅድመ ጋብቻ ወሲብ ክልከላዉ መታቀብን የሚያበረታታ ከመሆኑ አኳያ በግብረስጋ ግንኙነት የሚዛመቱ እንደ ኤች. አይ. ቪ ኤድስ የመሳሰሉትን በሽታዎች ለመከላከል ይረዳል፡፡ እንዲሁም ባላገቡ ወጣቶች ዘንድ ያልተፈለገ እርግዝና እንዳይከሰት በማድረግ በኩል ጉልህ አስተዋጽኦ አለዉ፡፡

በመኢኔት ብሔረሰብ ጋብቻን እጅግ ተፈላጊ የሚያደርገው ሌላዉ ጉዳይ አለማግባት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያስከትለው መገፋት፣ መናቅ፣ የሚያሰጠው ክፉ ስምና የሚያሳድረው ከፍተኛ የስነ ልቡና ጫና ነው፡፡ በመኢኔት ብሄረሰብ ዘንድ ማግባት ባለበት ጊዜ ያላገባ ወይም እስከመጨረሻው ሳያገባ የሚቀር ሰው “ሾሽ” ይባላል፡፡ ሾሽ ማለት ምንም ነገር የሌለው፣ ድሃ፣ ስራፈት፣ ዋልጌ፣ ቦዘኔ፣ ለትዳር ያልተመረጠ፣

የተገፋና የተናቀ ማለት ነው፡፡ [76] አንድ ሰው “ሾሽ ” ሚል ስም ከተሰጠው በማህበረሰቡ የሚሰጠው ግምት አናሳ ይሆናል፡፡ እሱም የዚህ አመለካከት ተገዥ በመሆን ዝቅተኛነቱንና ሙሉ ሰው አለመሆኑን አምኖ በከፍተኛ ድብርት ውስጥ ህይወቱን ለመግፋት ይገደዳል፡፡ ለዚህም የተቀመጠው ብቸኛ መፍትሔ ጋብቻ የማጠይቀውን ዋጋ ከፍሎ ጋብቻን በጊዜው መፈፀም ነው፡፡[77]

ይህን በተመለከተ ፀሀፌ-ተውኔት አስታጥቃቸው ይሁን በተውኔቱ ውስጥ ከ ኮሮይ ገፀ- ባህርይ ጋር አያይዞ በሚከተለው መልኩ ያነሳዋል፡፡

> **ኮሮይ፡- እኔ ባባ---- በመኢኔት ባህል መሠረት ሾሽ ተብዬ ተዋርጄ ክብሬን አጥቼ ከምኖር ሀገር ጥዬ እጠፋለሁ፡፡**
>
> **አቶ ሙርዴች፡- ወዴት ነው የምትጠፋው?**
>
> **ኮሮይ፡- ወደ አንዱ... አውሬም ቢሆን ይብላኝ እንጂ ዕድሜዬ ግፍቶ ለጥሎሽ የሚሆን ሀብት ካላጠራቀምኩ ድፍን መኢኔት ታናሽ፣ ቆሞቀር ብሎ ንቆ ሲያሳልቅብኝ፣ ሾሽ የሚሉት ስም ሰጥቶኝ ዕድሜ ልኬን ተሳቅቄና አዝኜ ከምኖር አውሬ ይብላኝ፣ ወይ... ገደልም ቢሆን እገባለሁ... መቼም ጨክኜ በአንገቴ ላይ ገመድ አላስገባም፡፡**
>
> **(ገቢ1፣ ትዕ. 1: 9)**

---

[76] ብሩክ ተፈራ፣(2004)፣ “የተከፋኝ ሐገረሰባዊ ልማዶች ስርዓት በመኢኔት ብሔረሰብ ”፣ ለኢትዮጵያ ብሔሪዊ ቴአትር ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ጥናትና መርምር ክፍል፣ ለኪነጥበብ ሥራዎች ግብዓት ታስቦ የተዘጋጀ፡፡

[77] በመኢኔት ብሐረሰብ ጋብቻ መመስረት ለወንዱ ቀላል ተግባር አይደለም፡፡ ከፍትኛ መስዋተነትን ይጠይቃል፡፡ ለወንዱ ጋብቻን ፈታኝ የሚያደረግበት ዋናው ነገር ደግመ ማህበረሰቡ ለሴት ልጅ ማጫና ጥሎሽ በሶስት መንገድ የሚከናወን ነው፡፡ ይኸውም በጥሬ ገንዘብ፣ በከብተና በመሳሪያ ናቸው፡፡ አንድ ወጣት አግብቶ ከህይወተ አጋሩ ጋር በአንድ ቤት ለመኖር ከ 4-8 ሺ ጥሬ ገንዘብ፣ ከ 8-15 የቀንድ ከበቶች እና መሳሪያ ለሴቷ ቤተሰብ መክፈል ይጠበቀበታል፡፡ በጠለፋ ወይም ቅድመ ጋብቻ ወሲብ በመፈፀም በግልግል የሚፈፀም ጋብቻ ከሆነ የጥሎሽ መጠን ከፍ ይላል፡፡ የጥሎሽ መጠን በዚህ ብቻ ሳይሆን በሽማግሌ የህሊና ፍርድና በቤተሰቦች ቅንነት ሊወሰን የሚችልበትም ሁኔታ አለ፡፡

ይህም ቀደም ሲልም እንደተገለጸው ጋብቻ በመኢኔት ብሄረሰብ በጥብቅ ከሚፈለግባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ምናልባትም ዋናው ጉዳይ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ቀጥሎ በቀረበው ቃለ ተውኔት ዉስጥ ደግሞ በመኢኔት ባህል ለጋብቻ ስለሚቀርበዉ ጥሎሽ እንመለከታለን፡፡

ኮሮይ፡- ባባ... ለመሆኑ ለጊብዚኒ አንተ ለጋበቻ ያሰብክላት ሰው አለ?

አቶ ሙርዴች፡- አዎን... ያውም ምን የመሰለ የሀብታም ልጅ፡፡ ግን መጀመሪያ የፈቀደችው ቢሆን ይሻላል ብላ እናትህ ስለጨቀጨቀችኝ ነው እንጂ በልቤማ የመረጥኩላት አለ፡፡

ኮሮይ፡- ባባ... የቤተሰቡ ተስፋ ሁሉ ጊብዚኒ ናት.... ለእኔም፣ ለኢፋይም ለአንተና ለእማማም ጊበዜኔ ናት፡፡ እሷ ተድራ በሚመጣ ጥሎሽ ነው ተስፋችን፤ ሰውነታችን የሚለመልም፡፡ ስለዚህ ሃያን እንደምንም አሳምናትና ጊብዚኒ ከትምህርት ቤት ወጥታ ትዳር፡፡ እኛ ቆመን ከምንቀር "ሾሽ" ተብለን ተዋርደን ከምንሞት ይሻላል፡፡ ትምህርቱ የት ያደርሳታልና ነው፡፡

(ገቢ 1፣ ትዕ.1 :9)

ለጋበቻ በወንዱ በኩል የሚቀርበው ጥሎሽ ከፍተኛ በመሆኑ ከላይ እንደተገለጸዉ ኮሮይ ታናሽ እህቱ ጊብዚኒ ተድራ በሚገኘው ጥሎሽ እሱ እንደሚያገባ ተስፋ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ጊብዚኒ ትምህርቷን አቋርጣም ቢሆን እንድታገባ አባቱን አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አንደኛዉ ጉዳይ በመኢኔት ማህበረሰብ ለጋብቻ የሚቀርብ ጥሎሽ ውድ ዋጋን የሚጠይቅ መሆኑን ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ጥሎሹ ተወራራሽ ገጽታዎች የሚስተዋለበት መሆኑን ነው፡፡

ይኸውም በኮሮይ ንግግር ዉስጥ እንደተመለከትነዉ ፣ እህት ተድራ/አግብታ በሚገኘዉ ጥሎሽ/ሀብት ወንድም ያገባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ጥሎሽ ክፍያ ሌላውም ወንድም እንደዚሁ ያገባል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተውኔቱ ውስጥ

የተጠቀሱትን አራቱን የመኢኔት ብሔረሰብ የጋብቻ አይነቶች ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

• በጠለፋ ላይ የተመሰረተ ጋበቻ /ቀረን/

በማህበረሰቡ ጠለፋ ማለት ወንድ ልጅ የወደዳትንና ለትዳር አጋርነት የፈለጋትን ወጣት ከህጋዊ ጋብቻ በፊት ወደ ቤቱ በመውሰድ በህጋዊ ጋብቻ ዙሪያ መደራደረን የሚመለከት ሲሆን ሁለት መልክ አለው፡፡ አንደኛው የጠለፋ መልክ ሁለቱ ተጋቢዎች ተዋደውና ተፈቃቀደው ነገር ግን ቤተሰብ የማይፈቅድ ከሆነ፣ አልያም የጋበቻው ሂደት በቤተሰብ የሚጓተትና ሁለቱ ተጋቢዎች አብሮ የመኖር ፍላጐታቸው ትዕግሥት ሲያሳጣቸው የማፈፀም ነው፡፡ ሁለተኛው የጠለፋ መልክ ደግሞ እንዲትን ልጃገረድ ወንዱ በጣም ከወደዳትና ሴቷ ፈቃደኛ ሳትሆን በምትቀር ጊዜ የሚፈፀም ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አንድ ወጣት አንዲትን ልጃገረድ በፈቃዷም ሆነ አሰገድዶ ከመጥለፉ በፊት የሚያልፋቸው ሂደቶች አሉ፡፡[78]

አንድ ወንድ አንዲትን ልጅ ከመጥለፉ በፊት ቀልቡ ሊያርፍባት ይገባል፡፡ ለዚህም የመጀመሪያው ሂደት የመተያያ አጋጣሚዎችን መጠቀም ነው፡፡ ወንድ ልጅ በሀብት ደረጃ ለጥሎሽ የሚሆኑ ነገሮችን አሟልቻለሁ ብሎ ካመነ በዘፈን /ጉሌ/ ቦታዎች፣ በደቦ፣ በገበያ እና መሰል ቦታዎች ልቡ የሚያርፍባትን ወጣት ያፈላልጋል፡፡ ድንገት በአንዱ አጋጣሚ ከተገኘች በነ+ዚህ አጋጣማዎች ፍላጐቱን ይገልፃል፡፡ ከሚገልፅባቸው መንገዶች ውስጥ መዳራት፣ጡቷን መነካት፣ ትንባሆ እንድትሰጠው ወይም እንድተቀበለው መጠየቅ፣ ቦርዴ እንድትጋብዘው ወይም ግብግቦውን እንድትቀበል ማግባባት ይገኙበታል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ሴቷ ቀልቡ ቢያርፍባት እንኳ በቀላሉ እሽታዋን አትሰጠውም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማግባባት ጥረት ያደርጋል፡፡ ከነዚህ ጥረቶች ውስጥ አንዱ እሷን በጣም

[78] ብሩክ ተፈራ፣(2004)፣ “የተከፋኝ ሐገረሰባዊ ልማዶች ስርዓት በመኢኔት ብሔረሰብ ”፣ ለኢትዮጵያ ብሔሪዊ ቴአትር ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ጥናትና መርምር ክፍል፣ ለኪነ-ጥበብ ሥራዎች ግብዓት ታስቦ የተዘጋጀ፡፡

የምትቀርባትን ወጣት የሥጋ ዘመዷን ወይም ጓደኛዋን በአማላጅነት መላክም ሌላው መንገድ ነው።።[79]

ከብዙ ድርድር በኋላ እሽታዋን የመግለጽ አዝማሚያ ሲታይባት የተለየዩ ጥያቄዎችን ታቀርብለታለች።። ከነዚህም ጥያቄዎች የመጀመሪያውና ዋነኛው "ቤተሰቦቼ ለእኔ ይህን ያህል ጥሎሽ ይፈልጋሉ።። አሟልተሃል? ወይም በከንቱ ስሜቴን አስነስተህ ልትሸሽ እንዳይሆን?" በሚል ነው።። ወንዱ በደንብ በዚህ በኩል መዘጋጀቱን ከገለፀ "በመካከላችን ዝምድና አለመኖሩንስ አረጋግጠሃል?" የሚለው ይከተላል።። ይህንንም በሚገባ ከመለሰ ቀጠሮ ሰጥታው ይለያያሉ።። በቀጠሮው እለት ከመገናኘታቸው በፊት እሷ በመካከላቸው ዝምድና መኖር አለመኖሩን፣ የልጁን ስነምግባር፣ የዘር ሀረጉንና የቤተሰቡን የክብር ደረጃ ከቤተሰቦቿ ጋር እያነፃፀረች ታጠናለች።። ጥናቱን ካጠናቀቀች በኋላም ቤተሰቦቿን ፈቃድ ትጠይቃለች።። እሱም ነገሩ ወደ መስመሩ መሆኑን ስለሚገነዘብ ለጋበቻ የተቀመጡ የማህበረሰቡን ቅድመ ሁኔታዎች እያሰበ ለማሟላት ሲወጣ ሲወርድ፣ ሲዘጋጅና ሰው ሲያማክር ይሰነብታል።። ሁለቱም በየበኩላቸው የቤት ሥራቸውን ሠርተው በቀጠሯቸው እለት ከተቀጣጠሩበት ቦታ ይገናኛሉ።። በተገቢው መጠንና ጉዳይ ላይ በደንብ ከተነጋገሩና ከተግባቡ በኋላ ሙሉ እሽታዋን ትሰጠዋለች።። ትንባሆም ይገባበዛሉ።። ቦታው ምቹ ከሆነም ግብዣው ወደ ጠጅና ቦርዴም ሊያድግ ይችላል።። ቤተሰቦቿ ጋብቻን ካልፈቀዱ ወይም ቢፈቅዱም ሂደቱን የሚያዘገዩ ከሆነ በፍጥነት ከእሱ ጋር መሆን ስለምትፈልግ "ያው ጥሎሽ ነው ምን ይመጣል? ጥለፊኝ" በማለት ትነግረውና ለጠለፋው የምተገኝበትን ቀንና ቦታ ተቀጣጥረው ይለያያሉ።። በዚህ መሰረትም ጓደኞቹን አዘጋጅቶ በመጥለፍ ወደቤቱ ይወስዳታል።።

በሌላ በኩል ግን ወንዱ የሴቷን እሽታ ለማግኘት ያዋጣኛል የሚለውን መንገድ ሁሉ ሄዶ አወንታዊ ምላሽ ካላገኘ፣ አሰገድዶ የመጥለፍን መንገድ ይከተላል።። የቅርብና የልብ ያላቸውን ጓደኞቹን፣ የሥጋ ዘመዶቹንም ሊሆን ይችላል ምክር ይጠይቃል።። "ብለምን ባስለምን እምቢ አለችኝ፣ ለመተው ብሞክርም አቅም አነሰኝ፣ ሰለዚህ በዚህ ቀን እዚህ ቦታ ጠብቁ ለመጥለፍ ወስኛለሁና አጓቱኝ[80]"

[79] ዝኒ ከማሁ

[80] አጓቱኝ ማለት ለመጥለፍ አግዙኝ ለማለት ዘያዊ ቃልነዉ።።

በማለት እርዳታ ይጠይቃል። ከተመረጡት ሰዎች ጋርም በደንብ ከተመከረበትና ስልቱ ከተመረጠ በኋላ ልጅቱም ሆነ ቤተሰብ ሳይፈቅድ ጠለፋው ይከናወናል።

• በተጋቢዎች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጋብቻ

ይህ የጋበቻ አይነት በተጋቢዎች መፈቃቀድ፣ መዋደድና መፈቃቀር ተጠንስሶ ወደቤተሰብ የሚሄድ፣ የቤተሰብ ሙሉ ፈቃደኝነት ታክሎበትም ወደ ጋብቻ ህጋዊ መስመር የሚገባ ነው። በዚህ ጋብቻ ወንዱና ሴቷ በገበያ፣ በዘፈን፣ በደቦ ወይም ሌሎች አጋጣሚዎች በመተያየትና በተለያዩ የመገናኛ አጋጣሚዎችን በመፍጠርና ወደ ጥልቅ ፍቅርም በመግባት አብሮ የመኖር ፍላጐትን ያሳድራሉ። ሁለቱም በሀሳብ ብቻ ሳይሆን በአካልም ለመገናኘት በየበኩላቸው ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ። ትንባሆ እየተቀባበሉ በማጤስ፣ ጠጅና ቦርዴ በመገባበዝ፣ በሙፈራ /ጉሌ/ ቦታዎች ተፈላልገው በጋራ በመጨፈር፣ ወንዱ ጡቷን በመንካት፣ ሴቷም ፈቃደኛ በመሆን የፍቅራቸውን ደረጃ ከፍ ያደርጋሉ።

የፍቅራቸው ደረጃ ተገናኝቶ ለመለያየት ሀቅም ሲየሳጣቸው፣ ሰዋዊ የተፈጥሮ ስሜታቸው አይሎ ሲፈታተናቸው፣ በጋብቻ ሁኔታዎች ላይ በጋራ ይመክራሉ። የጋራ ስልት ይነድፋሉ፤ ከቤተሰቦቻቸው የጋብቻ ፍላጐትና ከሚጠይቁት ቅድመ ሁኔታ አንፃር መረጃ ይለዋወጣሉ። የሥጋ ዝምድና በመካከላቸው አለመኖሩን በጋራ ያጣራሉ። በተለይ ሴቷ ለጋብቻ ቁልፍና አይቀሬ የሆነውን የጥሎሽ መጠን ፍላጐት በተመለከተ በደንብ አጣርታና አስረግጣ ትነግረዋለች። ወንዱ ይህን ሁኔታ እስከሚያሟላም በፍቅርና በትግስት እንደምትጠብቀው ገልጻ በፅናት ትጠብቀዋለች።

ወንዱ የጥሎሹን ጉዳይ ከሞላ ጐደል ማሟላቱ በሁለቱም ተፈላላጊዎች ከተረጋገጠ ሁለቱም ፍላጐታቸውን ይዘው ወደየቤተሰቦቻቸው ያመራሉ። በልጆቹና በቤተሰቦቻቸው መካከል መፈራራት ከሌለና መግባባት ካለ የተፈቃሪዎቻቸውን የጀርባ ታሪክ በግልፅና በትክክለ በማስረዳት ለጋብቻ እንዲ ፈቅድላቸው፣ የእነሱም ፍላጐት ከፍተኛ መሆኑን ይገልፃሉ። ቤተሰቦቻቸውን የሚያፍሩና የሚፈሩ ከሆነ ደግሞ ለቤተሰብ ቅርብ ተሰሚነቱ ከፍ ያለ የሥጋ ዘመድ ወይም ጉረቤት በአማላጅነት ይልካሉ።

ጉዳዩ ቤተሰብ ከደረሰ በሁለቱም ቤተሰቦች በየግል ይመክሩበታል። በሁለቱም ቤተሰብ በኩል አስፈላጊው ምክክርና ማጣራት ከተደረገ በኋላ በየግል ስምምነት ላይ ይደርሳል። በተለይ በዚህ ሂደት የወንድ ልጅ አባት በሀሳብ ይወጠራል። "ይህ ልጅ እዳ ይዞብን መጣ፤ ነገር ግን ዕድሜያቸው ነው ምን ይደረጋል? የመረጠው ቤተሰብመ መልካም ነው፤ ልጅቱም ጥሩ ናት፤ ምን ይደረጋል" በሚል አቅሙን ይፈትሻል፤ ለጥሎሽ የሚሆነውን ሀብት መጠን ይመዝናል። የጐደለውን ከልጁ ጋር በመሆን ተመካክሮ ያሟላል። በጥሎሹ በኩል እርግጠኞች ሲሆኑም "ልጃችሁ ለልጃችን " በማለትና ሽማግለሌ ተልኮ በመደራደር የማህበረሰበቡ ማህበራዊ ስርዓት በሚፈቅደዉ መንገድ ወደ ሕጋዊው የጋብቻ መስመር የሚገባበት ሁኔታ ይፈጠራል። ወደ ሴት ቤት ሽማግሌ ከተላከ በኋላ ያለው የጋብቻ ስርዓት ከሞላ ጎደል ከጠለፋው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አንዳራዊ በሆነ መልኩ ግን የዚህ ጋብቻ ሂደት ከጠለፋ ጋብቻ በተለየ መልኩ ቀለል የለ ነው።

• በቤተሰብ መፈቃቀድ ላይ ተመሰረተ ጋበቻ /ጋመን/

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረዉ ፣ ጋብቻ ሂደቱ ከባድ ቢሆንም በማህበረሰቡ አይቀሬ እና ተፈላጊ ጉዳይ ነው። በመሆኑም መኢኔቶች በቤታቸው ወንድ ልጅ ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ከባድ የቤት ሥራ ይጠብቃቸዋል። ልጃቸው ለጋበቻ ይበቃ ዘንድ ሀብት ያጠራቅማሉ፤ እራሳቸውን በሥነምግባርና በመልካም ስም በማነፅ ተፈላጊ ቤተሰብ ሆኖ ለመገኘት ይጥራሉ፤ ልጁም ሀብት እንዲያከማችና በመልካም ሥነ ምግባርም ታንጾ በትክክለኛው ወቅት ለትዳር እንዲበቃ የበኩላቸውን ድጋፍ ያደርጋሉ። ከዚሁ ጐን ለጐን ግን ለልጃቸው የሚበጅ፣ በትዳር የሚያዛምዳቸውን ቤተሰብ ያፈላልጋሉ።[81]

በቤተሰብ መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተው የጋብቻ ሂደት "እናቲቱን አይተህ ልጅቱን አግባ" አይነት ነው። አንዲት ሴት ለመታጨት የቤተሰቦቿ የሀብትም ሆነ የመልካም ሰነምግባር የጀርባ ታሪክ ወሳኝነት አለው። በብሄረሰቡ ሀብታም መሆን የጥንካሬና የታታሪነት መገለጫም ጭምር በመሆኑ፣ የሴት ወገንም ሴት ለጅ ለትዳር

[81]አስታጥቃቸዉ ይሁን (ቃል- መጠይቅ)

መፈለግ የእሱ በቻ ሳይሆን የቤተሰበ ማንነት ወሳኝ መሆኑን ሰለሚያውቅ በቁስም ሆነ ህሊናዊ ሀብት ተፈላጊ ሆኖ ለመገኘት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።።

የወንድ ቤተሰብ ለልጁ የሚያጭበት፣ ለዝምድና የሚመረጠው ቤተሰብ አባት ጠንክሮ የሚያርስ፣ ከብትና ንብ የሚያረባ፣ ተናግሮ የሚደመጥ፣ ጠርቶ የሚያበላ፣ አመት እስከ አመት ቤቱን እራብ የማያውቀው፣ እናት የፈጨችው የገንፎ እህል ተርፎ የሚነሳ፣ የጠመቀችው ቦርዴ የጣፈጠ፣ ሠርታ የማትደክም መሆኑ በብዙ ጥናት ከተረጋገጠ፣ በቤት ከወለዲቸው ልጆች አንዲን ለልጃቸው ይመኛሉ።። የምትታጨው ልጅ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልትሆንም ላትሆንም ትችላለች።። ምክንያቱም የምትታጨው ልጅ ታጨች ማለት በቀጥታ ትዳር ይመሠረታል ማለት ባለመሆኑ።። [82]

ልጅቱ ከተመረጠች በኋላ የወንዱ እናትና አባት እንዲሁም የቅርበና የልብ ወዳጅ ዘመድ ጊዜ ወሰዶ ይመክርበታል።። “ይህችን ልጅ ለልጃችን ብንድር እንዴት ታድለናል? አባቷም እናቷም የተከበሩ መልካም ሰዎች ናቸው፤ እሷም መልካምና ጠንካራ ሴት ናት።።” በማለት ቤተሰቡ አንድ መቋጫ ሀሳብ ላይ ይደርሳል።። ይህ ሁሉ ሲሆን ልጁ እንዲያውቅ አይደረግም።።

ቤተሰቡ የቁርጥ ዉሳኔ ላይ ከደረሰ ፣ በቀጥታ ወይም በልጁ የልብ ወዳጆች ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለልጃቸው ይነገረዋል።። ከተነገረው ዕለት ጀምሮ ውሃ የምትቀዳበትን፣ እንጨት የምትሰብርበትን፣ በጉሊ ጭፈራ የምትገኝበትን፣ ገበያ የምትወጣበትን ወዘተ... ቦታና ሰዓት አጣርቶ ይመለከታታል።። ወንዝ ስትወርድ ውሃ በመቅዳት፣ እንጨት ስትሠብር አስሮ በማሸከም፣ ሰትጨፍር አብሮ በመጨፈር፣ ተንባሆ አብሮ በመሳብ፣ ቦርዴ በምተጠጣበት በመገኘትና በመጋበዝ የሚበቃውን ያህል ያጠናታል።። በመጨረሻም ልጅቱን ወደዳትም ጠላትም የቤተሰብ ፍላጐት አይጣስምና ይሁንታውን ይገልፃል፤ ባይገልፅም ቤተሰብ ቀጣዩን ሂደት ይሄዳል።።

ልጅቱም በተለይ ደግሞ ለአቀመ ሄዋን ለመድረስ የተጠጋች ከሆነች ወንዱ በዙሪያዋ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አልያም በወሬ ወሬ ጉዳዩን ትገምታለች።። እሷም ምንም

[82] እሰራኤል አድማሱ(ቃል- መጠይቅ)

እንኳ እምቢ የማለት መብት እንደሌላት ብታውቅም ጥርጣሬዋን በልቧ ይዛ የቻለችውን ያህል ታጠናዋለች፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነገሮች እየተብላሉ የወንድ ወገን ጊዜው አሁን ነው ብሎ ባመነ ጊዜ የልጅ እናት “ልጃችሁን ለልጄ” በማለት በልጅቱ አንገት ላይ “ጨሌ”[83] ታሥራለች፡፡ መጀመሪያም የወንድ ቤተሰብ ሲያሳዩ አቅሙን አውቆ አቻውን ለይቶ ምላሹን ገምቶ በመሆኑ እሽታውን ለሴት ወገን ይገልፃል፡፡

የሴት ወገን እሽታውን ከገለፀ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ጉዳዩን ለሴቷ ማሳወቅ ነው፡፡ “ልጄ ለተከበረ፣ ለተወደደ፣ አንቱ ለተባለ ቤተሰብ፣ መልካም ሥነምግባር ላለው ልጅ ልንሰጥሽ ነው ይኸው ጨሌ የሠራችልሽ ሴት አማችሽ ናት” በማለት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ባሏ እከሌ ፣ቤተሰቦቹም እነከሌ መሆናቸውን አውቃ ጊዜው ደረሰ ጋበቻ እስኪፈፀም እራሷን በማስከበር ለቤቷ የሚሆን ንብረት ለማፍራት ላይ ታች በማለት እንድትቆይ ይነገራታል፡፡

ሴቷም መጀመሪያም በተለያዩ ምልክቶችና ወሬዎች ቤተሰቦቿ ለዚህ ጉዳይ እየተዘጋጁ መቆየታቸውን ሰለምታወቅ ጉዳዩ በዙም እንግዳ አይሆንባትም፡፡ በእምቢታ የማንገራገር ስልጣኑም የላትም፡፡ ምክንያቱም በቤተሰብ የመጣን የጋብቻ ጥያቄ ለመግፋት መሞከር እርግማንን፣ መቅሰፍትን ያመጣል ተብሎ በጥብቅ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ለቃሉ ተገዥ በመሆን የጋበቻውን ቀን በጽናት ትጠብቃለች፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልጅቱን የመንከባከብ፣ ህፃንም ከሆነች አስፈላጊውን ነገር እያሟሉ የማሳደጉ ጉዳይ የሁለቱም ቤተሰብ ይሆናል፡፡ ጨሌውን ካሰረች ጊዜ ጀምሮም በማህበረሰቡ መለኪያ መሠረት ለአቅመ ሄዋን ደርሳ ህጋዊ የጋብቻ ሥርዓቱ እስኪፈፀም ድረስ የእከሌ ሚስት እየተባለች ተጠብቃ ታድጋለች፡፡ ወንዱም የወደፊት የትዳር አጋሩ መሆኗን ተገንዝቦ ቀኑን ከመጠበቅ ባለፈ ምንም አይነት ግንኙነት እንዲያደርግ አይፈቀድለትም፡፡

[83] ከአንገት የሚታሰር ጌጥ፡፡

• የውርስ ጋብቻ /ቀነስኤ/

የውርስ ጋብቻ አንድ ሰው ከሚስቱ ቀድሞ ከሞተ ሴቷ የምትፈፅመው ዳግም ጋብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ከሚስቱ ቀድሞ ከሞተ ከሟች ወንድሞች አንዱ ሚስቱን ተረክቦ /ወርሶ/ የሚያስተዳድርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ሟች ወንድሞች ከሌሉት እንኳ የአክስት ወይም የአጎት ልጆች ሊወርሱ ይችላሉ፡፡ ወራሽ የሚወርሰው ሚስቱን ብቻ ሳይሆን የሟችን ንብረትም ስለሚሆን የሟችን ልጆች እንደ ልጆቹ በማየት የማሳደግ ግዴታ ይጣልበታል፡፡[84]

ሟች ብዙ ወንድሞች ቢኖሩትና አንዱ የወንድሙን ሀብት በማየት በፍላጐቱ የወንድሙን ሚስት እወርሳለሁ ቢል አይፈቀድለትም፡፡ የሟችን ሚስት ወራሽ የመምረጡ ስልጣን ለቤተሰብ ተሰሚ ሽማግሌዎች የተተወ ነው፡፡ በመሆኑም ሟች ከሞተ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ “ካሉት ወንድሞቹ መካከል ሀብትና ንብረቱን ወርሶ ልጆቹን በትክክል የሚያሳድግ ማን ነው” በማል የቤተሰብ ሽማግሌዎች ከመከሩ በኋላ ከታላቅ ወንድሙ ጀምሮ ይመረምራሉ፡፡ ተክክለኛ ያሉትን ሰው ከመረጡ በኋላም የማዋረስ ሥርዓቱ ይፈፀማል፡፡ የሟች ሚስት “አይ ሀበት ንብረቴንና ልጆቼን ይገፍ፣ ሌላ ባል አግብቼ እኖራለሁ” ብትል እንኳ አይፈቀድላትም፡፡ ምክንያቱም ሚስት ወደዚህ ቤተሰብ ሰትቀላቀል ብዙ ጥሎሽ ተከፍሎባት በመሆኑ ይህን ሀብት ለሌላ ባዕድ አሳልፎ እንደመሰጠት ሰለሚቆጠር ማህበረሰቡ ለዚህ ያለው የማህበረሰባዊ ህግ ዝግ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሟች በህይወት ልጆች ወልዳ ሊሆን ስለሚችል ልጆች በባዕድ እጅ በበደል ያድጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ የልጆችን ህዘን ከፍ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሴቷም ቢሆን እንደ ልጅ ከኖረችበት ቤት ወጥታ አዲስ ቤተሰብና ባህሪ ለመልመድ ሰለምትቸገር ምንም እንኳ ባሏን ብታጣም ከቤተሰቡ ባለመለየቷ በተወሰነ መልኩ ትፅናናለች፡፡ መኢኔቶች ይህንን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት የውርስ ጋበቻን ይፈፅማሉ፡፡

የሟች ሚስት ዕድሜዋ የገፋና መውለድ የማትችል ከሆነ እንኳ “የእከሌ ሚስት” እየተባለች በባሏ ቤት ንብረቱን ይዛ በባል ዘመዶች እየተደገፈች ልጆቿን ታሳድጋለች፣ እንጅ ባሏ በመሞቱ ከልጆቿ ተነጥላ እንደ ባዕድ አትታይም፡፡

[84] እስራኤል አድማሱ (ቃል መጠይቅ)

ጋብቻን አስመልክቶ እስካሁን የቀረቡ ሀሳቦችን ለማጠቃለል ያህል፣በአጠቃላይ የተነሱት ሀሳቦች ከጋብቻ ጋር የተያያዙ እና የጋብቻን አስፈላጊነት የሚገልጹ ናቸዉ፡፡ ከዚሁ አንጻር ጋብቻ በወቅቱ መፈጸም እንዳለበት የሚመክሩ እንዲሁም ከጋብቻ በፊት የሚፈጸሙ የግብረሰጋ ግንኙነቶችን የሚያወግዙ ናቸዉ፡፡ በሌላ መልኩ ጋብቻን በወቅቱ መፈጸም ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኝ የሚገልጹ ሲሆኑ ከነዚህ መካከል አንዱ ጋብቻ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያሰጠዉ መልካም ሰም ነዉ፡፡ ከተግባራዊ ቲዎሪ አንጻር ሲታይ ደግሞ ጋብቻ በሰዉ ልጅ ሕይወት ዉደት ዉስጥ አሰፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ ፋይዳው ቤተሰብን ለመመስረትና ትዉልድን ለማስቀጠል ይረዳል፡፡ ስለዚህ በመኢኔት ማህበረሰብ ዉስጥ ጋብቻ አቢይ ስፍራ ያለው መሆኑን ይገነዘቧል፡፡

4.6.1.2 የ"አሻ" ባህላዊ የግጭት አፈታት[85] ስርዓትን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

እንደ አቶ እስራኤል አድማሱ (የዚህ ጥናት መረጃ ሰጪ) [86] አገላለጽ በ መኢኔት ብሄረሰብ አንድ ጥፋት የፈፀመ ግለሰብ በዘመናዊው ችሎት ቀርቦ ቅጣቱን ቢቀበል እንኳ እርቅ ማውረድ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም ዘመናዊው ህግ አስተማሪ ቢሆንም በሚች ወገን ልብ ያለን የቂም ቁርሾ አያደርቅም ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም በአንድ አካባቢ አንድ ግለሰብ አንድ ሰው ገድሎ ተደበቆ ከሆነ በገሳ መሪው የተመረጡ የአካባቢ ተወካዮች "እከሌ የተባለ ሰው የእከሌን ነፍስ አጥፍቶ እከሌ

---

[85] ግጭትና የግጭት መፍትሄ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው ተብሎ ይታመናል። የሰው ልጆች ዘወትር በግጭት ውስጥ ብቻ ሳይሆኑ መረጋጋትና ሠላምን ፈላጊዎች ናቸው። ይህ በመሆኑም እንደ Smith (1984) አገላለፅ የሰው ልጅ ግጭቶችን የሚፈታው አያሌ በሆኑ ዘዴዎችና የተለየዩ ሂደቶችን ማለትም መደበኛና ኢ-መደበኛ የሆነ መንገድ በመጠቀመ ነው። ከዚህም ውስጥ አንዱ የግጭት አፈታት ሲሆን፣ ተቃራኒ አካላቱ በውጊያ ወይም በማጣላት፣ የማጥቃት ድርጊት በመፈፀም ወይም ለሚገባው ተገቢውን ቅጣተ በመስጠት ነው። በተጨማሪም ግጭት በአበሳና በመከራ ወይም ወደፊት የሚደርሰውን(ማሚረት) መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል። በቡድን ማውገዝና መሳለቂያ ማድረግም ግጭትን ለመፍታት የሚጠቀምበት ሌላው ዘዴ ነው። በሶስተኛ ወገን ግጭትን ለማብረድና ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎች አሉ። እነሱም ድርድር (mediation)፣ ፍርድ (adjudication) እና የሶስተኛ ወገን ውሳኔ ሰጭነት ወይም (arbitration) ናቸው። Muliver (1979) በአደራዳሪ እና በፍርድ መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ አሰቀምጦታል። የሱ ስራም በይበልጠ ተኩረት የሰጠው ከዘመናዊ የፍርድ ሂደት ውጭ ያለውን የግጭት አፈታት ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ Muliver ሶስት ሐሳቦችን ያነሳል። እነሱም ስምምነት (negotiation)፣ የሶስተኛ ወገን ዳኝነት ወይም ሽምግልና (arbitration) እና ስምምነት (mediation) ናቸው። የመጀመሪያው ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጸው በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ሶስተኛ ወገን በመካከላቸው ሳይገባ፣ ለግጭቱ በራሳቸው ጥረተ ተቀባይነት ያለውን መፍትሄ የሚፈልጉበት ሂደት ነው። የሁለተኛው ፅንሰ ሐሳብ የማገልፀው በግጭት ውስጥ ያሉት ወገኖች ሶስተኛ ወገን ጣልቃ በመግባት የሚሰጣቸውን ውሳኔ ለመቀበልና ለማክበር የሚስማሙበት ሁኔታ ነው። ሶስተኛው ፅንሰ ሀሳብ ከሶስተኛ ወገን ዳኝነት የሚለየው ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች የአደራዳሪውን ውሳኔ ለመቀበል ይፋ በሆነ መንገድ አይስማሙም። በሽምግልና የሶስተኛ ወገን ተግባር በጠቡ ውስጥ ያሉ ወገኖች ተቀራርበው በመነጋገር እንዲግባቡ ማበረታታት ነው። በውስጡም ገለልተኛና የአድልኦ ነፃ የሆኑ አማካይ ሰዎች ወይም አንጋፋ የሀገር ሽማግሌዎችን የሚያካትት ነው። በመኢኔት ብሔረሰብ ውስጥ የሚታየውም ይህን መንገድ የተከተለ ነው ማለት ይቻላል።

[86] አቶ እስራኤል አድማሱ (የመኢኔት ብሄረሰብ ተወላጅ) ፣ ቃል-መጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ ህዳር 2010 ዓ.ም።

ቤት ተደብቋል። የሟች ወገኖች የበቀል ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት መፍትሔ ይበጅ" በማለት ለጐሳ መሪው ጥቆማ ይሰጣሉ። የጐሳ መሪውም ነገሩን ከመረመረ በኋላ ሳይውል ሳያድር ሶስት ሽማግሌዎችን በመምረጥ ወደ ገዳይ ቤተሰብ ይልካል። የሀገር ሽማግሌዎቹም ወደ ገዳይ ቤተሰብ በመሄድ ቤት ሳይገቡ ከገዳይ ወገን ትልቅ፣ በቤተሰብ የሚከበርና የሚደመጥ ሰው ካለ እሱ እንዲጠራላቸው ያደርጋሉ። ያም ሰው ከመጣና ሽማግሌዎችን ከአንድ ዛፍ ስር ቦታ ሰጥቶ ካስቀመጣቸው በኋላ ከፊታቸው በመቆም ቃላቸውን ለመስማት ይዘጋጃል። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ "እኛ የመጣነው እከሌ የተባለው የጐሣ መሪ ልኮን ነው። የእናንተ ሰው እከሌ የተባለን ሰው ህይወት አጥፍቶ ተደብቋል፤ እንዴት እንደዚህ ይደረጋል? የጠፋውን ሰው እንድትተካ፣ ሰውየውን እንድትከፍል፣ ቃል ይዘን መጥተናል" ይላሉ። የገዳይ ተወካይም "እንግዲህ ሁለት በሮች ተጣሉ አንዱ ገደል ገባ። ሁለት አንበሶች ተናከሱ አንዱ ቆሰሎ ሞተ። ዘመድ ሰብስቤ መክሬ እከፍላለሁ እንጅ ከሽማግሌ አልወጣም" ይላል። ሽማግሌዎቹም "ቶሎ በል አገር ሳይረበሽ ሌላ ነፍስ ሣይወድቅ" በማለት የተወሰነ ጊዜ ይሰጡታል።

ተወካዩ የሽማግሌዎችን ቃል ይዞ በመመለስ የቤተሰቡን አባል በሙሉ ያማክራል። "ጊዜዉን ጠብቆ ይሞት የነበረውን የሰው ሰው ጊዜ ሞቱ ሳይደርስ ሰብረነዋል፤ አጥፍተነዋል፤ ሰው አስቀይመናል" በማለት ለጊዜው ለሟች መቀበሪያ አንድ ኮርማ፣ ለመቃብር ቆፋሪዎች ምግብ ማዘጋጃ እስከ 2000 ብርና አንድ የሟችን ትዝታ ወልዳ የምትተካ ሴት ለጅ በካሳነት /አሻ/ በፍጥነት እንዲዘጋጅ የደረጋል። በዚያው ዕለትም ሽማግሌዎች ከተቀመጡበት ሳይነሱ ሶስቱም ጥያቄዎች ተፈጻሚ መሆን አለባቸው።

ኮርማ የሚዘጋጃው ሟች የሚቀበረው በበሬ ቆዳ ተሸፍኖ በመሆኑ ለከፈን ሲሆን፤ ሁለቱ ሺ ብር ደግሞ መቃብር ቆፋሪዎች ብዙ ላብ ስለሚያፈሱ ምግብ ተገዝቶ የሚመገቡበት ነው። ይህን ወጪ መሸፈን ደግሞ የአጥፊ ድርሻ ነው። ሴት ልጅ በአሻ / የደም ካሣነት/ የምትሰጠው ደግሞ "ሟች በመሞቱ አንድ ሰው ከቤተሰብ ጐድሏል በመሆኑም ይህች ሴት ከዚያ ቤት በምትቀላቀል ጊዜ በርካታ ልጆች ስለምትወልድ በምትወልዳቸው ልጆች አማካኝነት ሟች ቀስ በቀስ ይረሣል" በሚል እምነት ነው።

ተወካዩ የታዘዘውን ይዞ ወደ ሽማግሌዎች በመቅረብ "በታዘዝኩት መሠረት በሬውም፣ ብሩም ይኸው የምንሰጣችሁ ሴትም እከሊት ትባላለች፤ ጀግናውን ቅበሩት" በማለት እጅ ይነሳል። በዚህ ጊዜ ልጅቱ በዚያው ዕለት በአካል ስለማትሰጥ ወይም ሽማግለዎች ሰለማይረከቡ ሕፃንም ሆነች ድርስ እንዳስፈላጊነቱ ሽማግሌዎች በአካል ማየት ከፈለጉ ትታያለች። ከዚህ በኋላ ስሟንና እድሜዋን በመመዝገብና ቀሪ ስጦታዎችን ይዘው በመመለስ ለላካቸው የጐሣ መሪ ሪፖርት ያቀርባሉ።

የዚህ ቅድመ ሁኔታ መፈፀም በሚች ወገኖች ላይ መረጋጋትን ይፈጥራል። ከጥፋት፣ ከበቀልና መሰል ተግባሮች በመታቀብ በሶስት ቀናት ተረጋግተው የሚችን ሀዘንና ቀብር እንዲፈፅሙ ያደርጋቸዋል። ሟች ከሞተ ከሶስት ቀን በኋላና የሚች ወገኖች ፀጉራቸውን ከተላጩ ወደ ዋናውና የመጨረሻ ዘላቂ መፍትሔ ወደ ሚያመጣው እርቅ ይገባል። ሟች በሞተ በሶስተኛው ቀን የሟች ወገኖች ምግብና መጠጥ ይዘዉ ወደ ወንዝ ይወርዳሉ። የገዳይ ወገን ግን ከምግብና መጠጡ በተጨማሪ ለአሻ/ካሳ/ የተሠጠችውን ልጅ አልያም ሴት ልጅ ከሌለች በምትኳ ከሰባት ከብት ሌላ ተጨማሪ ሰባት ከብቶች ለካሣ፣ አንድ በሬ ለአክስት ልጅ፣ ለማስታረቂያ የእርድ በግ ወይም በሬ ይጠበቅባቸዋል።

ሁለቱም የሚበላና የሚጠጣ ነገር ይዘው የሚመጡበት ምክንያት ተበዳይ ቀድሞ ጥሉንና መከፋቱን የሚገልፀው የበዳዩን እህል ውሃ "አልቀምሰም" በማለት ስለሆነ የሁለቱንም ምግብ ቀላቅሎ በማብላትና በማጠጣት በእርቁ ሂደት የችግሩን አንድ አካል ለመቅረፍ ነው። በዳይ ወገን ለአሻ የምትሰጥ ሴት ልጅ ከሌለችው በእሷ ምትክ ሰባት ከብት መክፈል ይጠይቃል። ሰባቱ ተጨማሪ ከብቶች በማህበረሰቡ የተለመዱ የካሣ መጠኖች ናቸው።[87] አንድ በሬ ለአክስት ልጅ የሚሰጠውም ለሟች የቅርብ ዘመድ በመሆኑና ከሰባቱ ከብቶችም ስለማይደርሰው በግለ ቂም ይዞ "አገላለሁ" እንዳይል ነው። ሌላው አንድ በግ ወይም በሬ የሚያቀርቡት ግን እርቅ የሚፈፀመው በአንስሳ ደም በመሆኑ ለሰርዓቱ መፈፀሚያ ነው።

ገዳይ ሆን ብሎ አልሞና አቅዶ ግድያውን የፈፀመ ከሆነ ከላይ የተጠቀሰውን ሁሉ ካሣ የሚከፍለው በዚያው በእርቁ እለት ይሆናል። ምክንያቱም የተንኮሉን ያህል

[87] አስታጥቃቸው ይሁን፣ እስራኤል አደማሱ(ቃል መጠይቅ)

መጨነቅ፣ መጠበብና መጸጸት ስላለበት ነዉ። ነገር ግን ገዳይ የገደለው አቅዶ ሣይሆን በስሀተት ለእንሰሳት በወረወረው ጦር ወይም በተኮሰው ጥይት፣ ወይም መሣሪያ ባርቆ ... ከሆነ ሁሉንም ካሣ በአንዴ እንዲከፍል እይገደድም። ከ6 ወር እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ሊሰጠው ይችላል። ነገር ግን በእርቁ ዕለት አብላጫውን ይዞ መቅረበ አለበት።

ይህን ሁሉ አሟልተው ሁለቱም ወገኖች ወደ ወንዙ ከወረዱ በኋላ ወንዙን በመካከላቸው በማድረግ ማዶና ማዶ ይቀመጣሉ። ወንዙ በጥለኞች መካከል የሚሆነው በማህበረሰቡ ወንዝ አንድም እንደ ንጉሥ ሰለሚታይ አንድም "ቂም በቀሉን ይዞት ይወርዳል" ተብሎ ስለሚታመን ነው። በመቀጠልም በሁለቱም ወገን ሶስት ሶስት ሽማግሌዎች ተመርጠው በጥለኞች መካከል እየተመላለሱ የማደራደሩን ስራ በትልቅ ድካም ይወጣሉ።

የአሻ ክፍያው ሲጀመር በገዳይ ወገን ያሉ ሽማግሌዎች በመጀመሪያ ሶስት ከብቶችን ይዘው ወደ ሟች ወገኖች ያቀርባሉ። ይህ "የጦር ማሠሪያ" ይባላል። ከዚያ ጐን ለጐን ለአከሰት ወይም ለአጐት ልጅ ካለ በሬ ይሰጣል። በዚህ ጊዜ "ጦር ታሰረ፤ ጥል ታሰረ፤ ይባላል።" ሁሉም ሰው ይቀመጣል። " መንቀሣቀስ ጥላ ያስመታል ጦራችሁን፤ ጠብመንጃችሁን፤ ስለታችሁን መሬት አስቀምጡ" ማለት ነው። ጦር ከታሠረ በኋላ አራቱ ከብቶች ለሟች ወገን ይጨመራሉ። በዚህ ጊዜ ሴቷም ልጅ ለሟች ወገን ትበረክታለች። ሴቷ ከሌለችም ተጨማሪ ሰባት ከብቶች እሷን ተክተው ይሰጡና የከብቱ መጠን ከ14 እስከ 15 ከፍ ይላል።

የካሳ /አሻ/ ስርዓቱ ከተፈፀመ በኋላ ሁለቱም ወገኖች በአንድ ትልቅ ዛፍ ሥር ይሆኑና አንድ ከሁለቱም ወገን ያልሆነ ሰው ተመርጦ በጉን ወይም በሬውን ያርዳል። ደሙንም በእንዳውላ /ቃርዲ/ ቅጠል እየነከረ በሁለቱም ወገኖች እየረጨ "በፈሰሰው የሰው ደም ጥል ተፈጠረ፤ አሁን ግን በዚህ የእንሰሳ ደም ተፈውሷል" በማለት በቅጠሉ ይረጫል። የበሬውን አንጀት በማውጣትም በአንድ ወገን ጫፍ በዳይ በሌላው ጫፍ ደግሞ ተበዳይ እየዋጡ አስታራቂውም ዳግም ላይጋጩ ቃል ያሰገባቸዋል። በመጨረሻም "በእናንተ መካከል የተፈጠረው ጥል እንግዲህ ተቆርጧል" በማለት ሁለቱ ወገኖች እየዋጡ ያሉትን አንጀት በጦር መሃሉ ላይ ይቆርጣል።

በመቀጠልም ሁለቱም ወገኖች ያመጡት እህል ውሃ በአንድ ዕቃ ይቀላቀልና በጋራ በአንድ እቃ ለሁለት ለሁለት እየሆኑና እየተቀባበሉ እንዲጠጡ፣ በአንድ ማዕድም በጋራ እንዲመገቡ ይደረጋል። ከሽማግሌዎች አንዱም እህል ውሃውን በሚያገናኝ ጊዜም "ከዚህ በኋላ ምግቡና መጠጡ እንደተቀላቀለ ተቀላቀላችኋል፤ በአንድ እንደበላችሁና እንደጠጣችሁ አንድ ሆናችኋልና" እያለ ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላ የጥል ግድግዳ በትኩሱ ይፈርሳል፤ ሰላም ይፈጠራል፤ ህይወት በተረጋጋ መልኩ ይቀጥላል። ለአሻ የተሰጠችው ሴት በምትወልዳቸው ልጆችም የቂም ጠባሳው እየሻረና እየተረሳ ይሄዳል። ሴቷም የዝምድና የማይበጠስ ሰንሰለት በመሆን ታገለግላለች።[88]

በተውኔቱ ውስጥ የአሻን ጉዳይ የተነሳበትን መንገድ በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል። ይኸውም አንደኛው ከባህላዊ የግጭት አፈታት አንጻር ሲሆን ሌላዉ ደግሞ በሴቶች ላይ ካለው አለታዊ ተጽዕኖ አኳያ ነው። እነዚህን ሁለት ተቃራኒ የሚመስሉ ሐሳቦች ከዚህ በታች በቀረቡት ቃለ ተዉኔቶች አሰረጅነት በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

1. **አቶ ሙርዴች፡- ምን መሆነህ ነው አቶ ሻያ? ... ለእኔም እዘንልኝ እንጂ። ከሀገር ልማድ ከሀገር ወግ ወጥቼ እንዴት ልሆን ነው? ... ደም ይድረቅ... ልጃችሁን ጊብዚኒን ለአሻ ካሣነት ስጡ ብሎ ... አሽ ብለን ቃላችንን ሰጥተን ከመጣን በኋላ ምን አርግ ተለኛለህ?**

   አቶ ሻያ፡- ያንድ ልጅህ ጉዳይ እኮ ነው።

አቶ ሙርዴች፡- እና የሆነስ እንደሆን? ... እንዴ ... ምን መሆነህ ነው። እውን ይህቺን መተኪያ የሌላት ልጅን ሳልወዳት ... ወደማታውቀው ጨለማ ስሰዳት ሆዴ ሳያዝን ... ሳልረበሽ ቀርቼ መስሎህ ነው?... ግን ምን ልሁን? ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነዉ። ዛሬ በእኔ ላይ ሲደርስ አሻፈረኝ ብል ... በየጊዜዉ አስታራቂ ሽማግሌ የሆንኩ ልጃቸዉን ለአሻ እንዲሰጡ ስበይንባቸዉ የኖርኩ ሰዉ ነኝ። መኢኔት ምን የሚለኝ መስሎሃል?

[88] አስታጥቃቸዉ ይሁን፣እስራኤል አድማሱ(ቃል መጠይቅ)

አቶ ቢለሙ፡- ቆይ ያልገባኝ ነገር ... አቶ ሻያ ... ምንድነው ይሁን የምትለው?

አቶ ሻያ፡- እስኪ እንምከርበት፡፡

አቶ ቢለሙ፡- /ድነገት ቱግ ይላሉ/ ምነድነው እንምከርበት ማለት? ...ኧ? ... ያገር ልማድ ... ያገር ባህል እናፍርስ ነው?

አቶ ሻያ፡- እናፍረስ ሳይሆን...

አቶ ቢለሙ፡- ነው እንጂ... እናፍርስ ነው እንጂ የምትለው ... እንዴ? ... ያገር ሽማግሌ በስንት ገጽ የጨረሰውን ነገር? ... የግዳይ ቤተሠብ በባህሉ ... በወጉ .... በሰረዓቱ መሠረት የአሻ ክፍያውን ልጃገረድና ሰባት ከብት ለክፍያ ያዘጋጅ፣ እንዲሁም ለቀበር ማስፈፀሚያ ሁለት ሺህ ብር ይሰጥ ብሎ... አኛም እሺ ብለን ተስማምተን ... የሟችም ቤተሠብ ወደ በቀል እንዳይገባ ተብሎ ተወስኖ እያለ መልሶ እንመካከር ይባላል ?...

(ገቢ 1፣ ትዕ 3፣ 27)

ከላይ ከቀረበዉ ቃለ ተዉኔት መረዳት እንደሚቻለዉ ፣አቶ ሙርዴች ምንም እንኳ ልጃቸው ጊብዚኒ የወንድሟ የደም ካሳ ከፋይ ሆና ለአሻ መሰጠቷ እንደ ወላጅ አባት ለእሳቸው መራራ ሀዘን ቢሆንም፣ የሀገር ልማድ ሰለሆነና ከአሁን በፊት ድርጊቱ በሌሎች የመኢኔት ሴቶች ላይ ሲፈፀም እያዩ ከመቃወም ይልቅ እየደገፉ የኖሩ ከመሆናቸው አንጻር አሁን በእራሳቸው ልጅ ላይ ሲደርሰ “አይሆንም” ብለው የሚያስቆሙበት ምንም አይነት የሞራል አቅም አላገኙም፡፡ ስለሆነም ሐሳባቸው ለሁለት ተከፍሎ ከገዛ ህሊናቸው ጋራ ሙግት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በመጨረሻም አንዱን የግድ መምረጥ ስለነበረባቸው በልጃቸው ላይ ፈርደው፣ የማህበረሰቡን የቆየ ባህልና እምነት ደግፈው አሻዉን ተቀብለዋል፡፡ በሌላ በኩል ጊብዚኒና መሠሎቿ የመኢኔት ሴቶች እነሱ ባልሠሩት ስራ፣ ባልፈፀሙት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ እየተፈረደባቸው ለአሻ የሚሰጡበት ይሄ ባህላዊ ሰርዓት ያልተዋጠላቸው የአገር ሽማግሌ አቶ ሻያ ጉዳዩን “ቆም ብለን እናስብበት ” የሚል ሐሳብ አቅርበዋል፡፡ በአንጻሩ ሲወርድ ሲወራረድ ከኖረው የመኢኔት ብሔረሰብ ባህል በተቃሪኒ ሆኖ ያገኙት ይህ የአቶ ሻያ ሐሳብ ክፉኛ ያስቆጣቸው ሌላኛው የአገር ሽማግሌ አቶ ቢለሙ “ምን ሲደረግ” ሲሉ አቶ ሻያን ሞግተዋል፡፡ የእሳቸው የተቃውሞ ሐሰብ ዋና

ማጠንጠኛ ሆኖ የቀረበዉ ደግሞ “የአገር ሽማግሌ በገዳይና በሟች ቤተሰብ መካከል እርቅ እንዲወርድ የለፉበት ጉዳይ ነዉ” የሚለው ነው፡፡ ይህም ከተግባር ቲዎሪ አንጻር ሲታይ“ አሻ” በመኢኔት ብሄረሰብ ዘንድ የነፍስ ግድያን ተከትሎ ሊከሰት የሚችል ቂምና በቀልን በማስወገድና በገዳይ እና በሟች ወገኖች መካከል እርቅና ሰላም በዘላቂነት እንዲፈጠር በማድረግ ረገድ ያለውን ፋይዳ ያመለክታል፡፡

2. **ጊብዚኒ ... መኢኔት መልስልኝ!! ለምን!! ... ለምን!!!... ለምን!!! ሴት ልጅህ አይደለችም... ሴት.... እህትህ አይደለችም... ሴት እናትህ አይደለችም... ሴት ሚስትህ አይደለችም... ሴት ፍቅርህ አይደለችም... የህይወት መራራ ስፍነግ የሚጣፍጠው በሴት አይደለም... የሞት ሠራዊት ትውልድ እንዳያጠፋ በልጅ ጻዳ ዳግም ህይወት የምታሳይህ ሴት አይደለችም... ለምን በሴት ትጨክናላችሁ? ... ለምን... መልሱልኝ!! ... አቤት ጭካኔ... በራሳችሁ ላይ እንዲመጣ የማትፈልጉትን የመከራ ሸክም በእኛ ላይ ሰትጭኑ አያማችሁም... ፍቅር፣ ህይወት፣ ደስታ፣ ሰላም የምንሰጣችሁ እኛ ላይ ትጨክናላችሁ? ... ፍቅር የምንሰጣችሁ እኛ ሴቶች ላይ ስትጨክኑ ምንም አይቆረቁራችሁም?... እንግዲህ ተስፋዬን አጥቻለሁ፣ ፍቅሬን አጥቻለሁ፣ ደስታዬን ተቀምቻለሁ ሁለት ሰዎች መሃል ወድቄአለሁ፡፡ ፈጣሪ ...ቱም ሐይል ስጠኝ! አንዱን ሰይፍ እንድመርጥ ፈጣሪ ቱም ሐይል ስጠኝ፡፡**

(ገቢ 1፣ ትዕ 1፣ 20)

በዚህ ቃለ ተውኔት “ለምን?” ስትል ማህበረሰቡን አጥብቃ የምትጠይቀው ወንድሟ ሰው በመግደሉ የእሱን ዕዳ ለመክፈል በአሻ (የደም ካሳ) ተላልፋ ለሟች ቤተሰብ እንድትሰጥ በመኢኔት የባህል ህግ መሠረት የተፈረደባት ጊብዚኒ ናት፡፡ ከፌሚኒዝም ቲዎሪ አኳያ ሲታይ ፣ጊብዚኒ እንደገለጸችዉ፣ አሻ በሴት ልጅ ላይ የሚፈጸም እጅግ የከፋ በደል ስለሆነ ሊቆም ይገባዋል ፡፡ ይህን መልዕክት ለማስተላለፍም ይመስላል ፣ ደራሲዉ በተዉኔቱ ፍጻሜ ላይ ጊብዚኒን ለ አሻ ከመስጠት ይልቅ ፣ ኢፋይ ለሟች ወገን እጁን እንዲሰጥና እንዲገደል እሷም ነጻ እንድትወጣ ማድረግን የመረጠው፡፡

4.7. ፋቡላ

ፋቡላ የተለያዩ እንስሳት የሰውን ባህሪይ ተላብሰው የሚጫወቱበት ኮሜዲ ተውኔት ነው።።ይህ ተውኔት በሀገራችን የመጀመሪያው ቴአትር ተደርጐ ይወሰዳል። ለዚህ እንደማስረጃ ሊጠቀሱ ከሚችሉት መካከል አንደኛው፣ ከዚህ በፊት ምንም አይነት የተፃፈ ወይም ለመድረክ ተዘጋጅቶ የቀረበ ተውኔት የሌለ መሆኑ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ፀሐፊው፣ በጅሮንድ ተክለሐዋርያት እራሳቸው በተውኔቱ መግቢያ ክፍል የገለፁት እንዲህ የሚለዉ ሐሳብ ነው። "... **እኛ ግን መጀመሪያ ቲያትር እንዲቋቋም ምሳሌውን ለማሳየት ይህን ፋቡላ-የአውሬዎችን ኮሜዲያ ጽፈናል ። የአገራችንን ሰዎች በመልካም አስተያየት ይቀበሉናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን**" (ተክለሀዋርያት፣1906፡1) ። ይህን ሐሳብ የሚያጠናክር እንዲህ የሚል ጽሑፍ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰፍሮ ይገኛል። "... **ይህ ጥቅም ያለው የትያትር መጽሐፍ ክቡር በጅሮንድ ተክለሐዋሪያት ጽፈው ለህፃናት አስጠንተዉ በ1906 ዓመተ ምህረት በሙሴ ቴራሲ ሆቴል የቴአትሩን ጨዋታ አሳይተው፣ ጥቂቶቹን ሰዎች እንጂ ብዙዎቹን ደስ ለማሰኘት አልሆነላቸውም ነበር። ምክንያቱም በዚያ ዘመን ከአዋቂዎች አላዋቂዎች ስለበዙ ነው**"[89]። በዚህ ተዉኔት የተሳተፉት ሁሉም ገጸ ባህርያት እንስሳት ሲሆኑ፣ ቃለ ተዉኔቱ የቀረበበት መንገድ ደግሞ በተረት አማካኝነት ነዉ። ከዚህ አንጻር ስናየዉ በዚህ ጥናት ከተካተቱት ተዉኔቶች በሙሉ ፋቡላን የተለየ ያደርገዋል።

4.7.1. ፋቡላ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

ቀደም ሲልም እንደተገለጸዉ በዚህ ተዉኔት ዉስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች በተረት[90] ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ በዋናነት ገላጭ ተረቶችን እና ፋቡላዎችን

---

[89] አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ህዳር 29 ቀን፣ 1925 ዓ.ም፣ ገጽ 2።።

[90] ዘሪሁን አስፋዉ ስለተረት ምንነት ሲያብራራ "...ይህ የስነ ቃል አይነት በእንስሳትና በአራዊት፣ በተፈጥሮ ገፅታዎች፣ እንዲሁም በሰዎችና ከእውነት ዓለም ሰዎች ለየት ያለ መልክ፣ ባህሪና፣ ችሎታ በተሰጣቸው የምዕናብ ዓለም ሰዎች አማካይነት የሰዎችን ሠናይና እኩይ ባህርያትና የተለያዩ ድርጊቶች ያሳያል" በማለት ይገልጻል (1992፡29) ።

ይመለከታለ።።[91] በመሆኑም እያንዳንዳቸዉን ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር የምንመለከታቸዉ ይሆናል።።

4.7.1.1 ገላጭ ተረቶችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ተውኔት የምናገኛቸዉ ገላጭ ተረቶች የዓለምን አፈጣጠር የሚተርኩ፣ የልዩ ልዩ ነገሮችንና ፍጥረቶች ባህርይና ከዚህ ጋር ተያይዘው የሰው ልጅ ገጠመኝ የሚገልፁ ናቸው።። ቀጥሎ በቀረቡት አስረጅዎች አስደግፈን እናያቸዋለን።።

1. <u>አንደኛ በግ ፡-</u>

ዓለምን እግዚአብሔር በጥበብ መስርቶ

በንዋይ በሲሳይ አሳምሮ ሞልቶ

ነፍሶችን በድኖችን በያይነቱ ፈጥሮ

ፀሀይን ጨረቃን ከዋክብትን ቆጥሮ

ሙቀትን ነፋስን ውሃንም ቀምሞ

ሁሉን እርስ በርሱ አቻችሎ ገጥሞ

ለሁሉም ማፍረሻ አጥፊውን ሰጥቶታል

<u>ሁለተኛ በግ ፡-</u>

ደግሞ እልም ብሎ ጭራሽ እንዳይጠፋ

መመከቻቸውን አብሮ ፈጥሮለታል

<u>ሶስተኛ በግ ፡-</u>

መድሃኒቱን ሲያበጅ ማርከሻ አድርጐለታል

---

[91] ፍቃደ አዘዘ ተረቶችን በተለያዩ መንገዶች ከልስፎ (Classify አድርጎ) ማጥናት የሚችል መሆኑን ለማሳየት የ Okepho ሶስት የ Classification ዘዴዎችን ይጠቅሳል።። እነሱም፡- ሌጀንድ፣ ገላጭ ተረቶች (Exploratory tales)፣ እና ፋቡላዎች (Fables) በማለት እንደሆነ ይገልጻል (1991፡51-62)።።

<u>አራተኛ በግ</u>

እንዲህ በመካከል ሳትጠብ ሳትሰፋ

ዓለም ትኖራለች ታመት ዓመት አልፋ

(ገቢ.1፣ ትዕ.3)

ከዚህ በላይ በተራቁጥር 1 ላይ የቀረበው ተረት ስለዓለም አፈጣጠር እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ **"እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ፣ ብርሃኑን በጨለማው መካከል ለዩ፤ ... ጠፈር አድርጐ፣ ከጠፈር በላይና በታች ያሉትንም ውሆች ለዩ፤... በምድርም ላይ በየወገኑ ዘሩ በውስጡ የሚገኘውንና ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ ታብቅል አለ፤... ሁለት ታላላቅ ብርሃንን አደረገ፣ ትልቁን ብርሃን ቀንን እንዲመግብ፣ ትንሹን ብርሃን ከከዋክብት ጋር ሌሊትን እንዲመገብ አደረገ፤... የምድር አራዊትን እንደየወገኑ፣ እንስሳትንም እንደየወገኑ በምድር የሚንቀሳቀሰውንም ሁሉ እንደየወገኑ አደረገ..."** (ዘፍ.1፣1-29)[92] እንደሚለው ሁሉ፣ ይህም ተረት እግዚአብሔር ዓለምን እረቂቅ በሆነ ጥበቡ እንደፈጠረው፣ ይህን ሲያደርግም እያንዳንዱን ሕይወት ያለውና የሌለውን ነገር እንደ ባህርይው ለያይቶ መሆኑን ይገልጻል። የተረቱ ይዘት ከሀይማኖት ቲዎሪ አንጻር ሲታይ ተጠይቃዊ ያልሆነውን የሰውልጅና በአጠቃላይ የዚህ ዓለም አፈጣጠር ይመለከታል። ከፋይዳ አንጻር ደግሞ ሰለነገሮች አፈጣጠርና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሰውልጅ ሊገነዘባቸው ስለሚባው ጉዳች አስመልክቶ ትምህርት ይሰጣል።

2. **<u>በግ ፡-</u>**

በማንም ሳንደርስ ሳር ግጠን በበላን

ከቶ ስለምን ነው ምቀኛ የሞላን?

<u>እባብ ፡-</u>

ከድንጋይ ሥር ሆኜ ተሰማኝ ነገርሽ

---

[92] የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር።*መጽሀፍ ቅዱስ* (የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት)፣ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፣ 1980፣ ገጽ 1-2።

በጐን እንዳላማ ፊት ለፊት ልንገርሽ

ነገር በቀጥታው ካልተተረጐመ

ሰበብ ቢያበዙለት ምኑን ተጠቀመ

ነገር በምሳሌ ጥንትም ይሰየማል

ድንጋይ በባህሪው እግር ያነቅፋል

ውሃም የጠባዩን ወደታች ይጋፋል

ያገኘውን ሁሉ አይተውም ያጠፋል፡፡

ድንጋይና ውሃን ጥንቱን ሲፈጥራቸው

ክፉ በጐን እዩ ብሎ አላዘዛቸው

በማንም ላይ ቢሆን ልዩ ቂም የላቸው፡፡

ሁሉም ጥቂት ጥቂት ምቀኝነት አለው

አይታይም እንጂ እየሸፋፈነው

የኔግን በገሃድ የተገለጠ ነው፡፡

አዳምና ሄዋን በከንቱ ተቀጡ

በኔ ምቀኝነት ተገነት ውስጥ ወጡ

ባለመዋልነትን ተግዜር ባይባቸው

ሆነ ብዬ ሄጄ በግድ አገትኳቸው፡፡

<u>በግ ፡-</u>

ወየውጉድ ይገርማል እጅግ ያስደንቃል

እንዴት ያለው ታሪክ እያደር ይፈልቃል

የገዛ ነውርሽን ጉድሽን ስታወሪ

ቢታዘቡኝ ብለሽ ጥቂትም አታፍሪ

እባብ ፡-

ደሞ እፍረት ምንድነው ጅብዱዬን ስቆጥር

መመካቴን ትቼ እንደ ልጅ ላቀርቅር?

እረ ስሚኝ እቴ ይልቅስ ልንገርሽ

ያንቺ አይነት ፊሪነት ተምንድን ሊያድንሽ

አንድ ነገር ሲያምር ያየሁት እንደሆነ

ያንን ታላጠፋሁ ከቶ ምንም ቢሆን

እረፍት አላገኝም እንቅልፍ አይወስደኝም

ቅን ነገር አይቼ እኔ አያስችለኝም፡፡

በግ ፡-

ንግግርሽ ሁሉ እንደሳት ይፋጃል

ከቶ ምቀኝነት ለምንድን ይበጃል?

እባብ ፡-

የናንተ ቅንነት ለምንድን በጃችሁ

ትንሹም ትልቁም ሁሉም ሲገጫችሁ

ነገርማ ሁሉ ምቀኛ ባይኖረው

ለፍፃሜ ሁሉ ምን ወሰን ባይኖረው

ማናቸውስ ሐሳብ በቅን ተወጥኖ

በትክክል መንገድ በቀጥታ ሆኖ

እስቲመቻችና እስቲፈፀም ድረስ

በመሀሉ እንቅፋት ገብቶ ታላጠፋው

ከምን ሥፍራ ይግባ ተንኮል ወዴት ይድረስ?

ይኸማ ተቀረ ሁሉስ ምን አለፋው?

ጠቅላላውን ነገር እንደዜ ልንገርሽ

ወዲያውም ልብ አርጊው አጥብቂ ልምከርሽ

ለስራችን ሁሉ ሕውከት ባይኖርባት

በሰውነታችን ሞትን ባይፈጥርባት

እግዚአብሔር መኖሩን በምን ታውቂው ነበር?

ይልቅ ተጠንቀቂ አትበይ ደንበር ደንበር

ጥንቱም አደጋን እግዜር የፈጠረው

ለመጉጃ አልነበረም ለማስጠንቀቂያ ነው፡፡

(ገቢ.2፣ ትዕ. 2)

በተራ ቁጥር 2 የቀረበዉን ይህን ተረት ከተግባራዊ ቲዎሪ አንጻር ስንመለከተው፣ በዋናነት ስለልዩ ፍጥረቶች ባህርያትና ከዚህ ጋር የተያያዘውን የሰው ልጅ ገጠመኝ ይገልጻል፡፡ ድንጋይ የሰው እግር እንደሚያደናቅፍ የታወቀ ነው፡፡ ውሃ ወደታች መፍሰሱ ተፈጥሮአዊ ነዉ፡፡ ሽቅብ ከሚወጣ ይልቅ ቁልቁል የሚወርድ ውሃ ከፍተኛ ጉልበት አለው፡፡ ይህ የሁለት ግዑዝ አካላት (ድንጋይና ውሃ) ተፈጥሮአዊ ባህርይ ነው፡፡ በግ በባህርዩ ሰውን የሚተናኮል ወይም አስቦና አቅዶ ጉዳት የሚያደርስ እንሰሳ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከሰው ልጅ ጋር ተላምዶ ይኖራል፡፡ በሌላ በኩል የእባብን ባህርይና ከሰው ልጅ ጋር ያለዉን ገጠመኝ ካየነው የተለየ ነገር እናገኛለን፡፡ እባብ ከምድር አራዊት ሁሉ ተንኮለኛ ስለሆነ አዳምና ሔዋንን

አሳስቶ በፈጣሪያቸው የተከለከሉትን እጸበለስ እንዲበሉ እንዳደረጋቸውና ተደላድለው ከሚኖሩበት ቦታ (ከገነት) እንዳባረራቸው በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ (ዘ.ፍ.3፣ 1-16)[93] ተጽፎ ይገኛል።

4.7.1.2 ፋቡላዎችን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ይዘትና ፋይዳ ትንተና

Okepho ስለ ፋቡላዎች ዓላማና ትኩረት ሲገልጽ "የፋቡላዎች ዓላማና ትኩረት የገጠመኞችን ምዕናባዊ ድራማ በሚያስደስት መንገድ ማቅረብና ሰዎች፣ እንስሳትና መናፍስት ገፀባህሪያት ያሉበት ትረካ መተረክ ብቻ ነው። ተራኪውም ተረቶችን እንዴት መፍታትና መተርጐም እንዳለብን የሚሰጠን ገለፃና ማብራሪያ ወይም ግፊት የለም። ስለዚህም ትርጓሜው ለየአድማጩ ፍላጐት ክፍት ተትቷል" ይላል (Okepho, በፈቃደ ውስጥ፣ 1991: 62)።

ይህን፣ የ Okepwho ሐሳብ መሠረት በማድረግ፣ በዚህ ንዑስ ርዕስ ከተውኔቱ ሁለት ፋቡላዎችን እንደ ምሳሌ ጠቅሰን ትርጉማቸውን እንመለከታለን። ሁለተኛው፣ ስለ አይጠች መንግስት የማቋቋም ጉዳይ ይተርካል።

1. /ተኩላና ግልገል ተፋጠው ይነጋገራሉ/

<u>ተኩላ ፡-</u>

ኧረግ! ኧረግ !ኧረግ!

እኔ ጥሩ ውሃ ሞያዬን ስፈልግ

ለካ አንተ ኖረናል ያደፈረሰክብኝ

ምንኛ ጠግበሃል እንዲህ የምትባልግ

ቆይ አንተን ሳልቀጣ እንዳላገጥህብኝ።

[93] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 2-3።

ግልገል ፡-

ኧረ ክቡር ጌታ እግዜር ያሳይዎ

እርስዎ ሲመጡ ከወደ ላይ አየሁ

እኔ የነበርሁት ከወደታችዎ

እስቲ እንዴት አባቴ አደፈርሳለሁ ?

ተኩላ ፡-

ሆሆይ ደግሞ ተማጥፋቱ የማስተባበሉ

እንዲህ ያለጥጋብ አሁን እስቲ በሉ

እንዴውስ አንተማ አምና አልሠደብከኝም

ግልገል ፡-

ኧረ እንደምን ችዬ አምና ሳደብኩዎ ?

እኔ ከተወለድኩ አመት አልሞላኝም

እናቴ እንኳ ጠቷን አላስጠለችኝም

ስለ እግዚሐር ብለው ይተው እባክዎ

ተኩላ ፡-

አንተም ባትሰድበኝ ወንድምህ ሰድቦኛል

ተንኮላችሁ ሁሉ እጅግ ሠለችችኛል፡፡

ግልገል ፡-

እኔ የበሀር ልጅ አንድ ወንድም የሌለኝ

ተንኮል የማልሠራ ገና እርም ታህል ነኝ

ልጅነቴን ዓይተው የዛሬን ይማሩኝ

ባልሠራሁት ሥራ በከንቱ አያማሩኝ

ዳግመኛ አይለምደኝም አንድ ጊዜ ወቀሱኝ

የዳኝነትዎን የውነት ፍርድ አይንሱኝ፡፡

<u>ተኩላ ፡-</u>

ወንድም ባይኖርህ ዘመዶችህ ሁሉ

እንኔን ባዩ ጊዜ አገር ያምሳሉ

ዘወትር እነሱ ደግሞ እረኞቻቸው

በሩቅ ያባሩኛል ተነውሾቻው፡፡...

(ገቢ.1፣ ትዕ. 1)

በዚህ ፋቡላ የቀረበዉ ቃለ ምልልስ በተኩላና በበግ ግልገል መካከል የተደረገን ሲሆን፣ ይኸውም ተኩላ ግልገልን ለመብላት፣ ግልገል ደግሞ ላለመብላት በየበኩላቸው የሚያቀርቧቸውን ሰበበ ምክንያቶችና አንዱ ሌላውን የሚሞግትበትን ነገረ ሐልዮት የሚመለከት ነው፡፡ ገፀባህርያቱ እንስሳት ሲሆኑ፣ አተራረኩ አስደሳች ስሜት የመፍጠር አቅም አለዉ፡፡ ተኩላ ግልገሉን ለመብላት ሲል የሚደረድራቸው ሰበቦች፣ እሱ ከላይ እየጠጣ ከበታቹ የሚገኘውን ግልገል **“ውሃዬን አታደፍርስብኝ”** የሚለው፣ ከተወለደ ዓመት ያልሞላውን ግልገል **“እምና ሰድበኸኛል”** ማለቱና ይህም ሳያዋጣው ሲቀር፣ **“እንተም ባትሆን ዘመዶችህ ስድበውኛል”** ብሎ ሌላ ሰበብ መፍጠሩ ወዘተ... ስንሰማ ፈገግ ማለታችን አይቀርም፡፡ ይህም ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ ፋቡላው ደስታን ከማስገኘት አንጻር ያለውን ፋይዳ ያመለክታል፡፡

2. <u>ፍየል</u> ፡-

ሚ.ማ.ሚ.ማ በጐች እንዴት ናችሁ

መስንበታችሁን ምን ወሬ ሰማችሁ ?

ብትሰሙም ባትሰሙሙ እኔ ላውጋላችሁ

አይጠች አገኙ እውቀትን በሙሉ

የማህበር መንግስት ሊያቆሙ ነው አሉ

ለማህበራቸው አለቃ ሊሾሙ

ግድ ቀርቶ በውድ በምክር ሊስማሙ

እንዲህ ያለ ዘዴ ተባህር ተማዶ

አግኝተዋል ብሎ አውራልኝ ዘንዶ

<u>በግ፡-</u>

ሃሃሃ የዛሬውስ ወሬሽ እውነትም ያስቃል

ሃሃሃ አይጥ ብሎ መንግስት ማን ሰይሞት ያውቃል?

ኧረ ጥንቱን ማነው ለዚህ ያበቃቸው

ላይጠች መንግስትን የፈቀደላቸው?

ጨዋታ ነው ምነው መንግስት ቢላቸው

ለአይጠች ለሥራ ህግጋት የላቸው

አንዱ አንዱን አይሰማው ደንባቸው አይረጋ

በነሱ ዳኝነት ማን ይሆናል ዜጋ

ይኸን ተይውና ይልቅ ሌላ እናውጋ

መንግስት ለማቋቋም እንኳንስ ለአይጠች

አስቸግሮአል አሉ በምድር ላሉ ሰዎች

ይልቅስ አይጠች አንድ ሙያ አላቸው

የሰው ቤት ለማፍረስ ማነም አያህላቸው

ለማጥፋት ከሆነ በእውነት ጎበዝ ናቸው

ማልማት የለም እንጅ ለዚህ ማን ብሎአቸው !

ደህናውን ጥሩውን የሚያምረውን እቃ

ማሰሪያውን ሸማ ካባ ወይም ጣቃ

በጣጥሶ ለመጣል ለማበላሸት

ይህ በነሱ ያምራል የቀረው ግን ውሸት

ያይጠችስ መንግስት ያውም የማህበር

እርሻን መመኘት ነው በጉሽ ያለቀንበር

ያይጠችን ማህበር ያለቃቸውንም

ምንም ብትነግሪኝ እኔ ከቶ አላምንም

ከድመት የሚበልጥ ላይጠች አለቃ

ምንም ቢሆን አይመጣም ተከተተ በቃ።።

(ገቢ.3፣ ትዕ.1)

ከላይ በተራ ቁጥር 2 ላይ በቀረበዉ ፋቡላም እንዲሁ ገፀባህሪያቱ እንስሳት ሲሆኑ፣ **“የአይጠቹ መንግስት የማቋቋም ነገር”** በራሱ ዘና የሚያደርግ ነው።። ይህም፣ ቀደም ሲል የ Okepho ን ሐሳብ ወስዶ ለመግለፅ እንደተሞከረው የፋቡላዎች ዓላማና ትኩረት ሲሆን፣ ትርጉማቸውን በሚመለከት ግን ለአድማጭ ክፍት የተደረገ በመሆኑ ግለ ምልከታን የሚጠይቅ ይሆናል።። በመሆኑም በእኔ እይታ የሁለቱ

ፋቡላዎች ትርጉም ጠቅለል ባለመልኩ ከተምሳሌታዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በተራ ቁጥር 1 ላይ የቀረበዉ ፋቡላ በዋናነት ሞራላዊ ጉዳዮች ላይ ያጠነጥናል፡፡ እራስ ወዳድ ሰዎች ፍላጐታቸውን ለማሳካት ምን ያህል ርቀት እንደሚጓዙ በእነሱ ዘንድ ሞራል የሚባል ነገር ጨርሶ ቦታ እንደሌለው፣ ይልቁንም ዋናዉ ነገር የግልን ጥቅምን ማስጠበቅ ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም ጉልበተኞች አቅመቢሶችን ለማጥቃትና ለመጉዳት ምንም አይነት ተጠይቃዊ ምክንያት እንደማያስፈልጋቸው በግልፅ ያመለክታል፡፡ በተራ ቁጥር 2 ስለ አይጦች መንግስት የማቋቋም ሃሳብ የሚተርከዉ ፋቡላ ተምሳሌታዊ ትርጉም አዬ ምኒልክ ካረፉ በኋላ እሳቸውን ተክተው ስልጣን የጨበጡትን ልጅ እያሱን እና የመንግስታቸውን አስተዳደር ይመለከታል፡፡ በልጅ እያሱ ዘመን (1905-1908ዓ.ም)[94] የኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደር ተዳክሞ የታየበት ጊዜ እንደነበርና ለዚህ ደግሞ ዋነኛዉ ምክንያት የእሳቸዉ ሀገር የመምራት ዕውቀትና ብስለት ማነስ እንደሆነ ይገለጻል(ተክለጻዲቅ፣ 1965፤ሙሉቀን 2008፤ባህሩ፣2007)፡፡ በተለይ ከዚህ በታች ስለ ልጅ እያሱ የተገለጸዉ ይህንኑ ሀሳብ የበለጠ ያጠናክራል፡፡

> ***ልጅ እያሱ አዘውትሮ ከአዲስ አበባ በመውጣት ቀድሞ የምኒልኪ ሹማምንት የነበሩትን በመሻር አዳዲሶቹን እየተካ እና አዲስ የግንኙነት መስመር እየፈጠረ ከረመ፡፡ በርካታ የመገናኛ መስመሮች ተዘርግተው ከተለያዩ የክልል ግዛቶች ጋር የተገናኘችውን አዲስ አበባን በመተው በክልሎች መዘዋወር ያበዛው እያሱ ከተማዋን እና አገሪቱን ያላስተዳደር አስቀራት፡፡ ከ1911-13 እ.ኤ.አ ባሉት አመታት የኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደራዊ መዋቅር ተዳከመ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ጥንካሬያቸውን ይዘው የዘለቁት የክልል ግዛቶች ግብር ላለመክፈል እስከማንገራገር የሚያደርሳቸውን አቅም ገነቡ፡፡ የሐረርጌ ግዛትን ያስተዳድሩ የነበሩት ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ለልጅ እያሱ አስተዳደር ላለመገዛት ማንገራገር ጀመሩ (ሙሉቀን፣2008፣30) ፡፡***

[94] http://am.wikipedia.org (Retrived:17/01/2018)

ከዚህ አንጻር፣ የተዉኔቱ ፀሀፊ ተክለሐዋርያት ተክለማሪያም (በጅሮንድ) የልጅ እያሱን ሐገር የመምራት ችሎታ እና አቅም አነስተኛ መሆን በፋቡላው አማካኝነት መግለጻቸውን መረዳት ይቻላል ፡፡ ይህም በሌላ በኩል ከተግባራዊ ቲዎሪ አኳያ ሲታይ ፀሀፊዉ ሀገር የመምራት ጉዳይ ተራ እና እንደቀልድ የማይታይ መሆኑን በዘመኑ ለልጅ እሱ የመከሩበት መንገድ ነዉ፡፡

ምዕራፍ አምስት

5. ከፎክሎራዊ ጉዳዮች የተገኙ ዋና ዋና ፋይዳዎች

የፎክሎር ምሁራኑ ፣ Sims and Sephens (2005፡1750), Vancina (1980፡100) እንደሚገልጹት በፎክሎር ዘርፎች እና በየዘርፎቹም ውስጥ የሚገኙት አያሌ ዘውጎች ለአንድ አይነት ፋይዳ (ለባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ.) እስካልሰሩ ድረስ ቀጣይነት አይኖራቸዉም፡፡ ከዚህ አንጻር በተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱትን ፎክሎራዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ ፋይዳዎችን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዘትና ፋይዳ በተነተንኩበት ክፍል የእያንዱን የፎክሎር አይነት (Folklore Item) ይዘትና ፋይዳ የተመለከትን ሲሆን በዚህ ክፍል የማተኩረዉ ጠቅለል ባለ መልኩ ዋና ዋና በሚባሉ ፋይዳዎች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

5.1. ባህላዊ ፋይዳ

- በተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ባህልን ለተከታታይ ትውልድ በማስተላለፍ ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግ ጠቀሜታ አላቸው፡ ለምሳሌ፣ በቃቄ ወርዶወት ተዉኔት ዉስጥ አንቂት (የሴት ልጅ እርግማን) ለማንሳት የአገር ሽማግሌዎች ወተት በቅልና ለምለም ሳር ይዘዉ አነቂቱ ወደሚነሳላት ሴት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ወተቱና ለምለሙ ሳር ባህላዊ ትርጓሜ ያላቸዉ ሲሆን ይህም የሴቷን ቀጣይ ተስፋ የሚያመለክቱ ናቸዉ፡፡ ይህም የጉራጌ ባህል የሚያዝዘዉ ስርዓታዊ አተገባበር ነው (ገቢ.3፣ ትዕ፣2፣ 69-70) ፡፡
- በዚሁ ተዉኔት ዉስጥ የጀፎረን ባህላዊ ይዘት በመሀላ (በብሄረሰቡ አጠራር “ጎርዳ”) ጠብቆ ስለማቆየት የተገለፀዉ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ጀፎረ ላይ የሚደረጉ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች (የፊረስ ግልቢያ ፣ ትግል ፣ ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ስርዓት ወዘተ...) ባህልን ከማስተዋወቅና ለቀጣይ ትዉልድ ከማስተላለፍ አንጻር ጉልህ ድርሻ አላቸዉ (ገቢ.2፣ ትዕ. 1፣ 28-29) ፡፡

- አሁንም ከዚሁ የቃቄ ወርዶወት ተዉኔት ሳንወጣ **መረራ** ሸሚሮ ባህላዊ ዘፈን ክዋኔ ላይ የሚጠቀሙባቸዉ ልዩ ልዩ ግብዓቶች፣ ልጃገረዶች የሚለብሱት ከወገብ በላይ የቆዳ ልብስ፣ ከወገብ በታች ከቃጫ የተሰራ ልብስ ሁሉም ባህላዊ መልእክት አላቸው (ገቢ.. 1፣ ትዕ. 1፣ 10) ።።
- በአሻ ተዉኔት ውስጥ **የአሻን ስርዓት** ለማስፈጸም በጎሳ መሪዉ ተመርጠዉ ወደ ሟች ቤተሰቦች የተላኩት ሽማግሌዎች ሁለቱን ወገኖች (የገዳይና የሟች ቤተሰቦች) ለማስማማት የሚወስኑዋቸዉ ዉሳኔዎች የባህላዊ ፋይዳ ማሳያ ናቸው (ገቢ..1፣ትዕ.3፣27) ።።
- በቃቄ ወርዶወት ዉስጥ **የእጆካ ሽንጎ መልእክተኞች**፣ እነ አጋዝ ፉርችየ እና አጋዝ ሲቆራ በሽንጎዉ ፊት ቀርበዉ ምርቃት ሲሰጣቸዉ ከእድሜ አንጋፋዎቹ የሚጀመርበት ስርዓት ታላላቆችን ከማክበር አኳያ የሚያስተላልፈዉ የራሱ የሆነ ባህላዊ መልእክት አለዉ (ገቢ.2፣ትዕ.2 6፡)፡
- በዚሁ ተውኔት ውስጥ በጉራጌ ባህል የተለያዩ ተግባራትን ለፈጸሙ ሰዎች የሚሰጡ ባህላዊ የማዕረግ ስሞች የዚያ ማህበረሰብ ባህላዊ መገለጫዎች ከመሆናቸው አንጻር ፋይዳቸዉ የጎላ ነዉ።። ለምሳሌ፣ **አጋዝ**፣ **አባ ገዳ**፣**አሲህ አርብ** (ገቢ.2፣ትዕ.1፣22-23፣ **አጀት** (ገቢ.1፣ ትዕ.፣1፣5)
- በአሻ ልጅ ተውኔት ዉስጥ በመኢኔት ብሄረሰብ ከጋብቻ በፊት የግብረስጋ ግንኙነት የፈጸመች አንዲት ሴት በሬ ታርዶ ደሙን ተቀብታ የመንጻት ስርዓት እስካልፈጸመች ድረስ ከህብረተሰቡ ጋር መቀላቀል አትችልም ።። ይህም የብሄረሰቡ ባህል መገለጫ በመሆኑ የራሱ የሆነ ፋይዳ አለው (ገቢ..1፣ትዕ1፣15) ።።
- በሾተላይ ተዉኔት ዉስጥ **ከአባይ ቆሌ ጋር** በተያያዘ የተገለጹት በወንዙ ዳር የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ለምሳሌ፣ (እንስሳትን ማረድ ፣ ከበሽታ ለመፈወስ በወንዙ ዉሀ መታጠብ ፣ሎሚ መወርወር ወዘተ...የመሳሰሉት) በአካባቢዉ ማህበረሰብ ዘንድ ይሁንታን አግኝተዉ ከትዉልድ ትዉልድ፣ ከአንዱ ወደ ሌላዉ እየወረደና እየተወራረደ የኖሩ የባህል ነጸብራቆች ናቸው (ገቢ፣1 ትዕ .5 30)።።

- በያላቻ ጋብቻ ተዉኔት ዉስጥ ሀ/ “**አዋቂ ሳይጠየቅ ልጅ አይዳርም** ” ሚለዉ የወይዘሮ አልጋነሽ ዱብዳ ብሂል እርሳቸዉና መሰሎቻቸዉ ከኖሩበት ማህበረሰብ ባህል የተቀዱ የኑሮ መመሪያዎች ናቸዉ (ገቢ.1፣ትዕ፣2) ፡፡ ለ/ የሁለቱ ደጋግ የሃማኖት አባቶች **አለቃ** እና **ሀጂ** ግንኙነት ፣ የሀይማኖት ልዩነት ያልገደበዉ አብሮነትና ለረጅም ጊዜ የዘለቀዉ ወዳጅነታቸዉ፣ሀገራችን ለዘመናት የምትታወቅበት በተለያዩ ሀይማኖት ተከታዮች መካከል ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር ባህል ማሳያዎች ናቸዉ (ገቢ፣2 ትዕ .1፣55) ፡፡

5.2. ማህበራዊ ፋይዳ

- የቃቄ ወርዶወት ውስጥ **የእጅካ ባህላዊ ፍርድ ሸንጎ**፣ ከፍርድሸንጎ አገልግሎቱ በተጨማሪ ማህበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር በማህበረሰቡ መካከል የእዉቀትና የልምድ ልዉዉጥ ለመፍጠር ይረዳል (ገቢ.4፣ትዕ.1 ፣77-78) ፡፡
- ሽምግልና የክብርና የማህበራዊ ደረጃ አንዱ መገለጫ ተደርጎ ሲታይ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የሞራል ልዕልና ይፈጥራል፤ በራሱ ማንነት የሚኮራና ከባዕድ ተፅእኖ ነጻ የሆነ ትዉልድ ይኖራል፡፡ የቃቄ ወርዶወት ዉስጥ አጋዝ ፉርችየ ለእጅካ ሸንጎ ዳኞች በህብረተሰቡ ለተመረጡ ሽማግሌዎች ፣ እንደዚሁም በያላቻ ጋብቻ ዉስጥ ባህሩ አዳሽነህ እና ወይዘሮ አልጋነሽ ለ **አለቃ እና ሐጂ**፣ የሰጡት ክብር ይህንኑ የሚገልጽ ነው (የቃቄ ወርዶወት፣ ገቢ.3፣ትዕ፣1፣44፤ያላቻ ጋብቻ፣ ገቢ.2፣ትዕ. 3፣55)፡፡
- በቃቄ ወርዶወት ተውኔት ውስጥ **በጀፎረ** ተሰብስበዉ ስለ አካባቢያቸዉ ጉዳይ የሚመክሩት በጉራጌ የችሃና ሌሎች አካባቢ ነዋሪዎች፣ ያጠፋዉን ለማረም፣በዚያው መጠን በጎ ተግባር የፈጸመዉን ለመሸም የሚያከናውኗቸዉ ተግባራት ሁሉ የማህበራዊ ፋይዳ አንድምታዎች ናቸው (ገቢ.2፣ ትዕ.1፣28-29) ፡፡

- በዚሁ ተዉኔት ውስጥ ሰርግን ለማድመቅ እናቶች፣ ወጣት ልጃገረዶች ሁሉም በየፊናቸዉ የሚያደርጓቸዉ ጭፈራዎችና በዚህ መሀል የሚሰነዘሩ ቀልዶች ፣ ተረባዎች፣ ምልልሶች ወዘተ. የመሳሰሉትሁሉ ማህበራዊ ፋይዳን ጠቋሚዎች ናቸው (የቃቄ ወርዶወት፣ገቢ.1፣ትዕ.1፣5-6) ፡፡
- በ የአሻ ልጅ ተዉኔት ዉስጥ በመኢኔት ባህል ከጋብቻ በፊት የሚደረገዉ የወሲብ ክልከላ ፣ ከማህበራዊ ህይወት ጭምር የሚያገልጸው ጥብቅ ማህበራዊ ስሪት፣ ከወሲብ ጋር ተያይዘው ለሚመጡ እንደ ኤች . አይ . ቪ ኤድስ፣ የአባላዘር በሽታዎች፣ ያልተፈለገ እርግዝና ወዘተ. ችግሮችና በዚህ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ማህበራዊ ቀውሶችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጉልህ ፋይዳ አለዉ (ገቢ.1፣ ትዕ.1፣15) ፡፡
- በዚሁ ተውኔት ዉስጥ እንደተመለከትነው በማህበረሰቡ ዘንድ ነፍስ ማጥፋት በሚከሰትበት ወቅት ገና ከመነሻው ጸብና ቁርሾ፣ ቂምና በቀል በገዳይና ሟች ቤተሰብ መካከል እንዳይኖር ከሽማግሌዎቹ የሚሰጠው ማሳሰቢያ ማህበራዊ አንድነትን ማጠናከሪያ ነው፡፡
- በቃቄ ወርዶወት ተውኔት ውስጥ በእጆካ ሽንጎ የቃቄ ወርዶወትን አንቂት በማንሳት ከተጠናቀቀ በኋላ ሰብሳቢው አባገዳ ጅባቦ **“ወደ እኔ ቤት እንሂድ በጉ ታርዶ ምሳ ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል”** በማለት የሽንጎውን አባላት መጋበዛቸው ሀሳብ እንዲቀባበሉ፣ እንዲጨዋወቱ በር ይከፍታል፡፡ ይህ አይነቱ አብሮነት የማህበራዊ ፋይዳ አካል ነው (ገቢ.4፣ትዕ.2፣78) ፡፡

5.3 ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

- በአልቃሽና ዘፋኝ ተዉኔት ዉስጥ **የእዝማሪ ግጥሞች** ለማሩ ፣ **የሙሾ ግጥሞች** ደግሞ ለአስጋርጅዉ የገቢ ምንጮችና ኑሮአቸዉን የሚመሩባቸዉ (መተዳደሪያቸው) ናቸው (ትዕ.ሀ፣15-25፣ትዕ.ለ፣ 30-35) ፡፡
- በያላቻ ጋብቻ ተውኔት ዉስጥ **ኮከብ ቆጠራ** ለደብተራ ልዝቡ ፣ **ጠጠር መጣል** ለአባ ማሚቶ ከጥንቆላ ባሻገር የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎች ጭምር ናቸዉ (ገቢ.1፣ትዕ.2፣52፣ገቢ.2፣ትዕ.1፣74) ፡፡

በዚሁ ተዉኔት ውስጥ **ሀሰበ ህመምን** አስመልክቶ የተነሳው ጉዳይ፣ ለማይተርፍ በሽተኛ በህክምና ስም ገንዘብ እንዳይባክን ይረዳል። ይህም ለሚች ቤተሰብና ዘመዶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው (ገቢ.2፣ትዕ.1፣74)።

- በአሻ ልጅ ተውኔት ውስጥ እንደተገለጸው፣ በመኢኔት ባህል ወንድ ልጅ ለጋብቻ የሚጠየቀው ከፍተኛ የሆነ ጥሎሽ አንድ ልጅ ከህጻንነቱ ጀምሮ ብር ማጠራቀም (መቆጠብ) እንዲለምድ ያስገድደዋል። ይህም በሌላ በኩል ሲታይ ለዚያ ሰው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው (ገቢ.1፣ትዕ.1፣9)።
- በዚሁ ተውኔት እንደተመለከትነው በመኢኔት ሴትን ልጅ በስርዓት አንጸ ማሳደግ የቻለ ወላጅ ልጁቱ በምታገባ ጊዜ በዛ ያለ ስጦታ ስለሚያገኝ የሀብት መጠኑ ያድጋል። ይህም ከኢኮኖሚ ፋይዳ አንጻር የሚታይ ነው። (የአሻ ልጅ፣ገቢ. 1፣ ትዕ.1፣9)።
- በቃቄ ወርዶወት ተውኔት ውስጥ የእጅካ ባህላዊ ሽንጎ ፣የመደበኛ ፍርድቤቶችን ስራ ያቃልላል፤ ጊዜ ይቆጥባል። ይህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው (ገቢ.4፣ ትዕ.2፣77-78) ።
- በ ሾተላይ ተዉኔት ዉስጥ በአባይ ቆሌ አማካኝነት የኢትዮጵያን ወንዞች ስለመገደብ የተላለፈዉ መልእክት ለሀገር ካለዉ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አንጻር የሚታይ ነዉ (ገቢ.5፣ ትዕ.1፣90) ።
- በ አሻ ልጅ ተዉኔት እንደተገለጸዉ የገዳይ ቤተሰበብ የሚችን ቤተሰብ እንዲክስ ሲፈረድበት ፣ የካሳው መጠን ከአቅሙ በላይ ከሆነ በመኢኔት የመረዳዳት ባህል ቤተዘመዱና ጎሳው ያዋጣለታል። ይህም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው (ገቢ.2 ፣ትዕ.1፣26) ።

5.4 ስነ ልቡናዊ ፋይዳ

- በቃቄ ወርዶወት ተዉኔት ዉስጥ ስለ ቃቄ ወርዶወት አስተሳሰብና የህወት ፍልስፍና ረጅም ዘመን ወደ ኋላ ሄዶ በፎክሎር አማካኝነት ማወቅ መቻል በሌላ መልኩ ሲታይ ትኖርበት የነበረዉን ማህበረሰብ ስነ ልቡና ለመረዳት ያስችላል።

- በዚሁ ተውኔት ውስጥ ምርቃት በጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ቦታ፣ለተመራቂዉ የሚሰጠዉን የስነ ልቡና እርካታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በአካባቢው የሚታቀዱ የልማት እቅዶች በቀላሉ ግባቸውን የሚመቱበትን እቅድና ዘዴ መንደፍ ይቻላል፡፡

- በቴዎድሮስ ራዕይ እና ባልቃሽና ዘፋኝ ተውኔች ዉስጥ የተነሱትን በአንድ የተወሰነ ዘመን የተሰሙ የእረኛ ዘፈኖችን እና የአዝማሪ ግጥሞችን መነሻ በማድረግ የህብረተሰቡን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚ ጥያቄዎች፣ የአስተሳሰብ ደረጃ ወዘተ... ማወቅና መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም በሌላ በኩል ሲታይ ከስነ ልቡና ጋር ይያያዛል (የቴዎድሮ ራዕይ፣ት፡1፣16.፤ አልቃሽና ዘፋኝ፣ት፡ለ ፣30) ፡፡

- በአሻ ልጅ ተዉኔት ዉስጥ ስለ አሻ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የተገለጸዉን መነሻ በማድረግ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ለግጭት መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮችንና ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን መመርመርና ማወቅ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችን በቀላሉ ለመፍታት ይረዳል ፡፡ ይህም የማህበረሰቡን ስነ ልቡና ጠንቅቆ ከመረዳት ይጀምራል፡፡

5.5 ፖለቲካዊ ፋይዳ

- በቴዎድሮስ ራዕይ ተውኔት ውስጥ እንደተመለከተው ፣ታሪኩን ጠንቅቆ የሚያውቅ ህዝብ በማንነቱ ይኮራል፡፡ በማንነቱ የሚኮራ ህዝብ ደግሞ ለውጭ ጠላትና ወራሪ ሀይል በቀላሉ እጅ አይሰጥም ፡፡ ይህን ከመግለጽ አንጻር ደግሞ የተራኪ ቃል ግጥሞች ሚና ከፍተኛ ነው (ት፡1፣1)፡፡

- በሾተላይ ተውኔት ውስጥ በሙት መንፈስ አማካኝነት ለማስተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ አንድነት የሀገር ፍቅር አንዱ መገለጫ መሆኑን ያሳል፡፡ ስለዚህ ከጥንት ጀምሮ የምንታወቅበትን አንድነታችንን ጠብቀን መዝለቅ ይኖርብናል የሚለው ሀሳብ ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዳለው ግልጽ ነው፡፡(ገቢ.1፣ት፡. 5) ፡፡

- በ ፋቡላ ተውኔት ውስጥ ሀገር መምራትና ማስተዳደር እውቀትን፣ ጥበብን እና ብልሀትን ይጠይቃል የሚለው መልእክት ፖለቲካዊ ፋይዳው ጎልቶ ይታያል (ገቢ.3፣ትዕ.1)።

- በአሻ ተዉኔት ዉስጥ ከቀረበዉ በመነሳት ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ዘላቂ ሰላምን ከማስገኘት አንጻር ፋይዳ ያለው መሆኑን በማስረዳት እንደ ሀገር አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

5.6 ትምህርታዊ ፋይዳ

- በፋቡላ ተውኔት ውስጥ የቀረቡት ተረቶች ስለ ደግነት፣ ስለ መልካምስራ፣ ከስህተት ስለመማር፣ ስለ ስራ ክቡርነት ወዘተ. ስለመሳሰሉት በቀልድ እያዋዙ ቁምነገር የሚያስጨብጡ በመሆናቸው አስተማሪ ናቸው (ገቢ.1፣ትዕ.፣1፣23፣ ገቢ.4፣ ትዕ.5 ፣27-29)።

- በ ቃቄ ወርዶወት ተዉኔት ዉስጥ ምሳሌያዊ ንግግሮች የአኗኗር ስርዓትን፣ ምግባርን፣ ብልሀትን ያስተምራሉ። ከዚህ አንጻር አንድን ማህበረሰብ በማነጽ በሰውልጅ የማህበራዊ ህይወት ዉስጥ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ (ገቢ.2፣ትዕ.1፣28-36) ።

- በ አሻ ልጅ ተዉኔት ዉስጥ ሾሽን አስመልክቶ የተነሳዉ ሀሳብ የጋብቻን አስፈላጊነትና ክቡርነት የሚያሳይ በመሆኑ ጋብቻን በአለታዊ መልኩ ለሚመለከቱት ሰዎች ብዙ የሚሰጠው ትምህርት አለ (ገቢ.1፣ትዕ.1፣27-29)።

- በ ሾተላይ ተዉኔት ዉስጥ ኢትዮጵያ በ ሾተላይ እናት ተመስላ የቀረበችበት መንገድ የእርስ በርስ ጦርነት ሐገሪቷን ምን ያህል እንደጎዳት የሚያሳይና ለወደፊቱ አንዳይደገም ትምህርት ሊወሰድበት የሚችል ጉዳይ ነዉ (ገቢ.1፣ትዕ.3) ።

5.7 ሞራላዊና ግብረገባዊ ፋይዳ

- በፋቡላ ተውኔት ውስጥ የቀረቡት አብዛኞቹ ተረቶች ሞራልና ግብረገብን የሚያስተምሩ ናቸው ፡፡ ይህ ደግሞ በተለይ እንደ እኛ (ኢትዮጵያዉያን) ለሞራልና ስነ ግብረገባዊ ጉዳዮች ትኩረት በሚሰጥ ማህበረሰብ ውስጥ በአንድ በኩል እኩይ ተግባራትን ከመገታትና ከመቆጣጠር፣ በሌላ መልኩ ደግሞ ሰናይ የሚባሉትን አስጠብቆ ከማቆየትና ከማስቀጠል አኳያ ጉልህ ፋይዳ አለው፡፡

5.8 *መንፈሳዊ ፋይዳ*

- በ ያላቻ ጋብቻ ተዉኔት ውስጥ ስለ ሀይማኖት መቻቻልና መከባበር የተነሳው ጉዳይ ከማህበራዊ ብቻ ሳይሆን ከመንፈሳዊ ፋይዳዉ አንጻር ጭምር መታየት የሚችል ነው ፡፡ ሀጂ እና አለቃ እርስበርሳቸው ሲከባበሩና ሲዋደዱ በአንድ በኩል ለማህበራዊ ኑሮአቸው ዋስትና እየገቡ ሲሆን በሌላ በኩ ደግሞ “ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ!” ፤ “ማንንም እንዳት ነኩ!” ወዘተ. የሚሉትን የሁለቱ ሰዎች ሀይማኖታዊ ትዕዛዞች እየፈጸሙ መሆኑን ይገነዘቡዋል፡፡

5.9 ስነ ጽሁፋዊና ኪነ-ጥበባዊ ፋይዳ

- በተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፀሀፌ-ተውኔቶች ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ይዘታዊ ቁምነገር በመቅሰም ሰራዎቻቸውን የበለጠ ማስዋብና ማርቀቅ እንዲችሉ ረድተዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ያላቻ ጋብቻ ውስጥ ፀሀፌ-ተውኔት መንግስቱ ለማ የተጠቀሙት የደብተራ ልዝቡ ኮከብ ቆጠራ፣የ አባ ማሚቶ ጠጠር መጣል ከወይዘሮ አልጋነሽ ዱብዳ ፍላጎትና ምኞት ጋር ተያይዞ የሚፈጥረው ድባብ ለተውኔቱ ውበትና ለዛ ሰጥቶታል (ገቢ.1፣ትዕ.2፤ ገቢ.2፣ትዕ.1) ፡፡

- በ ቴዎድሮስ ራዕይ እና የቃቄ ወርዶወት ተውኔቶች ውስጥ ባህላዊ ዘፈኖች እና ባህላዊ ጭፈራዎች ሙዚቃዊ ቴአትርን ማዘጋጀት የሚወዱ የቴአትር ባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ ረገድ ጠቀሜታ አላቸው (የቴዎድሮስ ራዕይ፣ገቢ.1፣20 ፣ትዕ.2፣የቃቄ ወርዶወት፣ገቢ.1፣ትዕ.1፣10) ፡፡
- ከዚሁ ጋር በተያያዘ የቃቄ ወርዶወት እና የአሻ ልጅ ተውኔቶች በብሄረሰቦች ትውፊታዊ ክዋኔዎች ዙሪያ በተደረጉ ጥናቶች ላይ ተመስርተው የተጻፉ ከመሆናቸው አኳያ በሀገራችን ትውፊታዊ ቴአትርን በማሳደግና ማስፋፋት ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ምዕራፍ ስድስት

6. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

6.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በኢትጵያ ቴአትር ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳን በተመረጡ ተዉኔቶች አስረጅነት ለማሳየት ተሞክሮአል፡፡ ጥናቱ በዋናነት ያተኮረዉ ከስነቃልና ሀገረሰባዊ ልማዶች ጋር በተያያዙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ ከተግባራዊ ቲዎሪ እና ከሌሎች የተለያዩ ደጋፊ የመተንተኛ ቲዮሪዎች አንጻር ተተንትነዉ ቀርበዋል።

ስነ ቃል የአንድን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያሳይ እንደመሆኑ መጠን ፀሀፊ-ተዉኔቶች በተዉኔቶቻቸዉ ዉስጥ ያነሱዋቸዉ ስነ ቃላዊ ጉዳዮችም ተተኳሪ የሆነዉን ማህበረሰብ ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊና መሰል ጉዳዮችን በመግለጽ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው የጥናቱ ዉጤት ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ከዘመን አንጻር ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዎችን እንደሚያንጸበርቁ በዚህ ጥናት ተረጋግጡዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የዘርፉ ምሁራን የሆኑት (Finnegan, 1970, Okpho, 2004) ስነ ቃል ወቅታዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ጉድለቶች ግልጽ በማድረግ በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የማስተማር ሚና ያለዉ መሆኑን ይገልጻሉ። በተመሳሳይ Bascom (1954) የአፍሪካ ምሳሌያዊ ንግግሮች የማህበረሰቡን ስነ-ምግባር እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ውጤታማ መሆናቸዉን ያብራራል። ከነዚህ አንጻር በተዉኔቶች ዉስጥ የቀረቡት አንዳንድ የስነ ቃል ዓይነቶች የሚያስተምሩ፣ እንዲሁም በመምከር፣ በማስጠንቀቅ እና በማስፈራራት የሚቆጣጠሩ እንዳሉ በጥናቱ ታይቶአል።

በሌላ በኩል ሀገረሰባዊ ልማዶች የአንድ ህዝብ የባህል እና የእምነት መገለጫዎች ናቸዉ፡፡ ልማዳዊ ህጎች ማህበረሰባዊ ስርዓት እንዳይናጋ፣ ተከባብሮ መኖር እንዲሰፍን፣ ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር ወዘተ. የሚጫወቱት ሚና አለ፡፡ ለምሳሌ፣ በቃቄ ወርዶወት ዉስጥ ተመራቂው በመመረቁ በቅድሚያ የስነ ልቡና እርካታ

ያገኛል፤ የተበረከተው ምርቃት እውን ሲሆን ደግሞ ተመራቂው ማህበራዊ ኑሮውን በአርአያነት ይመራል፤ ማህበረሰቡም በመመረቁ በተገኘውም ስኬት ይኮራል፡፡ ከዚህ አንጻር ምርቃት ማህበረሰብንና ግለሰብን፣ ማህበረሰብን እና ማህበረሰብን የማስተሳሰር ሚና ይኖረዋል፡፡ በአሻ ልጅ ተውኔት ውስጥ የተነሳዉ የአሻ የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ሽማግሌዎች በገዳይና በሟች ቤተሰብ መካከል ቂም በቀል እንዳይኖር፣ እርቁን በንጹህ ልብ እንዲተገብሩት የሚያደርጉት ጥረት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

በአጠቃላይ በተውኔቶቹ ውስጥ የተመለከትናቸው ስነ ቃል እና ሐገረሰባዊ ልማድን የተመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ባህላዊ ፣ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ስነ ልቡናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሞራላዊ፣ግብረገባዊ፣ መንፈሳዊና፣ ስነ ጽሁፋዊና ኪነ-ጥበባዊ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ዉጤት ያረጋግጣል፡፡ ይህን ውጤት የመነሻ በማድረግም የጥናቱ ይሁንታ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

6.2. ይሁንታ

ፎክሎርን በተለያዩ መንገዶች ሰብስቦ በስብስቡ አንድ ፋይዳ መስራት እንደሚቻል Gramisci & Jones (in Dundes, 1995) የስዊዲን፣ ፊንላንድ፣ ጀርመን እና አሜሪካን ተሞክሮዎች በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡ ስዊዲን ረጅም ታሪክና ባህል ያላት ሀገር መሆኗን ለሌሎች ተቀናቃኞቹዋ የአዉሮፓ ሀገራት ለማሳየት፣ፊንላንድ በታላቁ የሰሜን ጦርነት ምክንያት ከደረሰባት ጉዳት ለማንሰራራት በማሰብ ለነደፈችዉ የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮግራሟ ማስፈጸሚያ፣ ጀርመን ጠንካራ ብሄርተኝነት ለመፍጠር ፣አሜሪካ ወታደሮች በጠላት ባህል ውስጥ መኖርን እንዲለምዱ ለማድረግ፣የዘርና የሰራተኛ አመፅን ለማብረድ፣ ትምህርትን ለማስፋፋትና ለቱሪዝም መስህብነት ተጠቀመውበታል (ibid) ፡፡ በተመሳሳይ አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ባደረጉዋቸው ቀደምት (Primary) በሚባሉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፎክሎር አገልግሎት እንደነበረው Hurreiz (2006:15) ይገልጻል ፡፡ በ አፍሪካ በተለያዩ ሀገሮች በተካሄዱ የፀረ-ቅኝ ግዛት ተቃዉሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ ጀግናን የሚያወድሱ ግጥሞች፣ ተራኪ ቃል-ግጥሞች፣ ተረቶች፣ ሚቲዎሎጂዎች፣ ገድሎች ፣ቀረርቶዎች፣ ሽለላዎች፣ ፉከራዎች፣ የእረኛ ዘፈኖች፣ ወዘተ...የመሳሰሉ የፎክሎር አይነቶች የትግሉ ማቀጣጠያ መሳሪያዎች እንደነበሩ

Hurreiz (2006፡15) ይገልጻል፡፡ በሀገራችንም የጣልያንን ወረራ ለመመከት “ የሀገር ፍቅር ማህበር” የሚባል በ1928 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ተቋቁሞ በስብከት፣በዘፈን ፣በግጥም ወዘተ. በመሳሰሉት ለህዝቡ ቅስቀሳ ይደረግ እንደነበር ቀደም ሲል በዚህ ጥናት የዳራ ክፍል ተመልክተናል፡፡ ከዚህ አንጻር እንደ ማሳያ በተመረጡት ተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አገልግሎት / ጥቅም/ ላይ ከማዋል አንፃር የማነሰቸው የይሁንታ ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ✓ በተውኔቶች ውስጥ የቀረቡት እነዚህ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያ ተዘጋጅተው ለወጣቱ ትውልድ የሚደርሱበት ሁኔታ ቢመቻች፣ ትውልዱ ብዙ ነገሮችን ይማርባቸዋል፡፡
- ✓ በፋቡላ ዉስጥ የተነሱትን ምሳሊያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች ወዘተ. በተጓዳኝ ትምህርት (በ ቴአትር ፣ሚኒሚዲያ፣ ሙዚቃ ፣ ክርክርና ውይይት ወዘተ. በመሳሰሉት ክበቦች) አማካኝነት በተለይ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ ቢቻል ብዙ ቁምነገር ሊያገኙባቸው ይችላሉ፡፡

- ✓ ተራኪ-ቃል ግጥሞች (ቴዎድሮስ ራዕይ ውስጥ) ፣ ዜጎች (የቃቄ ወርዶወት ውስጥ)፣ቀረርቶ እና ፍከራዎች(የቴዎድሮስ ራዕይ ዉስጥ) የመሳሰሉ የስነ ቃል ሀብቶች የህዝብን ማንነት የሚናገሩ፣ ታሪክን የሚዘክሩ፣ጀግናን የሚያወድሱ በመሆናቸው ለጥናትና ምርምር በሚረዱበት ቦታ አከዋወናቸውና ትግበራቸው የሚታይበት ማዕከል ቢዘጋጅላቸዉ ጥሩ ነዉ፡፡

- ✓ እንደ የእጅካ ሸንጎ ያሉ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ተግቢው ትኩረት ተሰጥቶአቸው ከመደበኛ ፍርድቤቶች ጋር በትብብር እንዲሰሩ ቢደረግ መልካም ነዉ፡፡

- ✓ መንግስት፣ መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች፣የሲቪክ ማህበራት፣ የመገናኛ ብዙሀን ወዘተ... በዚህ ጥናት ለተመለከትነዉ ለእሻ እና መሰል ሌሎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ተገቢዉን ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩ ግጭትን ከማስወገድና ዘላቂ ሰላምን ከማስፈን አንጻር ጠቀሚታ ይኖራቸዋል፡፡

- ✓ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር ብሔራዊ የኤች. አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ያለ ጉዳዩ በዋናነት የሚመለከታቸዉ መ/ቤቶች በአሻ

ልጅ ተዉኔት ዉስጥ በመኢኔት ብሔረሰብ ባህል የሚታየዉን ቅድመ ጋብቻ ወሲብ ክልከላ አስመልክቶ የተገለጸዉን እንደ ሞዴል በመዉሰድና ወደ ሌሎች ህዝቦች ባህሎች በማስፋት ህብረተሰቡን ስለ ኤች .አይ. ቪ መከላከል ለማስተማር ቢገለገሉበት የተሻለ ዉጤት ሊገኝበት ይችላል፡፡

- ✓ የጉራጌ የባህልና የልማት ማህበርና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የጀፎረን ባህላዊ ይዘት በማስጠበቅ ለቱሪስት መስህብነት የሚውልበትን መንገድ ቢያመቻቹ ለአካባቢው ህብረተሰብም ሆነ ለሀገር የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

- ✓ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ጀፎረን በዩኒስኮ ለማስመዝገብ ጥረት ቢያደርግና ቢሳካለት አለም አቀፍ ትኩረትን እንደሚስብ ምንም ጥርጥር የለውም ፡፡

- ✓ ያላቻ ጋብቻ ተውኔት ውስጥ እንደታየው በተለያዩ ሀይማኖት ተከታዮች መካከል ያለ መልካም ግንኙነቶችና መቻቻልን የሚያሳዩ መገለጫዎች በጎልማሶች እና በመደበኛ ትምህርት መስጫ ተቋማት ለማስተማሪያነት ተመቻችተው ቢቀርቡ ጠቀሜታው ከፍተኛ ይሆናል፡፡

- ✓ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መቻቻል ለህዝቦችና ለሀገር አንድነት፣ ለዘላቂ ሠላም፣ ለመልካም አስተዳደር፣ ለዲሞክራሲና ለዕድገት መሠረት እንደመሆኑ መጠን በሳይንሳዊ ምርምር ውጤት ወይም እውቀት ላይ የተመሠረቱ የፖሊሲ መርሆዎችንና ዓላማዎችን መንደፍና በድርጊት ማዋል አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በመጨረሻም፣ለመደምደምያህል፣በንቀትና በአናሳነት ተጠቂ የነበሩ ብሔር ብሔረሰቦች ማንነታቸውን ለመጠበቅና ለማቆየት ዓለም አቀፋዊ ሆነ ብሔራዊ ተጽእኖዎችን ለመቋቋም በመድረክ (በቴአትር) እና በፊልም የሚቀርቡ የጥበብ ስራዎች በፎክሎር እገዛ እሴታቸው እጅግ ከፍያለ መሆኑን በጥናቴ ለመጠቆምና ለማስረዳት እወዳለሁ፡፡

ዋቢዎች

ቀዳማይ መዘርዝር

መንግስቱ ለማ፣ (1952)፣ **ያላቻ ጋብቻ**፣ (የታተመ ተዉኔት)።

አስታጥቃቸዉ ይሁን፣(2009)፣ **የአሻ ልጅ** ፣(ያልታተመ ተዉኔት)።

አያልነህ ሙላት፣ (1991)፣ **ሾተላይ** ፣ (የታተመ ተዉኔት)።

ጌትነት እንየዉ ፣ (2000)፣ **የቴዎድሮስ ራዕይ** ፣(ያልታተመ ተዉኔት)።

ጫንያለዉ ወልደጊዮርጊስ፣ (2005)፣**የቃቄ ወርዶወት**፣(ያልታተመ ተዉኔት)።

ፍስሃ በላይ ይማም፣ (1973)፣ **አልቃሽና ዘፋኝ** (ያልታተመ ተዉኔት) ።

ካልአይ መዘርዝር

አማርኛ

ሀገር ፍቅር፣(1991)፣ *ልዩ መፅሄት*።

መንገሻ አማረ፣(1992)፣ “የወገልጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና”፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት ፣ (1980) ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ሙሉቀን ታሪኩ (ተርጓሚ)፣(2008) ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከቀድመ አክሱም እስከ ኢህአዴግ መባቻ* ፣ አዲስ አበባ፣አልታ ማተሚ ቤት።

ማርታ ንጉሴ፣(1998)፣ “የሰላሌ አካባቢ የጉማ ስርአት ክዋኔዎች እና ተውኔታዊ አላባዎች”፣ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፣ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ።

ሞገስ እቁበ ጊዮርጊስ ፣ (1957) ፣ *መጽሀፈ ሰነፍጥረት ምስለ አዕመደ ምስጢር* ፣ ኮከብ ዘማህ በሀዋርያት ስርየ ሐይማኖት ማተሚያ ቤት፡፡

በላይ መኮንን፣(1999)፣ “የደቡብ ንግስት ከአፈ ታሪኩ አንፃር”፣ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡

ባህሩ ዘወዴ፣ (2007፣)፣ *የኢትዮጵ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983* ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲ ፕሬስ፡፡

ብርሃኑ መኮንን፣ (1973)፣ “የአማርኛ የሙሾ ግጥሞች ይዘት እና የዘይቤ አጠቃቀም”፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህር ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፡፡

ብሩክ ተፈራ፣(2004)፣ “የተከፋኝ ሐገረሰባዊ ልማዶች ስርዓት በመኢኔት ብሔረሰብ” ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር በማብቃት ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ጥናትና መርምር ክፍል ለኪነ-ጥበብ ሥራዎች ግብዓት ታስቦ የተዘጋጀ፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ (1995)፣ *የአማርኛ ሰነግጥም*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ብርሃንና ሰላም (ጋዜጣ)፣ ፷ኛ ዓመት ቁጥር ፱፣ አ.አ ህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፱

ተመስገን ፋናዬ፣(1995)፣ “የዛር ትውፊት እና በውስጡ የሚገኙ ቴአትራዊ አላባውያን በራያ እና ቆቦ አካባቢ”፣ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡

ተስፋዬ ገሠሠ፣(1966)፣ “አሞጵር የኢትዮጵያ ቴአትር ጥናት፣ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው”፣ ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም 2ኛው ዓለም አቀፍ ጉባኤ የቀረበ ጥናት፡፡

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣(1965)፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ይኮኖ አምላክ አስከ አፄ ልብነ ድንግል*፣አዲስ አበባ ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

አህመድ ኡብራሂም፣(1979)፣ “የኢትዮጵያ ፀሐፌ- ተውኔቶች አጭር የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸው” ፣ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡

አልማዝ አበበ፣ (1992)፣ “የአዝማሪ ግጥሞች በየጁ አውራጃ ” ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርት ስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡

አስፋው ዳምጤ፣(አርታኢ ሸፈራው በቀለ) (2004)፣*ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ሥነ ጥበብና ልማት፣ (በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች)*፣ ገጽ 181-190፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፡፡

እንግዳ ሐብቴ፣ (1984)፣ “የሶዶ ብሔረሰብ የጋብቻ ትውፊታዊ ድራማ” ፣ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍለ፣ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣(1948)፣ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መመዘገበ ቃላት ሐዲስ*፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፡፡

ካህሳይ ገብረእግዚአብሔር፣(2008)፣ *ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ*፣አፍሪካ ማተሚያ ኃላ.የተ.የግል ማኅበር ፡፡

እዬኤል ሙሉጌታ፣(1972)፣ “የቴአትር ይዘት በኢትዮጵያ እስከ 1966 ዓ.ም” ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፣ (1992)፣ *የስነ ጽሑፍ መሠረታውያን*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣(1993)፣ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ያዴሣ ቶሎሣ ወዬሣ፤ (2007)፣ *መሠረታዊ የጥናትና ምርምር ዘዴዎች*፣ (በተግባራዊ ምሳሌዎችና አስረጅዎች የተደገፈ)።

ደስታ ለሬንሶ እና ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ፣(2007)፣ "የቃቄ ወርዳዎት ታሪክና የጉራጌ ብሔረሰብ ባህል ስነ ቃልና ትውፊታዊ ትውን ጥበባት" ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር፣ ለትውፊታዊ ትውን ጥበባት ጥናትና ምርምር ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ።።

ደስታ ተክለወልድ፣(1962)፣ *አዲሰ የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1962።።

ጳዉሎስ ኞኞ፣ (1985) *አጤ ቴዎድሮስ* ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።።

ፈቃደ አዘዘ፣ (አርታኢ ሽፈራው በቀለ)፣(2004)፣ *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ ቁዘማ፣ ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ (በፎረም ፎር ሳሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች)*፣ ገጽ 97-134፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት።።

_____ *የሥነ ቃል መምሪያ* ፣(1991)፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አሳታሚዎች።።

English

Abrahams, M. H. (1981). *A Glossary of Literary Terms.* New York: Halt Rinehart.

Alvin, Goldfarb and Wilson(1994). *Living Theatre: An Introduction to Theatre History.* 2nd ed.

Austin, B. (1994). *Understanding Oral Literature*. Nairobi University Press.

Banks, J.A. Banks,C.A. McGee.(eds).(2001). *Multicultural Education: Issues And Prespectives (4th ed).* New York: John Wiley and Sons

Barnard A. & Jonathan S..(2002). Encyclopedia Of Social & Cultural Anthropology. London & New York.

Bascom, W. *Four Functions of Folklore.* Journal of Amarican Folklore (Oct- Dec 1954) 333-349.

Bauman, R. (1977). *Verbal Art as Performance*. Newbury House: Rowley.

_____ (1983). "The Field Study of Folklore in Context," in Hand Book of American Folklore. Bloomington.

_____ (ed.)(1992). *Folklore, Cultural Performances and Popular* Entertainment. Oxford: Oxford University Press.

Bayleyegn Tasew. (2009). *Metaphors of Peace and Violence in the Folklore Discourse of South Western Ethiopia:A Comparative Study*. Amsterdam.

Bell, C. (1997). *Ritual: Perspective and Dimensions.* Oxford: Oxford University.

Ben-Amos, D. (1975). *Folklore in Africa Society Research in Africa Litertaure.*

_____. (1979). *Toward definition of Folklore in context. The Journal of American Folklore, Vol. 84,No.331.*

_____. (1993). *Theorizing Folklore: Towards New Perspective on the Politics of Culture.*

_____. (2006). *Folklore in Context. Nordic journal of African Studies. NewDelhi: Vol.15.No.3. South Asia Publishers.*

Ben-sly, R. and Brooking, J. (2009). *Community Health Education Methods: A Practical Guide. Canada: Jones and Bartlett Publishers.*

Bentley, Eric (ed.). (1916). The Classical Theatre. 1st ed.

Berger Peter and Luckmann. (1966). *The Social Construction of Reality. United States of America.*

Best Jhon, & Jems V. Kahn. (1993). *Research in Education (7th ed.) New Delhi: Printice Hall of India Private Limited Press.*

Brunvad, V. (1979). *Reading American Folklore.*

Carter V.(1981). Good and Douglas E. Scates, *Method of Research*.

Creswell, J.W. (2nd ed.).(2007). *Qualitative Inquiry Research Design: Choosing Among Five Approaches.* Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications, Inc.

Crowley,D.j. (1982). *The Erotic, The Pornographic and The Vulgar in Africa Arts.* UCLA. Jams Coleman: African Studies Center.

Degnehard and Elizabeth. (2006).*Religion and Drama in Early Modern England: The Performance of Religion on the Renaissance stage http://* Wikipedia the free Enciclopedia, Retrived March 9,2015.

Dorson, R.M. (1963). Current Folklore Theories: Current Anthropology, Vl. 4, No. 1. (Feb., 1963), pp. 93-112. Stable URL; http:// www.jstor/stable/2739820. Accessed 17/02/2008 11:12

_____. (1972). *Concept Folklore and Folk life Studies: An Introduction. Chicago:* Chicago University press.

Dundes, A. (1965). *The Study of Folklore*. Englewood: N.J. prentice Hall Inc.

_____. (1980). *Interpreting Folklore*. Bloomington: Indian University Press.

_____. (1989). *Folklore Matters*:The Psychoanalytic Study of the Grimm's tales. USA Knoxville: The University of Tennessee Press.

_____. (2004). "Folkloristics in the Twenty - First Century" (AFS Invited Presidential Plenary Address). *Journal of American Folklore.* Vol. 118, No. 470, pp.2005.

Eahleman, J. Ross, Barbara G. Cashion, Laurence A, Basirico. (1993). *Sociology: An Introduction* (4th ed.) New York: Harper Collins College Pubilisher.

Egbe, D. (2000). *Mastering English Usage and Communication Skills*. Lagos: Tisons Limited Press.

Fekade Azeze, (2003) . "Teaching Material Selected and Compiled, Readers for Etli 621" of Ethiopian Languages and Literature.MA in Ethiopian Literature and Folklore Finnegan, R. (1970). *Oral Literature In Africa.* Nairobi University Press.

Finnegan, R. (1970). *Oral Literature In Africa.* Nairobi University Press.

Finnegan, Ruth (1992). "Oral Poetry," in Richard Bauman (ed.) Folklore,Cultural Performances and Popular Entrtainment. A Communication-centered Handbook. New York, Oxford: Oxford University Press.

Fitterman, D.M. (2010). *Ethnography: Step by Step.* 3rd Edittion. Sage Publication: Newdelly.

Geertz, Clifford.(1973). The Interpretation of Cultures. New York: Basic Books.

Goldstein, Kenneth S.(1964). *A Guide for Field Works in Folklore*. Pennsylvania, Folklore Associates Inc.

Georges, Robert A. and Michel Owen Jones. (1995). *Fokloristic: An Introduction.* Bloomington ; Indian University Press.

Gusfield, R. and J,M.(1984). *Secular Symbolism Studies of Ritual*: Ceremony and Symbolic in Modern Life Annual Review Sociology, Vol.10.

Hantnoll, Phyllis. (1968). *A Concise History of the Theatre*. London.

Harrold Marcus.(1994). *A History of Ethiopia*. University of California Press.

Hey, Samuel A. (1994). *African American Theatre: A Historical and Critical Analysis*: New York: Cambridge University Press.

Hurreiz, Sayyid. (2006). *Studies in Africa Applied Folklore*. Published on the Occasion of the African Universities Congress with Concurrent with the African Union Summit. Khartoum.

Kotharir, C. (2004). *Research Methodology : Methods and Techniques (Second Revised Edition).* New age International Publishers.

Lampher, L. and Pridel,E.(1974) *.Domestic Power of Women*.

Legman, G. (1962). *Toward a Motif- Index of Erotic Humor*. The Journa of America Folklore Misconception in Erotic Culture. American Folklore Society. Volume 48. No. 75.

Leach, Maria. (1949, 1950). *Standard Dictionary of Folklore, Mythology and Legend*. New York, 2 vol. 5.

Leacroft, Richard and Helen. (1958). *ıne Theatre.* London; Methwen and Co Ltd

Macdonald, A. (1972). “ Field Worke Collection in Oral literature”. Foklore and Folk life, an Introduction. Ed. Rechard Dorson. Chicago; University of Chigago Press.

Malinowski, B.(1946). *The Problem of Meaning in Primitive languages, In the Meaning of Meaning*. New York: Harcourt, Brace & World.

Marshal, C. & Rossman, G. (2006). *Designing Qualitative Research.* United States of America: (4th Ed.). Saga Publication Inc.

Matthews,B.and Ross L.(2010). *Research Methods: A Practical Guide for The Social Sciences*. University of Birmingham

Mieder,W. (1993). *Proverbs are Never out of Reason. Popular Wisdom in The Modern Age*. Oxford: Oxford University Press

Mills,M.A.*(2008).What is Theory? Journal of Folklore Research, Vol. 45, No.1. Indiana University: Dep. of Folklore and Ethnomusicology*

M.D Murphy.(2004) . *Anthropological Thiories, Culture and Personality*. University of Albama.

Motz, Mrkilyn. (1998).*The Practice of Belief. The Journ of Americal Foklore* .Vol.111.No.441.

Michael Owen Jones, (1994). *Putting Folklore to Use: Essays on Applied Folkloristic* ed. Lexington: The University Press of Kentuckly.

Mishquen College.(2012).*Research Methods*. .

Mullen, B. (1969).*The Function of Magic Follk Belief Among Texas Coas Fishermen . The Journal of Amedican Folkklore.Vol.82.No.325.*

Ododo, Sendey.(2001). “The Theaterical Aesthatics and Functional Values of in Nigeria Ekuechi Masquerade Ensemble of Ebira People” (Journal).Department of the performing Arts, University of Ilcrin, Nigeria.

Okpewho, I. (1992). *African Oral Literature. Bloomington: Indianapolis University Press.*

_____. (2004). *African Oral Literature. Background Character. Indianapolis: Indianapolis University Press.*

O’Neill, G. (1972). *Open Marriage.* New York: M. Evans Company Inc.

Oring, Elliott. (1986). *Folk Groups and Folklore Genres; An Introduction.* Logan, Utah State University Press.

Philip Kotak.(1994). *Anthrppolpgy :The exploration of human diversity*. MC Griline Printers.

Peoples, J. and Bailey, G. (2nd ed.).(1991). *Humanity: An Introduction to Cultural Anthropology.* West Publishing Company.

Pine, F. (1996) *.Gendre. In barnard,A and J .Spencer eds. Encyclopedia of Social and Cultural Abthropology,* New York routtilage.

Propp, Vledmir. (1984). *Theory and History of Folklore.Translated by Arradna Y. Martin and P. Martin and Others.Edited, with an Introduction and Notes, by Anatoly Liberman.* Minneapolis: University of Minesota Press.

Radcliff-Brown, A.R. (1935). “On the Concepts of Function in Social Science,” in American Anthropologist. No. 37.

Rapaport, Roy A.(1999). Ritual and Riligion in the Marking Humanity.Cambridge University Press.

Shipley, J.T. (1970). *A Dictionary of World Literary Terms*. Aston, The Writers' Inc. Publisher,

Shovel M..(2nd ed.).(2007). *Macmillan English Dictionary: For Advanced Learners*. New edition Free online access. International Student edition. Macmillan Publishers Lim.

Sims, C. Martha & Stephen Martin. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition*. Lagon: Utah State University Press.

Schoemaker H. George (ed.) (1990). *The Emergence of Folklore in Everyday life: A Field guide & Source Book*. Trickster press. Bloomington; Indiana: Trickster Press.

The Office of Graduate Studies and Research of the Addis Ababa University (2010) . *Research Methods* (Module)

Thompson, Stith. (1946). *The Folktale*. New York.

Turner, Victor (1977). *The Ritual Process structure and Anti- Structure.* New York: Cornell University Press. Van. Gennep, A. (1960). The Rites of Passage. Translated by M.B. Vizedom.

UNESCO (2005) . *Convention on the Protection and Promotion of Diversity of Culture Expression.* Paris.

Vansina, Jan. (1985) . *Oral Tradition as History.* Great Britain, London.

Wolcott, H. (1999). *Ethnography: A Way of Seeing.* America: A Division of Rowan & Littlefield Publishers, Inc.

Wilson, William A. (1986). *Documenting Folklore in Folklore Groups and Folklore Genres : An I ntroduction.* ed. Utah State University Press.

World Book Encyclopedia, Volume 5, 12, 15 and 21.

Zelalem Getahun (1997) . "Amharic Political Plays (1974-81) A Contextual Study" M.A. Thesis. School of Gradu ate Studies, Addis Ababa University.

አባሪ አንድ

የገፀ -ባህሪያት ስም ዝርዝር[95]

ሀ. በያላቻ ጋብቻ ተዉኔት ዉስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት ስም ዝርዝር

1. ወ/ሮ አልጋነሽ ዱብዳ..... የባህሩ አክስት፡፡
2. ባህሩ አዳሽነህ..... ዉጭው ሀገር ተምሮ የተመለሰ፡፡
3. ቦጋለ..... የባህሩ የጡት ልጅ፡፡
4. በለጠች..... የባህሩ ገረድ፡፡
5. አሸከር..... የእሜቴ በቅሎ ያዥ ተከታይ፡፡
6. ሀጅና አለቃ..... የመንደር ሽማግሌዎችና አብሮ አደግ ጓደኞች፡፡
7. አባ ማሚቶ..... ጠጠር ጣይ አዋቂ፡፡
8. ደብተራ ልዝቡ..... መጽሀፍ ገላጭ ኮከብ ቆጣሪ፡፡

ለ. በሾተላይ ተዉኔት ዉስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት ስም ዝርዝር

1. አሮጊቷ ..... በየወቅቱ ለተነሱ ጦርነቶች ልጆቿን የገበረች ሾተላይ እናት፡፡
2. ልጅቷ ..... በቅርቡ ከእናቷ ጉያ የተጠለፈች ኮረዳ፡፡
3. ምሁር ..... መንግስት ተለዉጧል፤ ሀገር ረግቷል፤ ሰለም ተገኝቷል፤ ብሎ ከፊረንጅ ሀገር የመጣ የአሮጊቷ ልጅ፡፡

[95] ፀሀፌ -ተዉኔቶች በገለጹት መልኩ የተቀመጠ፡፡

4. ጭላት..... ከወንድሟ ጋር ተመሳጥሮ ፣ ያለእናቷ እና
ያለራሷ ፈቃድ ልጅቷን የጠለፈ ጎረምሳ፡፡

5. ዶኖ..... ከጠላፊዉ ጋር ተሻርኮ እህቱን ያስጠለፈ፣
የልጅቷ ታላቅ ወንድም፡፡

6. እረኛ..... የአሮጊቷ ልጅ፤የትላንቱን አስታዋሽ፤
የኣሬዉን አዉጊ፤የወደፊቱን
ተንባይ፤የሚጠብቀዉ መንጋ የሌለዉ፤
መልካም እረኛ፡፡

7. ቆሌ ..... የአባይ ወንዝ ቆሌ፡፡

8. መንፈስ ..... በግፍ የተሰዉ ሰዎች፡፡

9. ከልጅ 1- ..... የተለያዩ የአሮጊቷ ልጆች፡፡

10. ሬሳዎች..... በኢትዮጵያና ኤርትራ የጦር ፍልሚያ ላይ
የተሰዉ ወታደሮች፡፡

11. ኮረሶች ..... በዘማሪነት የሚያገለግሉ ሬሳዎች

ሐ . በአልቃሽና ዘፋኝ ተዉኔት ዉስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት ስም ዝርዝር

1. አስጋርጂው ..... አልቃሽ
2. ማሩ ..... አዝማሪ
3. ሽማግሌው .....ለማኝ
4. ባላምበራስ ..... ቤት አከራይ
5. ባሻ ..... አራጣ አበዳሪ

6. አራጌ ..... የትምህርት ቤት ዘበኛ

7. መልዕክተኛ

መ. በ የቴዎድሮስ ራዕይ ተዉኔት ዉስጥ የሚገኙ ገፀ- ባህሪያት ስም ዝርዝር

1. አጼ ቴዎድሮስ / ካሳ ጎይሉ/

2. ተዋበች አሊ /እቴጌ/

3. ገብርየ ጎሹ / ፊታዉራሪ/

4. አለሜ ጓሉ /ደጃዝማች/

5. ገልሞ ወረኛ /ባላምበራስ/

6. መልክተኛ/ የእቴጌ መነን/

7. ካፒቴን ካሜሮን / የእንግሊዝ ቆንስል/

8. ልዑል አለማየሁ ቴዎድስ

9. ባለሟል

10. ተራኪ

11. ሌሎችም

ሠ. በ የቃቄ ወርዶወት ተዉኔት ዉስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት

1. ወርዶወት ቃቄ ..... የ27 ዓመት ወጣት

2. ዳሞ ቃቄ ወራቦ .....የወርዶወት አባት-ዕድሜ 59

3. አጀት አሚና..... የወርዶወት እናት - ዕድሜ 56

4. አጋዝ ፉርችየ ላምቢያ..... የወርዶወት የልጃገረድነት ባለቤት - ዕድሜ 45

5. አጋዝ ሽበታ ሶርገኔ.....የምሁር ጀግና -የጦር መሪ-ዕድሜ 55
6. አሲህ አርብ ፉጋ ጌረሞ..... የችሀ ጀግና - ዕድሜ 42
7. ማማ በነስየ.....በድፍን ጉራጌ በጣም የሚደነቅ ዌግ ደርዳሪ
8. የወንድ ወገን ተሟጋቾችና የሸንጎ መልእክተኞች...../ሁለት/
9. የሴት ወገን ተሟጋቾች...../ሁለት/
10. የእጅካ ሸንጎ አባላት...../ሰባት/
11. ሰርግ ላይ ዘፈንና ጭፈራ የሚያደርጉ ወንዶች...../ስድስት/
12. የወርዶወት ሚዜዎችና ዌግ የሚደረድሩ ባልቴቶች...../ስድስት/
13. የጋዝ ፉርችየ ጋሻ ጃግሬዎችና ሲያገባ የወንድ ሚዜዎች...../ሶስት
14. የአሲህ አርብ ፉጋ የወንድ ሚዜዎች...../ ሶስት/

ረ. በ የአሻ ልጅ ተዉኔት ዉስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት ስም ዝርዝር

1. አቶ ሙርዴች ..... የጊብዚኒ፣ኢፋይና ኮሮይ አባት
2. ኢፋይ .....የጊብዚኒ ታናሽ ወንድም ፣ የቤቱ የመጨረሻ ልጅ
3. ጊብዚኒ..... ...የአቶ ሙርዴች ሴት ልጅ
4. ኮሮይ.....የጊብዚኒ ታላቅ ወንድም
5. ወ/ሮ ሞርገሊን.....የአቶ ሙርዴች ባለቤት
6. አቶ ሻያ እና አቶ ቢለሙ.....የሀገር ሽማግሌዎች
7. ኪኒ.....የአቶ ሙርዴች የወንድም ልጅ
8. ሻምባይ.....የጊብዚኒ ጓደኛ
10. መምህር ባሌ.....የጊብዚኒ መምህር
11. ዊሽኔ.....የኢፋይ ፍቅረኛ
12. ባርኮሞይ.....የጊብዚኒ ፍቅረኛ

አባሪ ሁለት

የቃቄ ወርዶወት ታሪክ ክፍል ሁለት[96]

በሴቶች ላይ የሚፈፀምን በደል ለማስቀረት ባሰተባበረችው ዓታዊ ትግል /ፍልሚያ/ ያለመችው ግብ ያልተሳካላት ውርዶወት ዳግም ለፉርችየ ሚስት ሁኚ የሚለውን የሽማግሌዎች ልመና ጨርሶ የማይሞከርና የማታሰብ አድርጋ እስከ መጨረሻውም አንቂት ተነስቶላት ባሏን ፈትታ የትግልና የድል ስሜትዋ ደብዝዞባት ወደ ትውልድ ቀዬዋ ተመለሰች፡፡ ያቺን የምትወዳትን ባሪያዋን አስከትላ በበቅሎዋ ሆና ምሁር ዝርምየ ገባች - አባትዋ ዳሞ ቃቄ ቤት፡፡ የቁጡዋን ውርዶወት ባህሪ ለመንከባከብ ቤሰቦችቹዋም የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ፡፡ አንድ ቤት ለብቻዋ ተለቀቀላት፡፡ የምትፈልገውን ሁሉ በማሟላት እሷን ደስ ለማሰኘት ተሞከረ፡፡ ይሁንና ውርዶወትን ግን ማስደሰት ሳይቻል ቀረ፡፡ ብቸኝነትና ትካዜ ያዛት፡፡ አልፎ አልፎ የውጪውን አየር ለመቀበል ወጣ ከማለት በስተቀር አብዛኛውን ጊዜዋን በጎጆዋ ውስጥ ሆና ነዉ የምታሳልፈው፡፡ የትዳርን ዓለም አይንህ ላፈር አለች፡፡ ብዙ ሰዎች ለትዳር ጥያቄ ሽማግሌ ቢልኩም የወርዶወት መልስ ግን አሳፍርና አንድ ነበር ..... “ትዳር አልፈልግም” ብቻ፡፡ ዝናዋ ግን በጠቅላላ ጉራጌ ናኝቷል፡፡ በየዜማው ትወደሳለች፡፡ ይሄን ጀግነትዋን ሰምተው ከተደነቁት መሀል አንዱ ደግሞ አሳፍሩና ቀሳኮኑ የተመሰከረለት የቸሃው ጀግና የአሴህአርብ ፋጋ (የጌረሞ ፋጋ) ነበር፡፡ አሴሕአርብ የሚለው መጠሪያ በቀድሞው የጉራጌ ዘመን የጀግኖች የማዕረግ ስም ሲሆን ትርጉሙም የማይሸሽ ማለት ነው፡፡ የአሴህአርብ ፋጋ ታሪኳንና ውበቷን እንደሌላው ሁሉ ሰምቶ አድንቆ አልፏል፡፡ በአይኑ ግን አይቷት አያውቅም፡፡ በመላው ሰባት ቤት በ “ዌግ” ዜማ (ቀደምት የጉራጌ ህብረተሰብ የጀግንነት ማወደሻ ዜማ) አቀንቃኝነት የሚታወቀውና የቅርብ ወዳጁ የሆነው ዌጋማ (ዌግ ደርዳሪው) ማማ በነስየ በየጊዜው በዌግ ሲያወድሳት ሲሰማ ይቺን ተአምረኛ ሴት በአይኑ ለማየት ይጓጓ ጀመር፡፡ ተመኝቶም አልቀረ፡፡ አጋጣሚ ሲፈቅድለት እግረ መንገዱን ወደ እነ ቃቄ ውርዶወት መንደር ጎራ ይልና የተነገረው ውበት በእውነትም ያለ እንደሆነ

[96] ደስታ ሎሬንሶ እና ጫንለው ወልደ ጊዮርጊስ፣(2007) “ የቃቄ ወርዶወት ታሪክና የጉራጌ ባህል ስነ ቃል እና ትውፊታዊ ትውን ጥበባት” የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር፣ ለትውፊታዊ ጥናትና ምርምር ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡

በአይኑ ለመመልከት ይወስናል፡፡ እናም ተሳካለት፡፡ ያቺ እጅግ የምታምር ሴት ሀዘን በቀላቀለ ስሜት ሆና ያያትና ይመለሳል፡፡ ከዛች ቅጽበት በኋላ ግን ቆፍጣናው የጌረሞ ፉጋ (አሴህአርብ ፉጋ) ትካዜ ገባው፡፡ እሱም በበኩሉ ብቸኛ ሆነ፡፡ ብቻውን እየተንሳራደደ መብሰልሰል ሆነ፡፡

የአሴህአርብ ፉጋ የተጨነቀው በውርዶወት ዝናና ውበት ብቻ ሳይሆን ፈፅሞ ትዳር ቀርቶ ወንድ የተባለን ፍጡር እርም ብላለች ተብሎ በተነገረው ዜናም ነው፡፡ እንዲያ ያፈቀራት ሴት የማትነካ፣ የማትደፈር፣ የማትቀመስ መሆኗ!

ትካዜውን የተመለከተውና በቄግ ግጥምና ዜማ መንፈሱን መለስ የሚያደርግለት አፅናኝ ወዳጁ ማማ በነስየ በመጨረሻ ጠየቀው፡፡ አንድ እግሩ ስለሚያነክስ በጉራጌ ህዝብ ዘንድ ጅረ በነስየ (የሚያነክሰው የበነስየ ልጅ እንደ ማለት ነው) በሚል ስያሜ ነው የሚታወቀው፡፡ “ምን ሆንክብኝ ጌታዬ? ምነው እንደዚህ ትካዜህ በዛ? ምን ገጠመህ ወዳጄ?” አለው ፡፡

“ፍቅር ወደ ልቤ ገባ”፡፡ መለሰለት፡፡

“ፍቅር? ታዲያ ለፍቅር ነው እንዴ ይሄ ሁሉ ሃዘን? ደግሞስ ማንናት አንተን እንቢ እምትል ሴት - ጨርሶ አትኖርም፡፡ ለመሆኑ ባለትዳር ናት?፡፡

“ ባለትዳርስ አይደለችም፡፡ ግን እሺ አትለኝም፡፡”

“እንዴት እሺ አትልህም? ሞክረሃታል?”

“አልሞከርኩም፡፡”

“እንዴ!! ለመሆኑ ማናት ይቺ ሴት!!” አለ ጅረ በነስየ ተደንቆ፡፡

“ምን ይሠራልሃል ብነግርህ? የሚቻል አደለም፡፡”

“ንገረኝ ጌታዬ፤ እኔ የሚቻል አደርገዋለሁ፡፡ አንተኮ የጀግኖች ጀግና ነህ፡፡ አንተን እምቢ የምትል ሴት አትኖርም፡፡ የው ጌታዬ በኔ የቄግ ድርደራ ገድልህ ቀርቦላት የማትማረክ ሴት አትገኝም፡፡ ይልቅ ንገረኝ፡፡ ማናት እሷ?” ይለዋል፡፡

“በእርግጥ ይሄን ማድረግ ትችላለህ? እሺ ታሰኛታለህ?”

“በሚገባ ጌታዬ፡፡” አለ ጅረ በነስየ፡፡

“እንግዲያው እሺ ካሰኘህልኝ እቺን ላሜንና ያን ኮርማዬን ውሰድ፤ካልቻክ ግን ይሄ ደህነኛው እግርህም ይሰበር” አለው፡፡ “የወደድኳት ቆንጆ የቃቄ ውርዶወት ናት፡፡”

“አይዞህ ጌታዬ በኔ ጣለው፡፡ አሁን ተነስ፤ ትካዜህን አቁምና ታጠብ፤ የክት ልብስህን አድርገህ አጊጥ፤ እንደወትሮህ ያን ቃጭሉ ከሩቅ የሚሰማውን ማራኪ ነጩን ፈረስህን በጌጥ ሸላልመህ የጦር እቃህን ይዘህ ሶምሶማ ምታ፡፡ ሠንጋ ይታረድ፡፡ ለሠርግህ ተዘጋጅ” አለው ጅረ በነሲየ በሙሉ ልብ ቆሞ፡፡

“እውነትህን ነው?” አለ አሲህ አርብ ፉጋ

“ቃል ገብቼአለሁ፡፡”

ጅረ - በነስየ ለሶስት ቀናት ከልቡ ሲመክር ከቆየ በኋላ በፈጣን ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ወደ ምሁር ወረዳ ሲገሰግስ ሄደ፡፡ ውድማጠር - ቅራረት፡፡ የቆንጆዋ መንደር ዝርመኛ ድረስ፡፡

ጅረ በነሲየ በሂደበት ሁሉ የሚወደድ የሚከበር ትልቅ እንግዳ ነው፡፡ ምነው ወዲህ በመጣልን የሚባል ቄጋማ ነው፡፡ የቤቱ-ጉራጌ ጀግኖችን ታሪክ ልቅም አድርጎ የሚያውቅ እጅግ ውብ በሆነ ቋንቋ የሚገልፅ ውብ ድምፅ ያለው አንቱ የተሰኘ የቄግ ንጉሥ ነው፡፡ በባላባቱ በቃቄ ቤትም መልካም አቀባበል ተደረገለት፡፡ እዚያ ማደሩ ሲታወቅም የአካባቢው ሰው ሁሉ ሩቅ ድረስ እየተጣራራ ያንን ማራኪ ቄግ ሊሰማ ሊያድር በቃቄ ቤት ተሰበሰበ - ከውርዶወት በቀር፡፡ ጅረ በነሲየ በዚህ አልተደነቀም አልተደናገጠም፡፡ የጠበቀው ነው፡፡ ምክንያቱም በዛች ሌሊት አሥር ሜትር ያህል እንኳ በማይርቀው ጎጆዋ ሆና ውርዶወት ሳትታይ ቄጉን ልትሰማ እንደምትጓጓ ያውቃል፡፡ ከብቶች ገብተው፣ እራት ተበልቶ፣ በወንድ ጎልማሶች አረቄ እየተጠጣ ምሽቱ ጀመርመር እንዳደረገ በጉጉት የሚጠበቀው የጅረ በነሲየ ቄግ መደርደር ጀመረ፡፡ በዛ ረጭ ባለ ምሽት የሚያስገመግመው ድምፁ ጨለማውን እየሰነጠቀ የጉራጌ ጀግኖችን ከነፍልሚያቸው በአካል ያቆማቸው ይመስል ያቀርበው ገባ፡፡፡ በጎጆው ውስጥ ከስሜቱ ጋር አብሮ በሚርገበገበው የጧፍ ብርሃን ዙሪያ ግርግዳውን ከብቦ ያለው ሳይንቀሳቀስና ትንፋሽ ሳይል የሚመለከተው ሰው ሁሉ በተመስጦ

ያደምጠዋል፡፡ በነሲየ እየተጋጋለ ሄዶ ፊቱ ላይ ላቡ ቸፍ ብሎ እጅግ ከፍ ያሉ ጀግኖች ገድል ጋ ሲደርስ ለአድማጩ በአንድነት እንዲቀበል አዝማች የመሰለ ቃል ሰጠው፡፡ የእከሌ ጀግንነት፣ በዛ ፈረሱ፣ በዛ ወኔው፣ በዚህ ቦታ እያለ ያወድሰውና በውዳሴው መጨረሻ ላይ “የሆነስ ሆነና ቆፍጣናውን የአሴህአርብ ፉጋን የሚስተካከል ጀግና ይገኛል ወይ?” ብሎ ዙሪያው ያሉትን ሁሉ ይጠይቃል፡፡ ሁሉም በአንድነት “አይገኝም” በማለት ይመልሳሉ፡፡ እጅግ ድንቅ የሆኑ ጀግናዎችን ገድል ያነሳና አሁንም በመዝጊያው ላይ ያቺኑ ጥያቄ ለዙሪያ ገባው ይጠይቃል፡፡ አሁንም ያቺኑ መልስ ያገኛል፡፡ ከዚያም የአሴህአርብ ፉጋን ጀግንነት ያወሳል፡፡ “በነጩ ፈረሱ ከአይን በሚፈጥነው ቃጭሉ ሲሰማ እንደጥይት ፉጨት የሚያርበደብደው፤ ጀግናዬ! ወዘተ.” እያለ የጀግንነት ታሪክ ርቂት ብቸኝነትና ትካዜ መላ መንፈሷን አቀዝቅዞባት በሕይወት ተሰላችታ የነበረችው የውርደወት ነፍስ በዛች ሌሊት በአዲስ ብርሃን ተሞላች፡፡ ግርግዳዋን ተደግፋ በአይነ ህሊናዋ ገሠገሠች፡፡ “የቱ ነው የአሴህአርብ ፉጋ?”

ለቃቄ ውርዶወት የጅረ በነሲየ አመጣጥ ምክንያት ግልጽ ነበር፡፡ የአሴህአርብ ፉጋንም በአካል ሳታየው ወደደችው፡፡ እንደሌሎቹ ትዳር ጠያቂ ወንዶች ያረጁ ሽማግሌዎች አደለም የላከው፡፡ የጀግንነቱን ገድል ነው የላከላት፡፡ ወንድነቴን ከወደድሽው ነይ ነው ያላት፡፡ ነይ ይሄን ክንዴት ተንተራሽው፣ ነይ ከዚህ ዝና ጋር ኑሪ ነው ያላት፡፡ አላወላወለችም፡፡ ይኼ የጀግኖች ጀግና ነው የሷ ባል፡፡ ነጋ፡፡ ጅረ በነሲየም ሊሄድ ነው፡፡ እዛ ቤት ላነጋው የአካባቢው ሰው ቁርስ ቀርቦ ተበልቶ ቡና እየተጠጣ ሳለ ድንገት የፈረስ ግልቢያ ኮቴና የቃጭል ድምፅ ይሰማል፡፡ ሁሉም አንገቱን አሰግጎ “ማነው”? ብሎ ሲመለከት ባጌጠ ወተት ነጭ ሰንጋ ፈረስ ጋሻና ጦሩን የያዘ ሰው በፍጥነት እየጋለበ በቀጥታ ወደጎጆው ሲገሰግስ መጥቶ የጎጆው ደፍ ጫፍ ሊደርስ ሁለት እርምጃ ሲቀረው የፈረሱን ልጓም አንቆ ቢይዘው ፈረሱ በሁለት እግሩ ወደ ላይ ቆመ፡፡ ኮቴው ባስነሳው አቧራ ውስጥ ሲመለከቱ በፈረሱ ጀርባ ያለው ጎበዝ ሌሊቱን ሲሞገስ ያደረው የአሴህአርብ ፉጋ መሆኑን አልተጠራጠሩም፡፡ ሁሉም ነገር በአጭር አፍታ ነበር የተከናወነው፡፡

በዚህ ጊዜ ጅረ - በነሲየ ለሰው ሳይሆን ለአምላክ እንደሚሰገደው አይነት “ኤቸሁ!” አቤቱ አውጣን! ማረን!/ ብሎ በግንባሩ ተደፋ፡፡ ወዲያውም ተነስቶ እየሮጠ ወደ

ቃቄ ውርዶወት ገባና “እመቤቴ - በቃ መሞቴ ነው ዛሬ! እመቤቴ!” ማለት ሲጀምር ውርዶወት በአፏጭሩ አቋረጠችው፡፡ “አንተም አትሞት፤ እኔም እዚህ አልቀር፡፡” አለችውና ግራ እንደተጋባ በቀጥታ ወደምትወዳት ባሪያዋ ዞራ “በቅሎዬን ጫኚልኝ፡፡” አለቻት በቅሎዋ ቀረበላት፡፡ መጀመሪያ ውርዶወት ወጣች፡፡ ባሪያዋም ተፈናጠጠች - ያንን የዘወትር የባህል ጃንጥላ ለእመቤትዋ ከፍ አድርጋ ያዛችላት፡፡

ገርሟቸው የሚመለከቷቸውን መላጆቿን፣ ዘመዶቿንና አካባቢውን “ደህና ሰንብቱ” ብላ ወደ ቸሃ ተጓዘች፡፡ የአሴህአርብ ፉጋ እየመራ፣ ጅረ በነሲየ ከኋላ እያጀባቸው - ለሁለተኛ ጊዜ ሞኸርንና ላጤነትን ተሰናብታ፡፡

ቸሃ የአሴህአርብ ፉጋ ወንድም ቤት አረፉ፡፡ ለሁለት ምክንያት ፡፡አንድ ለአቀባበሉ በተደረገው ቅንብር ሚስጥሩ ተነግሯት የነበረችው የኤሴህአርብ ፉጋ ወንድም ሚስት እቅዱ ከተሳካ እሷ ዘንድ እንዲመጡ ተዘጋጅታ ትጠብቃቸዋለች፡፡ ዋናው ደግሞ የአሴህአርብ ፉጋ ጀግነነት እንጂ ሀብት ስለሌለው ደመቅ ያለ ዝግጅት ማድረግ ስለማይቻልና ያንን ቀዝቀዝ ያለ ቤት ለዛች ድንቅ ሙሽራ መቀበያም ሆነ መሰንበቻነት የማይመጥን መሆኑን ልባቸው ሰግቶባቸዋልና፡፡

አመሻሹ ላይ ቸሃ ገቡ፡፡ ወንድምየው ቤት - ለብቻቸው ክፍል ተሰጥቷቸው፣ እራትም አለበት ድረስ ቀርቦላቸው ተመግበው አረፍ አሉ፡፡ ሌላውም ቤተሰብ በየፊናው ወደመኝታው ገባ፡፡ የአሴህ አርብ ፉጋ ሚስት ይዛ እንደመጣ እንጂ ማንነቷን ያላወቀው ወንድምም ነገሩን ብዙም አክብዶ አላየዉም ነበርና ተዝናንቶ ተኝቷል፡፡

ጅረ በነሲየ ግን እንቅልፍ እምቢ ብሎት ተቸግሯል፡፡ ያቺ ዝነኛ ትልቅ ሴት በአሴህ አርብ ፉጋ ትንሽ ሀብት ረክታ መቀመጥ እንዴት ትችላለች በማለት ክፉኛ ሰግቷል፡፡ ያ ሁሉ ልፋት ከንቱ እንዳይሆንበት መፍትሔ ፍለጋ ይብሰለሰላል፡፡ መፍትሔው ደግሞ መዘግየት የለበትም፡፡ አለበለዚያ ዋጋ አይኖረውም፡፡

መላ ፍለጋ ሲያሰላስል ሌሊቱ እየገፋ ሄደ፡፡ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ግድም በነሲየ ብድግ ብሎ ተነሳና ወደወንድምየው ሄዶ ቀሰቀሰው “ና ጉድ ላሳይህ” ብሎ ከምድጃው ፍም በደረቅ ስንደዶ እሳት ለኩሶ እየመራ ውርደወትና የአሴህአርብ ፉጋ ወደተኙበት ጎጆ ወሰደው፡፡ እናም አሳየው በዛች ስስ የስንደዶ ብርሃን ውርዶወት

ከደረቷ በላይ ተገልጣ የአሴህአርብ ፉጋ ክንድን ተደግፋ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዷታል - ያቺ የውበት ምትሐት።።

ያልጠበቀውን ይሄን ህልም የመሰለ ውበት የተመለከተው የፉጋ ወንድም መላ ሰውነቱ ይርድበታል።። እናም በነሲየ የለኮሳትን ስንደዶ በመዳፉ ጭብጥ አድርጎ ያጠፋትና በዝግታ አንቆ እየሰባው ይዞት ወደ ደጅ ይወጣል።።

“ይሄንን ልዩ ውበት አየኸው?” ይለዋል በነስየ።።

ወንድምየው ግን እየተንቀጠቀጠ “እና ወንድሜን እንድገለው ነው የምትፈልገው?” አለው አንቆ እንደያዘው።። በነስየ ግን ተረጋጋ።። ወደጆሮው ቀርብ አለና “እኔ ይሄንን ውበት ሰጥቸዋለሁ፣ አንተስ ለዚህ ውበት ማስተዳደሪያ ምን ትሰጠዋለህ?” አለው።።

የአሴህአርብ ፉጋ በዚህ ዓይነት በቂ ላሞችና ኮርማዎችን አገኘ።። ውርዶወትም ያንን የምትወደውን የጀግንነት ገድል ከራሱ አንደበት ክንዱን አቅፉ እየሰማች፣ በወደደች ጊዜ ደግሞ የበነስየን ቄግ በምሽቶች እየኮመኮመች በጥሩ ሁኔታ መኖር ጀመረች።።...

የቃቄ ውርዶወት ታሪክ በዚህ አላበቃም።። የተነሳችበት የተበደሉ ሴቶችን መብት የማስከበር ትግል ባለመሳካቱ የሰላም እንቅልፍ አልነበራትም።። በግል ህይወቷ ግን በተግባር ምሳሌነቷን ለማሳየት አሳሪውን ባህላዊ የትዳር ህግ አሸቀንጥራ ነፃነቷን አውጃለች።። ቀጣዩ የውርዶወት ህይወት አንቂት የተነሳላት ሴት መብትን በመጠቀምና ጀግንነትን መውደዷን በሚያሳይ መልኩ በሰባት ቤት ጉራጌ እየዞረች ታዋቂ የጉራጌ ጀግኖችን በፍቅር እያንበረከከች፣ በራሷ ውሳኔ ባልን የማግባትም ሆነ የመፍታት የግል ፈቃዷ መሆኑን እያሳየች፣ ያሻትን የማረካትን ጀግና እያገባች፣ እሷ የመረጠችው አቤት ደስታው! - አቤት እድለኛነቱ! - በደስታ ከብት አርዶ ይቀበላታል።። ባሻት ጊዜ እየፈታች እሷ የፈታችው እንዴት ያዝን ይከፋ! “ድረድግ!” ነውንጂ ምን ያባላል።። ብቻ በዚህ መልኩ በአማካኝ ከ4-5 ዓመት ኖራለች።።

በሰላሳዎቹ አጋማሽ እድሜዋ ወደ ዘናበነር ስትጓዝ (የዘወትር አገልጋይዋን አስከትላ) ጭራት የተባለው አካባቢ በመብረቅ ተመታ መሞቷን በአብዛኛው የሰባት ቤት ጉራጌ ህዝብ ዘንድ ይታመናል፡፡

አባሪ ሶስት

በቃለ- መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ማሳያ

ቃል -መጠይቅ አንድ

የመረጃ ሰጭ ስም፡- መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኝ ፣ እድሜ ፡- 73፣ ስራ፡- ቤተክህነት ፣ ልዩ ሙያ፡- መጽሀፍ ገላጭና የሀገር ባህል መድሀኒት አዋቂ፣ መኖሪያ፡- ደብረ ማርቆስ

መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን ፡-የካቲት 16 ቀን 2009 ዓ.ም ከ 10፡00-11፡00 ሰዓት

መረጃ ሰብሳቢ፡- ወሰን ባዩ

ስለኮከብ ቆጠራ መንግስቱ ለማ የተባሉ ፀሀፊ ያላቻ ጋብቻ በሚለዉ ተዉኔታቸዉ ዉስጥ ያነሳሉ፡፡ እስቲ ኮከብ ቆጠራ ማለት በእርስዎ እዉቀት ምንድን ነዉ?

ኮከብ ቆጠራ ማለት የሰውየውን ስም አስራሁለቱን ሀዋርያትን ይወክላሉ፡፡መጀመሪያ አስራ ሁለቱን አውራህ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ አዉራህ ማለት ወራት ማለት ነዉ፡፡በየአንዳንዱ ወር ይወጣሉ ፡፡ መስከርም አንዱ ጥቅምት አንዱ ህዳር አንዱ ወ.ዘተ አስራ ሁለቱ አውራህ አመቱን የያዙት እነሱ በሚመሩበት ልጅ ይወለዳል፡፡የልጁ ስም ይቆጠራል የአንድ ቤት የአስር ቤት የመቶ ቤት አለ፡፡ ያ ሁሉ በአስራ ሁለት ይቀነሳል፡፡ በዘጠኝ ይቀነሳል በሰባት ይቀነሳል፡፡ በአስራ ስምንት እንዲሁም በአስራ አምስትም ይቀነሳል፡፡

የኮከብ ቆጠራ አላማ ምንድን ነዉ?

የሰዉየዉን እድልና እጣፋንታዉን ለማወቅ ኮከቡ ተቆጥሮ ሰዉ የሚወለድበት ከአስራ ሁለቱ አውራህ ስለማያልፍ በነዚህ ወራት የሚወጣ መሪ ኮከብ አለ፡፡ያ ኮከብ አስትሮሎሚ ወይም ቲዮ ሎጊያ ይባላል፡፡ ቲዮ ማለት አምላክ ማለት ሲሆን ሎጊያ ማለት ደግሞ ጥበብ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት ይህ ሳይንስ ይረቀቃል፡፡ ይህም በግእዝም በእብራይስጥም በላቲንም በአረብም መጠቀም ይቻላል፡፡ ነገር ግን አሁን ይህን ትምህርት እዚህ ላይ ዘርግቶ ማሳየት አይቻልም፡፡

የ አንድን ሰዉ ኮከብ ቆጥሮ ስለባህሪዉ መናገር እንደሚቻል ሰምቻለሁ ይህንን ቢነግሩኝቸ?

መልካም እሱን ልነግርህ ነዉ። በዚህን ጊዜ ይሞታል፤ በዚህን ጊዜ ተወለደ፤ ወደዚህ ሃገር ቢሄድ እንዲህ ይሆናል። ለዚህ ሁሉ ተነብዮ አለዉ። እድል ፈንታዉን ጽዋ ተርታዉን ቢይዝም ባይዝም ተጽፎ ይገኛል። አዉደ ነገስት በሚባለዉ መጽሃፍ ላይ ይህ ሁሉ ሰፍሮ እናገኘዋለን። አዉደ ነገስት ደግሞ ሃሰት የለዉም ፊደሉ ከተገናኘ ፊደሉም ለምሳሌ ሶስቱም ሀ- አሉ እነዚህን ፊደላት ደግሞ ተለይተዉ መቀመጥ አለባቸዉ። ሞክሼ ያላቸዉ ፊደላት ሌሎችም አሉ ለምሳሌ አ- እንዉሰድ አለም ለማለት አይኑ ዐ መሆን አለበት። የመጀመሪዉ ሃመል እሳት ይባላል በመቀጠል ደግሞ ስወር መሬት ሶስተኛዉ ገወዝ ነፋስ አራተኛዉ ሸርጥ መሬት አምስተኛዉ አሰድ እሳት ስድስተኛዉ ሰንቦላ መሬት ሰባተኛው ሚዛን ነፋስ ስምንተኛዉ አቅራብ ዉሃ ዘጠንኛዉ ገዉዝ እሳት አስረኛዉ ጉዲ መሬት አስራ አንደኛዉ ዲላዊ ነፋስ የመጨረሻዉና አስራ ሁለተኛዉ ሁት ዉሃ ናቸዉ።

በተከታይነት ደግሞ የአሰራ ሁለቱንም ኮከብ መገለጫ ባህሪያት ቢነግሩኝ

መልካም አስራ ሁለቱም የራሳቸዉ የሆነ ባህሪ አላቸዉ ልምሳሌ ፦

1. **ኮከቡ አሰድ እሳት የሆነ ሰዉ ልዩ መገለጫ፦**
    - ቸርና ለጋስ ነዉ፤ሀብታም ነዉ፤ አጋንንት ይጠናወቱታል።
    - ሴቶች ብዙ ጊዜ ይንቁታል ፤ ገንዘብ አይበረክትለትም።
2. **ኮከቡ ስዉር መሬት የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፦**
    - አይነጥላ አለበት፤ ገንዘብ ይቆጥባል።
    - ብዙ ጊዜ ጠላት አያጠቃዉም ጠንቃቃ ነዉ።
3. **ኮከቡ ገዉዝ ነፋስ የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፦**
    - የታወቀ ገበሬ ይሆናል የእርሻ ሰዉ ነዉ። የምርት ሰዉ ነዉ።
    - ብዙ ከብት ይኖረዋል።
4. **ኮከቡ ሸርጣ የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፦**
    - የዉሸት ሰዉ ነዉ፤ ወንበዴ ጭምር ነዉ።
5. **ኮከቡ አሰድ እሳት የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፦**
    - ቸርና ለጋስ ነዉ፤ በሴቶችም ተፈላጊ ነዉ።እሱም በአንድ ሴት አይረጋም።

6. **ኮከቡ ሰንቡላ መሬት የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፡-**
   - ቀና ነዉ ነገር ግን የራሱን ክብር መጠበቅ አይችልም፡፡
7. **አቅራብ ዉሃ የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፡-**
   - ጠንካራና ንፉግ ነዉ፡፡
8. **ኮከቡ ጀዲ መሬት የሆነ ሰዉ መገለጫ ባህርያት፡-**
   - ሀገር ያስከብራል ፤የዉትድርና ስራ ይሆነዋል፤ደሙ ቢፈስ ግድ የለዉም፡፡
9. **ኮከቡ ገዉዝ እሳት የሆነ ሰው መገለጫ ባህርያት፡-**
   - የሆድ በሽተኛ ይሆናል
   - በሰዉ እጅ ይሞታል፡፡
10. **ኮከበ ሑት ውሃ የሆነ ሰው መገለጫ ባህርያት፡-**
    - ነገሩ ሁሉ ጠንካራና ጥብቅ ነው፤ ቁጡና ደፋር ነው፡፡
11. **ኮከቡ ደለዊ ነፋስ የሆነ ሰው መገለጫ ባህርያት፡-**
    - ቁምነገረኛ ነው፤ ቁጠባና ብልህነት ዕድሉ ነው፡፡
12. **ኮከቡ ሚዛን ነፋስየሆነ ሰው መገለጫ ባህርያት፡-**
    - ፍርሀት የለውም፤አደጋ ጣይና ጨካኝ ነው፡፡

እስቲ ስለ አራቱ ባህርያተ ሰጋ ይንገሩኝ?

የሰዉ ልጅ ከአራቱ ባህርያት ነዉ የተፈጠረዉ ማለትም ከእሳት ከዉሃ ከመሬትና ከነፋስ ማለት ነዉ ፡፡ እነዚህን ማግኘት ካልቻለ የሰዉ ልጂ መኖር አይችልም፡፡ እነዚህ አራቱ አስራ ሁለቱ ሶስት ሆነዉ ነዉ የሚካፈሉት ለሶስት ሲካፈሉ ሶስት ጊዝ ይደርሳሉ፡፡ ለምሳሌ አንተ አሰድ እሳት ብትሆን እሳት ነህ ማለት ነዉ፡፡ እሳትነትን በራስህ ወሰድክ አሁን ደግሞ መሬት ያስፈልግሃል፡፡ ሰዉ የመሬት ክፍል ነዉ፡፡ከመሬት ሰዉርን ታገባለህ፡፡ ከዉሃ አቅራብን ከንፋስ ገለዊን፣ ከእሳት ደግሞ አሰድ እሳት እነዚህ ናቸዉ፡፡የሰዉ ልጅ ከአራቱ ባህርያት አይወጣምና፡፡

ሃራ ዘመን ማለትስ ምን ማለት ነው?

ሃራ ዘመን ማለት የዘመን ዉጤት ነዉ፡፡ጎደሎና ሙሉ ቀን ጥሎኝ ይባላል ምክንያቱም የሚጥልም ቀን አለና ነዉ፡፡ሀሳበ ጋብቻና የፈውስ እሳት የሚባል አለ፡፡

በጠጠር መጣልና በኮከብ ቆጠራ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ጠጠር ለባህሪ ማሳ ነው፡፡ጠጠሩን አይቶ ለመተንበይ ያገለግላል፡፡ኮኮብ ቆጠራ ግን መሰረት ነዉ፡፡ክርስቶስ የተወለደዉ ኮከብ ሰባሰገድ እየመራ መምጣቱ እተወለደበት ድረስ ከታሪክ ተምረው ስለሆነ ኮኮብ ቆጠራ ከመጽሃፍ ቅዱስ ጋር የተያዘዘ ነው፡፡ እንደ አራቱ ወንጌላውያን አራት ከዋክብት አሉ እንደ ሃዋርያምአስራ ሁለት ከዋክብት አለ፡፡ያንን በዘመነ አሪት ሲጠቀሙበት ነበር፡፡

እነዚህ አራቱ ማን ማን ናቸው?

እነዚህ አራቱ ሄልመሊክ፣ አርያል፣ኤርናኪና ምንየል ይባላሉ፡፡እነዚህ አራቱ ባህርያት የላቸዉም፡፡ እነሱ አለቆች ናቸው፡፡አምሳ ሁለትን በሰባት ስናበዛዉ ዉጤቱንም ለአራት ሲካፍል ዘጠና አንድ ይመታል፡፡እያንዳንዱ ወቅት ሶስት ወር ከአንድ ቀን ነዉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዘጠና አንድ ቀን የሚኖሩ ሹሞች ናቸዉ፡፡ ብርሃናትን የሚቆጣጠሩ ፣ከዋክብትም እነዚህ ሲሾሙ የሚወጡበት ቀን ነዉ ዘጠና አንዱ፡፡ እነዚህ የሰራዊት አለቃ ናቸዉ፡፡ አንዱ ከዋክብት ወዲያዉ ሲወጣ ልጅ ይወለዳል፡፡ በዚህም መሰረት ለልጁ ስም ይወጣል፡፡ ኮኮቡም አብሮ ይወሰናል፡፡ ጸሀይ የአለም መሪ ናት ፡፡ ግን ከክርስቶስ የምታንሰዉ ክርስቶስ የባህርይ አምላክ ነዉ ጸሀይ ግን የተፈጥሮ ህግ ናት፡፡ ብርሃኗ ፣ሙቀቷና ክቧ አላት፡፡ ክርስቶስም በአራት ወንጌላዉያን ይችን አለም ይመራል፡፡ መመሪያዉም በሃዋርያት ጸደቀ፡፡ ለ ህዝብም ተዳረሰ ህዝቡም ደግሞ ወንጌልን ተቀበለ የተቀበለዉም በሃጢያት ወድቆ ነበርና በዚሃ የተጠመቀ እና ከመንፈስ ቅዱስ የተወለደ እሱ ዳነ የኔም ስም ተጠራ እንዳለ ኢየሱስ ክርስቶስ፡

ጠጠር መጣልስ ለምን ይጠቅማል?

ጠጠር ለጦር ሜዳ ለሃብትም ለሌሎች ነገሮችም ይደረጋል፡፡ እንዴዉም ጨሌ የሚዞር ጠጠር ጣይ እና ሞራ ገላጭ የሚባልም አለ፡፡ከጋብቻ ጋር በተገናኘም ጠጠሩን አይተዉ ብቻ እጣ ክፍልህ ናት ይላሉ በልጅቱ ስም ጠጠር ይሰጠዋል የጠጠሩ ብዛት ግን አይታወቅም፡፡

ሾተላይ ማለት ምን ማለት ነዉ?

ሾተላይ ማለት የሰይጣን ባህሪ ነዉ፡፡ በህልመ ሌሊት ይመታል፡፡ በሴቷ ጭን አድሮ በኋላ ላይ ልጁ ሲወለድ የምቀኛ አይነት ስለሆነ ልጅ ከተወለደ በኋላ ላይ ወይም በማህጸን ዉስጥ እንዲሞት ያደርጋል፡፡

ቆሌ ምንድን ነዉ?

ቆሌ ማለት በአይን አይቶ የሚወጋ እድሜን የሚያሳጥር ነዉ፡፡ ደም ፈላጊ የከብት፣ፍየል የበግ የዶሮና የሰዉም ይፈልጋል፡፡

ለምሳሌ የአባይ ቆሌ ሲባልስ?

የአባይ ቆሌ ሰዉ ሰራሽ ነዉ፡፡ ቆሌ ወንዝንም ይቆራኘዋል፡፡ ሁሌ ወንዝ ጋ አትሂዱ የሚባለዉ ለዚህ ነዉ ሌሊት ሲተፋበትንና ሲሸናበት ስለሚያድር ነዉ፡፡ ለምሳሌ ዶሮ በስምንት ሰአት ሲጮህ መንፈስ ቅዱስ ይወርዳል፡፡ ዉሃዉም ይቀደሳል፡፡ እንግዲህ ቆሌ ዛር ነዉ፡፡ መምለኪያ ጣኦት ሰዉ ወንዝ ይገዛል፡፡ ወንዙን እናከብረዋለን ይላል፡፡

እርኩስ መናፍስት ሲባልስ ምን ማለት ነው?

እርኩስ መናፍስት ሲባል የጽድቅ ስራ የሌላቸዉ፣ ለሰዉ የማይራሩ፣ ፈጣሪያቸዉን የሚክዱ፡ ለፈጣሪቸዉ የማይገዙ ከአግዚአብሄር በቅጣት የተባረሩ የማይታዩና የማይዳሰሱ ሰዉ ወግተዉ የሚጥሉ ናቸዉ ርኩስ መናፍስት፡፡

የሙት መንፈስ ማለት ምን ማለት ነዉ ጣረ ሞትስ?

የሙት መንፈስ ማለት ከመቃብር ቀስቅሶ የሚስነሳ ሲሆን ጣረሞት ደግሞ ነፍሱ ሳትወጣ ያለዉ ሂደት ነዉ፡፡ የሙት መንፈስ ስዉር ቡዳም ነዉ ይባላል፡፡

ጸሎት ማለት ምንድነዉ? ከዚህጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች ሰለሚለዉ ጸሎት ቢነግሩኝ?

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች፡፡ለልጆቿም ትጸልያለች ተብሎአል፡፡ ጸሎት ማለት እንግዲ ህ ከአምላክ ጋር ንግግር ነዉ፡፡ሰአት ጠብቆ ሰዉ አምላኩን ሲያመሰግን እግዚአብሄርም አምላክም የልመናዉን ዋጋ ይከፍለዋል ማለት ነዉ፡፡ እንደኔ እምነት ጸሎት ባይኖር ኖሮ በሀገር መኖር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ነጻነት በጸሎት ተገኝቶአልና፡፡ ኢትዮጵያ ታበጽ እድዊሃ ህበ አግዚአብሄር ማለት መዝሙረ ዳዊት ቁጥር ስድሳ ሰባት ላይ ተመልከት፡፡ ያሬድም ዳዊቱን በሰላሳ መዝሙር ከፍሎታል፡፡ የሰኞ ሰላሳ የምክሰኞ ሰላሳ ወዘተ እያለ፡፡

ንግርትና ትንቢት የሚሉት ቃላትስ ትርጉማቸዉ ምንድን ነው?

ንግርት ማለት ትንቢት ማለት ነዉ፡፡ በዚህ ዘመን እንዲህ ይደረጋል እህል ይረክሳል ፤ጦርነት አለ ፤ ወ.ዘ.ተ ብሎ መተንበይ ነዉ ንግርት፡፡

ለንግርት ወይም ለትንቢት መነሻ ካለው?

መነሻዉ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ፡፡ ዳዊትና ሙሴ ሊቀ ነብያት ይባላሉ፡፡ ሌሎችም አስራ ሁለት ደቂቀ ነብያት አሉ ፡፡ እነዚህ ትንቢት የተናገሩ ናቸዉ፡፡አራቱ በኩር ነቢያት ይባላሉ፡፡ እነሱም፡- ኢሳይያስ፤ ኤርምያስ፤ ህዝቅኤልና ዳንኤል ናቸዉ፡፡ በኩረ ነብያት ማለት መሪዎች ማለት ነዉ፡፡ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ብሎ የተነብየዉ ነብዩ ኢሳይያስ ነዉ፡፡ በድንግልናዋ በተመለከተ ተጸንሶ መወለዱን ደግሞህዝቄል ትንቢት ተናግሮአል፡፡ ኤርምያስም ስለ ዐለም ምጽአት ትንቢት ተናግሮአል፡፡

ህዝቅያስም ታቦተ ጽዮን ትማረካለች ብሎ ትንቢት ተናግሮአል፡፡ ታቦተ ጽዮንን በተመለከተ ፕሮቴስታንቶች ታቦተ ጽዮን የለም ይላሉ፡፡ማርቲን ሉተርም ስለዚህ በስፋት ጽፎአል፡፡ታቦተ ጽዮንን ሰለሞን አግኝቶአት ሙሴ ተከተተባት፡፡ ሙሴ በተቀበረበት ተራራ ናባብ በሚባለዉ ነበር ይህ የተደረገዉ፡፡ ከዚያ አዉጥቶ ሲመራ ቆዬ፡፡ በዘመነ ሳሙኤል ታቦቷ ተማርካ አሎፍሊ የሚባል በርትቶ ወሰዳት ፡፡

ይህ ሲቁጠር መቶ ሃያ ዘመን ነዉ፡፡ ዘመነ መሳፍንት አልቆ ዘመነ ክህነት ከዚም ቀጥሎ ዘመነ ነገስት በዘመነ ነገስትም ኢየሩሳለም ገባች፡፡ በዳዊት ተማርካ ሄዳ በዳዊት ዘመነ መንግስት ገብታለች፡፡ ዳዊትም ቤተ መቅደስ ለማሰራት ሞክሮ ነበር፡ ሳይሰራዉ እንደሞተ የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ፡፡በዘመነ ነብያት በነኤርምያስ ዘመን በዝናብ ምክንያት ፈረሰ፡፡ ከዚያም በኋላ ባቢሎን ቆይተዉ በሰባ ዘመን መጥተዉ ከእግዚአብሄር ጋር እንደተጣሉ መጽሃፍ ቅዱስ ላይ ሰፍሮ እናገኘዋለን፡፡

ግእዝን በተመለከተ ቋንቋዉን እንዴት ማሳደግ እንችላለን? እንዲስፋፋስ ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?

ባለቤት የሆንነዉ እኛ እያለን አሁን ቋንቋውን እየተገለገለበት ያሉት ሌሎች ናቸዉ። በሀገራችን አሁን አሁን ቀባጣሪ እንጂ የምስጢር ሰዉ እያጣን ነዉ። ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆነዉ ሊቃዉንትን ካለበት በማሰባሰብ እነሱ እንዲያስተምሩ ማድረግ ብቻ ነዉ። አለበለዚያማ የአሁኑ ትዉልድ የግእዝን ቋንቋ ምስጢሩን፡ መሪነቱን፡ ብልሃቱን ሊረዳዉ አልቻለም። ተጠያቂዉ ሊሆን የሚችለዉ በኔ አስተሳሰብ መንግስት ነዉ። ባለስልጣኑ መዶሻ እየቀጠቀጠ፣ ሊቃዉንት እንዳይሰሩ ማጥፋ፡ ማባረር ፣ ማበሳጨት እንደኔ እምነት ቤተክርስቲያን ስትደገፍ የኖረችዉ በመንግስት ነዉ። መንግስትን ስትመራ የመጣች ነች። በስርአት ደረጃ ኮምኒዝም፡ ሶሻሊዝም ህብረተሰባዊነት ብሎ የእረኛ ሀገር፣ ፈጣሪ የሌላት ወታደር ከሜዳ የመጣ እረኛ ያወጀባት ሀገር ሆናለች። በዚህ ዉስጥ አፍና ገበሬ ሰለጠነ። በዚህም ሊቃዉንቱን ያንተ እግዚአብሄር ያነተ ክርስቶስ ማለት ጀመረ። ከጊዜ በኋላም ይህ ስርአት ወደቀ። ለምን ቢባል ስላልተማረ አይፈረድበትም። አታዉቅም ሲባል ደግሞ ሰዉ ይገላል። ሊቃዉንቱ እጣ ፋንታዉ የቁም እስረኛ ሆኖ መሰቃየት ሆነ። ከዚህም አልፎ የፖለቲካ ጥገኛ ካልሆነ የአፈ ሙዝ ጥገና አድርጎ ይገለዋል። የመጨረሻ እጣ ፋንታዉ ይህ ሆነ። ሊቅ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ አያደርግም ነበር። እነ ዘርአዳዊት፣ እነ እንባቆም እንዚህን የመሳሰሉ ሊቃዉንቶች ሊቆች ናቸዉ ብሎ ከአፈ ሙዝ አላተረፋቸዉም።

በቤተክርስቲያን መሪዬታ ሲቀጠር ወይም አስተዳዳሪ ሲሾም በምን መስፈርት ነው?

ሰዉ ከጠፋና አዋቂ ከሌለ አታዉቅም አይባልም። አድማ አለ፡ ገንዘብ አለ፤ ወገን አለ፤ እሱም ወደ ወገኑ ያደላል። ገንዘብ ይከፍላል፤ ሹም ይቀጥራል። ለስሙ ፈተና ይኖራል ግን ቀላል ነዉ የሚሆነዉ ፤ ምስጢር ላይ አይገባም ቅዳሴና ዉዳሴ ብቻ ይሆናል ፈተናዉ። በዚህና በሌሎች ምክንት አሁን ቤተክርስቲያን ሳንቲም ወደመሰብሰብ ተሸጋግራለች ። የሚፈትነው ሰዉዬ እራሱ አፈ ቀላጤ ዘመድ ያለው ነው የሚስገባው እንደዚ ነው።

በመጨረሻ ለዚህ ሁሉ ችግር መፍትሄዉ ምንድን ነዉ ይላሉ?

መፍትሄዉ እንግዲህ የሚሰጠዉ ባለቤቱ ነዉ፡፡ የባህሪ አምላክ የሆነ እሱ ክርስቶስ ነዉ፡፡ መንግስት ለሀገር እድገት ቤዛ ነዉ፡፡ መንግስት እዉቀት ይስፋ ይላል፡፡ መሪዎች ካላሰቡበት ሊቃዉንትን ማሰባሰብ አለባቸዉ፡፡ እነዚህ ሊቃዉንት አንዱ የሌላዉን እዉቀት ሳይንቅ ተግላልጠዉ፣ ተከራክረዉ መፍትሄ ማምጣት አለባቸዉ ባይ ነኝ፡፡

ቃለ- መጠይቅ ሁለት

የመረጃ ሰጭ ስም፡-አስታጥቃቸዉ ይሁን (የአሻ ልጅ ተውኔት ፀሀፊ) ፣ እድሜ ፡- 53፣ ስራ፡- ብሄራዊ ቴአትር የትዉፊታዊ ትእይንት ጥበባት ጥናት ምርምር ከፍተኛ ባለሙያ ፣ ፀሀፌ-ተዉኔትና ተዋናይ ፣ መኖሪያ ፡- አዲስ አበባ
መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን ፡- ጥር 20 ቀን 2010 ዓ.ም ከ 4፡00-5፡00 ሰዓት
መረጃዉ የተሰበሰበበት ቦታ፡- በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር
መረጃ ሰብሳቢ፡- ወሰን ባዩ

እሰቲ በመጀመሪያ በዚህ የአሻ ልጅ በተባለዉ ቴአትር ውሰጥ ያንተ ሚና ምንድን ነዉ?

በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር የትዉፊታዊ ትእይንት ጥበባት ጥናት ምርምር ከፍተኛ ባለሙያ ነኝ፡፡ ለዚህ ለአሻልጅ ቲያትር መነሻዉ የመኢኔት ብሄረሰብ የአሻ ስርአት ነዉ ፡፡ ይህም በነፍስ ግድያ ወቅት ደም ለማድረቅ ሲባል ሴት ልጅን በካሳ ክፍያ የምትሰጥበት ስርአት ነዉ፡፡ የአሻ ልጅ ማለት ለሟች ቤተሰብ የገዳይ ሴት ወገን ፣ የገዳይ እህት፣ የአክስት ልጅ፣ ወደ ጎን ተቆጥሮ የሚካስበት ነዉ፡፡ በዚህ ስርአት ላይ ነዉ ለማተኮር የሞከርኩት፡፡ ትዉፊታዊ ትዉን ጥበባቱ ላይ ነዉ ጥናቱ በዋናነት የሚያተኩረዉ፡፡ ከዚህ ዉስጥ ትኩረቴን ያደረኩት የዚህ የአይሻ ስርአት ህሊናየን ስለገዛኝ ምን መስጠት ይቻላል ምንስ ፋይዳ መንቀስ ይቻላል የሚለዉን ሳስብ ይህን በጣም ትኩረት ሰጥቸ ነዉ፡፡ ተዉኔቱ ጥሩ ሆኖ ነዉ የተዘጋጀዉ፡፡ ብሄረሰቡ የራሱን አድናቆት እየሰጠ ማህበራዊ ፋይዳ እንዲኖረዉ ያደርጋል፡፡ ለማህበረሰቡም ጠቃሚ ስለሆነ ነዉ፡፡ ይህንን ግጭት የምንፈታበት መንገድ አንድ ትልቅ ባህል ነዉ፡፡ በደም ማድረቅ የሚያጠፋ የሰዉ ህይወትን የሚያተርፍ ፣ በቀል ይዞ መፈላለግን እስከ መጨረሻ ዳር ድረስ የሚያስቀር ነዉ፡፡ በአሻ የተሳሰረ ቤተሰብ የገዳይና የሟች ወገን ዳግም በደም አይፈላለግም፡፡ ግን እዚህ ላይ መረዳት ያለብን ህግ መንግስታችን ለሴቶች የሰጠዉን መብት ከግምት ዉስጥ ማስገባት አለብን፡፡ ስለዚህ ህብረተሰቡ ይህም አለ

እንዴ ብሎ እንዲያስብ ለማስቻል ነዉ። የብሔሩ ተወላጅ የሆነዉም በቲያትሩ ዉስጥ እራሱን ያይበታል።

በዚህም የተነሳ ፋይዳዉ ትልቅ ነዉ ብዬ አስባለሁ። ተመልካቹ የሚያይበት ትዉፊታዊ እይታ ማድነቅ የሚጀምርበት ስርአት መሆን አለበት። ቀደም ሲል በቃቄ ዎርዶዎትና አሁን ደግሞ በአሻ ልጅ ተጀምሮ ሙከራዎች ተደርገዋል። እነዚህ ቴአትሮች የመስክ ጥናት ተደርጎባቸዉ የተሰሩ ናቸዉ። በጥናት ላይ የተመሰረቱ ስለሆኑ ከሌሎች ቲያትሮች ይለያሉ።

በመኢኔት ብሔረሰብ ዘንድ የሚታወቁት የጋብቻ አይነቶች ምን ምን ናቸው?

የመጀመሪያዉ ከሁለቱም ተጋቢዎች ወገን በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ጋብቻ ነዉ። ሁለቱ ተፈቃቅደዉ ወደ ቤተሰብ ሽማግሌዎች የሚልኩበት ስርአት ነዉ። ወንዱ ለሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌ የሚለክበት ነዉ። ሌላዉ የጠለፋ ጋብቻም አለ። የዉርስ ጋብቻ አለ። በማህበረሰቡ ስርአት ጥሎሽ መጣል ካልቻልክ ትናቃለህ። እስከ አርባና ሀምሳ ከብት ድረስ ለጥሎሽ መጣል አለበት። አንድን ሴት በቀላሉ ለማግባት አይቻልም። አንድ ወንድ ካላገባ ደግሞ ሾሽ ተብሎ በማህበረሰቡ ይገለላል። ሾሽ ማለት የማህበረሰቡ አጠራር ማግባት ባለበት ጊዜ ያላገባ፣ ዋልጌ፣ ስራፈት፣ ወዘተ. ማለትነዉ። ስለዚህ ከማህበረሰቡ ያገለላል። ለጋብቻም አይፈለግም። ልክ እንደ ዝቅተኛ ሰዉ ይቆጠራል። የዚህ አይነት ወንዶች ብዙ ጊዜ ስደት ይሆናል እጣፈንታቸዉ። ስለዚህ ይህን ስለሚፈሩ በማህበረሰቡ ዘንድ ገና ወንድ ልጅ ሲወለድ ጀምሮ ብዙ ከብቶች እንዲኖሩት ከብት በስጦታ መልኩ ያደራጃሉ። ገና ህፃን ሆኖ ሶስት አራት ከብቶች ሊኖሩት ይገባል። የቀንድ ከብቶች ብዛት የማንነት ጥያቄና የህልዉና ጉዳይ ስለሆነ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። በብሔረሰቡ ጋብቻን ከባድ የሚያደርገዉ አንዱ ምክንያት ይህ ነዉ - ጥሎሽ።

በመኢኔት ባህል ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ክልክል እንደሆነ በተውኔትህ ዉስጥ ገልጸሀል - ይህንን ብታብራራልኝ?

አዎ በመኢኔት ባህል መሰረት ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ክልክል ነዉ፡፡ ወንድ እና ሴት በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገናኛሉ፡ ሰርግ ላይ፣ ሀዘን ላይ በጉሌ ጭፋራ ላይ ወዘተ. የትዉዉቅ ጊዜ ይኖራቸዋል፡፡ አብረዉ ይዉላሉ፤ ባህላዊ ጠላ ወይም ቦርዴ፣ ትንባሆ የመሳሰሉትን ይገባበዛሉ ፡፡ ነገር ግን ከጋብቻ በፊት ምንም አይነት የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ ባህላዊ ህጉ አይፈቅድላቸዉም፡፡ ጨዋነት የተሞላና ጥንቃቄ የታከለበት ግንኙነት ነዉ የሚኖራቸዉ ፡፡ ከጋብቻ በፊት ምናልባት ግን ሴቷ ግብረ ስጋ ግንኙነት አድርጋ ብትገኝ ከባድ ግርፋት ይጠብቃታል የደፈራትን ወንድ እንድትናገር ትገደዳለች ያ ሰዉም እንዲከስ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከብት ታርዶ ደሙን ተቀብታ የመንጻት ስርዓት እስካልፈጸመች ድረስ ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል አትችልም፡፡

የአሻ ባህላዊ የግጭት አፈታት አሰርዓት ምን ፋይዳ አለው ?

ፋይዳዉ ለማህበረሰቡ ትልቅ ጥቅም አለዉ፡፡ በተለያየ መልኩ ግጭትን ያስወግዳል፡፡ የደም ብቀላ ስርአትንም ያጠፋል ፡፡ በአሻ የተሰጠች ሴት ሃዳ ልጅ ትወልዳለች፡፡ በምትወልደዉም ልጅ ሚች ይረሳል፤ በሁለቱ ቤተሰቦች መሀከል ማለትም በገዳይና በሚች ቤተሰብ መሀል ልጅ ስላለ ደሙ ይደርቃል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሌላ መልኩ ግን ይህ የአሻ ስርዓት የሴቷን አካላዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ መብቷን ያሳጣታል፡፡ ምክንያቱም የምትፈልገዉን ባል የማግባት እድል አታገኝም፡፡ ምርጫ የላትም፡፡ ለደም ማድረቅ ሲባል በግድ ያለፍላጎቷ ትሰጣለች፡፡ ብዙ ሴቶች በዚህ መልኩ ወደ ጋብቻ እንደሚያመሩም መታዘብ ችያለሁ፡፡ እራሳቸዉን እስከ ማጥፋት ድረስ የሃዱ ልጅ አገረዶች እንዳሉ ሰምቻለሁ፡፡

ቃለ- መጠይቅ ሶስት

የመረጃ ሰጭ ስም፡- ተስፋየ ጎይቴ (በቃቄ ወርዶወት ተውኔት ላይ ከባህላዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በአማካሪነት የተሳተፉ) ፣እድሜ ፡- 48፣ ስራ፡- የጉራጌ ባህልና ልማት ማህበር ዋና ዳይሬክተር ፣ መኖሪያ ፡- አዲስ አበባ

መረጃዉ የተሰበሰበበት ቀን ፡- ጥር 15 ቀን 2010 ዓ.ም ከ 8፡00-10፡00 ሰዓት

መረጃዉ የተሰበሰበበት ቦታ፡- በጉራጌ ባህልና ልማት ማህበር ዋና ጽ/ቤት፣ አዲስ አበባ

መረጃ ሰብሳቢ፡- ወሰን ባዩ

አሰቲ እንደ መነሻ ሰለ ቃቄ ወርዶወት ጠቅለል ያለ ነገር ይንገሩኝ?

ብዙ ኢትዮጵያውያንና የዉጭ ሃገር ሰዎች ጉራጌ ሲባል የሚያዉቁአቸዉና ቶሎ የሚመጣላቸው ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ፣ ክትፎ በቆሮ አንዱ የጉራጌ መገለጫ ነው፡፡ ጠንካራ የስራ ባህል፣ በየደረሱበት አብሮ ተቻችሎና ተከባብሮ መኖር እነዚህና መሰል ነገሮችም አዚህ ላይ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ነገርግን ብዙ ሰዎች የማያውቁት ግን ደግሞ መታወቅ አለበት የምለው የቃቄ ወርዶወት እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እገሌ የተባለ አርቲስት ከዚህ ቦታ በቀለ ስንል የሆነ ነገር ከዚያ ማህበረሰብ ከጠጣዉ ዉሃ፣ ከተማረበት ማህበረሰብ ትምህርት ቤት፣ ከብቶች ሲያግድ ከነበረበት ጊዜ ሁሉ ይዞት የመጣው የሆነ ነገር አለ ማለትነው ፡፡ ወርዶወትም ከጉራጌ ማህበረሰብ የተገኘች እንደመሆኗ በተለይ ደግሞ ጥንት አመጣጧን ስንመለከት ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ አጋዝ ሽበታ የተባለ በዚያ ዘመን በአገሪቱ ገዥዎች የሚታወቁ መሬት የሚያንቀጠቅጥ ጀግና የነበሩ አጎቷ ናቸው፡፡ ስለዚህ መሰረቷን ስንመለከት ከጀግና እና ለጋስ ቤተሰብ፣ ርህሩህና ደግ ከሆኑ እናትና አባት የተገኘች ናት፡፡

ስለ ቃቄ ወርዶወት ቴአትር እና እዚህ ዉስጥ ስለ ተካተቱት ጉዳዮች ስንነጋገር አስተሳሰረን ነዉ ማየት ያለብን፡፡ አለበለዚያ ቁንጽል ይሆንብናል፡፡ ሴቶች ዛሬ በሐገራችን ኢትዮጵያም ይሁን በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች የሚያነሱዋቸው የሴቶች የመብት ጥቄዎች ጥንስሱ ከመቶ ሃምሳ ዓመት በፊት በቃቄ ወርዶወት ፊታውራሪነት እንደ ጀመረ ልብ ልንለው ይገባል፡፡ የቃቄ ወርዶወት ይዛዉ የተነሳችዉ የመብት ጥያቄ ዋናው አንድ ወንድ በአንድ ሴት ይወሰን የሚለዉ

ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ የመሬትና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ለብዙ አመታት ቆይቶ በተለያዩ ሐገራት ሴቶች ለመብታቸዉ መታገል የጀመሩት በቅርብ ነዉ፡፡ የቃቄ ወርዶወት የትግል ጥንካሬ የሚያሳየዉ በነዚያ ሁሉ ችግሮች ዉስጥ አልፋ ለሴቶች መብት በጽናት መከራከሯን ነው፡፡

ጀፎረ በቃቄ ወርዶወት ቴአትር ዉስጥ በጉልህ ከተነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፤ ለመሆኑ ጀፎረ ምንድን ነው?

ጀፎረ የጉራጌ መገለጫ ከሆኑት የባህልና የቱሪዝም ሃብቶች ዉስጥ በመጀመሪያዉ መስመሮች ዉስጥ የሚቀመጥ ነዉ፡፡ጀፎረ ማለት ጥሬ ትርጉሙ በመንደርና በመንደር መካከል የሚገኝ የጋራ አደባባይ ወይም የጋራ ባህላዊ አዉራ ጎዳና ማለት ነዉ፡፡ አዚህ ላይ ባህላዊ ያልንበት ምክንያት ምንድን ነዉ? ከዘመናዊው በምንድን ነዉ የሚለየዉ? ወደሚለዉ መሄድ አለብን ማለት ነዉ፡፡ ጀፎረ የሚባለዉ ነገር በኢትዮጵያ ምድር የትም ክልል የትም ዞን የትም ወረዳ ከጉራጌ አካባቢ ዉጭ የትም ብንሄድ የማናገኛቸዉ የጉራጌ ህዝብ ካለፉት ምእተ አመታት ጀምሮ እንዳይነካና እንዳይሻር በጉርዳ ጠብቆት የኖረ ነዉ፡፡ ጉርዳ ማለት የጉራጌኛ ቃል ሲሆን በአማርኛ ቃል ኪዳን ማለት ነዉ፡፡የጀፎረ ወሰን እንዳይገፋ በቃል ኪዳን ይጠበቃል፡፡ ትንሹ ጀፎረ የሚባለዉ ምናልባት ከ20 እስከ 60 ሜትር ስፋት ያለዉ ነዉ፡፡ የአዲስ አበባ ቀለበት መንገድን ስናስብ ወይም ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ የሚወስደዉን መንገድ ብንመለከት በዘመናዊ እዉቀት ተቀይሶ የተሰራ ነዉ፡፡ ይህም ማለት በሌላ በኩል ሰዎች ቴክኖሎጂን ተጠቅመው የሰሩት ዘመናዊ መንገድ ነዉ ማለት ነው፡፡ ጀፎረ ደግሞ ፊደል ባልቆጠሩ፣ የቄስ ትምህርት ቤት ደጃፍ እንኳን በወጉ ባልረገጡ የጉራጌ ጥናታዊ አባቶች ተፈጥሮ የሰጣቸዉን ጥበብ ተጠቅመዉ የሰሩት ነዉ፡፡ ጀፎረ አካፋና ዶማ ሳይነካዉ፣ ሜትር የሚባል መለኪያ ሳይኖር ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከወዲም ከወዲህም እንዳይገፋ ህብረተሰቡ በቃልኪዳን ጠብቆ የኖረ / እየኖረ ያለነው ፡፡

ጀፎረ ላይ የሚከናወኑ ጉዳዮችና ከዚህጋር ተያይዞ ያለው ጠቀሜታ?

የጀፎረ አንዱ መገለጫዉ በለምለም ሳር ያጌጠ ሰፊ መንገድ መሆኑ ነዉ፡፡ግን ደግሞ የማህበረሰቡ የጋራ ጉዳይ የሚከናወንበት ቦታም ነዉ ፡፡ ከዚህም ሌላ ሰፈርን፣ ወረዳን ፣ ቀበሌን ያገናኛል፡፡ ጀፎረ ሁልጊዜ አረንጓዴ ከመሆኑ የተነሳ በአካባቢው የሚኖሩ የመንደሩ ነዋሪዎች በግና ከብቶቻቸዉን ከግቢያቸዉ አስወጥተዉ ወደ

ትልቁ መስክ እስኪሰማሩ ድረድ በጀፎረ እንዲቆዩና የአካባቢውን ሳር እንዲግጡ ያደርጋሉ፤ በተመሳሳይ ቀኑን ሙሉ መስክ ዉለዉ ማታ ወደ ቤታቸዉ ከመግባታቸዉ በፊት በጀፎረዉ አካባቢ ቆይተው ወደ ማደሪያቸዉ ይገባሉ፡፡

በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶ የጀፎረ ጥቅሙ ብዙ ነዉ፡፡ ባለፉት በርካታ አመታት የጉራጌ ማህበረሰብ እንደዛሬዉ ድኳን ባልነበረበት አዳራሽ ባልተሰራበት ዘመን በየጀፎረዉ መካከል በሚገኙ ተፈጥሮ ያበቀለቻቸዉ ትላልቅ ዝግባና ዋርካዎች ስር በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ሲፈጸሙ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ ዛፎች ስር ባህላዊ የዳኝነት ስርአት ይካሄድባቸዋል፤ ሰርግ፣ ለቅሶ ወይም ሌላ ትልቅ ዝግጅት ሲኖር ከጫካ ቅጠል ቆረጥ ቆረጥ ፤ተደርጎ ይመጣና ዳስ ተሰርቶ እንግዳ ይስተናገዳል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ፤ የፈረስ ግልቢያ፣የትግል ውድድር ወዘተ. ይካሄድበታል፡፡ ጀፎረ የግለሰብ አይደለም የጋራ ሃብት ነዉ፡፡ ጀፎረን መግፋት አይቻልም የተቀደሰ ነዉ፡፡ ቢገፋ እንኳን የቤተሰብ እልቂት(ሞት) ያመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

የቦታው አቀማመጥ ምን ይመስላል?

በጀፎረ ግራና ቀኝ የሚገኙ መንገዶች ቀጥ ብለዉ የሚሄዱ ናቸዉ፡፡ በአካባቢው ባሉ ቤቶችና በጀፎረ መካከል ቁመቱ አንድ ሜትር ገደማ የሚደርስ ድንዴ የሚባል የአፈር ወይም የሳር ካብ አለ፡፡ ይህም ዉሃና ጎርፍ ወደ ጀፎረዉ ቢመጣ ወደ መንደሩ ቤቶች እንዳይገባ ይከላከላል፡፡ ድንዴዉ ላይ አጥር ዋርካና ዝግባ ደግሞ በየመሀከሉ አለ፡፡ ይህም ጀፎረን ዉበቱ የተለየ እንዲሆን አስችሎታል፡፡ጀፎረ ሄዶ ሄዶ ወንዝ ቢያጋጥመዉ ወንዙን ተሸግሮ ይቀጥላል፤ ተራራም ቢያጋጥመዉ እንደገና ከተራራዉ በኋላ ሌላ ጀፎረ ይኖራል፡፡

ስለ ዴሰነ ጀፎረ ምን ማለት ይቻላል?

የደሰነ ጀፎረ ማለት በጣም ታሪካዊ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ዲሰነ ማለት የመንደር ሰም ነው፡፡ በችሃ ወረዳ አገሃ በሚባል ከተማ ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ አካባቢ የሚገኘው ጀፎረ ደግሞ የዴሰነ ጀፎረ በተለምዶ የዴሰነ ጀፎረ እየተባለ ይጠራል፡፡

ከቃቄ ወርዶወት ጋር በያያዘ የዴሰነ ጀፎረ ምን የተለየ ታሪክ አለዉ?

በትክክል የተለየ ታሪክ አለዉ ፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ታሪኩን በዝርዝር ለማንሳት ያህል የቃቄ ወርዶወት በምሁር ወረዳ ዉስጥ ዉድማጠር የሚባል ጎሳ ተወላጅ ናት፡፡ ተወልዳ ያደገችበት የመንደር ስም ደግሞ ኸርምየ ነው፡፡ ባለቤቱዋ

አጋዝ ፉርችየ ደግሞ የእጣ ወረዳ ሰዉ ነው። አጋዝ ፉርችየ ጀግናና ጦረኛ ስለሆነ በዚያ ዘመን በነበረው ባህል መሰረት ብዙ ሚስቶች ማግባት ይችል ነበር። ሁለቱ ተጋብተዉ ገና የሙሽርነት ጊዜያቸዉ ሳያበቃ ወደሌላዋ ሚስት ሊሄድ መሆኑን ለቃቄ ወርዶወት ነገራት። ይሁንና በዚህ ጊዜ የቃቄ ወርዶወት ይህን ስትሰማ በእጅጉ ስለተቆጣች አትሄድም ትልና ይጣላሉ። በመሆኑም በጉራጌ ማህበረሰብ የዳኝነት ስርአት መሰረት ለመንደሩ ሽማሌዎች ጉዳዩ እንዲታይላት ታቀርባለች። ሽማግሌዎቹ ግን በቀላሉ ሊፈቱት አልቻሉም፤ ምክንያቱም ከባድ ጉዳይ በመሆኑ። ከእኔ ውጭ ሌላ ሚስትጋ መሄድ የለበትም አለች ። ይህም የመጀመሪያ ጥያቄዋ ነዉ። የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥያቄ ሁለተኛ ነዉ። ከዚያ በኋላ ነገሩ ነገር እየወለደ ሄዶ እሱ ሌላ ሚስት ጋ የሚሄድ ከሆነ እኔም ሌላ ባል ጋ መሄድ አለብኝ አለች። ይህንን ሃሳብ ያነሳችዉ ሌላ ወንድ የማግባት ፍላጎት ኖሩአት አይደልም፤ ወንዶች ይደነግጣሉ ብላ ስላሰበች ነበር። ነገር ግን የቃቄ ወርዶወት በመንደር ሽማግሌዎች የትም አትደርስም ተብላ ተናቃች። ከዚህ በኋላ ወርዶወት በርካታ ሴቶችን ከጎኗ በማሰለፍ ዴሰነ ጀፎረ የሚባለዉ ቦታ ላይ የሚቀመጥ የእጅካ ሸንጎ ስለነበረ ለዚህ ሸንጎ ጉዳይዋን በድጋሚ አመለከተች። ስለዚህ ዴሰነ ጀፎረን የተለየ የሚያደርገዉ የቃቄ ወርዶት ክርክር በእጅካ ፊት የተካሄደበትና አንቂት ይውረድልሽ ተብላ የመጨረሻዉን ፍርድ ያገኘችበት ቦታ በመሆኑ ነዉ።

አንቂት ሲባል ምን ማለት ነዉ?

አንቂት የጉራጌ ማህበረሰብ የቆየ ፍልስፍና እምነት የሚንጸባረቅት ጥልቅ ሃሳብ የያዘ ጉዳይ ነዉ። አንቂት ማለት ጥሬ ትርጉሙ የሴት ልጅ እርግማን ማለት ነዉ። ወንዶች ሴቶችን ፈትቼሻለሁ እስካላሉ ድረስ ሌላ ባል እንዳያገቡ የሚከለክል እርግማን ነዉ።

የእጅካ ሸንጎን ጨምሮ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት በጉራጌ ምን ይመስላል?

ዋናው በዚህ በቃቄ ወርዶወት ተውኔት ውስጥ የተገለታ የእጅካ ባህላዊ ሸንጎ ሲሆን በክስታኔ ጉራጌ የጎርዳ ሴራ የሚባል ባህላዊ የዳኝነት ስነ ስርዓት አለ። የቀድሞ ሰባት ቤት ጉራጌ የምንለዉ ነዉ። ይህም በጉራጌ ዞን ምእራባዊ ወረዳዎች የሚተዳደሩበት ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ነዉ። እነዚህ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቶች ዛሬም ድረስ አሉ። ጉራጌ ውስጥ ላሉ ብቻ ሳይሆን እዚህ አዲስ አበባም

በጉራጌዎች ዘንድ አለመግባባት ሲኖር ሐገር ቤት ድረስ ተጠርተዉ በባህላዊ የዳኝነት ስርዓት እርቅ እንዲፈጽሙ ይደረጋሉ፡፡

በዚህ ባህላዊ የዳኝነት የሚያገለግሉት ዳኞች የሚመረጡት በምን መሰፈርት ነው?

ዳኞች የሚመረጡት ከአንድ ቦታ ወይም አካባቢ አይደለም ፡፡ ከታችኛው ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ላይኛዉ የእጅካ የዳኝነት ቦታ ድረስ የሚመጡ ዳኞች በአካባቢያቸው ማህበረሰብ ጥቆማ መሰረት ነዉ፡፡ ይኸዉም በሚኖሩበት ማህበረሰብ ዘንድ በሚኖራቸዉ ከበሬታና ተቀባይነት ነዉ፡፡ እነዚህ ዳኞች ክፍያ የላቸዉም፡፡ የእነሱ ክፍያ በጸበኞች መሀከል እርቅ ወርዶ ማየት ብቻ ነዉ ፡፡ ስለዚህ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ከዘመናዊ ፍርድ ቤት በብዙ ነገር ይለያል ማለት ነዉ፡፡ ይኸዉም መደበኛ ፍርድ ቤት ጥፋት ሲፈጸም በዳይና ተበዳይ ፍርድቤት ከቀረቡ በኋላ ፍርድ ቤቱ ግራና ቀኙን አይቶ ጥፋተኛዉ ላይ የዉሳኔ ብይን ያስተላልፋል፡፡ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ግን አንድም ዉሳኔ ይሰጣል፤ ሁለት ደግሞ በዳይና ተበዳይ ታርቀዉ እንዲሄዱ በሁለቱም በኩል ዘላቂ እርቅ እንዲወርድ ያደርጋል፡፡ ይህም የባህላዊ ዳኝነቱ ቁልፍ ተግባር ነዉ፡፡

ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ምን ፋይዳ አለው?

በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ከዉጭም ሆነ ከዉስጥ ግጭቶች ሲኖሩ ህብረተሰቡን አስተባብረዉ የመጣዉን ጠላት ጦር ጥቃት መመከት አንዱ የባህላዊ ዳኝነት ሃለፊነት ስለሆነ በዚህ ረገድ ትልቁን ድርሻ እንሱ ይወጣሉ ማለት ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ ማህበረሰቡ እርስ በርሱ ሲጣላ ለምሳሌ፣ ግለሰብ ከግለሰብ፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ ባል ከሚስቱ፣ ወረዳ ከወረዳ ወዘተ. ሲጣላ የማስታረቅ ሃላፊነታቸዉን ይወጣሉ፡፡

ህብረተሰቡ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ፣ ኑሮዉን ያለምንም ችግር እንዲመራ፣በረባ በልረባው ጸብ እንዳይፈጠር ቢፈጠር እንኳን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ የበኩላቸዉን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የጉራጌ ማህበረሰብ ቱባ ባህልና ማህበራዊ እሴቶች ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እንዲሸጋገሩ በማድረግ በኩልም ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ እነዚህን ማህበራዊ እሴቶች የሚጥስ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜም ባህላዊ የዳኝነት ስርአቱ የመቆጣጠር ሚናውን ይጫወታል፡፡

ለምሳሌ፣ ሆን ብሎ ወንጀል የፈጸመ ሰው ካለ አካል የሚሰጠዉ የፍርድ ቅጣት በዚያዉ ልክ ከባድ ይሆናል፡፡ ለዚህም በባህላዊ የዳኝነት ስርአቱ የሚያስቀምጣቸው የቅጣት ደረጃዎች አሉት፡፡ ስለዚህ ባህላዊ የዳኝነት ስርአት ለጉራጌ ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ለሐገራችንም ትልቅ ጠቀሜታ አለዉ ማለት ነዉ፡፡ ባህላዊ የዳኝነት ስርአት መኖሩ ለመደበኛ የፍርድ ስርዓቱም ቢሆን ጠቅሞታል፡፡ ምክንያቱም መደበኛ ፍርድ ቤት ላይ የሚሟገቱ ባለጉዳዮች የሚቆሙት በባህላዊ የዳኝነት ስርአቱ ስለሆነ፡፡

ቄግ ምንድን ነዉ?

ቄጎች ብዙ ጊዜ በማህበረሰቡ ዘንድ(በጉራጌ ማህበረሰብ) ዘፈን ተብለዉ ነዉ ትርጉም የሚሰጣቸዉ፡፡

ነገር ግን እነዚህ ቄግ ዘፈኖች የሚዘፈኑት በአመዛኙ የጎላ ወይም ትልቅ ታሪክ ላላቸዉ ግለሰቦች ፣ ቤተሰቦች ወይም ጎሳዎች ነዉ፡፡ ትልቅ ታሪክ ማለት ለምሳሌ፣ የዉጭ ወራሪዎች ሐገራችንን ዳር ድንበሯን ለመድፈር ሲመጡ ወደዚያ የጦር ግንባር ሄደዉ ጠላትን ታግለዉ ለሐገራቸዉ መስዋዕትነት ከፍለዉ የመጡ ፊታዉራሪ፣ ቀኝ አዝማች ፣ ግራ አዝማችራ እንደሚባሉት ለጀግኖች አባቶችና እናቶች የሚዘፈን ዘፈን ነዉ፡፡

የዚህ አይነት ክብር ላላቸዉ ወይም አኩሪ ስራ ለሰሩ ሰዎች በግጥሞቹ ዉስጥ የዚያን ሰዉ ጀግንነት የሚያወድሱ ናቸዉ፡፡ አንድ የቄግ ግጥም ሁለት ወይም ሶስት ደቂቃ ሊረዝም ይችላል፡፡ የቄግ ዘፋኝ ወይም ድምጻዊ ተቀባይ የግድ ያስፈልገዋል ፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ቤት ዉስጥ ሰርግ ካለ የሙሽራዉ ወይም የሙሽራዋ እናት ወይም አባት ትልቅ ታሪክ ወይም ስም ካላቸው ወይም የነሱ ጎሳ ትልቅ ስም ካለው የዚህ አይነት ዘፈን በሰርጉ ወቅት ይዘፈናል፡፡ ሰርጉ ሊደረግ ሳምንት ወይም ወር ሲቀረዉ ሊሆን ይችላል ማታ ማታ ዘመድ አዝማድ ተጠራርተው ቡና እየጠጡና እየተጫወቱ ቄግ ይዘፍናሉ፡፡ብዙ ጊዜ ቄግ የሚዘፈነዉ ቁጭ ተብሎ ነዉ፡፡ አንዱ ቄግ ሲያልቅ ሌላው ቄግ ይጀምራል፡፡ አንድ ጎሳ ወይም ግለሰብ አንድ ቄግ ብቻ ሊኖረዉ ይችላል፡፡ እንደ ሁኔታው አምስት አስርም ሊዘፈንለት ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሞቅ ያለ ቄጎች አታሞ ወይም ከበሮ እየተመታ ተቀባዮቹ ከበዉ እያጨበጨቡ ይዘፈናሉ፡፡ ስለዚህ በጀግንነታቸዉ የሚታወቁ ሰዎች፣ ለምሳሌ የዱር አራዊት

የገደሉ ፣ በጦር ግንባር ጀብዱ የሰሩ ወዘተ. ታሪካቸው እየተነሳ ይዘፈንላቸዋል። ይህ ብቻ አይደለም፤ አንድ ሰዉ ለጋስና ቸር ከሆነም እንዲሁ ይዘፈንለታል።

የቃቄ ወርዶወት እናትና አባትም ለጋስና ቸር በመሆናቸዉ ዜግ ተዘፍኖላቸዋል። እሷም የዜግ ዘፈን አላት። ምክንያቱም የቃቄ ወርዶወት የጉራጌን ባህላዊ ሽንጎ እጅካን ያንቀጠቀጠች ጀግና በመሆኗ ነው። ። ሌሎች ደግሞ ለምሳሌ፣ አሲህ አርብ ፉጋ ያለምንም ፍርሀት በጦር ሜዳ ከጠላት ጋር አንገት ለአንገት ተናንቆ በማሸነፉ ተዘፍኖለታል። ስለዚህ ዜግ የምንለዉ በተለያዩ አጋጣሚ ታሪክ ለሰሩ ሰዎች የተዘፈነላቸዉን ዘፈን ነዉ። ባጭሩ ዜግ ማለት ታሪክ የሰሩ ሰዎችን በዘፈን ማወደስ ማለት ነዉ። ልክ እንደ ወደድኩህ ወደድኩሽ አይነት ዝም ብሎ ተራ ዘፈን አይደለም። ዜግ አንዳንዴ የሩቅ ዘመንን እያነሳ ያወድሳል፤ ከዘፈኖች ሁሉ ተወዳጅ የሆነ ታሪክን በስፋት የሚያነሳዉ የዜግ ዘፈን ነው።

ጎይታ ምን ማለት ነዉ?

ጎይታ ማለት ፈጣሪ ወይም አምላክ ማለት ነው ። ለምሳሌ፣ የጉራጌ ማህበረሰብ ሲመርቅ " ጎይታ አይቤ" ይላል። እግዚአብሔር ይስጥልኝ እንደማለት ነዉ። ከዚህም ሌላ ቤተሰብ ልጆቹን ሲመርቅ ጎይታ ያሳድግህ ብሎ ነዉ። ስለዚህ የቃሉ አጠቃላይ ትረጉም እግዚአብሔር አምላክ የሁሉም ፈጣሪ እንደማለት ነዉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሰለ ምርቃትና ፋይዳው ምን ማለት ይቻላል?

ለምሳሌ፣ በመስቀል ጊዜ በየትኛዉም የሐገራችን ክፍል የሚኖሩ የጉራጌ ተወላጆች ወደ ቤተሰቦቻቸዉ ሲሄዱ አቅማቸዉ እንደቻለ በሬ ወይም ልብስ ገዝተው ለቤተሰብና ለወዳጅ ዘመድ ስጦታ በሚሰጡበት ጊዜ ወላጆች አብዝተዉ ይመረቃሉ። "ጎይታ ይስጥልን" ተብሎ ይመረቃል። ምርቃትና የጉራጌ ማህበረሰብ ልክ እንደ ደምና ስጋ የተዋህዱ ናቸዉ። ምርቃት በሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ዘንድ ሊኖር ይችላል፤ አዚህ ግን የተለየ ነው። የጉራጌ ልጆች ሁልጊዜ ለእድገታቸዉ ሁለት ምክንያቶችን ያስቀምጣሉ። የመጀመሪያዉ ጠንክረዉ በመስራታቸዉ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ከማህበረሰቡ በሚያገኙት ምርቃት ነዉ። ጉራጌ የቱንም ያህል ጥበብ የተሞላበት ስራ ብሰራ ምርቃት ከሌለኝ ልፋቴ ዋጋ የለዉም ትርፋማም አልሆንም ብሎ ስለሚያምን ስራዎች ሁሉ ምርቃት ማግኘት አለባቸዉ።

በጉራጌ ባህላዊ የማዕረግ ስም አሰጣጥ ምን ይመስላል?

የማእረግ ስሞቹ የሚገኙት በሁለት አይነት መንገድ ነዉ፡፡ አንደኛዉ መንገድ ከተዉለድ ወደ ትዉልድ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ዉርስ የሚገኘዉ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ የአካባቢዉ ማህበረሰብ በባህሪህ በምታደርገዉ ነገር ማለት በስራህ ስም የሚሰጥበት ሂደት ነዉ፡፡ በዉርስ የሚመጣዉ "አዝማች" ይባላል፡፡ ንጉስ እንደማለት ነዉ፡፡ የአንድ አካባቢ ወይም የአንድ ጎሳ አስተዳዳሪ ነዉ-አዝማች፡፡ በጉራጌ ማህበረሰብ ታሪክ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ የማእረግ ስም አስጣጥ አለ፡፡ ስለዚህ አያት በሚሞቱበት ጊዜ በሚወለዱ ልጆች አንጋፋዉ ወይም የተመረጠዉ ንግስናዉን ይቀበላል፡፡ የንጉሳዊያን ዘር ለመሆኑ ማሳያም እጅ ላይ የሚጠለቅ ብራስሌት መሳይ ምልክት አለ፤ " ጎርዳ" ይባላል፡፡ ከዚያ ከአያት ቅድመ አያት የተወረሰዉ ንግስናዉን ሲቀበል ይህን ጊዜ ንጉስ ይባላል ፡፡ ስለዚህ በማህበረሰቡ ዘንድ ንጉስ ይከበራል፤ ከሌላዉ ማህበረሰብ በበለጠም ከበሬታ ይቸረዋል፡፡ በተጨማሪም ንጉስ ከሆኑ በኋላ የሚዘፈንላቸዉም አለ፡፡

ሁለተኛዉ በጦር ሜዳ ዉጊያ በሰሩት ጀብዱ ወይም ደግሞ በለጋስነታቸውና በሀብታቸው ብዛት የጉራጌ ማህበረሰብ ይህ የክብር ስም ይገባዋል ብሎ የሚሰጠው የክብር ስም አለ፡፡ ለምሳሌ፣ የቃቄ ወርዶወት አባት ዳሞ ቃቄ በሀብታቸዉ ብዛትና በለጋስነታቸዉ ነዉ ዳሞ የተባሉት ፡፡ ዳሞ ማለት ደግሞ ብዙ ሀብት ያለዉና የተከበረ እንዲሁም ለጋስ የሆነ ሰዉ የማእረግ ስም ስለሆነ ዳሞ ተባሉ፡፡ በጦር ግንባር ወይም ደግሞ ትላልቅ የዱር አራዊትን በመግደል ጀግና ሆኖ ብዙ ጠላቶችን የተዋጋም የማእረግ ስም ይሰጠዋል፡፡ ይኸዉም "አሲህአርብ" ይባላል፡፡ ትርጉሙም "አርብ" ማለት ጦርነት ማለት ወይም ዉጊያ ማለት ነዉ ፡፡ "አሲህ" ማለት ደግሞ የማይሸሽ የማያፈገፍግ እንደ ማለት ነዉ፡፡ የማእረግ ስም አሰጣጡ በደረጃ ነዉ፡፡ ለምሳ አባገዳ (ሳይጠብቅ) ነገር አዋቂ ማለት ነዉ፡፡ አስተዋይና ሰዉች ሲጣሉ እንዴት ማስታረቅ እንዳለበት የሚያዉቅ ትልቅና ብልሃተኛ ሰዉ ነዉ፡፡

አንድ አካባቢ ላይ አጋዝ ሊኖር ይችለል፤ አሲህርብ ሊኖር ይችላል፤አባገዳ ሊኖር ይችላል፤ አንዳንዶቹ የማእረግ ስሞች በተለያየ ደረጃ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ግቻምቄ እና አጀቶ ስለተባሉት ባህላዊ ዘፈኖች ቢያብራሩልኝ?

እንደማንኛዉም የሀገራችን ማህበረሰብ ጉራጌም እጅግ በርካታ ባህላዊ ዘፈኖች አሉት፡፡ ግቻሜ አንዱና ትልቁ ባህላዊ ዘፈን ነዉ፡፡ ምሁር አክሊል ወረዳ ላይ ሌላ እንደ አሸንዳ አይነት በየአመቱ እርጥብ ቅጠል እየቆረጡ ሴቶቹ በማገልደም የሚዘፍኑት ባህላዊ ዘፈንም አለ፡፡ ይሽኛዉ እጅግ ጥንታዊ እንደሆነ ነዉ ከአባቶቻችን የሰማንዉ፡፡ ሌላዉ ደግሞ ሶዶ ወረዳ ዉስጥ ለሰርግ ዋዜማ እንሾሽላ ተብሎ እንሾሽላ በሚሞቅበት ጊዜ የሚዘፈን ዘፈንም አለ፡፡ ይህም የራሱ የሆነ የአጨፋፈር ስልትና ዘይቤ አለዉ፡፡ በግቻምቄ ዘፈን እያወደስክም እየነቀፍክም የምትዘፍንበት ሂደት አለ፡፡ ጭፈራዉም በጣም የተለየ ነዉ፡፡ ብዙ ጊዜ ይህንን የዘፈን አይነት የሚጫወቱት ሴቶች ናቸዉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ወንዶችም መዝፈን ጀምረዋል፡፡ ሌላው አጀቶ ብዙ ጊዜ በገና በአል ጊዜ የሚጨፈር ዘፈን ነዉ፡፡ በዋናነት ግን ዘፈኑ የሚታወቀውም የዉዳሴ ዘፈን ተብሎ ነዉ፡፡ ለምሳሌ፣ የቃቄ ወርዶወት ተውኔት ውስጥ እንደተመለከትነው የላቀ ሙያ ባለቤት ለሆነችው አጀት አሚና (የቃቄ ወርዶወት እናት) “አጀቶ- አጀት አሚና ” እየተባለ ተዘፍኖላታል፡፡

ማረጋገጫ (Declaration)

በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ በፎክሎር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሠራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ዋቢ መረጃዎችም በትክልል ዋቢ የሆኑ ናቸው። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የዚሁ ጥናት ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ወሰን ባዩ ደሌ ፊርማ_____ ቀን፡-_____